የወያኔው

ታላቅ ሤራ

በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ

የሀዋሓት የቀድሞ አባላት የነበሩት የአቶ አብርሃም ያየህና
የአቶ ገብረመድህን አርአያ ቃለ ምልልስ
(ክፍል 1 እና 2)

አዲስ አበባ
ጥር 1982

t.me/OLDBOOKSPDF

የወ/ኤው

ታላቅ ሚራ

በቀድሞው አባላቱ ሲጋለጥ

የሠላሳ የቀድሞ አባላት የነበሩት የአቶ አብርሃም ደየሀና
የአቶ ገብረመድህን አርአያ ታለ ምልልስ

አዲስ አበባ
ጥቅምት 1982

t.me/OLDBOOKSPDF

መግቢያ

የኢትዮጵያ ልጆች ብሔረሰብና ሃይማኖት ሳይለያቸው በከፈሉት መሥዋዕትነት የተገነባችውን አንዲት ኢትዮጵያን ለመበታተን በረ የኢትዮጵያ አንድነትና ደህንነት ኃይሎች ከፍተኛ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ናቸው ። የዚህ የኢትዮጵያ ስትራተጂክ ጠላቶች ዒራ አራማጅ የሆኑት "ሻዕቢያ"ና "ህወሓት" በሚያካሂዱት የተቀናጀ የጥፋት ዘመቻ ዛሬ የኢትዮጵያን አንድነት በመፈታተን ላይ ናቸው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢትዮጵያ አንድነት ውስጥ ለሚሰፍን ሰላም ፡ እኩልነትና ማኅበራዊ ዕድገት ያለውን ፍላጐት በማጤን የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለሰላም ጥረት በሚያደርጉበት በአሁኑ ወቅት መሠረታዊ ዓላማ ያንኑ ኃይሎች ጠርንት እያሰፋፉ ነው ። ዓላማቸውን ለማሳካት በሰላማዊ ሕዝብ ላይ ከሚያካሂዱት ሽፍቶታዊ በተጨማሪ የሕዝቡን አንድነትና የሀገር ፍቅር ስሜት ለመሸለብ የፕሮፓጋንዳ ጦርንት ከፍተዋል ።

ራሱን "ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ" ብሎ የሰየመው ጠባብ ብሔረተኛ ቡድን የተቀበለውን ኢትዮጵያን የመበታተን አደራ ለማስፈፀም በአንድነት በመተባበር በኖሩ ብሔረሰቦች መካከል ጥላቻን በመፍጠር የእርስ በርስ ጦርንት በማካሄድ ላይ ይገኛል ።

ደህንን በወያኔውና በተባባሪዎቹ የተጠነሰሰውን ሀገርን የመከፋፈል ዒራ "ማን ይናገር የንበረ ፡ ማን ያርጽ የቀበረ" ንውና የ"ህወሓት" የቲድሞ አባላት የንበሩት አቶ አብርሃም ያየሀና አቶ ገብረመድህን አርአያ በጥቅምት ወር 1982 በመገናኛ ብዙኃን አማካይንት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አሳውቀዋል ። ሁለቱም ሚስጢራቸው በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተደቀነውን ዒራና በዚህ ዒራው ዜሬ መሰረት "ህወሓት" ልዩልዩ ስያሜ በማንጠልጠል የሚጫወተውን መሠረታዊ ዓላማ በተመለከተ ከጋዜጠኞች ጋር ያደረጉትና በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣው ቃለ ምልልስ "የወያኔው ታላቅ ዒራ በቲድሞ አባላቱ ሊጋለጥ" በሚል ርዕስ በሁለት ክፍሎች ታትሟል ። በዚህ እትም ደግሞ በክፍል ፣ እና ፪ ተከፍሎ የንበረው ቃለ ምልልስ በአንድ ላይ እንዲጠቃለል ሆኗል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ክብ ኤብርሃም ያሳየው
የመሰዋዕት
እቃዎች ናቸው ።

ሽምግሌ — ክብ ኤብርሃም ያሳየው ልበቅንነት ሥጦታ ያህል ከእኛ ምንም
ውጭ በሆነው ሁሉን መስዋ ትእዛዙ ከነበረ ወር እኛስ ምንድን ልንደርግለት
ይገባናል። ወደ ክርስቶስ የሚመለስን ሁሉ ምን ዓይነት ሥራ ማሠራት
ይገባናል?

ዘመልከ— በመሠረቱ እኔ በትግራይ ከ ወገር በእድሜ ከፋ ማለ
ተወልድኩ። ከዚያም በኋላ በመተዳር በአዲስ አበባ ተምሬ እስከ ዩኒቨርሲ
ቲ ገብተ ነበር ። በዚህም አጋጣሚ እስከ ዩኒቨርሲቲ ተምሬ መንግሥት
ከሚቀጥረኝ ሳይ ይደርስ ነገረኛው ችግር በማም ያጋጠመኝ ከመንግስት ሠራተኛ
ድጣም አሥቱ በአዲስ አበባ ከተማ ሰሃያ ዓመታት በማለት ተቀምጠው ብዙ
መኖሬ ያሳሰኝ ከወጪተሰባሰቦው ተወልጄተው ሠናቴ በመሆኑ በዘሊያ መንግሥት
ላይ ከሰውተኛ ተታሥውሞ ነበረኛ ።

ከዚያም በኋላ በሰውተኞችና በሠርግ እሰከሰው በሰጀቴ ቁጣር
በእግዚአብሄር መሠረታዊ ሐውጥ ያሳፈጽሙ የሚል እምነት ከመነበረኛ
በተማረውም ሆነ በሥራተኛው ማገለገር እንዳለብኝ. በዚህተኛ ደረጃ
እሳተፍ ነበር ። በሥራተኛ ማገለገር በመቀጠሌም ከሰውተኛ ችግር ደርቦብ
ኛል ። በዚህም በመንግሥት ቁጣጥር ሥር ላይ ፈጠሰኝም ተብተሣፈ
በሚሰጠኝ ከርቻው ። በመጨረሻ በአገርቱፈ ከ ወገር ጀምሬ ከሰዎ ጊዜ
በማሳውተው ነገር ከሰውተኛ ሰዎች ደረስኩኛ ። ይህንን ሰዎች ከመታወም
ፒታማኞችንትና ወንጌሉት ያመጡልኩትን ሕዝብ ቅድ ከሰዎት ሥራት ሰፈት
ከሰደት ወር ሰውን ጣዩ ።

ሰውን እንድሰማው ወንጌሉ ሕጎብ ሰም የሚጋቶሰውን ድርጅት
ሰፈጠው። ይህም ሳልሰማቸው ወንጌሉርት ትጣራይ የሚሰጡ ድርጅት ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

እኔም በትግራይ ጉዳይ ላይ ቀደም ብዬ መሠረታዊ ናቸው ብዬ የማምንባቸው ችግሮች እንዳሉ እገነዘብ ነበር ።

«ሕወሓት» ባጠቃላይ ቆሜለታለሁ ፣ እታገልለታለሁ የሚለውን ዓላማ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ሳይሆን ለትግራይ ችግር መልስ ያስገኛል ብዬ ከማምንበት አንጻር በመካከላችን ያለው ልዩነት እንዳለ ሆኖ በማምንበት ብቻ ኢትዮጵያዊ የሆነ መፍትሔ ሊያስገኝ ይችላል በሚል እምነት የዚሁ ቡድን ዋነኛ ደጋፊ በመሆን ባለፉት ሰባት ዓመታት ያህል ስንቀሳቀስ ቆይቻለሁ ።

በእውነቱ የዚህን ድርጅት አመጣጥ ለመናገር ቀላል ባይሆንም ለሰባት ዓመታት ያህል አብረን ከተጓዝን በኋላ በሙስሙም ለሙጥ ለማምጣትና የተቻለውንም ያህል ኢትዮጵያዊ የሆነ መልክ እንዲይዝ እኔም ሆንኩ ሌሎች ጓደኞቼ ጥረት ብናደርግም ሳይቻል ቀርቷል ። በእዚህ ዓይነት ችግር ላይ እንዳለን በቅርበት አትጣሄውን ለውጠ ለትግራይ ችግር መፍትሔ ለማስገኘት ሳይሆን በተጭኑ ኢትዮጵያ እንድተከፋፈል ፡ እንድትቆራረስና ህልውናዋም ጨርሶ እንዲጠፋ የሚያ ድርግ ማለትም የሌሎች ቡድኖችን ጉዳይ ለማስፈጸም በመሣሪያነት ማገልገል መሆኑን ለመገንዘብ ችያለሁ ። እኔ ብቻ ሳልሆን በነፍተኛ አመራር ላይ የነበሩ ፡ ድርጅቱን የመሠረቱና በቡድኑ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው ያሁኑን ሁኔታ በመረዳት ድርጅቱን ትተው ሲወጡ እኔም ትቼው የግል ሥራዬን መሥራት ጀመርኩ ።

ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት ሱዳን በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ውጥረት ያለበት አገር ነው ። እንኳን ባይተዋርና ስደተኛ ለሆነው ሰው ተርፎ ለሀገሩም ሕዝብ በጣም ከፍተኛ ችግር የደረሰበት በመሆኑ ፡ አየሩም ለጤና የማይስማማ በመሆኑ ሁኔታውም ሆነ አየሩ ለሥራ ወደሚያመች ሥፍራ ተዛውሬ ለመሥራት ስለፈለኩ ፡ በኢትዮጵያ አንድነትም የማያወላውል አቋም ያለኝ በመሆኑ ባጠቃላይም ለትግራይም ሆነ ለተጠረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ያልዋለ ዓላማ በመከተል ከዚያ በፊረሃ የምኖርበት ምክንያት ስላልታየኝ ይህንኑ ለኢትዮጵያ መንግሥት ኤምባሲ አሰረድቼ የኢትዮጵያ ፓስፖርት በማስወጣት ከዚያ ለቅቄ በልዩ ልዩ ቦታዎች ስሠራ ቆየሁ ።

ባለፉት ሰባት ወራት በተለያዩ ቦታዎች የግል ሥራዬን ለመሥራት

t.me/OLDBOOKSPDF

በመካከለኛው ምሥራቅና በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች እየተዘዋወርኩ በምሰራበት ወቅት በአጋጣሚ ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ አስገብቶ የሚያሠራኝ ሥራ በማግኘቱ ስለዚሁ ሥራ አንዳንድ ጥናቶች ለማድረግና ከሰዎች ጋር ለመገናኘት ባለፈው ጠር በራሴው ፈቃድ አዲስ አበባ ገባሁ ። አዲስ አበባ ስለኖርኩ በርካታ ሰዎችንም አውቃለሁ ። ወደ አዲስ አበባ መምጣቴ ብዙዎቹን ሲያስገርም አንዳንዶቹንም አስደንግጧል ። ይህ የሆነበት ምክንያት የታወቀ ነው ። የነበርኩበትንም ሁኔታና ቦታ የሚያውቁ ሰዎች እንዴት እንደመጣሁ ስለገረማቸው ነው ። ይህም ብቻ ሳይሆን ከሰው ጋር በተገናኘሁ ቁጥር በተለያ እኛ የትግራይ ተወላጆች በኢትዮጵያ አንድነት ላይ አደረስነው የተባለው ፈተና በጣም አንገብጋቢና ሕዝቡም በእውነቱ እኛ ኢትዮጵያውያን ሆነን ለኢትዮጵያ አንድነት መናጋት የከፈትነው በር አጣብቂ ያለመሆኑን እየነተፈ ስለሚናገርና ያኸው ሁኔታም የትግራይ ሕዝብ ፍላጐት አለመሆኑን ለማስረዳት የሚጠፋው ጊዜ በጣም ረጅም ነው ።

አንዳንድ ወዳጆቼና የማውቃቸው ሰዎች ግለትም የትግራይም ሆኑ የሌላ ብሔረሰብ አባሎች ይህ የማስረዳቸው ነገር ሌላው ጎብረቲስብ በትክክል ቢገነዘበው ጠቃሚ ይሆናል በሚል በጉ አመለካከት በብሔራዊ ሚዲያ መጠቀም ያለብኝ መሆኑን ብዙ ግፊት አድርገውብኛል ። የእኔ አመጣጥ ለመንግሥት የናሮፓጋንዳ መሣሪያ ለመሆን መጀም ደግም አሁን ያለውን የኢትዮጵያን ሁኔታ ለመግለጽ አይደለም ። ብዙ ሰዎችን ሊያሳምን በሚችል መንገድ ትግራይ ውስጥ ያለው ሁኔታ በሚዲያ ታውቆ ኢትዮጵያ በሚቀጥለው ዘመናት ለረኽም ጊዜ ጠርነት ውስጥ ሊያስገባት የሚችልና አንድነቷን ከከባድ ፈተና ላይ የሚጥል መሆኑን እንዳሳውቅ ብዙ የተማሩና አገራቸውን የሚወዱ ሰዎች ስለገፋፉኝና ወዲያውም እንዚህ ሰዎች ያደረጉትን መገፋፋት በመገንዘብ ይህ ዕድል ሊሰጠኝ በመቻሉ በመካከላችሁ ልገኝ ችያለሁ ።

<u>ጥያቄ</u>፡ በ«ሕወሓት» ዙሪያ ውስጥ በነበሩ ጊዜ የነበረዎት ሚና ምን ነበር? የአመራር አባል ነበሩን?

<u>መልስ</u>፡ «በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ» ውስጥ አባል በነበርኩበት ጊዜ በአመራር ውስጥ አልነበርኩም ። በውጭ አገር የሚሰሩ ብዙ ሥራዎች ስላሉ በዚያ የሚከናወኑትን ተግባራት አከናውን ነበር ። ከዚህ በተጨማሪ በድርጅቱ ውስጥ በአመራር ሁኑ ላይ ያሉ ሰዎች አብዛኞቹ

t.me/OLDBOOKSPDF

ክተ በት ጀምሮ አብሮ አደጉቹና ጓደኞቹ አልፎ ተርፎም በመጽሔቱ የነበሩ ናቸው ። በተለይም «ሕወሓት» የሚለው መጠሪያ ከመሰየሙ በፊት የድርጅቱ ሊቀመንበር የነበረው ወልደሥላሴ ወይም ስብሐት ነጋ የተባለው የአክስቱ ልጅ ነው ። በንቃተ ህሊናም ሆነ በሌላም ነገር በአመራር ላይ ከነበሩት ተመላሚዎች ስለሆንኩ ስለድርጅቱ ብዙ ለማወቅ ዕድሉ ነበረኝ ።

<u>ጥያቄ</u>— የዚህ ድርጅት አፈጣጠር እንዴት እንደሆነ ቢገልጹ ልን? .

<u>መልስ</u>— በዕውነቱ የተሰጠኝ መድረክ ሰፋ ያለ ከሆነ ስለዚህ ድርጅት አፈጣጠርና በየጊዜውም ስሙን የሚለዋወጥበትን ምክንያት እንዲሁም በአሁኑ ሰዓት ያለበትን ሁኔታ በተከክል አንጠርጥሮ ማወጣት የሚቻል ይመስለኛል ።

የትግራይ እንቅስቃሴ በአዲስ አበባ ከተማ ከ1966 1967 ሲጀመር «ማኅበት» ወይንም «ማኅበር ነስገስቲ ብሔረ ትግራይ» በሚል ስያሜ ነው ። ማኅበት በሚል መጠሪያ የተመሠረተው እንቅስቃሴ ዓላማ በትግራይ ሠስተ ያሉትን የብሔረሰብ ችግሮች አውቀን እነዚህን ችግሮች ኢትዮጵያዊ የሆነ መልስ ለማስገኘት በሚል ዓላማ ነበር የተመሠረተው ። ከዚያ በኋላ ይህንን መልስ ለማስገኘት የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር የተመሰኑ ሰዎች በሽሬ በከል ደደቢት በሚባል ቦታ ትግል ጀመሩ ። ስለዚህ እንቅስቃሴ የሚያውቅ ብዙ ሰው አልነበረም ። በጣም ጥቂት የሆኑ ሰዎች ብቻ ነበሩ የሚያውቁት ። ከዚያ በኋላ ድርጅቱን የመሠረቱት ሰዎች በተለይ ደግሞ አረጋዊ በርሄ ከመሥራቾች አንዱና የወታደራዊ ጉዳይ ኃላፊ የነበረው ግለሰብ ባቀረባቸው ዕውሮች እንዳስረዳው ሁሉ «የብሔር ትግል» በማካሄድ በትግራይ "ብሔራዊ ጥያቄ" ላይ መልስ እንዲያገኝ ስትራቴጂው ወይም የመጨረሻ ግቡ ግን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በአከልነት መመሥረት የሚል ነበር ።

እንደምታውቁት የትግራይ ሕዝብ የራሱ የሆነ ብሶት አለው ። በእውሩ በትግራይ ከአድዋ ጦርነት ወዲህ እንኳን የተካሄደውን ሁኔታ ስናይ የአድዋ ፡ የማይጨው ፡ የተምቤንና የሽሬ ከፍተኛ ጦርነቶች የተደረጉት በትግራይ ውስጥ ነው ። ሠራዊቱ ወደዚህ ከልል አገርን ከውጭ ጠላት ለመከላከል ለጦርነት ሲመጣ ለምግብ ማብሰያውም ሆነ ለምሽግና

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰሊላም ንጣር ዛፉንና ቅጠሉን እየቆረጠ ነበር የሚጠቀመው ። በእሱን አጠራሩ የትግሬ ራስ ገዝ ነፍተኛ የኑሮ ችግር የደረሰበት እለል ነው ። በዚህም የተነሣ እነዛቢው በመራቅ ሕዝቡ ወደ ጉረቤት አገሮችና ወደ ተቀረው የኢትዮጵያ ክልል ለመነገዝ ተገደል ። በየትኛውም ክለል ብንሄድ የትግራይ ሕዝብ ያልገባበት ሥፍራ የለም ። ያሀ ራሱ ትልቅ ብሶት አሳድሮ ያለፈ ሁኔታ ነው ።

ከዚህ ሌላ ወላቸውም እንደምትረዱት እኛ ራሳችን አርሰ በርሳችን ስንፋጅ የኖርን ነን ። ትግራይ የኢትዮጵያ አካል እንደመሆኗ መጠን በትግራይ መሳፍንት መነሳል ያነሄድ በነበረው ጦርነት ምክንያት ራሱን የቻለ ቅራኔ ተከስቷል ። ከዚህ በኋላ አገራችን በአፄ ምኒልክ ዘመን መንግሥት የዘመናዊ አስተዳደር ባለቤት የሆንችበት ወቅት ነበር ። ዛሬ ንጉሶ ሥላሴ ድግም የከፋፍለህ ግዛ ሳላማ የሚያራምዱ ስለነበር እንደሌላው በትግሬዎም የብሔረሰብ ጭቆና ነበር ። ምንም እንኳን ከትግራይ ውስጥ በመሣፍንቱና በመኳንንቱ መነሳል የሥልጣን ሽኩቻ ቢነሄድም የመጀመሪያው ወያኔ ተብሎ የሚጠራው እንቅስቃሴ በነዚህ ከፍተኛ ችግር ተፖ ነው ያለፈው ።

የወያኔን እንቅስቃሴ ለመመከት ሳጂኮል ሥላሴ ከእንግሊዞች ጋር በመስማማት ከኤርን አውሮፕላን እያስነሱ ሰላማዊ ሕዝብ ያሰፈጁ ስለነበር በዚህ የተነሳ የትግሬዎ ሕዝብ ብዙ ጊዜ ያሀን እንደ ትልቅ ዘይል አድርጎ ነው የሚያነሳው ። እንግዲህ ውኔዎች እንዲህ ባለበት ወቅት ‹‹ማኅበር ገስገስ ብሔረ ትግራይ›› (ማኅበት) ሲመሠረት በአርቱራዎ ደግሞ ተደም ሰል ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲካሄድ ቀደል ። በዚያን ወቅት ‹‹ማኅበር ገስገስ ብሔረ ትግራይ›› (ማኅበት) ሲመሠረት በመጀመሪያ የሕዝቡን ብሶት አውቶ ያሀንን መሣሪያ ለማድረግ የሞከረው ‹‹ተጋድሎ ሐርነት አርትራ›› (ጀብሃ) የሚሉት ቡድን ነው ። «ጀብሃም» ነሰው ብሶት አንጻር የማኅበት ‹‹ንቅሳቃሴዎችን በማሰልጠን ፡ በማስታጠቅ የትግል ስልት በመንደፍና በመሳሰሉት ንሮች መረጃት ጀመረ ። በዕውነቱ ያህ የ«ጀብሃ» ድርጊት የትግራይን ሕዝብ ችግር ለማስወገድ ወይም ፍትሐዊ መፍትሔ ለመስጠት ታስቦ የተደረገ ነው ብዙ አልገምትም ። ለማኅበትም ከፍተኛ ድጋፍ የሰጠበት ምክንያት የትግራይ ሕዝብ ካል ተንሳሳበአርትራ ውስጥ ያሉ ሁድኞች የተነሱበት ዓላማ ከዳር ሲደርስ እንደሚያችል ስለሚያውቁ ነው ። እንደሚታወቀው እኛና የአርትራ ተወላጅች የሚያቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ራርዑንና የሚያመሳስሉን ነገሮች በርካታ ናቸው ። ትረዚኦምኺ ነን ፣ በጋብቻ እንተሳሰራለን ፣ አንድ ዓይነት ቋንቋ እንናገራለን ፣ አንድ ዓይነት ባህል አለን ፣ የክርስትና የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ይገኙብ ናል ። በዚህ ረገድ «ጅብሃ» «ማንበር ገዐገስኒ ብሐሬ ትግራይን» (ማገብት) በመርዓት እንቅስቃሴው እንደሚጠናከር በማመን ደንግ ሰጥቷል ።

ከዚህ በኋላ ይህ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ላለ «አሕአፓ» ደግሞ ወደ ትግራይ በመጣጣት መሸነ ። ይህም በ«በእሕአፓና» «በተ·ግ·ኤል·ኤፍ·» መካከል ራሱን የቻለ ቅራኔ እንዲፈጠር አደረገ ። «አሕአፓ» ሕዝባዊ መንግሥት ለመመሥረት ከፍተኛ ትግል መካሄድ አለበት የሚል ሃሳብ ያዘ ሲነሳ ፣ «ማገብት» በኋላ«ተ·ግ·ኤል·ኤፍ·» የሆነው ደግሞ እኛ የምናካሂደው «የብሔር ትግል» ነው በሚል በመካከላቸው ልዩነት ተፈጠረ ። በሁለቱ መካከል በተፈጠረው ግጭት «ጅብሃ» ቀድም ሲል ከ«ተ·ግ·ኤል·ኤፍ·» ጋር አለመግባባት በመፍጠሩ «አሕአፓን» ሲረዳ «ሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኦርትራ» ደግሞ «ተ·ግ·ኤል·ኤፍን» በመደገፍ በእንድነት «ጅብሃን» በመምታት ዓላማ ሲቆራኙ ቻሉ ።

በትግራይ ውስጥ የተፈጠረው ድርጅት ከራሱ ከትግራይ ጉዳይ የመነጨ ይሁን እንጂ በአብዛኛው የኦርትራ ድርጅቶች የፈጠሩት ቡድን ነው ። እስካሁን በትግራይ ያለውን እንቅስቃሴ ስንገመግም በኦርትራ ያሉት ቡድኖች ኦርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ያላቸውን ፍላጐት ለማስፈጸም ሲሉ የፈጠሩት መሆኑን እንረዳለን ። ከዚህ በኋላ በ«ማገብት» በራሱ ውስጥ ለኦርትራ ነፃነት መገኘት በማሰብ ሰርገው የገቡ እንዳንድ ሰዎች ነበሩ ። አረጋዊ በርሄ በትረብ ጊዜ ካቀረበው ጽሁፍ መገንዘብ እንደሚቻለው "ማገብት" የሚል እንቅስቃሴ እየተካሄደ ላለ አመራሩ ሳያውቅ ካርቱም ውስጥ አንድ ፕሮግራም ተነደፈ ። ይህም "የማገብት" ፕሮግራም በእነዚህ በምትመሠረት ኢትዮጵያ የትግራይን ችግር ለመፍታት ቀድም ሲል ያቀደውን የሚያረጋግጥ ነበር ። ይህ በሱዳን የተነደፈው ፕሮግራም በጉባኤ ላይ በነበሩ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ በአንመለስ ዜናዊ (የኦርትራ ተወላጅ የሆነ) የተነደፈና በዓላማውም የትግራይ ሪፐብሊክን እንመሠርታለን ፣ የምንታገለው ትግራይን ከኢትዮጵያ ነጥለን ራሱን የቻለ ሪፐብሊክ ለማድረግ ነው የሚል ነበር ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፕሮግራሙ በሱዳን ታትሞ ሲሰራጭ «ኢሕአፓ ዎችን አማኞቻችን በዚህ ላይ በመመሥረት የራሳቸውን ፕሮፓጋንዳ ማካሄድ ጀመሩ ። ይህ ሲሆን በትግራይ ውስጥ በአመራር ላይ ያሉት ሰዎች ፕሮግራሙን አላዩትም ። ድሮም ቢሆን «ማንብት» በአማራ ብሔረሰብ ላይ ያለውን ጥላቻ ለመግለጽና አሁንም በፕሮግራሙ ላይ የትግራይን ሪፐብሊክ እንመሠርታለን ያለው የጠባብ ብሔረተኝነት ትግል ለማካሔድ የተነሳ ነው በማለት «ኢሕአፓ» ቅስቀሳ ማካሄድ ቀጠለ ።

በወቅቱም «የማንብት» አመራር አካሎች ይህ «የኢሕአፓ» ቅስቀሳ ሕዝቡንለማወናበድ ሲባል የቀረበ መሆኑን በትግራይ ውስጥ ግንዛቤ እንዲኖር ጥረት በማድረግ ላይ እንዳሉ የታተመው ፕሮግራም ከሱዳን ደረሳቸው ። ፕሮግራሙን እንደተመለከቱትም እሱ በእነርሱንት የምትመራት ኢትዮጵያን ለመገንባት እንጂ እንዲት «የትግራይ ሪፐብሊክን ለመመሥረት» የሚል ፕሮግራም ትንድፋላችሁ በማለት ሃያቱአችሁን ለእነ መለስ አቀረቡ ። የተሰጣቸውም የማጠንበቂ መልስ ብሔረሰቦች እርስ በርሳቸው ስለማይተማመኑ ሰየብቻ መታገል ስላለባቸውና የራሃብ ሊኩ ምሥረታ አስከመገንጠል ድረስ ይሄዳል በሚል ግንዛቤ ነው ፕሮግራሙን ያወጣነው የሚል ነው ። ወደፊትም በሂደት በማረሚያ መልክ እናወጣዋለን በማለት የማጭበርበሪያ መልስ ሰጥተዋቸዋል ። አረጋዊ ባቀረበው ጽሁፍ ላይም ይኸው ስህተት ከፍተኛ ውዝግብ የሚያስከትል ቢሆንም ባለን የትግል ግንኙነትና ከነበረን የትግል ልምድ ማነስ ወደፊት እርስ በርሳችን ተማምነን ለመኖር ስንል ይህን አልፈነዋል ብሏል ። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች እንደ ኤርትራ ትግራይንም በራሃብሊክ መልክ ለመቅረጽ ያፈልጉ እንደ ነበር መገንዘብ ይቻላል ።

ከዚህ በኋላ የተጠለው «ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ» (ተሓሕት) ነው ። «ተሓሕት» በእነ መለስ ዜናዊ (የቡድኑ የፕሮፓጋንዳና ፖለቲካ ንላፊ) ሥር የሚንቀሳቀስ ሠፕ ትግራይን በጠባብ ብሔረተኝነት ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የተለየ እንደሆነ አድርጉ በማንጸባረት ነበር እንቅስቃሴ ያካሂድ የነበረው ። <u>እራሱ «ተሓሕት» ቀድም ብሎ ከ ሽ በሚሆኑ ኮሚዎች ቀለመጠያት አዘጋጅቶ ሕዝቡ ስለድርጅቱ ያለውን አስተያየት እንዲሰጥ ሞክሮአል ። ሕዝቡም "የትግራይ ሪፐብሊክ ብሎ ነገር የለም ። ትግራይ ከኢትዮጵያ አካል ተንጥላ የምትገኝ አይደለችም"</u>

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚገኙት ሰዎች ሁኔታ ዘርዘር አድርገው ቢያስረዱን?

መልስ፡— በእሁኑ ጊዜ በአመራር ላይ ያሉት ሰዎች በእውነቱ ማንነታቸው የታወቀ ነው ። መለስ ዜናዊ የራሱ የሆነ የቤተሰብ ታሪክ አለው ። እናቱ የኤርትራ ተወላጅ ሲሆኑ የአንድ ደጃዝማች ልጅ ናቸው ። መለስ ወደ ኤርትራ ጉዳይ ስሜቱ የሚያዘነብል ሲሆን ፡ በእሁኑ ሰዓት «የማርክሲስት ሌኒኒስት ሊግ ትግራይ» (ማሌሊት) ዓቢይ አንቀሳቃሽ ነው ። ዓባይ ፀሐዬ የፓርቲው ሲከረታሪ ቢሆንም ፡ ዋናው ሞተሩን የሚያንቀሳቅሰው ግን የኤርትራው ተወላጅ መለስ ዜናዊ ነው ።

የማን ዚዳኔ ሌላው «የማሌሊት» የአመራር አባል ሲሆን ፡ የወሻፅቢያው» መሪ ኢሳይያስ አፈወርቂ የአክስት ልጅ ነው ። ኢሳይያስ አፈወርቂ በእናቱ ትግራይ ነው ። ስለዚህ የማን በከፊል የኤርትራ በከፊል ደግሞ የትግራይ ተወላጅ ነው ማለት ነው ። ሌላው በውጭ ከፍተኛ የፖለቲካ ሥራ በመሥራት በዕርዳታው መስክ ገንዘብ የሚያስገኙላቸው ከቁጥር የማይገባ የትግራይ ዘር ያለውና በኤርትራ ተወልዶ ያደገው ዶ/ር በለጮን እንቋይ የተባለው ነው ። «ማኅበረ ረድኤት ትግራይ» በሚል ስያ እንደሰብአዊ ድርጅት ያለ ከፍል አቋቁሟል ። ሌሎችም ብዙ ቢኖሩም አድርጉ የተባሉትን የሚያደርጉ የትግራይ ልጆች የሆኑ እንደነ ሃይሎም የመሳሰሉት ይገኘባቸዋል ። እንደነ ተወልደ ገብሩ የመሳሰሉ ጤናማ አመለካከት ያላቸው የትግራይ ተወላጆችም በዙድኑ ውስጥ አሉ ። ዛጠቃላይ የ«ሕወሓት» አመራር እጅግ በረቀቀ ዘዴና ሰልት በ«ሻዕቢያ» ተተብትቦ የተያዘ ነው ።

ጥያቄ፡— «ሕወሓት» በየጊዜው የተለያየ ዓላማ ይዞ የሚንቀሳቀስ እንደመሆኑ በተለይ በአሁኑ ሰዓት በትግራይ ሕዝብ ስም የሚያራምደውን የተሳሳተ ዓላማ እናንተ በዙድኑ ውስጥ አባል የነበራችሁና የትግራይ ተወላጆች የሆናችሁት እንዲት ትመለከቱታላችሁ?

መልስ፡— በእኛ ስም በሚደረግ እንቅስቃሴ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋራ ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ እንዳንገባ እሰጋለሁ ። እዲስ አበባ ብዙ የመሀል አገር ተወላጅ ጓደኞች አሉኝ ። እነሱም እናንተን የመሰሉ ሰዎች እያሉ እንዴት እንዲህ ይደረጋል? በትግራይ ሕዝብ ስም እንዴት ኢትዮጵያን የሚከፋፈል ድርጊት ይካሄዳል? እያሉ ይጠይቁኛል ። በውጭም የሚያውቁን ሰዎች እንዴት እንዲህ ዓይነት አሳዛኝ ነገር ትፈጽማላችሁ በማለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ይወቅሱናል ። እኛም በምንዘዋወርበት ሥፍራ ሁሉ በትግራይ ሕዝብ ስም የሚካሄደው እንቅስቃሴ ቅጥፈት የተሞላበት መሆኑን በግል ከማስረዳት አልተቆጠብንም ። በእሁኑ ጊዜ ይህን በትግራይ ሕዝብ ስም ዓላማውን ስቶ የሚካሄደውን እንቅስቃሴ የሚቃወም ቡድን ተፈጥሮአል ። እኔ በዚህ ቡድን ውስጥ ባልኖርም ሌሎች በውስጡ የሚገኙ አባላት ትክክለኛ ውን ሁኔታ በአውሮፓ ፣ በሰሜን አሜሪካ ፣ በአፍሪካና በሌሎችም አገሮች በመዘዋወር እያስረዱ ይገኛሉ ።

ዋናው ቁምነገር ግን በየዕለቱ በሚፈጠሩ ቡድኖች ለትግራይ ሕዝብ የሚያመጡለት ተጓምር ሊኖር አይችልም ። እስካሁን የሞተውም ፣ የገደለውም ፣ ከቤት ንብረቱ የተፈናቀለውም ኢትዮጵያዊ ነው ። ወንድማማቾች ናቸው የተላለቁት ። መፍትሔው ሁላችንም በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን ለሕዝቡ ሠላም ለማስገኘት ጥረት ማድረግ ነው። ሰላም በአሁኑ ጊዜ በዓለም ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ዓቢይ ጉዳይ ነው ። ሁላችንም ተወቃቅሰንና ተስማምተን ለትግራችን መፍጅ አንድ ቁልፍ ማበጀት አለብን ነው የምለው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- «ሕወሓት» ከአነሳሱ የትግራይ ሪፐብሊክ ለመመሥረት አሁን ደግሞ «የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት» እንደሚታገል የገለጸ ሲሆን፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራን መገንጠል የሚደግፍ መሆኑን ይናገራል ። ስለዚህ እነዚህ እቋሞች እርስ በርሳቸው ሊቃረኑ አይችሉምን? ይህን በተመለከተ ያለዎትን አስተያየት ቢሰጡን ?

<u>መልስ</u>፡- <u>የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለመመሥረት የሚፈልግ ማንኛውም ከፍል መጀመሪያ ኢትዮጵያዊ መሆን አለበት። «ሕወሓት» ለመመሥረት የተነሳው ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤርትራን ለብቻ ገንጥሎ በማስቀመጥ ነው ? ወይስ የኤርትራ የኢትዮጵያ አካልነት እንደተጠበቀ ነው ? የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መነሳት ያለበት ዓቢይ ጉዳይ ነው ። በ«ሕወሓት» ፕሮግራም ውስጥ «የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው» በሚል ሐረግ የኤርትራን መገንጠል ይደግፋሉ ። በሌላ በኩል ደግሞ በዚሁ ፕሮግራማቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን ያረጋግጣሉ ። እንግዲህ እነዚህን ሁለት ዓቢይ ነጥቦች ስናጤን የ«ሕወሓት» ሰዎች ትልቅ ቅራኔ ውስጥ መውደቃቸውን እንረዳለን ።

የኤርትራ ጥያቄ «የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው» ይላሉ ። በኤርትራ ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገብቶታለቀውየትግራይ መጣት ብዙ መሆኑ መጠቀስ ይኖርበታል ። ስለዚህ እንዚህ ሰዎች ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ነገ ከኢትዮጵያውያን ጋር ተቀምጠው በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ እንድ ውሳኔ መስጠት ሊኖርባቸው ነው ። በኤርትራ ጉዳይ ላይ ይህን መንግሥት ከሚቃወሙ ኢትዮጵያውያን ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር ብዙ የሃሳብ ልውውጥ እናደርጋለን ። በዚህም በኤርትራ ጉዳይ ላይ ያላቸውን በጎ አቋም እናውቃለን ። እንግዲህ ይህ ጎደኝነት አቋም ካላቸው ወገኖች ጋር እነ መለሰ ዜናዊ ፡ ሰለሞን እንቋያ ፡ የማነ ኪዳኔ ቁጭ ብለው ሲነጋገሩ ነው ማለት ነው ። ይህ ከሆነ እነሱን ጨምሮ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚነጋገር ሰው ለምሣሌ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ስለሆነች ይህን ለማስከበር እንዋጋ ቢል «የሕወሓት» ሰዎች የሚኖራቸው መልስ «እኛማ ትናንትና ኤርትራ ነፃ ትውጣ ብለን ስለነበር ኤርትራ በፍጹም ነፃ መውጣት ይኖርባታል ነው» የሚሉት ። እንግዲህ እነሱ እንደሚሉት ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመሥረት ቆመናል፡ ኢትዮጵያውያን ነን ፡ እያሉ ለኤርትራ ነፃ መውጣት ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሆነው ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ሊዋጉ ነው ማለት ነው ። በኤርትራ ጉዳይ ላይ በአሁኑ ጊዜ የሰላም ውይይት እየተካሄደ ሳለ በትግራይ ውስጥ ለኤርትራ ነፃ መውጣት ውጊያ የተከፈተ መሆኑን ስንመለከት በጣም የሚያሳዝንና የሚያንገበግብ ነው ። በኢትዮጵያዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለመሰርቱ እየፈለጉ ኤርትራ የሉለች በት ሪፐብሊክ ለመመሥረት ከሆነ የሚታገሉት እሰቲ መፈረሻቸውን ለማየት ይብቃን ።

<u>ጥያቄ</u>፡ «ሕወሓት» በየጊዜው ዓላማውን እየለዋወጠ የሚሄድ በት ምክንያት ምንድን ነው ?

<u>መልስ</u>፡ ቀደም ብዬ ለመናገር እንደሞከርኩት <u>«ሕወሓት» የትግራይን ችግር ኢትዮጵያዊ በሆነ መልኩ መፍትሔ ለማስገኘት ሳይሆን «የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል» እንዲሉ ኤርትራ ነፃነቷን እንድታገኝ በተሸረበው ሤራ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው ። «ሕወሓት» የትግራይን ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ብሔረሰብ ጋር ከፍተኛ ትራኔ ውስጥ ለመክተት በተዘጋጀ ሰዎች የሚመራ ነው ።</u> ለምሣሌ አሁን ያገረው ወደ አዲስ አበባ ባልመጣም በድራማ መልክ ለትስቀሳ የተዘጋጀ አንድ ካሴት ከር አለኝ ። በድራማውም መካከል የ«የሕወሓት» አባላት

t.me/OLDBOOKSPDF

ገብቶታለቀውየትግራይ መጣት ብዙ መሆኑ መጠቀስ ይኖርበታል ። ስለዚህ እንዚህ ሰዎች ኢትዮጵያዊ ከሆኑ ነገ ከኢትዮጵያውያን ጋር ተቀምጠው በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ እንድ ውሳኔ መስጠት ሊኖርባቸው ነው ። በኤርትራ ጉዳይ ላይ ይህን መንግሥት ከሚቃወሙ ኢትዮጵያውያን ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር ብዙ የሃሳብ ልውውጥ እናደርጋለን ። በዚህም በኤርትራ ጉዳይ ላይ ያላቸውን በጎ አቋም እናውቃለን ። እንግዲህ ይህ ጎደኝነት አቋም ካላቸው ወገኖች ጋር እነ መለሰ ዜናዊ ፡ ሰለሞን እንቋያ ፡ የማነ ኪዳኔ ቁጭ ብለው ሲነጋገሩ ነው ማለት ነው ። ይህ ከሆነ እነሱን ጨምሮ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የሚነጋገር ሰው ለምሣሌ ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ስለሆነች ይህን ለማስከበር እንዋጋ ቢል «የሕወሓት» ሰዎች የሚኖራቸው መልስ «እኛማ ትናንትና ኤርትራ ነፃ ትውጣ ብለን ስለነበር ኤርትራ በፍጹም ነፃ መውጣት ይኖርባታል ነው» የሚሉት ። እንግዲህ እነሱ እንደሚሉት ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመሥረት ቆመናል፡ ኢትዮጵያውያን ነን ፡ እያሉ ለኤርትራ ነፃ መውጣት ደግሞ ኢትዮጵያዊ ሆነው ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ሊዋጉ ነው ማለት ነው ። በኤርትራ ጉዳይ ላይ በአሁኑ ጊዜ የሰላም ውይይት እየተካሄደ ሳለ በትግራይ ውስጥ ለኤርትራ ነፃ መውጣት ውጊያ የተከፈተ መሆኑን ስንመለከት በጣም የሚያሳዝንና የሚያንገበግብ ነው ። በኢትዮጵያዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለመሰርቱ እየፈለጉ ኤርትራ የሉለች በት ሪፐብሊክ ለመመሥረት ከሆነ የሚታገሉት እሰቲ መፈረሻቸውን ለማየት ይብቃን ።

<u>ጥያቄ</u>፡ «ሕወሓት» በየጊዜው ዓላማውን እየለዋወጠ የሚሄድ በት ምክንያት ምንድን ነው ?

<u>መልስ</u>፡ ቀደም ብዬ ለመናገር እንደሞከርኩት <u>«ሕወሓት» የትግራይን ችግር ኢትዮጵያዊ በሆነ መልኩ መፍትሔ ለማስገኘት ሳይሆን «የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል» እንዲሉ ኤርትራ ነፃነቷን እንድታገኝ በተሸረበው ሤራ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው ። «ሕወሓት» የትግራይን ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ብሔረሰብ ጋር ከፍተኛ ትራኔ ውስጥ ለመክተት በተዘጋጀ ሰዎች የሚመራ ነው ።</u> ለምሣሌ አሁን ያገረው ወደ አዲስ አበባ ባልመጣም በድራማ መልክ ለትስቀሳ የተዘጋጀ አንድ ካሴት ከር አለኝ ። በድራማውም መካከል የ«የሕወሓት» አባላት

t.me/OLDBOOKSPDF

በውጊያ ላይ ሳሉ ደጀን ካለው ጎደላቸው ጋር በራዲዮ ግንኙነት ሲያደርጉ «አማራ ከሆነ እንዳትለቀው ፈሪ ነው—» የሚል ቃል ይገኝበታል። ሌላም በቪዲዮና በካሴት የተቀረፀው ዘፈኖቻቸውም ቢሆኑ «አማራ ገዢዎቻችን—» በሚል በጠባብ ብሔረተኝነት ቃላት የታጀቡ ናቸው። እውነት ለመናገር ጉጂም፣ ጉንደር መይንም ከዚህ ከአዲስ አበባ ደብረ ብርሃን መስመር 80 ኪሎ ሜትር ብንሄድ የምናገኘው እጉላ የለበሰው መንዜና ተጉለቱ ሁሉ ጨቋኝ ነው ሊባል ነው? እዴ ጎደለ ሥላሴ አማርኛ ተናግረው በመጨቆናቸው የአማራ ብሔረሰብ በሙሉ ጨቋኝአል ብለን መናገር በዕውነቱ እጣብብ አይደለም።

ባሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉት ቤተክርስቲያናት የአማራና የትግሬ ተብለው ተለይተዋል። በጣም የሚያሳዝን ነው። እኔ እዚህ በኖርኩበት ጊዜ በትግሬነቱ ምንም የደረሰብኝ ነገር የለም። ምናልባት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንደሚያጋጥመው ችግር ደርሶብኝ ካልሆነ በስተቀር። ትግሬ ወይም የኤርትራ ተወላጅ የሆነ ሁሉ በሌላው ወገን ምንም የደረሰበት ነገር እንደሌለ ስለዕውነት ሰል እመሰክራለሁ። የትግራይ ተወላጆች ብንሆንም ከሌሎች ብሔረሰብ ሴቶች ጋር ጓደኝነት መስርተናል፣ ተጋብተናል፣ ወልደናል፣ እኛ በከፈትናቸው ሆቴሎች ሌሎች የብሔረሰብ አባላት እንመገብም በማለት ረግጠው አልወጡም። ባጠቃላይ ፀረ—ትግሬና ፀረ—ኤርትራ እንቅስቃሴ እንደሌለ ማንኛውም ቅን ዜጋ የሚረዳው ነው። ዘረኝነት በጣም አደገኛ ሁኔታን የሚያስከትል መሆኑ እየታወቀ፣ ዘፈኖቻቸውም ሆኑ መፈክሮቻቸው ሁሉ ፀረ አማራ ቅስቀሳ ያራምዳሉ። ስለዚህ በጣም የሚያሳዝነው ነገር የሚፈለገው እርስ በርሳችን እንድንተላለቅ ነው።

በአንድ ወቅት በስደት ላይ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የሚደርስብንን ችግር በተደራጀ መልክ ለማስወገድ እንዲቻል ማኅበር ለማቋቋም ፈለግን። በዚህ ወቅት የገጠመን ችግር የማኅበሩ መጠሪያ ምን ይሁን? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት የተፈጠረው ሁኔታ እጅግ አድርጉ የሚያሳዝነኝ ነው። ይኸውም ከፊሉ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሌላው ደግሞ የአሮሞ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ስደተኞች ማኅበር መባል አለበት በሚል ንትርክ መፈጠሩ ነው። አንድ የአሮሞ ብሔረሰብ አባል አግኙተን ስለ ሁኔታው ስናነጋግረው ይህ ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ሳይሆን የውጭ ባህርይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያለው ሁኔታ ነው የሚል መልስ የሰጠንን ሳስታውስ በጣም ቅር ይለኛል። እኛ እዚህ እርስ በእርሳችን ስንተላለቅ አውሮፓውያን በሚተዳደሉት ምስትና አራት ዓመታት አንድ ለመሆንና የጋራ ገንዘብ ለማውጣት እየተዘጋጁ ነው። ስለዚህ ይህንን እጅግ አስከፊና አሳሳቢ የሆነውን የጦርነት፡ የዘረኝነት ስሜት አንድ ቦታ ላይ ማቆም አለብን። የፈለገው ነገር ይሁን እንጂ እኛ ኢትዮጵያውያን ሀልውናችንን ማረጋገጥ አለብን።

<u>ጥያቄ</u>፡- ይህ የትግራይ የወንበዴ ቡድን በአሁኑ መቅት በጉንደርና በመሎ የሚያደርገው እንቅስቃሴ «የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር» በሚል ስም ነው። ይህ እየደረሰ ያለው ጥፋትን የማዘመት ድርጊት አቅጣጫው ወይም አዝማሚያው ወዴት እንደሚያመራ ያለምትን አስተያየት ቢገልጹልን ?

<u>መልስ</u>፡- ይህን ለመመለስ አስቸጋሪ አይደለም። አሁን ወደ ጉንደርና ወደ ወሎ የተደረጉት እንቅስቃሴዎች በጣም ስትራተጂያዊና ተንኮል የተሞላባቸው ናቸው። በእንዚህ አካባቢዎች እንቅስቃሴ የተጀመረው የሰላሙ ጥረት በተጀመረ ማግስት ነው። ይህ ማለት የኤርትራን መንግስት የትግራይ ወንበዴ ከልብ የሚደግፈው ለመሆኑ ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ሊኖር አይችልም። <u>በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም በሚፈልግበትና በኤርትራ ለ28 ዓመታት የቆየውን ችግር ለመፍታት የጉላ እንቅስቃሴ ሊሚያደርግበት ሰዓት የትግራይ ወንበዴ በጉንደርና በወሎ የጀመረው እንቅስቃሴ ተደም ሲል የተወነለበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚሯሯጥ መሆኑን ያመለክታል።</u> ለ28 ዓመታት ያለፈው ሕይወት የድሃው ሕዝብ ነው። ያለቱት ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ናቸው። ስለዚህ በበኩሉ በእድርባይነት ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀመረው የሰላም ጥረት እስኪሳካ ፋታ ሊያገኝ ይገባል የሚል እምነት አለኝ። በዚህ አስቸጋሪ ወቅት በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ የምናስቀምጣቸው ጉዳዮች አሉ። <u>መጀመሪያ የሀገርን አንድነት መጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው።</u> አሁን «ሻዕቢያ» ብርጌዶቹን ወደ ጉንደርና ወደ ወሎ በመላክ በዚህ ማርማር ሰዓት ኤርትራን ነፃ ለማውጣት ይሯሯጣል። በማንኛውም የሽምቅ ውጊያ ታሪክ ውስጥ ወንበዴ ከተማ ይዞ ሲያስተዳድር ሰምተንም አይተንም አናውቅም። ጉራማ ሞታት ስንዝር ማምለጥ ነው ተግባሩ። አሁን እንደምናየው ትግራይ በድርቅ የተጎዳ ክልል ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወንበዴውም ማስተዳደር ስለማይችል ሕዝቡን በመሰብሰብና በማስታጠቅ እዚህ በረሃብ ከምታልቅ ወደ ወሎና ጐንደር እየሄድክ ዘርፈህ ብላ እያለ በማዝመቱ ሰላማዊ ሰዎች ሕይወታቸው እያለፈ ፡ ከቤት ንብረታቸው እየተፈናቀሉ ለከፋ ችግር ተዳርገዋል ። ይህ ዘርፈህ ብላ ለእነ መለስ ዜናዊ ወይም ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ ሊጠቅም ይችላል ። ይሁን እንጂ ነገ የትግራይና የወሎ ሕዝብ አብሮ ነው የሚኖረው። ስለዚህ የሚያስከትለውን አደጋ አርቀው አለመመልከታቸው የሚያሳዝን ነው ። ያም ሆን ይህ የ«ሕወሓት» የአሁኑ ሩጫ ከ«ሻዕቢያ» በሚደረግለት ድጋፍ የኤርትራን ነፃነት ዕውን ለማድረግ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። በጦርነት በአንድ ቀን ብዙ ነገር ማጥፋት ይቻላል ። ነገር ግን ያን በአንድ ዕለት ያጠፋነውን ንብረትና ሕይወት መልሰን ለመተካት ብዙ ጊዜ እንደሚወስድ ማወቅ ይኖርብናል ።

ጥያቄ፡— በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምን በከፍተኛ ደረጃ ይፈልጋል ። መንግሥት ችግሩን በሰላም ለመፍታት ብዙ ጊዜ ጥረት አድርጓል ። ይህንን ጥረት እንዴት ይመለከቱታል ?

መልስ፡— ማንኛውንም ቅራኔ በሰላም ለመፍታት መቻልን የመሰለ ትልቅ ጉዳይ የለም ። ጦርነት ሕይወትንና ንብረትን ከማጥፋቱም በላይ ለውጭ ጠላት በር ይከፍታል ። በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከኤርትራ ተቃዋሚ ቡድን ጋር በአትላንታ የጀመረው የሰላም ውይይት እኛ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል በጦርነቱና በድርቁ ሳቢያ ዕርዳታ ሲያደርጉልን የቆዩትን የውጭ አገር መንግሥታትና ሕዝቦችን ጭምር ያስደሰተ ርምጃ ነው ። የአትላንታው ውይይት ሲጀመር ኬንያ ነበርኩ ። በዚያ የሚገኙ ኬንያውያን ወደ እኔ በመምጣት እንኳን ደስ ያለህ ፡ ለምንድነው እርስ በርሳችሁ የምትተላለቁት? እያሉ ይሰሙኝ ነበር። ሰላም ባለመኖሩ ልጆቻችን አልተማሩም ፡ በየጫካው ነው ያሉት ። ኧኛ አውን አወናብድን ፡ አሥበርብረን መቸር አንሸሳለን ፡ አኛ ሰናልፉ አንዚህ ልጆች ሜዳ መቅረታቸው ነው ። ስለዚህ ሰላም ለሁሉም ወሳኝ ነው። እኛ የትግራይ ሰዎች አዕምሮአችን ትክክል የሚሠራ ከሆነ ለሰላሙ እርምጃ መላክት ረጋ ብለን ልንወያይና ለጥረቱ ውጤት ማማንት የበኩላችንን ድጋፍ ልንሰጥ ይገባል ።

ጥያቄ፡— ራሱን «ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ ነኝ» እያለ የሚጠራው ፀረ—ሕዝብ ቡድን የሚያካሂደው የጥፋት ተልዕኮ ከጮኑ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ፦ የእኔቅድስት መንግሥት በሰማይ የሕንፃችንን ከፍል ችግር በሰማይ ለመፍታት በተዘጋጀም ከአፈርቅራ ተቀናቃኝ በድን ጋር መታደስ በማድረግ ላይ እያለ ለምንድነው «ሕዝቦች» ባሉት ጊዜ መርጋት ለማለፍ የሚቸኩረው ?

መልስ፦ ባለፉት ጊዜ መርጋት የፈጸመበት ምክንያት ግልጽ ነው ። ትክክል ሲሉ ለመገለጽ ምክረአእሊው ። እንደሚታወቀው መንግሥት በመሻሻሊያው ጋር በጠየቁ መታደስ ጅምሮው ። «ሕዝቦች» የመሻሻሊያ ቡችላ ወይም ተቀናቃኝ በመሆን በዘሀበ መካከል ግርግር በመፍጠር ለአፈርቅራ ገዢ መወጣጫ ታጣቂዎቹን ለማፈናቀሉ በመፈለጉ ነው ። የእኔቅድስት መንግሥት የአፈርቅራም ሠንዳቅሚኒስቱ አቶ እሸቴ ጀመረ ብለው ያምናሉ ። ጀነራል ፃድቃ ከሥልጣን ተነስተው የመከላከያ» ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ ። ከዚህ ጀምሮ ጀነራል ፃድቃ ከአፈርቅራ ጋር ያላቸው ግንኙነት ቀስ በቀስ እየቀዘቀዘ ሄደ ።

መንግሥት የይለፍና በዚያ የተቀመጡትን የ«ማሌሊት» ሰዎች ማነጋገር ይኖርብኛል ማለት ነው ። እነዚህ ሰዎች ደግሞ በጠባብ ብሔርተኝነት ስሜት የሚሰበሰብ ብዙ ገንዘብ ስለሚይዙ በየቦታው ቅምጥ በማስቀመጥና ውስኪ እንደ ውሃ በመቅዳት ሲዝናኑ ስለማይ ዓባይ ዐሐዩን ለማግኘት ወደ ትግራይ ከሄድኩ ይህን ጉዳቸውን የማጋልጥ አድርገው ስለሚገምቱ ሊተባበሩኝ አልፈለጉም ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከኤርትራው ችግር በፊት ከትግራይ ሁድን ጋራ የሰላም ውይይት ለማድረግ የበኩሉን ጥረት አድርጎ ነበር ። ይህን እኔም የተሳተፍኩበት ስለነበረ የማረጋግጠው ዐቅ ነው ። ባጠቃላይ «ሕወሓት» እሁን የሚያካሂደው ጦርነት የሰላሙን ጥረት ለማደናቀፍ ነው ።

ጥያቄ፦ መቼ ነው እርስዎ የድርጅቱ ዓላማ ወደ ስህተት እንደሚያመራ አውቀው ከሁድኑ የወጡት?

መልስ፦ እ·ኤ·አ· በ1988 መጀመሪያ ላይ ነው ። ሁኔታውን መበላሸት የጀመሩት ግን እ·ኤ·አ ከ1986 ጀምሮ ቢሆንም ለማወቅ የምፈልጋቸው ነገሮች በመኖራቸውና በውስጡ በመኖየት እንዳንድ ነገር ለመሥራት ይቻላል በሚል እምነት እስከተጠቀሰው ጊዜ ድረስ ስመቆየት ተገድጀለሁ ። ስለዚህ ድርጅቱን ትቼ ከወጣሁ አንድ ዓመት አልሞላኝም ማለት ነው ።

ጥያቄ፦ ድርጅቱን ትተው በመውጣትም በእርስዎ ላይ አደጋ ለመጣል አልሞከሩም?

መልስ፦ በእኔ ላይ ባይሆንም በሌሎች ሰዎች ላይ ሞክረዋል ። ለምሳሌ አንድ ሰው የአረጋዊ በርሄ የእህቱ ልጅ በመሆኑ ምክንያት ብቻ (ስለፖለቲካም ብዙ ዕውቀት የሌለው ነው) አሳንሰው አሥረውት ነበር ። በእኛና በውጭ የሰብአዊ ድርጅቶች ጥረት ከብዙ ስቃይ በኋላ ልናስለቅቀው ችለናል ። እኛ ሳናውቅ የተገደሉና የታፈኑ ሰዎች በርካታ ናቸው ። በእኔ ላይ ግን ይህን ማድረግ አይችሉም ። ምክንያቱም ከዘረኛው የምናርበትጊዜ«የማሌሊት»ካድሬዎችሊኖሩትችሉየተሻለአቅም ስለሪኝ ። ከብዙ ሱዳን ባለሥልጣኖች ጋር ስለምተዋወቅ ከእኔ ጋር እንዲህያለ ጨዋታ መጫወት አይችሉም ። ከትግራይ ሕብረተሰብም ሆነ ከሁንኛውም ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ጋር የተሻለ ቅርበት ስለነበረኝና

t.me/OLDBOOKSPDF

በሌላም ሌላ ምክንያት እኔን መንካት አይፈልጉም ። በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይም ያለኝ አቋም የብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን አቋም በመሆኑ በእኔ ላይ እዩጋ ቢያደርሱ ሌላ ችግር ስለሚያስከትልባቸው አይደፍሩኝም ።

ጥያቄ፡- «በሕውሓት» ቡድን ውስጥ ዲሞክራሲ አለወይ? ከአለ ምን መልክ አለው?

መልስ፡- ስለ ድርጅቱ ድክመት የሚናገር ካለ ይገረፋል ፥ ይገደላል ። «ማሌሊት ሲጋለጥ» በሚል ርእስ በግደይ ዘርዓጽዮን (የ«ሕወሓት» ም/ሊቀ መንበር የነበረ) ያዘጋጀውና አረጋዊ በርሄ «ማሌሊት ዘላሊ» በሚል ያቀረበው ጽሑፍ የ«ሕወሓት»ን አጠቃላይ ታሪክ ከእነ ድክመቱ የሚዳስሱ ነበሩ ። ሆኖም በ«ማሌሊት» በኩል መልስ አልተሰጠም ። አረጋዊ በዚህ ላያበቃ ግልጽ ደብዳቤ ለ«ማሌሊት» በማስተላለፍ እናንተ በምትመርጡት ቦታ ተገናኝተን እንወያይ ቢላቸው አሻፈረኝ ብለዋል ። ስለዚህ እንድ ድርጅት ዲሞክራሲያዊ ነኝ ካለ በውስጡ ከነበሩት አባላት ለተጻፈ ጥያቄ ወይም ሂስ መልስ መስጠት ነበረበት ። ስለዚህ <u>በ«ሕወሓት — ማሌሊት» ውስጥ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ዲሞክራሲ የሚባል ነገር ፈጽሞ የለም</u>።

ጥያቄ፡- በ«ሕወሓት» ሥር የተሰባሰበቡት አባላት እንደነዚህ ዓይነት ሁኔታዎችን አያውቁም ማለት ነው?

መልስ፡- ሁላችንም አንድ ማወት የሚገባን ነገር አለ ። ይኸውም የሕዝባችን ንቃተ ሕሊና ደረጃ ዝቅ ያለ መሆኑን ነው ። ባለፉት 15 ዓመታት ትንሽ ለመንቀሳቀስ ሞክሮን እንጂ ሕዝቡ ስለ ፖለቲካ ምንነት የጠለቀ ዕውቀት የለውም ። በ«ሕወሓት» ውስጥ በአባልነት የተመለመሉ ውና የሚዋጋው የነበሬ ልጅ ነው ። በፖለቲካ ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ ሽኩቻዎችን ፥ ሻጥሮችንና ውጣ ውረዶችን ለገንዘብ አይችልም ። ዕድሉም የለውም ። ሌላው ቀርቶ በተወሰነ ዕድሜ ክልል ውስጥ የኢትዮጵያን ራዲዮ ማዳመጥ የማይፈቀድበት ጊዜ አለ ። እኔ የምሸርባቸው ረቂቅ ነገሮች ታች ላለው ሕዝብ ግልጽ ሊሆኑ አይችሉም ። ስለዚህ እነዚህ የነበሬ ልጆች ስለሆኑ ማንዘቢያቸው በጣም ዝቅተኛ ነው ። ብዙዎቹ ደግሞ ወጣቶች ናቸው ። የእነዚህን መሣሪያ ሥነልቦና በረቀቀ ዘዴ ይሰልቡታል ። ባሬ በትግራይ ውስጥ ሲጋራ የማያጨስ ወይም የማያጨስ የነበሬ ልጅ የለም ። ወንድና ሴት ራቁታቸውን በወንዝ ውስጥ ይዋኛሉ ። ይህ «ዕድገት» መሆኑ ነው ። እንደፈለጉት ከዚተኃብ ቁጥጥር ውጭ መሆኗን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ነፃነት ትቆጥረዋለች ። ወንዱም እንደዚሁ ነው ። በአፍላ ዕድሜው ጠመንጃ ሲሰጠው በጀብደኝነት በመስከር ለጥፋት ይሰለፋል ።

ጥያቄ፡- ዛሬ በ«ሕወሓት» የጥፋት ድርጊት የትግራይ ሕዝብ ለስደት ፣ ለረሃብና ለችግር ተጋልጧል ። ለሕዝብ ቆሜያለሁ እያለ ይህን ዓይነት እስከፊ ድርጊት በመፈጸም ላይ ስለሚገኘው የትግራይ ወንበዴ ቡድን እናንተ በውስጡ የነበራችሁ ሰዎች ያላችሁ አስተያየት ምንድ ነው?

መልስ፡- የትግራይ ገበሬ አካባቢው በድርቅ የተጠቃ በመሆኑ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነው የሚኖረው ። «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ ፣ አሁን ደግሞ ለዕልቂትና ለመከራ አሳልፈው የሰጡት የ«ሕወሓት» መሪዎች ለከፉ ረሃብና ስደት ዳርገውታል ። በጣም የሚያሳዝነው ግን በድርቅ ለተጐዱ የትግራይ ሕዝቦች ከውጭ በርዳታ የሚመጡ አልሚ ምግቦች ፣ ፈርቃፈርቆችና ሌሎችም በካርቱም ለሱዳኖች ሲሸጥ በዓይናችን ተመልክተናል ። እዚህ ላይ ላንሳ የምወደው ፣ በትግራይ በደረሰው ድርቅ ሳቢያ እያሴ ወገኖቻችን ከሞት አፋፍ ላይ በሚገኙበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት እነዚህን ሰዎች ለም ወደሆኑት የአገራችን ክልሎች በማጓጓዝ ላይ በነበረበት ወቅት «ሕወሓት-ማሌሊት»ም ሆነ የምዕራብ ዜና ማሰራጫዎች ድርጊቱን ያወግዙ ነበር ይህም መንግሥት ሕዝቡን ለመበታተን ሆነ ብሎ ያደረገው ዘዴ ነው በሚል ነበር ቅሰቀሳ ይካሔድ የነበረው ። በነገራችን ላይ ከትግራይ ወደ ወለጋ የተንቀሳቀሱት ሰፋሪ ወገኖቻችን እዚያ ሲደርሱ ማርና ቅቤ ዘንበላቸዋል ብዬ ይፍራ አልናገርም ። ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል ። በቂ ቅድመ ዝግጅት ተደርጐ የተሻለ ሕይወት እንዲመሠርቱ ለማድረግ ደግሞ መንግሥት በጦርነትና በሌላም ምክንያት አቅሙ የጐላ እንዳልነ በረም አውቃለሁ ። ነገር ግን በዚሁ በድርቅ ምክንያት «ሕወሓት» ግማሽ ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ወደ ሱዳን አምጥቶ ሲያስፍር ሔጂ እንደተመለከትኩት ከሆነ በዕውነቱ እንደ የትግራይ ዘመዴ ሱዳን ከሚመጣ ወደ ወለጋ ቢሔድ እመርጣለሁ ።

በእውነት ለመናገር ቢያንስ ቢያንስ ወለጋ ያለው አየር ለወገኖቻችን እጅግ በጣም ተስማሚ ነው ። የሱዳን አየር ለኑሮ በጣም አስቸጋሪ ነው ። አንዳንድ ሰዎች ስለ ሱዳን አየር ሁኔታ ሲናገሩ በዓለም መጀመሪያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወይም መጨረሻ የተፈጠረ አገር ነው ይላሉ ። ከትግራይ ወደሱዳን የተወሰዱትም ፎቶግራፍ ተነሥተው ከዓለም ጎብረተሰብ ገንዘብ ለመለመን በመጣሪያነት እንዲያገለግሉ ነበር ። በተገኘው ገንዘብ «ማርክሲስት ሌኒንስት ፓርቲ (ማሌሊት)» ነው የተመሠረተው ። እኛ ማርክሲስት ፓርቲ በአገራችን መች አጣንና ነው ፓርቲ የሚመሠረተው? ዛሬ «ሕወሓት» ገበሬው ከብት በስጦታ አቀረበልን የሚለው ውሸት ነው ። የትግራይ ገበሬ የሚበላው የለውም ። ከብቱን ቀማነው ካልሆነ በስተቀር ሰጥቶናል የሚለው ቅጥፈት ነው ። ዘመዶቻችን እኛ ወደአለንበት ስለሚመጡ ያጫውቱናል ። ምን አመጣብን ነው የሚሉት ።

ጥያቄ፡- «ሕወሓት» በአውኑ ሰዓት ከተራ ውንብድና ጥቃት ግልጽ ወደሆነ ወረራ የተሸጋገረ ይመስላል ። ስለዚህ ከዚህ ድርጅት በስተጀርባ ምን ዓይነት ድጋፍ አለ? ድጋፉስ ከየት ነው የሚመነጨው?

መልስ፡- ከ«ሕወሓት» በስተጀርባ ማን ነው ያለው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ከመስጠቱ በፊት የኢትዮጵያን ታሪክ በመጠኑ መጥቀስ ተገቢ ነው ። የኢትዮጵያ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ለውጭ ጠላት ጥቃት የሚያጋልጣት ነው ። እንደሚታወቀው ዓባይ የሚመነጨው ከአገራችን ነው ። ይህ ወንዝ ከእኛ አልፎ በሱዳንና በግብጽ አድርጐ ስለሚያልፍ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል ። ይህ ውሀ ብዙ አልቲት አስከትሎብናል። በውሀው ሳንጠቀም በሥጋት እንድንኖር ነው የሚፈለገው ። እንግሊዞች አጼ ምኒልክ በጣና ሐይቅ ምንም ዓይነት የልማት ሥራ እንዳያካሂዱ ይከለክሉ ነበር ። በዓለም ሕግ መሠረት ከዓባይ ልንጠቀምበት የሚገባ የውሀ ድርሻ እንዳለን እናውቃለን ። ሌላው ድርቅ ጉዳት ሳያረሰባቸው ወገኖቻችን እየተባለ ከምዕራባውያን የሰብአዊ ድርጅቶች ዕርዳታ ይላካል። ይህ ዕርዳታ ለሕዝቡ ታስቦ ሳይሆን ለፖለቲካ ሥራ ማነሐሔጃ ነው የሚጐርፈው ። ይህ ዕርዳታ የሚጐርፍበት አካባቢ ደግሞ ማርክሲስት ነን ባዮችና ተገንጣዮች ናቸው የሚገኙበት ። እንግዲህ የዕርዳታውን አመጣጥ ስናጤነው በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት ማርክሲስት ስለሆነ ይህንን መንግሥት አዳክሞ ለምዕራባውያን በእሻንጉሊትነት የሚያገለግል ሌላ መንግሥት ለመመሥረት ማርክሲስት ነን በሚሉ እንደነ «ሕወሓት» ና «ሻዕቢያ» ባሉት ድርጅቶች አማካይነት ቀስ በቀስ የኢትዮጵያን መንግሥት ገዝግዞ ለመጣል ነው የሚሞክረው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ፦ በ«ሕወሓት»ና በሌሎች ሽብር ፈጣሪ ቡድኖች ሁከት መደሱዳን ተስደው የሚገኙ ወገኖቻችን ሕይወት ምን ይመስላል?

መልስ፦ በመሠረቱ ስደት በጣም አስከፊ ነገር ነው ። መቼም ሰው በሕይወቱ ላይ ከፍተኛ እደጋ ካላንጃበበት መሰደድ የለበትም ። ነገር ግን ዘርካታ ሰዎች ከስደት ብዙ በጐ ነገር የሚገኝ እየመሰላቸው ይሰደዳሉ ፡ አብዛኞቹ ስደተኞቻችን የሚገኙት በሱዳን ነው። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ሱዳን ውስጥ እንኳን ለስደተኞች ለራሱም ዜጐች የተመቻቸ ሁኔታ የለም ። ስለዚህ በሱዳን የሚገኙ ስደተኞች እጅግ አሳዛኝ በሆነ ሕይወት ውስጥ ይኖራሉ ። ብዙዎቹ ወገኖቻችን በአሥር ፡ በረሃብና በእርዛት እያለቁ ስለሆነ ፡ ይህ የሰላሙ ነገር መስመር ከያዘ መንግሥት በአፋጣኝ እንድ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል እላለሁ ። ስደተኛ ባለቤት የለውም ። እንደተፈለገ ይታሠራል ። በተለይ በእህቶቻችን ላይ የሚደርሰው ነገር በጣም የሚያሳዝን ነው ። ስለ ሰላም መናገር ቀላል ነው ፡ እንድ ቀን ሰላም አጥቶ መዋል ምን ያህል እንደሚያስጨንቅና እንደሚረብሽ የሰላምን ጥቅም ጠንቅቆ ለመገንዘብ ይረዳል ።

ጥያቄ፦ በአሁኑ ወቅት የትግራይ ሕዝብ በ«ሕወሓት» ላይ ያለው አመለካከት ምንድ ነው?

መልስ፦ በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ በትግራይ ውስጥ አይደለሁም ያለሁት ። ሆኖም ምሥራቅ አፍሪካ በነበርኩበት ጊዜም ሆነ እዚህም ብዙ ከትግራይ የመጡ ሰዎችን አነጋግሬአለሁ ። ዛሬ በትግራይ ውስጥ ምንም ነገር የለም። የመገበያያ ገንዘብ የለም ፡ ሕክምና ትምህርት ቤት ፡ የመሳሰሉት ነገሮች የሉም ። ሕፃናትና ወጣቶች ባልባሌ ቦታ ለመዋል ስለተገደዱ ወላጆች በጣም አዝነዋል ። አቅም ያለው ወደ ደሴና አዲስ አበባ መጥቷል ። «ሠይድን በጉመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለማማል» እንደሚባለው ዛሬ ሕዝቡን በተለያየ መንገድ ለያታልሉት ቢሞክሩ ፡ በሂደት ምንም ሊፈጽሙለት የሚችሉት ነገር ያለመኖሩ እየታዩ ነው ። የትግራይ ሕዝብ በበርም ይሁን በመስክት ትምጣ ሰላምን በጉጉት ይጠብቃል ። እነዚህ ማርክሲስቶች ነን ባዮች ሌላው ከሕዝቡ ጋር የሚያራርቃቸውን ድርጊት ሲፈጽሙ ይታያሉ ። ይህም ልዩ ልዩ የልማት ተቋሞችን ማፍረሳቸው ነው ። እንድ ዘንባ አውጪ ድርጅት ንኽ የሚል የተከለን ድልድይ በማፍረሱ ማንን ነው የሚጐዳው? መንግሥትን ነው? ማይክሮ ዌቭ ያፈርሳሉ ፡ ሌላም ሌላም እፍራሽ ድርጊት በመፈጸማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቸው ብዙ ሰዎች በትራታ ይነግሩኛል ። ባጠቃላይ ሕዝቡ በወንበዴው ላይ ያለውን ጥላቻና ያሳደረበትን ቅሬታ አምርሮ ነው የሚናገረው ።

ጥያቄ፡- የ«ሕወሓት» በጦርነቱ መግፋት የሚያስከትለው ውጤት ምን ይሆናል ብለው ያገምታሉ?

መልስ፡- የሚያስከትለውን ነገር ከወዲሁ መገመት ይቻላል ። በአገሪቱ ውስጥ ውሸንብር ይፈጥራል ፡ አሁንም ቢሆን የሚታየው እንቅስቃሴ ከውሸንብር መኖር የሚያንስ አይደለም ። ቀደም ብዬ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በታሪካችን እርስ በርስ የመጋጨታችን ሁኔታ እንደመኖሩ ሁሉ አሁን በተፈጠረው ሁኔታና ባለፉት 15 ዓመታት በተከሰቱ አንዳንድ ነገሮች ያከረፈውን ክፍል ጨምሮ በሚከሰተው ውሸንብር የመከራፈል ሁኔታ እንዳያኖር እሰጋለሁ ። ሌላው በዚህ በውሸንብር ሰዓት ወንበዴዎች ቀደም ሲል የተንሰላትን ኤርትራን ነፃ የማውጣት ዓላማ ከግብ ለማድረስ አመቺ ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው በማመን ይህ የውሸንብር ሁኔታ እንዲፈጠር ከመግፋፋት ወደ ኋላ የሚሉ አይደሉም ።

ጥያቄ፡- «ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ» (ሕወሓት) ብሎ ራሱን የሚጠራው ፀረ- ሕዝብ ቡድን ኤርትራ ትገንጠል ብሎ ሲወስን በውስጡ ያሉት አባሎቹ ምን ያህል ተወያይተውበታል? ወይንስ ይህ ለታክቲክ ተብሎ የማይነሳ ጉዳይ ነው?

መልስ፡- በመጀመሪያ ልገልጽ የምፈልገው ይህ ጉዳይ ከፍተኛ የአገር ጉዳይ መሆኑን በግሌ የምገነዘበው ነገር ነው ። እውነት ለመናገር ከሆነ እኔ ወደዚህ ስመጣ ይህን ያህል በመገናኛ ብዙኃንን ሰፊ ዕድል አግኝቼ የማውቀውን ነገር ለሕዝቡ አስረዳለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም። ስለዚህ ይህ ከፍተኛ የአገር ጉዳይ በመሆኑና እኔም በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያለኝን ሃሳብ ለማቅረብ መብቱም አለኝ ፡ ግዴታውም አለብኝ ። ቀደም ሲል የገለጽኩት ብዙ እድማሬችንና አንባቢያንን የሳበ ይመስለኛል ፡ ምክንያቱም እኔ በግሌ ብዙ የስልክ ጥሪዎች ደርሰውኛል ። በተለይ ብዙ የትግራይና የኤርትራ ተወላጆች አግኝተውኛል ። ይህም ከፍተኛ የመንፈስ ዕረፍት ሰጥቶኛል ። ይህ ብቻ ላይሆን ሕዝቡም ለአንድነቱ መጠበቅ ምን ያህል ከፍተኛ ጉጉትና ፍላጐት እንዳለው ለመረዳት ችያለሁ ። በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ ሰዎች ስለ ትግራይ ምንም

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳንድ ጊዜ ግራ ይገባኛል ። እንዚህ ሰዎች በመደብ ትግል ውስጥ ያሉን ማርክሲስት ሌኒኒስት ነን ይላሉ ። በእውነቱ እሱ አይደለም ችግሩ ። የነማን ልጆች እንደሆኑ ይታወቃል ። የእኔም የራሴ ቢሆን ። እርግጥ ትግራይ በደጃዝማቾችና ቀኛዝማቾች የታጠረ ነው ። ከጥንት ጀምሮ ታሪክ ያለው ሕዝብ ነው። እኔም ብሆን በናቴም ሆነ በአባቴ የብዙ ትልልቅ ታዋቂ ሰዎች ልጅ ነኝ ። እኔ የሞቱን ልጅ ነኝ ፡ እነሱ አይደሉም ለማለት አይደለም ። አብዛኛዎቹ ዘመዶቼ ናቸው ። እኔ ያለኝ መደባዊ ይዘት እነሱም አላቸው ። መለስ ዜናዊ ኮሚኒስት ነኝ ይለናል ። የደጃ አስረሱ የልጅ ልጅ ነው ። አሳቸው የታወቁ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ባለሟል ነበሩ ። የብዙዎቻችንን አባቶችና አያቶች ሲያሳስሩና ሲያስፈቱ፡ ግዞት ሲያስገቡ የነበሩ ናቸው ። ወልደ ሥላሴ ነጋ የኔ ዘመድ ነው ። ኃይሉምን ያነሳን እንደሆነ እሱም የደጃዝማች አርአያ ገብረእግዚአብሔር ልጅ ፡ የወይዘሮ ሮማን ልጅ ነው ። እነዚህ ሰዎች በዕውነት መደባዊ ይዘታቸው ሰሞቱን እንዲህ የሚያንገበግባቸውና የአልባኒያን ኮሚኒዝም እንዲከተሉ የሚያደርጋቸው አይደለም ። ቁም ነገሩ ግን እሱ አይደለም ። ማንም ከየትም ሊወለድ ይችላል ። ከመደብ ይዘቱ ውጭም ለሞቱን ሊቆም ይችላል። ይህ ሌላ ግንዛቤ ነው ። ዋናው ነገር ግን የእነዚህ ሰዎች ግላዊ ባህርይ ምንድነው፣ የሚለው ነው ። እንዳንድ ጊዜ በአመራር ካሉ ሰዎች ጋር ለውይይት ወደ ትላልቅ ሰዎች እንሔዳለን ። ከሱዳን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ዘንድ እንሔዳለን ። እዚያ ስንሔድ ከሰው ጋር ምን አቀራረብ ይናርሃል ለሚለው ስሜት የላቸውም ። የትግራይ ሕዝብ ባህል፡ የትግራይ ሕዝብ አነጋገርና ዘይቤ ፡ ስልት ፡ ትዕግሥትና ጸባዩን የሚያንጸባርቁ ሰዎች አይደሉም ።

ብዙ ሰው በጸባያችን ሰይተው ያውቁናል ። አውሮፓ ብትሔዱ እትዮጵያዊ ነህን በሚባዩ ይለይታል ። በር ስንገባ አንተ ቅደም አንተ ቅደም ስንባባል ፡ ፈረንጅ ከየት ነው የመጣችሁት ነው የሚሉን ። እንዚህ ግን ዋልጌዎች ናቸው ፡ ያሳፍሩናል ። የሕዝቡን ባህል የማያንጸባርቁ ሰዎች ናቸው ። የሱዳን ባለሥልጣኖችም ታዝበዋቸዋል ። በዚያ ሳይ ድፍረታቸው ወንበዴ የሚያስኛቸው ናቸው ። አልፎ አልፎ ልብ ያላቸው ሰዎች አሉ ። እነሱ ደግሞ በአመራሩ ላይ የሉም ። ታዛጮች ናቸው ። አይፈልጓቸውም ። በድርጅቱ ስም እንዚህ የታወቁ በመሆኑ እኛን

t.me/OLDBOOKSPDF

ያባርሩናል የሚል ፍራቻም አለባቸው ። ሌላው የነዚህ ሰዎች ችግር በነሱ ላይ ማንም ጥያቄ ማቅረብ አይችልም ። እነሱ ያሉት ከሰማያ ሰማያት የወረደ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው ። በነሱ ላይ አንዳንድ ጥያቄ በሚነሳበት ጊዜ ያህ የትግራይ ሰው ነመደ፣ የትግራይን ጉላይ ያመነላል ወይ ይላሉ ። ለእንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ እኔህ ለሕዝብ አገልግለን የሚሉ መሪዎች በድርቅ ጎንዘብ ያስተባበሯቸው ሰዎች የተለዩ ኦዮሎች አሳቸው። በትልበት ይጠቀማሉ ። ሰም ያጠፋሉ ፣ ለሰላን የጸጥታ ሠራተኞች ጉቦ በመስጠት ያሳስራሉ ። ይህ ነው የእነሱ ሰብዕና ። ሚዛጨቁ ፣ አፈና ሌላም ሌላም ። እነሱ በአመራር ላይ ተቀምጠው የሚሠሩትን ሥራ ለመቃወም ፣ በሁኔታው ላይ ለመወያየትና አንድ መልሰ ለማግኘት የሚያስችል ዘተዘራዮቻቸው ላይ ሊኖር የሚችል የአመቀት አቅም ነው ወሳኙ ። እርግጥ የትግራይ ሕዝብ ደንቁሮ አያደለም ። ይህ ፖለቲካ ነው ፣ ብዙ ውስብስብ ነገሮች አሉት ። አንድን ፖለቲካ የሚያራምድ መንግሥት፣ ግለሰብ ወይም ድርጅት ያንን ችሎ ተከራክሮ ማሳመን ይኖርበታል። እነሱን ለመከተል የሚያስችል ብሔራዊ ስሜት የሚፈጥሩበት ሰላባ ነገር ሊኖር ይችላል ። ግን ይህንን የሚላላቱትን ፣ የሚቀጥፉትን ሰብሰቦ ጨምቆ አስቀምጦ ይህ የምታረጉት መሠር ነው ፣ ወይም ጥሩ ነው ለማለት አንድም ነፃነቱ የለም ፣ ሁለተኛም ችሎታው የለም ። ያላንባቡት ነገር ቢኖር በየጊዜው ጥያቄዎች ተነስተዋል ። ግደይ ዘርዓ ፅዮንና አረጋዊ በርሄ ባላቸው ንቃተ ሕሊና ደረጃ በአመራር ላይ የነበሩ ሰዎች እንደመሆናቸው አቅርበዋል ። (ሁለቱም አሁን እዚያ ቦታ የሉም) በድርጅቱ ውስጥ ዴሞክራሲያዊአሠራርናውይይትቢኖርናቸውእንዴትሚለውመልስመሰጠት ይገባ ነበር (ትክክል ሊሆኑ ወይም ተሳስተው ሊሆን ይችላል) ። ሕዝቡ ግን ከሁለቱ መጭመቅ አለበት ። በውይይት ሕዝቡ ይማራል ። ያማም በየጊዜው ልዩነታችን በመድረክ ይውጣ ብለዋል ። ግን የታለ !

<u>ጥያቄ</u>፡ — ቀድም ሲል የወተሓሕት» በሣፊው አጠራር ወሕወሓት» ለተባለው ቡድን በሊቀመንበርነትና በወታደራዊ ኃላፊነት ያገለግል የነበረው አረጋዊ በርሄ ሰሞኑን በቪ.ቢ.ሲ. የሰጠው መግለጫ ያበት ምን እንደነበር ቢያብራሩልን?

<u>መልስ</u>፡ — አረጋዊ በርሄ በመግለጫው ላይ «ማሌሊት ዘላለ» በማለት ስላዘጋጀው ፅሑፍ ነው ያብራራው ። «ማሌሊት» (ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሊግትግራይ) ፍጹም ዴሞክራሲያዊ ያልሆነና በሠራዊቱና በሕዝቡ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቁላጭ ላይ ያለመመሥረቱን ፣ ጀብዱኛነቱን ፣ ጠባብ ብሔረተኝነቱን፣ የኢትዮጵያን ጉዳይ ፈጽሞ የማይመለከት መሆኑን ነው አረጋዊ ያብራ ራው ። እዚህ ላይ ለመጨመር የምፍልገው ባሁኑ ጊዜ የትግራይ ሕዝብያህ «ማሌሊት» የሚባለው ድርጅት ይህን ያህል ደም የሚያፋሰሰና የኢትዮጵ ያን እንድነት የሚያናጋ አሳፋሪ ተግባር ሲፈጽም የቡድኑ ተከታዮች እንዴት ዝምብለው ይመለከታሉ እያሉ በመጠየቅ ላይ መሆናቸውን ነው። በመሠረቱ ቡድኑን ለጊዜው ለመከተል በቂ ውኔታ አለ ። ባለኝ ብሔራዊ ስሜት በትግራይ ጉዳይ ውስጥ ልገባች ያለው ። ቁምነገሩ መግባቱ ብቻ ላይሆን በውስጡ የሚሠራውን ሥራ ትክክል ነው አይደለም ብሎ የማጤኑ ጉዳይ ነው ። ስለዚህ እኔ አሁን ከእናንተ ጋር ለመወያየት የቻልኩት በቡድኑ ውስጥ የሚካሄደው ነገር ሁሉ ትክክል አለመሆኑን ተረድቼ ነው። ይህን ስል የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ሊያገኝ የሚገባውን ነገር እንዲያገኝ ፣ ስሀገሩም የሚፈለግበትን ግዴታ እንዲወጣ በጉ ምኞት አለኝ ። ቀደም ሲል በሰጠሁት መግለጫ እንዳብራራሁት በቡድኑ ውስጥ ያሉት ወጣቶች ናቸው ። የገበሬ ልጆች ናቸው ። የፖለቲካው ሥራ የሚካሔደው ከላይ ባሉት የአመራር አባላት በመሆኑ ተራው አባል የሚያውቀው ነገር የለም ። የሚመለምሏቸው ደግሞ በዘረኝ ነው ።

እንደሚታወቀው ከለውጡ መጀሀ ነው የብሔረሰቦች እኩልነት የተጠበቀው ። ከዚያ በፊት ግን ይህ ዓይነት ገንቢ እገማሚያ ባለመኖሩ የነበረው ሥርዓት በሕገቡ ላይ በተለያየ መንገድ ተጽዕኖ ያደርስበት ነበር ። ስለዚህ እነዚህንና ሌሎቹንም ብሶቶቹን የሚነካከ ዘፈኖች ውን በወጣቶቹ ወገብ ላይ ያስራሉ ። በትግራይ ባህል በዘረኝ ወቅት ሴት በወንዱ ወገብ ላይ ነጠላ ካሰረች በኋላ ለሚደረግለት ጥሪ መደኋላ አይልም። ነጠላ ታስሮለት መደኋላ የሚል ወጣት ያው እንደሴት ነው የሚቆጠረው ። ከዚህም በላይ በወጣትነት ዕድሜው ከዜተሰብ ቁጥጥር ውጪ ሆኖ መሣሪያ መታጠቁ ሥራ እንደማግኘት ነው የሚቆጥረው ። ስለዚህ መደ ቡድኑ የሚገባው የቡድኑን ፕሮግራምና ዓላማ ተረድቶ ሳይሆን መኔ በሚቀሰቅሱ ዘፈኖች መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ። ሌላው ደግሞ ባሁኑ ጊዜ ማን ሞቶ ማን ይቀራል በሚል ወጣቱ እየተገደደ ነው የሚመሰመለው ። ባጠቃላይ አረጋዊ በርሄ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ያብራራው እንዚህን ውኔታዎች ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ፡- «ሕወሓት» የ«ትግራይን ሪፐብሊክ» እመሠርታለሁ በሚል አንድ የትግራይን ክልል የሚያሳይ ካርታ አውጥቷል። የዚህ ካርታ ይዘት ምንድነው?

መልስ፡- በመሠረቱ ካርታ እኔም ሆንኩ ጥቂት ሰዎች ሆነን በዘፈቀደ የምንቀርጸው ነገር አይደለም። ካርታ በዓለም አቀፍ ሕግ፡ ደንቦችና በአገር ደረጃ ከታሪክ በመነሳት በኤክስፐርቶች ተጠንቶ የሚቀረጽ ነገር ነው። በታሪክ የትግራይ ወሰን እስከ ሱዳን ነው የሚል ነገር የለም። የትግራይ ክልል በማንኛውም ጊዜ ከሱዳን ጠረፍ ጋር የተያያዘ ነው የሚል ታሪክ ፈጽሞ የለም። ይሁን እንጂ «የትግራይን ሪፐብሊክ እንመሠርታለን» በሚል ከጉንደር ወልቃይትን በመቁረጥ እስከ ሱዳን ድረስ፡ እንዲሁም ከወሎ ሰቆጣን፡ አሸንጌን አላማጣንና ቆቦን ወስዶ እስከ አሰብ ድረስ አዲስ ካርታ ተነድፏል። ይህ ካርታ ፈጽሞ በታሪክ የሌለ ከመሆኑም ሌላ አውንም ሆነ ወደፊት ከአጉራባች ክፍላተ ሀገር ጋር የሚፈጥረው ችግር ከፍተኛ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። የወሎንም ሆነ የጉንደርን መሬት የእኔ ነው ብሎ የሚነሳ ክፍል ከእነዚህ ሕዝቦች ጋር ከፍተኛ ቅራኔ መፍጠሩ የማይቀር ነው።

በአዲሱ ካርታ መሠረት የጉንደርና የወሎ ሕዝብ «የማሌሊትን" ሬዲዮ ሲያዳምጥ በትግርኛ ሊሆን ነው። ይህ ደግሞ ባህላችን በእኩልነት አላደገም ብለን የምንጠይቀውን የሚቃረን ይሆናል። አንዳንድ በውጭ የሚያገኙን ሰዎች ይህን ካርታ በተመለከተ በመደነቅና በመገረም ለመሆኑ እንዴት ያለ ድፈርት ቢናራችሁ ነው ይህን ዓይነት ካርታ የምትነድፉት? የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ይለናል ብላችሁ እንዴት አታስቡም? ኢትዮጵያዊ ሆናችሁ እንዴት ታሪካችሁን አታውቁም? ብለው ይጠይቁናል። ከታሪክ ውጭ የሚደረግ እንቅስቃሴ መቅሠፍት ነው። ስለዚህ እኛ ሌላው ቀርቶ ከትግራይ ብሔረሰብ መካከል በታሪክ በሳል የሆነ ዕውቀት ያላቸው ያስተምሩን እያልን በየጊዜው የቡድኑን አመራር አባላት እንጠይቃለን። ሰሚ ግን አላገኘንም። ባጠቃላይ ይህ የትግራይ ካርታ ተብሎ የተነደፈው በጥቂት የቡድኑ አባላት ስሜት በመሆኑ ከታሪክ ውጭና በማንኛውም ዘንድ ተቀባይነት የሌለው የቅዠት ሥዕል ነው። እነዚህ ሰዎች የጉንደርንና የወሎን መሬት ቢፈልጉም በላዩ ላይ የሰፈረውን ሕዝብ ፍላጐት ግን ማርካት አይችሉም። በዕውነቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF


ትግራይ
ቀይሕ ባሕሪ
ዓፋር
ክልተ ሓወላይትካ
ዓድዋ
ኣክሱም
ኣዲግራት
ሽረ እንዳ ኣቦ
ኣላማጣ
ዓዲ ግራት
ኮረም
ዓዲ ነፍሲ
ሽራሮ
ኣፅቢ
ዓዲ ጉዶም
ዓዲ ዳዕሮ
ሕንጣሎ
ዓዲ ሓጎስ
ዓዲ ሓቂ
ዓዲ ሓሩሽ
ዓዲ ሓሩሽ
ዓዲ ሓሩሽ

በድርጊቱ በጣም እዝናለሁ ። ከፍተኛ ቅሬታም ውስጥ ይገባሉ ።

በዚህ ካርታ ላይ ሊጠቀስ የሚገባ ሌላው ዓቢይ ጉዳይ ከትግራይ ሰዎች በኩል የትግራይ ክፍል የሆነ ወደ ኤርትራ ክልል የገባ ቦታ አለ እየተባለ በአፈታሪክ የሚነገር ጉዳይ አለ ። የሚገርመው እዚህ ላይ ነው ። «ሕወሓት» ስለዚህ ጉዳይ ሳይጠቅስ ፡ በኤርትራ ላይ ምንም ዓይነት የመሬት ጥያቄ ሳያነሳ ነው ያለፈው ። በአንድ ወቅት «ሻዕቢያ» ይህንን ነገር በማንሳት «የሕወሓት» ሰዎችን «በኤርትራ ክልል ቦታ አለን ትላላችሁ» በማለት ላነሳባቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ «እኛ ስለመሬት ሽንሸና ለመነጋገር አይደለም እዚህ የመጣነው ። ስለ መሬት ሽንሸናማ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆነን ነው የምንወስነው» ብለዋል ። እንግዲህ ምነው በጦንያር ፡ በወሎና በአሰብ መሬት ላይ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆነን በውይይት አልሸነሸንም፣ በኤርትራ መሬት ላይ ስንደርስ ምነው የሕዝብ ሙሳኔ አስፈለገ? ብለን ብንጠይቅ መልስ አይኖራቸውም ማለት ነው። ከመሠረቱም ቢሆን «ሕወሓት» የኤርትራን ጉዳይ ለማስፈጸም የተመሠረተ ስለሆነ በኤርትራ ላይ ምንም ዓይነት የመሬት ጥያቄ አላቀረበም ።

<u>ጥያቄ</u>፡ «የሕወሓት» የወታደራዊና የፋይናንስ አቋም ምንጩ ከየት ነው?

<u>መልስ</u>፡ በመጀመሪያ መግለጫዬ ላይ እንደጠቀስኩት በአገራችን የተፈጥሮ አቀማመጥ የተነሳ የስትራቴጂ ጠላቶች አሉን ። እነዚህ የስትራቴጂ ጠላቶች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ በአገራችን ውስጥ ያለመረጋጋት ፡ የእርስ በርስ መከፋፈልና መፋጀት እንዲኖር ይፈልጋሉ ። ከውጭ ተርቶ በአገር ውስጥ የሚነሳ የስትራቴጂ ጠላት ብዙ ነገሮችን የሚሠራው አንዱን ከአንዱ በመለያየትና በመከፋፈል ነው ። አንድን ጎበረተሰብ ከከፋፈሉት የወታደር አስፈላጊነት አይታየኝም ። ስለዚህ በተከፋፈለ ሕዝብ መካከል ዘው ብሎ መግባት ነው ። በትግርኛ አንድ አባባል አለ ። «መንገደኛ ፡ ባልና ሚስት የተጣሉበት ማዕድ ላይ አጋመጫን» ብሎ ይጸልያል ይባላል ። ባልና ሚስት ከተጣሉ መንገደኛው የተረበሙን ምግብ እንደልቡ ጥርግ አድርጎ ተመገቦ ይሔዳል ለማለት ነው ። ከዚህ አባባል የምንገነዘበው እኛ እርስ በእርሳችን ስንከፋፈል ስትራቴጂያዊ ጠላቶቻችን መግቢያ ቀዳዳ በማግኘት የሚፈልጉትን ለማድረግ ዕድል እንደሚያገኙ ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኢትዮጵያ ከተደ ባሀር ስትራቴጂያዊ አቀማመጫ ሴላ ብ
የማይገባን ማለትም በዓባይ ውሃ ምክንያት የሚደርስባት ተጽዕኖ ነው
ዓባይ ደለል ፡ አፈሩንና ሴላም ጠቃሚ ማዕድናትን ተሸክሞ በሱዳን
አልፎ ግብጽ ምድር ይገባል ። ዓባይ ብዙ ሕይወትን እዚህ አበላሽ
ከአገሩ ውጭ ለብዙ ሚሊዮን ሕዝብ ሕይወት የሚሰጥ ነው ። በሱዳንና
በግብጽ በዓባይ ውኃ ምክንያት ስፊ የእርሻ መሬት ይገኛል ። ከዚህ ሴ
የምግብ እህል እጥረት ያጋጠማቸው አንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ
አገሮችም ይገኛሉ ። እነዚህ አገሮች በነዳጅ ገንዘብ የሰከሩ በመሆኑ
ለምግብነት የሚያገለግላቸውን ነገር ከአውሮፓ ፡ ከሰሜን አሜሪካ
ከሴላም ሥፍራ በጣም ውድ በሆነ ዋጋ ይገዛሉ ። እንደሚታወቀው የነዳጅ
ዋጋ በየጊዜው ከፍና ዝቅ እያለ በመሔዱና በአንዳንድ አገሮችም ነዳጅ
እየተገኘ በመምጣቱ እነዚህ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ለምግብነት
የሚያውሉትን እህልና ሽቀጥ እንደተድሞው በውድ ዋጋ ከውጭ ለማስመ
ጣት ያላቸው አቅም እያነሰ መሔዱ የማይቀር ነው ። ስለዚህ እነዚህ
አገሮች በረከሰ ዋጋ የምግብ እህል ከግብጽና ከሱዳን ለመግዛት መቻል
ይኖርባቸዋል ማለት ነው ። ቅን ቢሆኑ ከኢትዮጵያም ቢያገኙ ደስ ይለኛል ።
ሱዳንና ግብጽ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም በጉርብትና
አብረን የኖርን ሕዝቦች ነን ። ከታሪክ እንደምንረዳው ቱርኮችና ግብጾች
ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ሩብረካ ለማቋቋም ሳይሆን ዓባይን ፍለጋ ነው ።
ለስትራቴጂ ጥቅማቸው ሲባል በዓባይ ላይ የተደረገው ውል ምን ያህል
እኛን ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ ሴራ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ። ዓባይ
ብቻ ሳይሆን ተከዜ ፡ መረብና ሌሎችም ወደዓባይ የሚገቡ በርካታ
ወንዞች አሉን ። ወደዓባይ የሚመጡ ገባር ወንዞችን ለመጠቀም መብት
መብት አለን ። በዓባይ ወንዝም ቢሆን የተወሰነ ድርሻ አለን ። ስለዚህ
ይህን ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታቸውን ለመጠበቅ ሲሉ አርስ በርሳችን
እንድንፋጅ ያደርጉናል ።

ሴላው ከዚህ አካባቢ የሚገኙ ዕርዳታዎች አሉ ። ለምሳሌ በአንድ
መቅት «ጅብሃና» «ሻዕቢያ» ከፍተኛ ጸብ ላይ በደረሱበት መቅት
«ጀብሃን» ከሚደግፉ ጥቂት የዓረብ አገሮች መካከል አንድኛው የሻዕቢ
ያን» ቢሮ ሲዘጋ «የሕወሓት»ን ቢሮ ግን አልዘጋም ። አርስ በርሳችን
እንዳንስማማና በሰላም እንዳንኖር ስለሚፈልግ ነው ይህን ያደረገው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሕወሓት» ከአንዳንድ ዓረብ አገሮች የተለያዩ ዕርዳታዎችን ያገኛል ። ከንግድና ከውጭ እርሻ እርዳታ ይገኛል ። ሱዳን ውስጥ እርሻ ያርሳሉ ። በዚያም ሆነ በሌላ ዕታም ንግድ ያካሒዳሉ ። ሌላው ከሰልት መዳጀቻቸው ጋር ግንኙነት አላቸው ። ይኽውም አንዳንድ በምዕራብ አገር ከሚገኙ የሃይማኖት ድርጅቶች የሚደረግላቸው ልዩ ልዩ ድጋፍና ዕርዳታ ነው ። ይሆን ድጋፍና ዕርዳታ የሚያድርጉ ክፍሎች የኢትዮጵያን ማርክሲስት መንግሥት ለመጣል ከእነ «ሕወሓት» ና «ሻዕቢያ» ጋር ለጊዜው መዳጀ መሰለው ይቀርባሉ ። ተሳክቶላቸው በኢትዮጵያ ማርክሲዝም ከተወገደ እንዚህን ማለትም እነ «ሕወሓት» ን ማጥፋት ስለሚቀላቸው ጊዜያዊ መዳጀነት ሊመሠርቱ ችለዋል ። ሊያጠፉቸው የሚችሉበትም ስልት የሚሰጡትን ዕርዳታ ማቆምና ሌሎች ችግሩን የሚያባብሱ አገሮች ዕርዳታ እንዳያሰጧቸው ተዕኖ ማሳደር ነው ።

የ«ማሌለት» ቡድን መሪዎች ማርክሲስት ነን ይላሉ ። የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን እናወድማለንም በማለት ፈጩኽታቸውን ያስተጋባሉ ። ሶቪየት ኅብረትንም ሶሻል ኢምፔሪያሊስት ስለሆነ መውደም አለበት ይላሉ ። ባጠቃላይ በእነሱ አባባል በዓለም ላይ ከአልባንያ በስተቀር ሌላው አድሀሮት ኃይል ነው ። እውነት ለመናገር አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ አልባንያ የምትባል አገር የት እንደሆነች በካርታ ላይ ፈጥኖ ሊያመለክት አይችልም ። በአልባንያ የኦርቶዶክስ ኮሚዩኒዝም እንዳለ አሰማለሁ ። ለእነ «ሕወሓት» ዕርዳታ የሚያደርጉ ምዕራባውያን አገሮች በሁኔታው ተገርመው ማፈሳቸው የማይቀር ቢሆንም ዋና ፍላጐታቸው ግን የኢትዮጵያን መንግሥት ማርክሲስትነት ለማስለወጥ ወይም ለመ ጣል ሲሉ አብረዋቸው ማዝገማቸው አልቀረም ። ሌላው ማንኛውንም ትን ዜጋ የሚያንገበግበው የብዙ ምንጫቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተርፏል ተብሎ በመገናኛ ብዙኃን ከፍተኛ ቅስቀሳ ተደርጉ በድርቅ ለተጐዱ ወገኖቻችን ተብሎ የሚመጣውን የእርዳታ እህልና ቁሳቁስ ለሱዳን ሕዝብ በመሸጥ የሚያገኙት ገንዘብ ነው ። ይሆን ሁኔታ በሱዳን በስደት ላይ የሚገኙት ወገኖቻችን በሚገባ ያውቁታል ። በየትኛውም የሱዳን ምድር በኩድ ገበያውን አጥለቅልቆት የሚገኘው በኢትዮጵያ ረሃብተኞች ስም የመጣ የዕርዳታ ምግብና ሸቀጣ ሸቀጥ ነው ። በሱዳን የሚገኙት ስደተኞች ወገኖቻችን እነ «ሕወሓት» ና «ሻዕቢያ» በፈጠሩት ችግርና መርነት ምክንያት የተነሳ ነው ለመሰደድ የበቁት እንጂ የሱዳን ምድርና

t.me/OLDBOOKSPDF

የአየር ጸባይ ለሕይወታቸው ተስማሚ ሆኖ አይደለም ። እውነት ለመናገር ከ10 እስከ 20 በሙቶ የሚሆነው ስደተኛ የትግራይ ሕዝብ ተገቢውን እርዳታ አግኝቷል ብዬ አልገምትም ። ባለፈው ጊዜ እንደገለጽኩት «ማሌሊት» የተመሠረተው ለድርቅ ተብሎ የመጣው ዕርዳታ ተጀመ በተገኘው ገንዘብ ነው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ድርጅቱ በሱዳን እንዳንድ እርሻዎች እንደሚያካሒድ ገልጸውልናል ። እርሻውን መንግሥት ሰጥቶአቸው በተወሰነ ክልል ነው የሚያካሒዱት ? በዚያ ላይ ንግድ ያካሒዳሉ ብለዋል ። ድርጅቱ ያቋቋመው ንግድ አለ ማለት ነው?

<u>መልስ</u>፡- ድርጅቱ በትራንስፖርት ንግድ ይሰማራል ። በከባድ የጭነት መኪናዎች ዕርዳታውን በየቦታው ለማድረስ ትግራይ ውስጥና ከትግራይ ውጭ ለአሉት ዕርዳታ ሰጭ ድርጅቶች የተለያየ መጠን ያላቸው ከባድ የጭነት ተሽከርካሪዎች በብዛት ያከራያሉ ። በንግድ ሥራም የድርጅቱን የፖለቲካ ሥራዎች በማከናወን ላይ ይሠማራሉ ። ይህን እንደሚያድርጉ ማንም የሚያውቀውና የሚመሰክረው ነው ።

ሱዳን ውስጥ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ማለትም ያላቸውን ከፍተኛ ተቋሞች ፣ ጋራገሮች መንግሥት ያውቃል ፣ ምንም ነገር የሱዳን መንግሥት ሳያውቀው አይደረግም ። ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስም ቢሆን መታመን ፣ መታወቅና ይለፍ ያስፈልጋል ። በየትናንሽ ቦታዎች ቁጥጥር አለ ። ዝም ብለህ የምታልፈው ጉዳይ አይደለም ። የውጭ አገርም ዜጋ ይሁን የራሱ ዜጋ እንቅስቃሴውን ይከታተላል ። ቀደም ብዬ ተናግሬአለሁ ፣ አስትራቴጂያዊ የሆነ ጥቅም አለው ። እኔ ሱዳናዊ ብሆን ያንን አደርጋለሁ ፣ ማን አለ ለሀገሩ የማይታገል ። ሱዳኖችን በከፍተኛ ደረጃ አውቃቸዋለሁ ። ከኤልኦሜሪ መንግሥት ጀምሬ ነበርሁ ። እራሱን የአልመሃዲን መንግሥትም ለውቃለሁ ። በፊትም በጀኔራል ስዋር አልደሃብ ጊዜ ነበርሁ እንዚህ ሁሉ ቋሚ በሆነ መንገድ አቋማቸውን ሳያለዋውጡ በኢትዮጵያ ላይ የሚደርሰውን ችግር እያወቁ ፣ ምን እንደሚደረግ እያወቁ ይተባበሩአቸዋል ። ያለነሱ ፈቃድም መንቀሳቀስ አይቻልም ። ጨዋታም አይደለም ። መንግሥቱ ሳያውቅ ማረስ ፣ መነገድ ፣ መንቀሳቀስ አይቻልም።

<u>ጥያቄ</u>፡- የስደተኛ ጉዳይ ሲነሣ የተራው ስደተኛ ኑሮ ምን ይመስላል? ከራስም ሕይወት ተነሥተው ቢያብራሩልን?

t.me/OLDBOOKSPDF

<u>መቼስ</u>፦ መቼም ከዚህ በፊትም አንሥቼዋለሁ ። በስደት መኖር አስቸጋሪ ነው ። በስደት መኖር በጣም የተዋረደ ፣ የተጉላቆለ ማንነትን ፣ ዜግነትን የሚያስረሳ ሕይወት ነው ። ሰው በአገሩ የማን ልጅ ነው እንዳይባል የሚወስዳቸው ጥንቃቄዎች አሉ ። በሱዳን አገርም ሆን በሌላ አገር የሚኖር ስደተኛ ምንም ይሁን ምን የተሻለ ኑሮ የለውም ፣ ምቾት የለውም።

በሱዳን ያለውን ሁኔታ ብዙ ኢትዮጵያውያን የሚያውቁት ነው ። ያን ሁሉ ስደተኛ ምንም ልታረገው አትችልም ። በከፍተኛ ወረድት ነው የሚኖሩት። እኔ ራሴ አንድ ጊዜ የሆንኩትን ልንገርህ ። ስደተኛ ብሆንም በተላለ እጄን የምሰጥ ስደተኛ አልነበርሁም ። ሱዳን በነበርኩበት ጊዜ ከዓባያ መንዝ ባሻገር እኖር ስለነበር ማታ ስሕድ ፖሊስች አስቆሙኝ ። ማነህ አሉኝ፣ በመልካቸን ከሱዳኖች ጋር ልዩነት ስለሌለን ። መታወቂያ ወረቀት አሳዩ ሲሉኝ ያሳየኋቸው የስደተኛ መታወቂያ ነበር ። መኪና ያዝ ስለነበር እንዴት መኪና በአገራችን ትነዳለህ ብለው ከፍተኛ ወርጅብኝ አወረዱብኝ ። በታሪክ የሚያስወቅሳችሁ ነው የምትሠሩት ። ያህ የምትጠሙት ውሃ ከእኛ አገር የሚመጣ ነው ። ብዙ የታሪክ ማንጉት ያለን ሕዝቦች ሆነን እንዴት ትናነሱሳችሁ ስላቸው ። ለመናገርም መብት የለህም አሉኝ ። ብዙ ጊዜ ሱዳኖች ያህን መሬት አሸትቱ ፣ ያገራችሁ መሬት መሰላችሁ ወደ ይሉናል ። ልክ እኛ መሬትም ፣ አገርም እንደሌለን።

ሌላው እንድ አብሮኝ የሚሠራ ሱዳናዊ የተማረ ጓደኛ ነበረኝ ። ምሳ ጋብዘኝ ስንበላ ያጋጠመኝ ነው ። ከሰሜን ሱዳን የመጣ ትልቅ ወንድሙ አገራችሁ ሙስጥ ሙሃ አለ ወይ ሲል ጠየቀኝ ። አገራችን ሙሃ የለም ከሱዳን እየሔደ እንጠጣለን ስለው ገረመው ። «ታዲያለህ እንዚህ ሰዎች የሚጠጡት ሙሃ አጥተው እንዴትያለ ችግር ላይ ነው ያሉት?» አለው ። ወንድምየው ግን ተናደ እነሱ እራሳቸው ሱዳኖች የሚጠጡት ሙሃ የእኛ መሆኑን ነገረው ። መቼም ለሱዳኖች እኛ አገር ያለን ፣ ባህል ያለን ፣ በነፃነታችን የምንኮራ ፣ ክብር ያለን እይመስላቸውም ። ልብስ ፣ ምግብ ፣ ሕክምና ከማጣቱ ይልቅ የነፃነት ማጣቱ ያበሳጫል ። በሰው አገር ማንም ተከብሮ አያውቅም ። ሰው የሚከበረው በአገሩ ነው ። የጊታ መሣይ ዘፈን ትዝ አለኝ ። በተዘፈነ ቁጥር ያስለቅሰኛል ። ምንም ነገር ቢሆን በአገር ነው የሚያምረው ፣ ስደተኛው በጣም ስቃይ አለበት ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሱዳን የሚገኙ እህቶቻችንን ያያችሁ እንደሆነ ታገኛላችሁ
እናቶቻችን በወግ በሥርዓት ታል ከዳን ገብተው ትዳር መሰርተ
የሚኖሩ አይመስላቸውም ። ብዙዎቹ ሱዳኖችና የመነከለኛው ምሥራ
አገሮች የኢትዮጵያውያን ሴቶች አመንዝራዎች ፡ ሴተላጪዎች ፡ ሰሴተ
አዳሪነት ብቻ የተፈጠሩ ነው የሚመስላቸው ። እዚያ ሲደርሱ የጉ
ችግር ስለአለ አብዛኞቹ የሀገራችን ሴቶች ሴተኛ አዳሪ ይሆናሉ ።

ባንክ ውስጥ ገብተው ወይም ሐኪም ቤት ገብተው ነርስ ሆነው
እይሠሩም ። ከሙቶ ዘጠናው ጉሮአቸው በሴተኛ አዳሪነት ነው ።
በትምህርትም የገፉት ሞራላቸውን ለማስነካት የማይፈልጉት ግርድና
ገብተው ይሠራሉ ። የኮሌጅ 2ኛ ወይም 3ኛ ዓመት የሆነች ተማሪ አንድ
ሱዳን ቤት በግርድና ትሠራለች ። ሱዳናውያን ፡ ከደቡብ ሱዳን
ከሚመጡት በስተቀር ገረድ የሚሆን የለም ። የእኛ ሰዎች በንጽሕናቸው
በባህሪያቸው ይመረጣሉ ።

በሱዳን አገር የኢትዮጵያን ጥያቄ በሚመለከት ወደ ሠላሳ ምስት
የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ ። በጣም የሚገርምና የሚያሳፍር ጉዳይ ነው ።
ብዙ ሰዎች ይነግሩናል ። ብዙ አገሮች ለምሳሌ አሜሪካ ከጀርመን
ከፈረንሣይ ፡ ከእንግሊዝ ወዘተ የመጡ ሰዎች በአንድነት የተባበረችውን
አሜሪካ መሥርተው ነው እድገታቸውን የሚያፋጥኑት ፡ የሚኖሩት ።
እናንተ ትናንሽ አገር ለመፍጠር ይህ ሁሉ ድርጅት ምንድነው? አሁን
የኢትዮጵያ መንግሥት ላንጋግራችሁ ቢል ከእነዚህ ሁሉ ድርጅቶች ጋር
ለመነጋገር ጊዜውም አይኖረውም ብለውኛል ። ይህን ያሉት በኤልኤሬ
ጊዜና ከዚያም በፊት የአገራቱ (የሱዳን) የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩ
እንደዚሁም በኢትዮጵያ የሱዳን አምባሳደር የነበሩት አልአሚን
ናቸው። ሰዎቹ ስለኢትዮጵያ የሚያውቁ ፡ የዓለምን ሁኔታ የሚገመግሙ
ናቸው ። እንግዲህ እነዚህ ድርጅቶች ለሚፈጥሩት ሽኩቻና ለሚፈጥሩት
ሁኔታ በሚያነሳሱት ችግር እያንዳንዱ ሰደተኛ እርስ በርሱ ይባላል ።
መገናኛን ሕዝባችን ስለሆነ ያንገሸገሸኛል ። በጣም እየተዋረደ ነው ።
ሌላው ሱዳኖች በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈጠሩ ችግሮች
ተባባሪዎች ናቸው ። ይህን ግንዛቤ ሰው የሚያውቀው ነው ። ብዙ ጉዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ፡ ለመሆኑ «ሕወሓት» የሕዝቡን ብሶት ለመቅሰቅስ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ምንድን ናቸው? የሚያውቁት ካለ ቢነግሩን?

መልስ፡ መቼም ፕሮፓጋንዳ እንደሚስማማህ እድርገህ የምታቀርበው ጉዳይ ነው ። እኔ በአሁኑ ሰዓት ፕሮፓጋንዳ እየሠራው አይደለም ። የምሠራ ቢሆን ኖሮ በደንብ እሠራዋለሁ ። ያለውን ነገር ነው መናገር የምፈልገው ። ፕሮፓጋንዳ ብዙ መንገድ አለው ። እንደኛ ከመሠረቱ ጀምሮ ራሱን የቻለ የብሔረሰቡ ቅስቀሳ አለ ። ለአንድ የትግራይ ሰው ስለትግራይ እንስተህብ ብትዘፍንለት ፣ ብታለቅስለት ፣ ለዚህ እታገልልሃለሁ ብትለው ከአለው ንቃተ ህሊና እና ሌሎችም ሁኔታዎች ፣ ታሪክን ካለማወቅ ለቅስቀሳ አመቺ ሁኔታ ያፈጥራል ። ይህ አንዱ ነው ። በሌላው በኩል ደግሞ ማየት የምንችለው ብዙ ሊያነሳሱ የሚችሉ ነገሮች አሉ ። እኔ አንድ ጥናት አለኝ ። በየጊዜው የትግራይ ሰዎች የኤርትራም ጭምር ይታሠራሉ ። ይህ መንግሥት ኢትዮጵያዊ ከሆነ እኛን በኢትዮጵያዊነታችን የሚያውቀን ከሆነ ለምን? ይላሉ ። እርግጥ በአካባቢያችን እንቅስቃሴ ስለአለ አትኩሮት ሊሰጥ ይችላል ። ለመንግሥትም አገልግሎት የሚሰጡ ሰዎች ጭምር በቁጥጥር ስር እየዋሉ እንዳንድ ነገር ሲደርስባቸው ምንድነው? የሚል ጥያቄ ያስነሳል ። ታሰረው ከተፈቱ ሰዎች ካርቱም ላይ እዚህም ሰሞኑን ብዙ ሰዎች አነጋግራለሁ ። እርስ በርስ መጠቂቆም ነው ። ቡድኑ የእሱን ዓላማ ሊከተሉና ሊያነሱ የሚያችሉ ፣ ወይም የማያፈቅዱ የትግራይ ሰዎችን የእሱ ተባባሪ በማስመሰል ብዙ ነገር ሊያስከትል ይችላል ። አንድ የሆነ ወረቀት ከተማ ውስጥ ሊበትኑ ይችላሉ ። በዚያ ላይ እንእከሌ እንከሌ የቡድኑ አባሎች እንደነበሩና ገንዘብ ያዋጡ እንደነበር መግለጽ ይችላሉ ። አንድ ሰው ሲያዝ አምስት ስድስት ሰው አምጣ ይባላል ። ድንገት ስትገባ እንእከሌ እንእከሌን ጠቁም ሊሉትም ይችላሉ ። እንዲሁም ደግሞ እስረኛ ከሙሉ ሰው ጋር ይገናኛል ። የእነሱ ሰው የሆነውንም መታሰር ካልቀረ እንእከሌን ሳብ ይሉታል ። በዚያ ላይ ሕዝብ በመንግሥት ላይ ሊያሳድረው የሚችል የመጠራጠር እና ያለመተማመን ጉዳይ እነሱ ተመዳጅና የተሻሉ ሆነው እንዲታዩ ይረዳል። እነሱ የሚሉት ደግሞ ይህም መንግሥት ይሁን ሌላም ይሁን በትግራይና በኤርትራ ሕዝብ በአጠቃላይ በትግርኛ ተናጋሪው ላይ ያለውን ጥላቻ ለመግለጽ እያሠረ ፈታ በማለት ለትስቀሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይጠቀሙበታል። እኔ ታስ መጠየቅ ያደረግሁላቸው አለ ። አንዱ ግደያ ገብረ መስቀል የሚባል ቫራ ላይ ዳኛ ነበር። እሱ "እውነት መስክረአለሁ" የሚል መጽሐፍ አየጻፈ መሆኑን ገልጾልኛል። ረዳቱንም አሳይቶኛል። አውን እሱ «ሕወሓት» ውስጥ ተዋጊ ነው። "እኔ እነ ያ መንግሥት ትክክለኛ ነው ብዬ ለትግራይ ሕዝብና በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጥ ያስፈልጋል ብዬ አምኜ በነፍጥኛ ደረጃ በአብዮቱ ተሳትፈአለሁ። ይህን ሁሉ አደርጌ ታመርዐና ተቀጣው ። ያኽ ቡድን ትክክለኛ እንዳልሆነ አውቃለሁ" ብሎኛል ። ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት አምባሲ ሂደው እኛ በገዳዩ የለንበትም ፡ ዝም ብላችሁ ነው ያሠራችሁን አውንም እዚህ መጥተን ተሰቃየን እባካችሁ ልጆቻችንን እናሳድግበት ወደአገራችን ላኩን ብለው ተመልሰዋል ። «የሕወሓት» አባል የነበረ ሰው ከአስር ቤት ተፈትቶ ሱዳን ከሄደ በኋላ ወደዚህ ይመጣል ። ሰዎቹ ስለአሉ ሊመሰክሩ ይችላሉ ። ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ እኔ እዚህ ከመጣሁ በኋላ የትግራይንም ሆነ የኢትዮጵያን ጉዳይ በአመራር ላይ ለአለት የመንግሥት ባለሥልጣኖች ያቀረብኩት ነው ። እሱ እንደነርሱንዳ ሆኖ ስለሚቀርብ እኔም የትግራይ ሰው ስለሆንሁና ስለምተዘለውም ነው ያነሳሁት ። እንደ ጎይለሥላሴ ዘመን ይህ መንግሥት በትግራይ ላይ ያደረገው ነገር የለም ፡ ከአብዮቱ ወዲህ እያንዳንዱ ክፍለ ሀገር የለውጡን ፀበል ተምሶአል ፡ እንድም ሁለትም ፋብሪካ አግኝቶአል ። በጉንደር በወሎ ፡ በሲዳሞ ፡ በሸዋ ፡ በወለጋም አለ ። እንዴት በትግራይ አልተደረገም? የሚል እኔ ራሴ የምጠይቀው ጥያቄ አለ ። እነሱም በነሮጋንዳ የሚያቀርቡት ሌላው ደግሞ «የትግራይ ህዝብ በአስተዳደር ሥራ ውስጥ መሥራት የሚችል ህዝብ ነው ። በየጊዜውም ወደ ትግራይ የሚላኩ የመንግሥት ተወካዮች የአስተዳደር ኃላፊዎች በየቦታውም ያሉ ሰዎች እንዴት የትግራይ ሰዎች ሊሆኑ አይችሉም" የሚል ነው ። «የአገሩን ሰርዶ ባገሩ በፊ» ስለሆነ ችግሩንም ለመፍታት ሌላም ሥራ ለመሥራት የአገሩ ሰው በአገሩ መሥራት አለበት ። ይህን ሳልፈራና ሳላፍር የጠየቅሁት ጥያቄ ነው ። የጠየቅሁአቸው ሰዎችም በቀላሉ የሚገመቱ አይደሉም ።

የትግራይን ልማት በተመለከተ የተረበው ምንድነው «ሰላም ስለሌለ ለሚፈርስ ነገር እዚያ ገንዘብ ማፍሰስ አስቸጋሪ ሆነብን ።» ይህ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደኛው ነው ። ሁለተኛው ደግሞ «መንግሥት በትግራይ ውስጥ ሊኖር የሚችል ማዕድን ሊፈልግና ሊመረምር የሚችል በከፍተኛ ደረጃ የጂኦሎጂ ኢንስቲትዩት ለማቋቋም እቅዱ ሥራው በሙሉ ተዘጋጅቶ እያለ ያለጨ የመርንት ሁኔታ ሊያሰራ አልቻለም» የሚል ነው ። ይህን ደግሞ የተረዳሁት ከሰንዶች ነው ። ከኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ድክመት አለ የምለው ይህን የመሰለ ዝግጅት ከነበረው ለህዝብ መግለጽ ነበረበት ። ይሆ ለእንቲ ፕሮፓጋንዳ ከመጋለጥ ያድናል ። ሁለተኛውን ጥያቄ በሚመለከት የአስተዳደር ሥራ እንዲሠሩ በተለያዩ ቦታዎች ተመድበው ይሠሩ ዘንድ የተጠየቁ ሰዎች ስም ዝርዝር ነው የተሰጠኝ ። «ለምን ትግራይ ሄዳችሁ ለመሥራት አልፈለጋችሁም» ብዬ አንዳንድ ሰዎችን ጠይቄአለሁ ። «እዚያ እሳት ውስጥ ሄደን መሥራት አንፈልግም ፣ እዚያ ሞትሞት ውስጥ መግባት አንፈልግም የትግራይ ሰው በመሆናችን ከሁለቱም ወገን እደጋ ቢደርስብን አንችልም» ነው ያሉት ። «መንግሥትም ክፍት ቦታ ልንተው ስለማንችል የተተበለውን እንልካለን» ነው የሚለው። የኢትዮጵያ መንግሥት የአብራሪው ነገር ስለሌለ ይህ ጥሩ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ሆኖ ይቀርባል ፣ ይችላልም ። ይህንንና ይህንን የመሳሰሉ የፕሮፓጋንዳ ሥራዎችን ይሠራሉ ።

ስለ ፕሮፓጋንዳ የሚነሱ ነገሮች አሉ ። አንድን ነገር ከመቃወም በፊት እውነተኛ መሆን አለብህ ። የኢትዮጵያ መንግሥት አንድ ነገር ሠርቶ ሊሆን ይችላል ። ጥሩውን ጥሩ ፣ መጥፎውን መጥፎ ብሎ ማሰቀመጥ ተገቢ ነው ። ነጭ ፣ ነጭ ነው ፣ ጥቁር ፣ ጥቁር ነው ብዬ መቀበል አለብኝ ። ህዝብን በመንደር ማሰፈር በከፍተኛ ደረጃ የተማሪው ፣ የምሁሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ነበር ። እኔ እራሴ የምጠይቀው ጥያቄ ነው ። ድሮ አንድ ጉርድን ግላሰር የሚባል ካናዳዊ ጓደኛ ነበረኝ ። ይህን ይመስላል አገራችን ብዬ ሰሚን ወሰጅ አሳየሁት ። እናንተ መሬቱን የህዝብ አድርጋችሁ ይህን ደረቅ መሬት ላይ ያሰን ሕዝብ ወደ ይበብ መሰዳችሁ ማሰፈር አለባችሁ ብሎኛል ። ካናዳዊ ነው ፣ የጎበረት እርሻ በምዕራቡም በዓለም ውስጥ በጎሉ ዘንድ ከፍተኛ ውጤት ያሰገኘ ነው ። እውነት ለመናገር ሰውን ወደ ሱዳን መውሰድ ይሻላል ወይስ ወደ አሊባቦር ፣ ከፋና ወለጋ የት ነው ሕዝብ የሚያልቅብ ፕሮፓጋንዳ ሕዝብ የሚተበለው ዓይነት መሆን አለበት ። ሰፈራም ሆነ መንደር ምሰራም ምንድን ነው የሚያመጣው ? አገልግሎት በትክክል ማቅረብ ያስችላል ?

t.me/OLDBOOKSPDF

እርግጥ ዝግጅት ያስፈልጋል ። ገበሬው ተበታትኖ በሚሠራበት ጊዜ በግ በየግሉ እያረባ ገበያ ያቀርብ እንደሆን በህብረት በሚሠራበት ጊዜ ምን መሆን እንደአለበት በጥናቱ ውስጥ ማስገባት ። ይህ ፕሮፓጋንዳ ሆኖ ይሰራበታል። ደግሞስ የ«ሕወሓት» መሪዎች መመሪያችን ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ነው ካሉ የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት መመሥረትን መቀበል ነበረባቸው ። ሱዳን ወስደው የአፈሰሱአቸው እርባና ሃምሳ ሆነው በአንድ ጉድጓድ የተቀበሩት ወገኖቻችን አላለቁም? ወደ «ተባረክ ችው ፡ ወደ ቀዝቃዛዋ በውሃና በአዘርእት ወደ ለመለመችው» ሱዳን ነው የመጡት? መልኃ መሄድ ግን ማለት ነው ለነሱ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ስላካሄደው ብቻ መሠረተ ትምህርትን ይታወሳሉ ። ሕዝብ ማንበብ እና መጻፍ እንዲችል ማድረግ ምንድነው ጥፋቱ? መሠረተ ትምህርት በዩኔስኮና በልዩ ልዩ የዓለም ሕብረተሰቦች ዘንድ ምስጋናን ያስገኘ ሥራ ነው ። ይህ መንግሥት ስለአደረገው ብቻ መጥፎ መባል አለበት?

ፕሮፓጋንዳ እውነታዊ መሆን አለበት ። አንድ ሰው ግምገማ ሲያደርግ እውነተኛ ዳኛ መሆን አለበት ። ይህ ጥሩ ነው—ይህ መጥፎ ነው ማለት መቻል አለበት ። ሕዝቡ በአለው ብሔራዊ ስሜት ቋንቋህ ተደፍሮብሃል ብሎ ህዝቡን ማነሳሳት የሚያመጣው ነገር ዳጅት ነው ። እኔ አንድ ሰው ነኝ በእግሬ ወጥቼ ጠፍቻለሁ ፡ ዛሬም የትም ቦታ መኖር እችላለሁ ። እዚህ አገሬ ውስጥ ብሞትም ክብሬ ነው ።

<u>ጥያቄ</u>፡ በውይይቱ ያላነሳናቸው ነጥቦች ከአሉ ህዝብ ማወቅ አለበት የሚሉትን ቢገልጹልን?

<u>መልስ</u>፡ እኛ ኢትዮጵያዊ ስሜት አለን ። ይህ ችግር እልባት ማግኘት አለበት ። መንግሥት በየጊዜው የሚቀየር ፡ ሊቀያየርም የሚችል ነው ። እኛ ሁላችን ላንኖር እንችላለን ። አሁን አለን ነገ የለንም ። አገር ግን ለዘለዓለም የሚኖር ለትውልድ የሚተላፍ ነው ። በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ መድረክ በማግኘቱ አመሰግናለሁ ። አጋጣሚውን በመጠቀም ልናገር የምፈልገው እርስ በርስ በጉጥ ስንታገል ለልዩ ልዩ ችግሮች ሀገራችንን ዳርገናታል ። ሁሉንም ነገር በሰላም መጨረስ አለብን ። መንግሥት ለሰላም እያደረገ ያለውን ጥረት ከልብ እቀበላለሁ ። ለአለው ችግር ሰላማዊ መፍትሔ በሚጠየቅበት ጊዜ ማንም ኃይል «ማሌሊት» ይሁን

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሕወሓት» የተዘጋጁ ሆነው ይህን ህዝብ አሁን ከአለበት ሁኔታ ማላቀቅ
ይኖርባቸዋል ።

በቅርብ አሥረኞች በተለይም የኤርትራ ተወላጆች መፈታታቸው
በጣም ደስ አሰኝቶኛል ። የትግራይ ሰዎች በቁጥጥር ስር የዋሉ እንዲ
እገምታለሁ ። እርግጥ በዓላማው አምነው ሊሆን ይችላል ። ጭራሽም
የሌለበትም ይኖራሉ ። እኔም የተገነዘብኩትን ያህል ይህ እንቅስቃሴ
ያስፈልጋል ብለው አምነውበት ሊሆን ይችላል ። መንግሥትና ወላጅ
አንድ ነው ፡ ይምራል ። ልጅ ቢያጠፋ አጥፍተሃል ብሎ የሚያባርር ወላጅ
የለም ። መንግሥት በወላጅና በፈጣሪ ስለሚመሰል በቁጥጥር ስር የዋሉ
ይኖራሉ ብዬ የምላቸውን ምህረት ሰጥቶ ከቤተሰባቸው ተቀላቅለው
እንዲኖሩ እንዲደረግ መንግሥትን በዚህ አጋጣሚ እለምናለሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በመስጠት ነው ። በሱዳን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጥሩ አቀባበል አድርጉልኛል ። አሁን በእናት ሀገሬ ከተወለድሁበትና ከእደግሁበት ኅብረተሰብ ጋር ተቀላቅዬ በጥሩ ሁኔታ ኑሮዬን እየመራሁ ነው ።

ጥያቄ፡— በድርጅቱ ውስጥ በቆዩበት ጊዜ የነበረዎ የሥራ ኃላፊነት ደረጃ ምን ነበር?

መልስ፡— በ1970 የአንድ ሪጅን የካፒታል ኃላፊ ነበርሁ ፣ ከ1972—75 ደግሞ የሕክምና ክፍሉን በማስተዳደር ሥራ ቆይቻለሁ ፣ በ1975 የ«ሕወሓት» ሁለተኛ ጉባኤ በተደረገበት ጊዜ የድርጅቱ ጠቅላላ ሀብት ማለት ንብረትና ገንዘብ ሙሉ ተቆጣጣሪ ሆኜ እንድሠራ ተደረገ ። በ1977 ደግሞ «ማሌሊት» ሲመሠረት የድርጅቱ የፋይናንስ ኃላፊ ሆኜ እስከወጣሁበት ጊዜ ድረስ ሠርቻለሁ ።

ጥያቄ፡— እንደገለጹልን የተሰጠዎት ቦታ ከፍተኛ እንደመሆኑ ፣ የ«ሕወሓት» አፈጣጠርና ሁኔታ በገርገር ቢያስረዱን? ሁለተኛም ድርጅቱ በየጊዜው ስሙን እና ዓለማውን ይለዋውጣል ። ለምንድነው?

መልስ፡— በድርጅቱ ለረዥም ጊዜ ቆይቻለሁ ። የነበረኝም ሥልጣን ቢሆን በእርግጥ ከፍተኛ ነው ። ጥያቄው ይህ ድርጅት እንዴት ተፈጠረ? በነማን ተፈጠረ? መቼ ተፈጠረ? ለምን ተፈጠረ? የሚሉትን ጥያቄዎች ያካተተ ይመስለኛል ። ድርጅቱ የተፈጠረው በቀድሞው ኃ/ሥ/ዩኒቨርስቲ ማለትም በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከ1965—67 ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ። ጥቂት የአካባቢው ተወላጅ ተማሪዎች በዩኒቨርስቲው ነበሩ ። ጥቂት ስል የዓላማው አራማጆች ማለቴ ነው ። ለእነዚህ በጊዜው የተማሪው እንቅስቃሴ መኖር አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው ። ይህን ድርጅት እንዲቋቋም ያደረገው አሁን የት እንዳለ የማላውቀው መለስ ተክሌ የሚባል ተማሪ ነበር ። መለስ ተክሌ «ከሻዕቢያ» ጋር የጠበቀ ግንኙነት የነበረው ሰው ነው ። ከ«ሻዕቢያ» በመገናኘትና ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ድርጅቱን የሚመሠርቱ አንዳንድ የኤርትራ ተወላጅ የሆኑትንና ትግራይ ውስጥ የሚገኙትን መልምሎ አሰባሰበ ፣ ወይም እነሱ እንዲደራጁ አደረገ ። ከነዚህ ውስጥ ግደይ ዘርዓጽዮን አክሱም ያደገ፡ የኤርትራ ተወላጅ መሆኑን በትክክል የማውቀው ፣ የግልም ግንኙነት ያለን፡ መለስ ዜናዊ ትክክለኛ ስሙ ለገሠ ዜናዊ አሁን በድርጅቱ ውስጥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ያለ የኤርትራ ተወላጅና የደኅዝማች አስረስ የልጅ ልጅ ፣ አትክልት ፀሐዬ አሁን ዓባይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወሕዱ ተብሎ የሚጠራው የ«ማሌሲትና የሕወሓት» ሊቀመንበር እሱም የኤርትራ ተወላጅ ነው ። ሥዩም በርሄ የሚባል የኤርትራ ተወላጅና አሁንም በከፍተኛ አመራር ላይ ያለ ፡ የትግራይ ወያኔ ነው ለማስኘትና በሽፋን እንዲያገለግል ለማመቻቸት አረጋዊ በርሄ ተቀላቅሎ በመጀመሪያ ጊዜ ስብሰባ አደረጉ ። እነዚህ በሚሰበሰቡበት ጊዜ «ማኅበር ገሥገሥቲ ብሔረ ትግራይ» (ማገብት) የሚል ስም ያለው ድርጅት አቋቋሙ ። እነዚህ ሰዎች ዓላማቸው ምንድነው? ለትግራይ ብሔረሰብ ሊታገሉ ነው የመጡት? ወይስ ሌላ ዓላማ አላቸው? ኤርትራዊ መሆናቸውን ገልጫለሁ ። በሽፋንነት «ማገብትን» ካቋቋሙ በኋላ ንቃተ ሕሊናቸው ገቅ ያሉትን አንዳንድ ሰዎች በማሰባሰብ በ1967 ጥር ላይ ወደ "ሻዕቢያ» ሄዱ ። "ሻዕቢያ» «ኢ·ፒ·ኤል·ኤፍ·» ማለት ነው ። እዚያ ሄደው አስፈላጊውን ትምህርት ከተቀበሉ በኋላ ትግራይ ውስጥ ሄዳችሁ መንቀሳቀስ ትችላላችሁ ተባሉ ።

የኤርትራ ተወላጅና በ«ሻዕቢያ» ውስጥ ከፍተኛ አመራር ውስጥ የነበረው ሙሴ ባራክ እንዲሁም አሁን በ«ሕወሓት» ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን ያለው በበረሃ ስሙ ጃማይካ ተብሎ የሚጠራው የማነ ኪዳኔ ፡ ማለት ሁለቱ ኃላፊ ሆነው እንዲመሩት ሆኖ መደትግራይ ገቡ ። ትግራይ ከገቡ በኋላ ይህ ድርጅት (ሕወሓት) ተመሠረተ ። ይህ ድርጅት የሚንቀሳቀሰው ከ«ሻዕቢያ» ባመጣው ፕሮግራም ነበር ። ፕሮግራሙ «ኤርትራ የኢትዮጵያ አይደለችም ፡ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ፡ ስለዚህ የኤርትራ ጥያቄ መፈታት አለበት ። እኛም በትግራይ ውስጥ የመጣነው ለትግራይ ብቻ አይደለም ። ለሁለቱም ነው ። ለኤርትራ መገንጠል ሙሉ ኃይላችንን እናውላለን ። እስከመጨረሻም ደማችንን እናፈሳለን ። የትግራይ-ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ መንግሥት እንመሠርታለን» የሚል አጭር ነበር ይዘው የወጡት ። ከነሱ መካከል አረጋዊ በርሄ ነበር ። ፕሮግራሙን እሱ ይዞት ቢመጣም አንዳንድ ጥያቄዎች ነበሩት ። እነዚህ ጥያቄዎች በመነሳታቸው ከ1968 ጀምሮ ትርምስ ተፈጠረ ፡ ይህ ደግሞ የራሱ ታሪክ አለው ። በአንድ ቃል ከመጀመሪያ እስከ አሁን ድርጅቱ (ሕወሓት) የራሱ ነፃ አመራር የሌለው ፡ ከሻዕቢያ እንዲመሩ እንዲደረጉ በተላኩት በሙሴ ባራኪና በየማነ ኪዳኔ የተፈጠረ ነው ማለትነው ።

ጥያቄ፡— ድርጅቱ ገና ሲነሳ የተጣመመ ዓላማ ነበረው ። የትግራይን ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ለመመሥረት ይፈል

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋል፡ ይህን እንዴት ተቀብላችሁ ገባችሁ? አርስዎ መቼ ወደ ድርጅቱ ገቡ? የትግራይ ልጆች እንዴት ሊቀበሉት ቻሉ? ተቃውሞ አልነበረውም በእውኑ ሰዓትስ ቢሆን በ«ሕወሓት» ሥር የተሠለፈው ኃይል ብዙኃኑ የትግራይ ተወላጆች ድርጅቱ በ«ሻዕቢያ» መቋቋሙን የ«ሻዕቢያ»ን ዓላማ ማራመዱን ያውቃሉ? ወይስ እነሱም ተቀብለው እያራመዱት ነው?

<u>በሀልስ</u>፡— መሠረታዊ ጥያቄ ነው ያነሳችሁት ። ወደ ብዙ ጉዳዮች ያገባናል ። ወደዚህ ድርጅት በ1968 መጋቢት መር ነው የገባሁት ከ1966—67 ድግሞ በከተሞች ማለትም በአድዋና በማይጨው መሬት እንቅስቃሴ አደርግ ነበር ። በጊዜው ማይጨው በመንግሥት ሥራ ላይ ነበረው ። በ1966 አረጋዊ በርሄን መተሲ ላይ አግኝቼው እንደዚህ ያለ ድርጅት ልናቋቁም ፈልገናልና ተስ በተስ ለትግራይ ልጆች ንገራቸው አለኝ። በዚያ ጊዜ ፈጣርሶ የፖለቲካ ዕውቀት አልነበረንም ። በሞኙን ዓይን «ትግራይ ትነጠላለች የትግራይ መንግሥት እናቋቁማለን» ነበር ያለኝ። አውን ሳስበው ያህ አንድ ጠባብ ስሜት ነው ። እንዴት ያህን ልናራምድ ቻልን? የሚለው ጥያቄ አውን እራሴን ያመታኛል ። መንፈሴን ያረብሸዋል ። በ1967 የካቲት 11 እንቅስቃሴ ሲጀምሩ ሥራዬን ትቼ እነሱን ፍለጋ ወደ በረሃ ሄጄ ነበር ። ወደ «ሻዕቢያ» ሄደው ስለነበር አሳግኝኋቸውም ። በዚያው ዓመት ክረምት ላይ ገጠር ቤተሰቦቼን ለማየት ከጓደኞቼ ጋር ሄጄ ሠርግ ላይ አረጋዊ በርሄንና በአውኑ ጊዜ የድርጅቱ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ የሆነውን ሥዩም ዮሴፍን አግኝቻቸው ። የት ጠፋህ አሉኝ ። እንቅስቃሴ የሚያረግበትን መንገድ ከገለጡልኝ በኋላ ለጥቂት ጊዜ ከተማ ውስጥ እንድቆይ ተነገረኝ ። በ1968 መጋቢት ከነሱ ጋር ተቀላቅዬ በረሃ ገባሁ ።

የኤርትራን መገንጠል ፡ የ«ትግራይን ሪፐብሊክ መንግሥት» ማቋቋምና «ከሕረሰብኝ የራሳቸውን መንግሥት እስክ መሠርቱ ድረስ መለያየት» የሚለውን «የ<u>ሕወሓት</u>ን» ፕሮግራም እያወቃችሁ ነው ሳታውቁ ተቀላቀላችሁ እስከአውን ድረስ የቆያችሁት እንዴት በዘምታ አያችሁት?» ብላችሁ ለጠየቃችሁኝ ወደ 1968 ልመልሳችሁ ። በዚህ ዓመት አረጋዊ በርሄ በኮሮጌዎ ላይ ያቀረበው ጽሑፍ ነበር ። ጽሑፉ «ስለትግራይ ጥያቄ ማንሳትና መዋጋት ጠባብ ብሔርተኝነት ስለሆነ ትግራይ ብቻ ማለት የለብንም ። የኢትዮጵያ ጎብረተሰብ በአገር ውስጥና

t.me/OLDBOOKSPDF

በውጭ ያለው የተማረው ወገን አይተበለንም ። ጠባብ ብሔርተኛ ናችሁ ብሎ ሊጠላን ይችላል ፣ ያስመታናልም» የሚል ነበር ። «በስትራቴጂያዊ ብሔራዊ ትግል እንደ ስልት ሆኖ ተቀምጦ በእኩልነት የምትመሠረት ኢትዮጵያን ማዋቀር እንደ ዓላማ በፕሮግራማችን ውስጥ መግባት አለበት» ብሎ ነበር ።

ከዚያ በኋላ በ1968 ከ«ቲ·ፒ·ኤል·ኤፍ·» ማንም ወያኔ ሳያሰበሰብና ሳያውቀው አባይ ፀሐዬ ፣ መለስ ዜናዊና ስብሐት ነጋ ወደ ሱዳን ሄዱ ። «የ1968 ማኒፌስቶ» የሚል ጽሑፍ ይዘው መጡ ። «በማኔፌስቶው» አረጋዊ በርሄ ያቀረበውን ሐሳብ ጥለው ፣ ኢትዮጵያን በእኩልነት እንመሥርት የሚለውን ሰርዘው <u>አንደኛ «የትግራይ ሪፐብሊክን መንግሥት መመሥረት አለብን ፣ የምንታገለውም ለዚህ ነው ፣ ሁለተኛ ብሔሮች ወይም ብሔረሰቦች ተገንጥለው የራሳቸውን መንግሥት ማቋቋም አለባቸው ፣ እኛ ስለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እኩልነት አንታገልም ። ከፕሮግራማችን ውጭ አድርገነዋል»</u> የሚል ጽሑፍ ይዘው መጡ ። በረሃ ለአሉት ሁሉ ተበተኑ ። እንደ «ኢሕአፓ» ያሉ ቡድኖች አገኙት ። «ኢሕአፓ» የትግራይ ወያኔ ጠባብ ብሔርተኝነት የተጠናወተው መሆኑን ፣ ኢትዮጵያን ሊያፈራርስና ሊቆራርስ ነው ለሚለው ክስማስረጃ አገኙ ። በዚህ ጊዜ በነመለስ ዜናዊ የተጻፈው ማኒፌስቶ የተለየ አተባበል ጠበቀው ። በ«ሕወሓት» ውስጥ የነበሩ ሰዎች «ይህ ጉባኤ ተጠርቶ ነው የተወሰነው ወይስ እንዴት ነው? ሌኢትዮጵያ እኩልነት ትግል ማካሄድ ከንቱ ነው ተብሎ የተቀመጠው እንዴት ነው?» የሚል ጥያቄ መጣ ። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ «በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ እኩልነት ብሎ መታገል ትልቅ ተራራ እንደመግፋት ያለ ፣ አልቂትን የሚያስከትል ነው» ይል ነበር ጽሑፉ ። «ኢትዮጵያ የሚል ነገር መነሳት የለበትም ፣ እኛ ለትግራይ ብቻ ተዋግተን ነፃ ከወጣን በኋላ የትግራይን መንግሥት ማቋቋም አለብን» አሉ ። በ1969 ላይ ይህ ሁኔታ ድርጅቱን አናጋው ። አንደኛ ፣ «ይህ የጠባብ ብሔርተኝነት ስሜት ነው ። ማኒፌስቶውን አንተበልም ። ይህን ተተብለን ብንታገል ጠባቦች ናቸው ተብለን በኢትዮጵያ ሕዝብ እንመታለን» በማለት ከፍተኛ ተቃውሞ ተነሣበት ። እንደሚታወቀው በአመራር ላይ ያሉትና አመራሩን ሙሉ በሙሉ የሚይዙት የኤርትራ ተወላጆች ናቸው ። በማዕከላዊ ኮሚቴ ለይስሙላ ከተወሰኑ ተወላጆች አረጋዊ በርሄ ብቻ ነበር ። ይህ ደግሞ «እኛን ለማያናገር

t.me/OLDBOOKSPDF

የነሱን አሠራር ለማቀላጠፍ የታሰበ ነው» በማለት ብዙ ሰው ተነሳ። «ሕወሓት» ሠራዊት እየወጣ ማማሸጉ ወደ መንግሥት ሲገባ ግመሽሹ ወደ ሱዳን ሄደ። ንዴቱ በብዛት ተናጋ። ተከፋፈለ። በዚያን ጊዜ አመራር ላይ የነበሩ ሰዎች እኔህ ተቀናቃኞች አንድ ነገር ሳያደርጉ እርምጃ መወሰድ አለበት አሉ። በዚያን ጊዜ ከ«ሻዕቢያ» የመጡ ሰዎችም ጉዳዩን በነሱ መነከል በአንድ ወቅት ተፈጥሮ ከነበረው ከመንካ እንቅስቃሴ ጋር አነፃፀሩት። ለትክክለኛ ዓላማ የቆሙት መምህር ዳዊት የተባለ የአዲግራት ተወላጅ፣ አጽብሃ ዳኘው የተባለ የአድዋ ተወላጅ፣ ዕቁባግዚ በየነ ከአክሱም፣ ሕንፃ ሽፈራው ከሽሬ፣ ወርቅነህ ሐጐስና በርሄ ጥላሁን ከአድዋ፣ መንገሻ በላይ ከሽሬ፣ አባይ ደግፈኢና ሙሉጌታ አብርሃም ከእንደርታ፣ (መቀሌ ነው የተማረው)፣ አልማዝ አሰፋውና ከዳኔ ግርማ (ሁለቱም መቀሌ ተወልደው መቀሌ ያደጉ) ሃዲሽ ዮሐንስ ከአዲግራት እነዚህ በሙሉ «ዓባይ ወሐዬና መለስ ዜናዊ የሚሠሩት ትክክል አይደለም እኛን ቆሎ በቱጥጥር ሥር ማዋል አለብን» ብለው ተንቀሳቀሱ። እስከመፈረሻው ሊገፉበት እንደተነሱ በሊሊት ታፍነው ተወሰደው ተገደሉ። እንቅስቃሴያቸው ያስገኘው ውጤት ግን አለ። የወያኔውን ንዴል ለሁለት በመክፈል የተወሰነው ድርጅቱን ጥሎ እንዲወጣ አድርጓል።

በዚህ ድርጅት እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ ለመፍጠር የቻለው የብሔርተኝነት ስልታዊ ሆኖ በስትራቴጂ ደረጃ በእኩልነት የምትመሠረተውን ኢትዮጵያን የሚያነቃቱትን የመጀመሪያ ፕሮግራሙን «ስንኩል ፕሮግራም ነው» በማለት «ሕወሓት» ውድቅ ማድረጉ ነው። ያን ውድቅ ባደረገበት ጊዜ እንደገና ተሠርቶ ይመጣል ያለት ፕሮግራም ነበራቸው። ዓባይ ወሐዬ፣ መለስ ዜናዊና ስብሐት ነጋ ሱዳን ሄደው የወጉሬያን ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት» ማቋቋም፣ የኤርትራ ሙሉ በሙሉ ቅኝ ግዛት መሆንና መገንጠል እንዳለባት ያመለከተ ብሔረሰባቸው ራሳቸው ተገንጥለው የራሳቸውን መንግሥት ሊመሠርቱ ይችላሉ የሚል ሁሉም ብዙ የጠቀስነውን ፕሮግራም ይዘው መጡ። በሳይንሳዊና በዲያሌክቲካዊ ትንተና አንድ ብሔረሰብ የራሱን መንግሥት መመሥረት ይችላል? እነዚህ ሰዎች ከሱዳን ይዘው በመጡት አቋም። በግንባሩ መነከል እንዳለባት ውዝግብ ተነሳ። ብዙ ሰው አለቀ። እነሱ ግን ከ«ሻዕቢያ» በሚያረማላቸው ድጋፍ ንዴላቸው ላያፈርስ አውንም ሥልጣን ላያ ናቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ፡— በ«ሕወሓት» አፈጣጠር ላይ የምንመለስበት ጥያቄ አለን፡ ራሱ «ማኅበረ ገሰገስቲ ብሔረ ትግራይ) ሲመሠረት በብሔር ስም ነው የተንቀሳቀሰው ። ከአጠቃላይ መሥፈርት አኳያ ትግሉ በትግራይ በራሱ ውስጥ ቢጀመር ኖሮ ብሔር የሚለውን ለመፍጠር የተሟላ መመዘኛ ነበር ወይ?

መልስ፡— ይህ በ1968 መጨረሻ በግለሰብ ደረጃ የምንነጋገርበት ጉዳይ ነበር ። ብሔር የሚባለው በሳይንስ የታወቁ መመዘኛዎች አሉት ። በቋንቋ ፡ በኢኮኖሚ ፡ በባሕል ወዘተ ፡ የሚጠቀሱት ነጥቦች መሟላት አለባቸው ። በዚያን ጊዜ ለዚህ እንቅስቃሴ መመዘኛዎች አልተሟሉም ። «ጠባብ ብሔረተኛ ያሰኘናል ። ስማችንን ያስጠላዋል» የሚል ተታውሞ ነበር ። እዚህ ላይ አንድ ነገር ልጥቀስ — በዚያን ጊዜ «ኢሕአፓ» አሲንባ ላይ ትንቀሳቀስ ነበር ። ሕዝብን የምንስተምረው «የሕወሓት ሰዎች ጠባብ ብሔርተኞች ናቸው» እያለች ነበር ። «እናንተ እንዴት ራሳችሁን ብሔር ብላችሁ ትጠሩላችሁ? እንዴትስ ብሔር ብላችሁ ትንቀሳቀሳላችሁ? ይህ ከሳይንስ ውጪ የሆነና ውዝግብ የሚፈጥር ነው። ሳይንሱን አላያችሁም» በማለት ሟትሟት ተፈጥር ነበር ። «ኢሕአፓም» በእኛ ውስጥ ጥሩ ድጋፍ ታገኝ ነበር ። ይህ ነገር እንዳለ ሆኖ በ«ሕወሓት» አመራር ወደድክም ጠላህም የበላይ አመራር ያመጣልህን ነገር እሱን አንብበህ በትክክለኛነቱ አምነህ ማስረዳት ነው ። ትግራይ ብሔር አይደለም ብለህ ብትከራከር ዋጋህን ታገኛለህ ። አንድ ጊዜ ስለገባህ ትከተላለህ ። «ሕወሓት ማሌሊት» ሊያሳስተን የቻለው ደግሞ ከእኔ ጀምሮ ሁላችንም ዝቅተኛ ንቃተ ኅሊና ስለ አለን ነው ። ንቃተ ኅሊና ቢኖረኝ ኖሮማ ይህን ፕሮግራም በማይበት ጊዜ «የተሳሳተ ነው ፡ የእርስ በርስ እልቂት ያፈጥራል ። አልሰማማበትም» ብዬ ወደ ቤቱ በመመለስ እናቱን አመር ነበር ።

በውስጣችን ይህን ለማስረዳት ይታገሉ የነበሩ አንጋ ፈጣሪዎች ናቸው ተብለው ይከሰሳሉ ። በ«ሕወሓት» ውስጥ የስለላ መረቡ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተጠናከረ ነው ። እኔ አንድ ነገር ለእያንዳንዱ ብነግረው ወይም እያንዳንዱ ቢነግረኝ በቀጥታ ለማዕከላዊ ኮሚቴ እከሌ እንዲህ አለኝ ብሎ መንገር አለበት ። ያ ሰው ባልሠራውና ባልጠረጠረው ሰዓት ተይዞ እርምጃ ይወሰድበታል ። አንድም በዚህ ሁለተኛም ፡ የምናውቀው

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሌለን ዝም ብለን እናፈጠሞብ ነበር ።

የ «ትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት» ለመመስረት የነበራቸው ዓላማ የተጋለጠው በአንዳንድ ሻል ብለው በተገኙ ሰዎች ነው እንጂ ብዙዎቻችን ዝም ብለን ስናፈጠሞብ ነበር የቆየነው ።

ጥያቄ፦ በመያኔው ቡድን «ሕወሓት» መባል እስክ ደረሰበት ድረስ «ተሓሕት» ወይም «ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ» ይባል ነበር። እና «ተሓሕት» በምን ነጥብ ነው ከ«ማኅበት» የሚለየው?

መልስ፦ «ማኅበት» «ማኅበር ገሥገሥቲ ብሔረ ትግራይ» ይባል የነበረው ነው ። የተመሠረተው በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው ። እንማን እንደመሠረቱትም ገልጫለሁ ። «ማኅበር ገሥገሥቲ ትግራይ» በማለቱ ብቻ የትግራይ ተወላጆች ከእኛ ጋር ይሰለፋሉ ተብሎ አቋም የተያዘበት ነው ። በዚህ ሰዎችን አሰባስበው ሲጨናነሩ የነበቱት 11/1967 በረሃ ከመጡ በኋላ «ተጋድሎ ሓርነት ትግራይ» የሚል አዲስ ስም መጣ ። ይህ ስም አንድ ወር ከአሥራ አምስት ቀን በ«ሻዕቢያ» ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ይዘውት የመጡት ነው ። በኅብስ ዘለላ ዙሪያውን የተከበበ የእነሱም ሐውልት ያለበት ብ«ሻዕቢያ» የተቀረፀ ማኅተም ተሰጥቷቸዋል። ስሙ የተሰጣቸው ከ«ሻዕቢያ» ነው ። በዚህ ስም እስክ 1975 ድረስ ተጠቀምንበት ። የስም መለዋወጥ የሚደረገው ለምሳሌ «ማኅበት» ሲፈጠር በአዲስ አበባና በሌሎችም ከተሞች ያሉ የትግራይ ተወላጆችን ለማሰባሰብ የተፈጠረ ታክቲክ ነው ። ሌላ ስም ቢመጣ ምን አገባን እንላለን ። እኔም በረሃ የገባሁት ትግራይን ስለነካ ነው ። ሌሎችም ልክ እንደኔ የመጡ ናቸው ። «ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ» የሚለው ስያሜ የተሰጠው ደግሞ አውንም ወያኔ ብሎ እራሱ ይህን ስም ስለያዘ የትግራይ ሕዝብ ይቀበለዋል ወይ? የትግራይን ስም ስለያዘ የትግራይ ሕዝብ ይቀበለዋል ። የትግራይን ስም ካነሳ በትግራይ ገጠሮች ለመንቀሳቀስ ይችላል ፡ ሕዝቡ ሲመታው አይችልም ። ለእናንት ብለን የመጣን ነን ብሎ ለማታለል ይመቸዋል ።

ጥያቄ፦ ፕሮግራም ነበረው?

መልስ፦ ነበረው ። ይህ ፕሮግራም አንደኛ ፡ «ኤርትራ ቅኝ ግዛት ናት» የሚል ነው ። ከፕሮግራሙ ላይ «የኤርትራ ሕዝብ ጥያቄ በታሪክ በሕጋዊ መንገድ በኢኮኖሚና ሠራዊት ትንታኔ አንፃር ስታየው ፍትሐዊ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሆነ አገራዊ ነፃነት የሚጠይቅ ነው ፡ ስለሆነም ለሀገራዊ ነፃነት በኢትዮጵያ ስር ያለውን የቅኝ ግዛት ሀገር ነፃ ለማውጣት የሚደረግ ትግል ነው» ሲል በፕሮግራሙ መግቢያ ላይ አስቀምጧል ።

«የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ስንል በአገር ውስጥና በውጭ ያሉ ብዙ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር መንግሥታት ለምን አይተበሉትም» ይላል ፕሮግራማቸው ። ከፕሮግራሙ እጠቅሳለሁ «ቱጥራቸው በጣም ብዙ የሆኑ አማርኛና የአማራ ገሸር መደባች የታሪክ ጸሐፊዎች በስፋት በዘረጉት የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ኤርትራን የኢትዮጵያ አካል እንደነበረች አስመስለው ያቀርባሉ ። ያህ አለ-ፃልታ ነፁራ መሬ አያልፍም» ይላል ጽሑፉ ። ስለዚህ ይላል ሲያጠቃልል «እንዚህ እክሎች ማለትም አማራና የአማራ ገሸር መደባች የራሳቸውን ጥቅም ለማስከበር ሲሉ ኤርትራን በቅኝ ግዛት ሲያማቅቋት ያገኛሉ» ይላል ። ያህ ከመጀመሪያ ፕሮግራሙ መግቢያ ላይ የሚገኝ ነው ። በአጠቃላይ ልጠቅስ የምፈልገው «ቲ-ፒ-ኤል-ኤፍ» ብዙ ታሪክ ጸሐፊዎችን ውሸታም ናቸው ብሎ ታንቋሽሽ ። ለምሳሌ ያክቡር አክለሉ ለማ የብሊሃርዚያን መድኃኒት ያገኙ ሰው ናቸው ። ጎለም አቶ፡ አክብሮት አግኝተዋል ። የዶክተር አክለሉ ግኝት አያረባም የሚል ሰው ካለ እራሱ ተሞርዶ ነው የሚሄደው ። መያኔም እንዲሁ ናት ። የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪዎች በጎለም ውስጥ ተዘዋውረው ያጠኑ ናቸው ። አንዱን የታሪክ ጸሐፊ አንተ ተንስተህ ውሸታም ነው ልትል አትችልም ። በምሁራን ላይ ያላት ንቀትና ማንኳሰስ እስከዚህ ነው ።

ጥያቄ፡ «ሕወሓት» በአንድ በኩል «ለትግራይ ብሔረሰብ አታገላለሁ» ይላል ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ «ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለሁ» ይላል ። በእሁኑ ወቅት ደግሞ በእኩልነት ለመመሰረት እታገላለሁ» ይላል ። እንደተገለፀው ደግሞ «የኤርትራ ጥያቄም በፍትሐዊ መንገድ መፈታት አለበት» ይላል ። ለሚከተሉትና መረዳት ለሚፈልግ እንዚህ አቋሞች የማይጣጣሙና እስከ ጋራ መስለው ነው የሚታዩት ። ያሀን ሁሉ አቋም በአንድ ጊዜ የሚያካሒደው ለምንድነው?

መልስ፡— አንድ መንግሥት ወይም ድርጅት ፕሮግራም አለው ስንል እስትራቴጂውንና ታክቲኩን ተያይሏል ማለት ነው ። ለዚህም ነው የመያኔው ቡድን በፕሮግራሙ የኤርትራን መገንጠል አምኖ ያስቀመጠው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አውን በሚነሣው አለባልታ «ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመመሰረት ነፃነትና እኩልነት ለማምጣት ነው» ይላል ። እናንተም ትሰማላችሁ እንም እሰማለሁ ። በአማርኛና በትግርኛ የሚያሰራጨውን አዘጋጅላለሁ ። አንዳንድ ጊዜ ያስቸኛል ፡ ያስዝመኛልም ። አንዳንድ ጊዜ ያስታ ያስቅል ፡ ሌላ ጊዜ ሀዘንም ያስቅል» ። እኔ ግን አስታለሁ ፡ አዝናለሁም ። ይህ ድርጅት ዋንኛ ዓላማውን ለመሸፈን ሲል «ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት» ይላል እኩልነት ነፃነት ለማምጣት ይላል ፡ ይህ ሐሰት ነው ። በ1981 መጋቢት ላይ የወጣው ፕሮግራም እስትራቴጂ ምንድነው ያዘጋጅከው?

የዚህ ፕሮግራም እስትራቴጂ አንደኛ የትግራይን መንግሥት ለማቋቋም ፡ ሁለተኛ ማንኛውም ብሔር አውን ኢትዮጵያ ተብላ ከምትጠራው ውስጥ (ኢትዮጵያ የምትባል አገር መኖሯን አያውትም ፡) የሚኖሩ ብሔረሰቦች ተገንጥለው የራሳቸውን መንግሥት ማቋቋም ይችላሉ ። ሶስተኛ በትግራይ ውስጥ ያው ብሔረሰቦች (ትግራይ እንደ እንድ ብሔር ተቆምጧል) የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን ተንጥለውም የራሳቸውን መንግሥት መመሥረት መብት አላቸው ይህ ፕሮግራምም ይህን ያረጋግጣል ይላል ። ቀጥሎ ደግሞ ሶስት ጉዳዮችን ያነሳል ። በአሁኑ «የትግራይ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ ወስኖ የትግራይ ሪፐብሊክ መንግሥት ያቋቁማል ፡ ሁለተኛ በትግራይ ውስጥ ያሉ ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል ራሳቸው ወስነው መንግሥት መመሥረት አለባቸው ፡ ሶስተኛ የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ስለሆነ አውን በኤርትራ ለሚነሣው ትግል እስከ መጨረሻ ደጣችንን እናረዳለን ፡ ነፃነት እናስጨብጣለን ያላል ። እነዚህ ሦስት አበይት ነጥቦች በእስትራቴጂ ደረጃ የተቀመጡ በመሆናቸው ትግላችን እንዚህ ግብ እስኪመቱ ነው» በማለት «በማሰሊት» ፕሮግራም ላይ ሰፍሯል ።

እዚህ ላይ ልናገር የምፈልገው ዓርማው ክብ ንፁር ነው ። ክበብ መጀመሻ ማጫድ ክላሽን አስበት ። የማጭድና የመዶሻው ያታወቃል ፡ ክላሽን ለምን ገባ የምትል ከሆነ «እስከ መጨረሻው ተዋጋቱን የትግራይ ርዝባለነ ተመሥርታ ፡ በሶሻሊስት ትግራይ ደግሞ ከሚኒስት ትግራይን እንመሠርታለን» የሚል ነው ።

"ነፃነት ወየማለለ ትን» አፈጣጠር በተመለከተ እንመለስበታለን አውን ያልነካነው ያለ ስለመሰለኝ ፡ ወደዚያ እንሂድ ። «ማኅበራ

t.me/OLDBOOKSPDF

«ተሐሕት» ተፈጥረዋል ተጥሎ የመጣው «ወያኔ ሐርነት ትግራይ» የሚለው ነው ። ይህስ ትርጹና ይዘቱ ምን ይመስላል? አፈጣጠሩ እንዴት ነው?

<u>ሠላስ</u>፡ «ማኅበት ፡ ተሐሕት» እንዴት እንደተቋቋመ አይተናል ። እሁን የወያኔውን ድርጅት «ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ» በመባል ነው የምናውቀው ። ያህ ድርጅት ስሙን ለመለዋወጥ ምክንያቶች አሉት። ቀድሞ የነበረው «ተጋድሎ ሐርነት» የሚለውን ለመለወጥ ምክንያት ነበረው ። በዚያን ጊዜ በኤርትራ ውስጥ የሚንቀሳቀስት «ሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራና» «ተጋድሎ ሐርነት ኤርትራ» ነበሩ ። በ«ተጋድሎ ሐርነት ትግራይ»ና በ«ተጋድሎ ሐርነት ኤርትራ» መካከል መመሳሰል ስለመጣ ስሙ ተለውጦ ሌላ ስም መውጣት አለበት ተባለ ። እናም በአባልነቱ ዐተገኘውበት በሁለተኛው ጉባኤ ላይ ነው ስሙ የተለወጠው ። በዚያን ጊዜ ሁለት ስሞች ተርበው ነበር ። አንዱ «ሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ትግራይ» ነበር ። ከዚህ ስም ውስጥ ግንባር የሚለውን «ወያኔ» እንበለው የሚል ሃሳብ ተረበ ። ለዚህ የተሰጠው ምክንያት «ግንባር ብለን ከተረብን የሻዕቢያ አራማጅች ናችሁ ፡ በኃሳ ነው የምትመሩት የሚለው ተቃውሞ ይጠናከርብናል» የሚል ነበር ።

መሐመድ ረመጻን የሚባል የሻዕቢያ ሊቀመንበር የነበረ በዚያ ጉባኤ ላይ ተሳትፎአል ። ሌላው የተሳተፈው ስብሐት ኤፍሬም የሚባል በሻዕቢያ ትልቅ ስፍራ ያለው ፡ በበረሀ ወዲ ኤፍሬም ብለን የምንጠራው ሰው ነው ። ስብሐት ኤፍሬም ከ«ሻዕቢያ» ተወክሎ ሙሉ በሙሉ ወያኔ ትግራይን የሚቆጣጠር ሙሉ ጊዜውንም በዚህ የሚያሳልፍ ሰው ነው ስለሆነም በጉባኤው ላይ የ«ሻዕቢያ» ሊቀ መንበርና ወዲ ኤፍሬም ተጣምሮ ማለት ነው ። ግንባር የሚለው ታክ ፡ነትን ግልጽ ስለሚያደርገው ወያኔ የሚለውን ቃል እንጨምር ተባ ፡ ። ያህ «ወያኔ» የሚለው ቃል የመጣው ከ1935 36 በትግራይ ኦነኒ «ወያኔ» ወይም «ኤፈና» የሚባል እንቅስቃሴ ነበር ። «አማራምች እኛን አይገሁንም ፡ አማራምችን ሁሉ በመምታት ራሳችንን ነፃ ማውጣት አለብን» ይል ነበር ። እንቅስቃሴው በትግራይ ባላባቶች የተፈጠረ ነበረ ። ወያኔ የሚለው አሁን መጣት አለበት ፡እንደሸፍንሦ ለያገለግልዎ ላል ተባለ ። በዚህ ጊዜእኔ ወዲ ኤፍሬም ግምባር የሚለው ተሰርዞ መያኔ ፡ ሚለው ይጣባ ሲል ሀሳብ

t.me/OLDBOOKSPDF

አተረጓጎም ። በአጠቃላይ የወደፊቱ ስም መለዋወጥ ሠንጠረዥ የተሠራ ነው ። ሕዝቡን ለማደናገር ያገለግላል ። «ሕወሓት» የ«ሻዕቢያ» ትዮረንኒድንም የሸፈነችበት ስም ነው ።

በዚያ ጊዜም ነበረው ። በዚያ የተገኘን ሰዎች ለሁለት ተከፍለን ነበር። «ሁለታችንም በመርህ ላይ ስለምንገኝ ሕዝባዊ ግንባር ትግራይ መባል አለበት ፣ ከሕዝባዊ ግንባር ኤርትራ ጋር አንድ ዓይነት ፕሮግራምና እስትራቴጂ የምንከተል በመሆኑ የሚስማማው ይህ ነው» የሚል ሀሳብም ነበር ። «እንዲያውም አስካሁን ድረስ የሻዕቢያ ግርፍ ፣ የሻዕቢያ መስመር አራማጅች ተብለን ስንጠራ ስለነበር ግንባር መባሉ ይበልጥ ግልጽ ያደርገዋል» በማለት ወደፊት የሚለው ታል ተቀባይነት አገኘ ። ተደም ሲል «በስምም ሠን በስትራቴጂ አንድ ነን» የሚል ጽሑፍ ነበራቸው ።

<u>ጥያቄ</u>፡ «ሕወሓት» ታሪክ ጸሐፊዎችን በተለያም ደግሞ የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎችን እንደሚንቅ ፣ እንደሚያንቋሽሽ አንስተው ነበር ለመሠኑ በምን ዓይነት ታሪክ ነው የሚያምነው? በተለይ የኢትዮጵያን አንድነት ታሪክ እንዴት ያየዋል?

<u>መልስ</u>፡ ይህ ጥያቄ ሰፊ ማብራሪያ ማግኘት ያለበት ይመስለኛል ። ወደፊው በኢትዮጵያ አንድነት ታሪክ ምን ዓይነት አቋም አለው? ብለን እንደጠየቅነው የኢትዮጵያ ታሪክ ምሁራን ለአማራውና ለአማራው ገዢ መደብ ተገዥ በመሆናቸው ጥቅማቸውን ለማግኘት ሲሉ ኢትዮጵያን የሦስት ሺ ዓመታት ታሪክ አሳት ብለው ያስተምማሉ ። እነዚህ ፍጹም ውሸታሞች ናቸው ። ስለታሪክ ሂደት ቅንጣት የማያውቁት የሰም የሚል አመለካከት እንዳላቸው ገልጫለሁ ። ወደአዘጋጂት መጽሐፍ እንሰፍ ። ኢ ነኢትዮጵያ ታሪክ ምን ይገልፃል? ምን ያስረዳል? ኢትዮጵያ በወደ ፣ ይን ምንድና?ለሁለም ከራሱ ከመጀመሪ ልዋቱስ «የባሪይቱ ኢትዮጵያ ብላ የምትጠራ ሀገር እንደኛ የሦስት ሺህ ዘመን ታሪክ አላት ፣ ሚገለው እንደንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ለአማራው የገዥ መደብ እንዲመ ም ። ሥራት . ታጥፊ ፡ ፈት ነው ። ይህ የሦስት ሺ ዓመት ታሪክ ምንም ያልነበረ ፣ ምንም ይዘትና ትክክለኛ አቋም ያልነበረው ነው ። የአክሱም መንግሥት አብዛኛውን የኢትዮጵያ ግዛቶች አያጥቃም ፣ አያጣምርም ።

ለትግራይ ብቻ የተመሰነ ነው ። አማራውና የአማራ ገዥ መደቦች የአክሱምን መንግሥት ታሪክነት ነው ብለው የሚያምኑበት ሌላ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቅጥፈት ፡ ሴላ ውሸት ነው ። ታሪክ ጸሐፊዎችም ለጥቅም የሳቱት ነው ። ስለዚህ ይህች ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራ ሀገር አንድ መንግሥት ያቋቋመችው ከምኒሊክ ወዲህ ሲሆን ይህም ገና አንድ መቶ ዓመትም አልሞላውም» ይላል ። የሦስት ሺ ዓመታት ታሪክነም እንድነኪንም ያጣረራል ። እንደነሱ ኢትዮጵያ የሦስት ሺ ዓመት ታሪክ የሴላት እንደመሆኗ መጠን ፡ የአክሱም መንግሥትም አብዛኛውን የትግራይን ቦታዎችና ከኤርትራ አንዳንድ ቦታዎች መያዙን ይጠቅሳል ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ሴላው የኢትዮጵያ ክፍል የአክሱም ታሪክ ታሪኬ ነው ብሎ ማመን የለበትም ነው የሚለት ?

<u>መልስ</u>፡- አዎ ሴላው የኢትዮጵያ ክፍል የአክሱም ታሪክ የእኔ ታሪክነው ብሎ መተበል የሃሰት ሃሰት ነው ብለው አስተምጠውታል ። ኢትዮጵያ የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ የላትም ብለው ስለሚነገሩ ፡ ከምኒሊክ ዘመን ጅምሮ መቶ ዓመት ያልሞላ ታሪክ አላት ስለሚሉና የአክሱም ዘመንም (በዛሬዋ ኢትዮጵያ ያሉትን አይመለከታቸውም) የትግራይ ብቻ ነው ባያ ናቸው ።

ባሞሩ የኢትዮጵያን ታሪክ ያጉድፋሉ ። ትናንት እንደተፈጠረች አድርገው ይገልጿታል ። የኢትዮጵያን አንድነት ፡ ነፃነት ፡ ለጎላዊነት በተመለከተ ያላቸውን አቋም ስናይ ራሱ በራሱ ግጭት ሲፈጥር እናገኘዋለን ማለት ነው ። ኢትዮጵያን ትናንት የተመለደች የተፈጠረች አገር አድርጉ እያቀረበ ለኢትዮጵያ አንድነት ፡ «የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እናቋቁማለን» ይላሉ ። «ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት እንደመሠኗ መጠን ከኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት መላቀቅ አለባት ። እኛም እስከመጨረሻ እንዋጋለን» ይላሉ ። ከዚያም ቀጥሎ «የብሔረሰብ ሸኽ መገንጠል ፡ ተገንዮሎም የራሳቸውን መንግሥት መመስረት አለባቸው ።» ይህ ሁሉ ከራሳቸው ሰንዶች የተገኘ ፡ እስከ 1981 መጋቢት ድረስ ባወጣቸው ፕሮግራሞች ላይ የቀረበ ነው ። ያጣሚ ለመግለጽ የምፈልገው ቡድኑ የኢትዮጵያን ረዥም ጊዜ ታሪክ ውድቅ ከማድረጉም በላይ ከኤርትራ ጅምሮ እያንዳንዱ ብሔረሰብ እንዲገነጣጠል ፡ ኢትዮጵያ እንድትበታተን የሚፈልግ ፡ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያጉድፍ ነው። ከቡድኑ ጋር ለረዥም ጊዜ ስለኖርው ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ብዬ መጠየቁ አልቀረም ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም ማወቅ አለበት ። ይህ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደካርታ ጨዋታ ቀላል አይደለም ። የኢትዮጵያን ነፃነትና አንድነት ማፍረስ ማለት ፣ ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለብዙ ጊዜ ይዞት የመጣውን አንድነቱን ያፍርስ ማለት ነው ። ይህ ቡድን የኢትዮጵያን አንድነት ለማፈራረስ የቆመ ነው ። ይህ ቡድን አሁን ውሸንብር በሚነሣበት እርኩስ ዓላማው ሕዝቡን እርስ በርሱ የሚያጋድልበትና ብዙ ያም የሚያፈስስበት ምንድነው? የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው ያስፈልጋል ። ኢትዮጵያ ብዙ ጀግኖች ፣ ብዙ ምሁራን ያሏት አገር ናት ። እንደምናውቀው ትግራይን ዘርፎ አሁን ደግሞ ወደመሃል አገር መጣ ። በዚህ ትጥረኛ ቡድን ሕዝቡ እስከሙቼ ሰላም ያጣል? ከንዱን አስተባብሮ አንድ እርምጃ መውሰድ አለበት ።

<u>ጥያቄ</u>፡- በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የታወቱትን ጀግኖች እንደሚያንቋሽሹ ከኘሮፓጋንዳቸው የምንሰማው ነው ። ይህ ከምን የመነጨ ነው?

<u>መልስ</u>፡- በታሪክ እንደምናውቀው ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት ሀይወታቸውን ያሳለፉ ብዙ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ የዓለም ታሪክ የመሰከረው ሀቅ ነው ። አፄ ቴዎድሮስን ፣ አፄ ዮሐንስንና አሉላ አባ ነጋን መጥቀስ ይቻላል ። ለሀገራቸው ፣ ለነፃነታቸውና ለአንድነታቸው የከፈሉት መስዋዕትነት በወያኔዎች አይነሳም ። እንዲያውም ያጥላላሉ ። «ቴዎድሮስም ቢሆን ለራሱ ጥቅም ማዙን ለማስፋፋት ክእንግሊዝ መሳሪያ እንዲመጣለት ነው ይሽን አደረጣሁ ይሽን ሠራሁ የሚለው» የሚል ጽሑፍ «ሕወሓት» አላት ። ዮሐንስንም ቢሆን «ለራሱ ግዛት ማስፋፋት ነው» ብላዋለች ። እርግጥ ዮሐንስ ትግሬ ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ በተለየ ዓይን ማየቷ አልቀረም ።

አሉላ አባነጋ እና አፄ ምኒልክ በወያኔው ዘንድ ታሪካቸው አይነሳም ፣ ለምሳሌ በሁለተኛው ዓለም ጦርነት በወረ ፋሽስት ትግል ብዙ ጀግኖቻችን ሀይወታቸውን አጥተዋል ። ይህ በነሱ ዘንድ ምንም ቦታ የለውም ። በጦርነቱ መስዋዕትነት የከፈሉት መሳፍንት እርግጥ ጠላትን አባረዋል። ግን የራሳቸውን ግዛት ለማስፋፋት ነው ጦርነት ያደረጉት ትላለች ። የተምታታ አቋም ነው ያላት ። በስፋት ለመግለፅ ስለማይሆን ላት እንደነድጋአሊ ያሉትን የጦርነት ቦታዎች አትጠቅስም ። ብትጠቅስም እንኳ እጅግ በጠባብና በተመጠነ መልኩ ነው ። ኢትዮጵያ ገና ሙት ዓመት ያልሞላው መንግሥት የመሠረቱት አገር ናት ብላ ስለምታምንም

t.me/OLDBOOKSPDF

የኢትዮጵያን ታሪክ በሙሉ ትነሰዋለች ። ከማሊያን ጋር የተያረገውን ጠርነትም አታነሳም ።

ጥያቄ፡- ሰኔ 3 1977 በተንቤን «ወርኢ» በተባለው ቦታ የሚሊ ሊት» መሥራች ጉባኤ ተካሂዷል ። እርስዎ በጉባኤው ተገኝተዋል፡ የጉባኤው ትኩረት ምን ላይ ነበር ? የአባላት ሰብጥር ምን ይመስላል ? ከአመሠራረቱ አኳያ ቢያብራሩት ?

መልስ፡ "ማሌሊት" ሰኔ 3 1977 መሥራች ጉባኤውን አካሂዷል ። «ማሌሊት» የራሱ ፕሮግራም አለው ። «ማሌሊት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና እኩልነት የሚታገል ለማስመሰል ወይም ለማደናገር የሚጠቅ ቸው ነገሮች አሉ ። ሦስም መሠረታዊ አቋሙ በፕሮግራሙ ተጠቅሷል

የፕሮግራሙ ይዘት ምንድነው ? ስለመንግሥት አቋቋም በሚለው ክፍሉ «የትግራይ ብሔር የራሱን እድል በራሱ በመወሰን የ«ትግራይን ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት» ይመሠርታል ። ሁለተኛ በዚህ ፕሮግራም መሠረት «ግንኙውም ብሔረሰብ ተገንዮሎ የራሱን መንግ ሥት ሊያቋቁም ይችላል ። የኤርትራ ትግል ፍትሐዊ እንደመሆኑ መጠን ኤርትራን ነፃነት እናስፈልብጣለን ፡ ስለዚህም ደጣችንን እናፈሳለን» ይላል። ሌሎች አንዳንድ ጉዳዮች አሉ ። ጠቅሚነታቸው መይም ክብደታቸው ዝቅ ያለ ስለሆነ አላነሳቸውም ። ፕሮግራሙ ይህ ነው ፡ ይዘቱም አቋሙም ይኸው ነው ።

ለኢትዮጵያ አኩልነትና አንድነት የሚል በዚህ ፕሮግራም ላይ ፈጽሞ የለም ። ግን «ማሌሊት ለኢትዮጵያ አንድነት ትታገላለች» ይላል ። ጥሩ ነው ራሱ እንዲህ ብሎ የሚናገር ድርጅት በፕሮግራሙ ውስጥ ማስገባት ነበረበት ። ግን ስለኢትዮጵያ የሚገልጽ ፡ ኢትዮጵያ የሚል በውስጡ አንድም ቃል አያገኝም ። ስለኤርትራና ስለትግራይ ግንኙነት ብቻ ነው ። ይህ ፕሮግራም ምን ምን ያካተተ ነው ? ማህበራዊ ፕሮግራም ፡ ኢኮኖሚያዊ ፕሮግራም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ፕሮግራም የሚሉ ክፍሎች አለት ። ስለኢትዮጵያ ባላቸው አቋም «ተሐሕት ፡ ማሌሊት» ሕወሓት» ሶስቱም አንድ ናቸው። ጉባኤተሰቡን ለማደናገር ነው ስም የሚለዋወ ጡት ።

ጥያቄ፡- እርስዎም ሲጠቅሱ ሆነ አንዳንድ ጊዜም ሲነገር «ሕወ ሓት - ማሌሊት» ይባላል ለምንድነው እንደዚህ የሚጠራው?

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀ/ልስ፡- «ሕመሓት ማሌሊት» ተብሎ የሚጠራው «ሕመሓት»ኒ ንደ አንድ መንግሥት ሲሆን «ማሌሊት» ደግሞ እንደ አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ሆኖ ግንባሩን የሚመራ ነው ። ባጠቃላይ የፓርቲው ፕሮግራም የግንባሩ ፡ የግንባሩ ፕሮግራምም የፓርቲው ፕሮግራም ነው ።

ጥያቄ፡ ወደ «ማሌሊት» መሥራች ጉባኤ እንመለስ ። በጉባኤው ላይ ተነስተው ያከራከሩ ነጥቦች የለም ወይ? ጉባኤ ሲጠራ ውያይት መካሄድ ከታሪክም አንፃር እንዳንድ ነገሮች መጠቀስ አለባቸው ።

ሀ/ልስ፡- ጉባኤው ሲመሠረት አንዳንድ ጥያቄዎች ተነስተዋል ፡ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የነበሩ ሰዎች እንዲባረሩ ተደርገዋል ። ለምሳሌ የድርጅቱ ሊቀመንበርና የወታደራዊው ክፍል አዛዥ የነበረው አረጋዊ በርሄና ማኦሄ ዘረንዕዮን የድርጅቱ ም ሊቀመንበርና ጠቅላላ የኢኮኖሚ ክፍል የበላይ ተቆጣጣሪ የነበረው የሚጠቀሱ ናቸው ። ከተነሱት ጥያቄዎች ውስጥ «ኤርትራ የኢትዮጵያ የቅኝ ግዛት ናት የሚለው ለምን እስከዚህ ይዘልቃል ? እኛ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንመክልም።» የሚለው የአረጋዊ በርሄ ጥያቄ ፡ የማይጭ ዘርዓዩን «የትግራይ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክን እንመሠርታለን እንላለን በ1967 በረሃ ስንወጣ ስንወያይ የነበረው በኢትዮጵያ አንድነት ውስጥ እኩልነት እንፈልጋለን የሚል አቋም ነበር ። ከመጀመሪያ ጠባብ ብሄርተኞች እየተባልን እየተሰደብን እስካውን መጣን ፡ ለምን መሻሻል አያደረግበትም ? ስለ ብሔረሰቦች ጥያቄ እስከመገንጠል የሚል አቋም መውሰዳችን ነባሩንስ የተገኘ ባያውንም በኢትዮጵያ ሕዝብ አያስመታንም ወይ?» የሚል ውዝግብ ተነሳ ። አረጋዊ በርሄ በሥራዊቱ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ስላለው ሊያሳሩት አልቻሉም ።ማይጭ ዘርዓዩን ከተያዘ አረጋዊ በርሄ ያለውን ሠራዊት እንቀሳቅሶ ያስመታናል በማለት ከሥልጣናቸው አውርደው እንዚህ ሁለቱን በቁም እስር ሳይነት እንዲንቀሳቀስ አደረጉ ። በዚህ ጥያቄ ላይ «ኢትዮጵያዊነታችንን ረስተናል» በማለቱ እንአረጋዊን ያጣው ሀሳቡን ገብረ ሕይወት የሚባል ተለፀ። የሚያሳዝነው ጉባኤ ላይ አንዱለዕረፍት እንደወጣ እሩነው ወሰዱት፡ አውን ኖት እንድረስ አይታወቅም ። ተነበሰ ሐዋዘ የአረጋዊ በርሄን አቋም ስለደገፈ በሳንጋ ላይ ግይጭ ዘርዓዩን ከሥልጣን ተነበሰ ሃዋዘ ያገልግል እን አረጋዊ በርሄና ማኦሄ ዘርዓዩን ከሥልጣን ተነበሰ ሃዋዘ ያገልግል ያስመታናል በማለት ነው የገደሉት ። አብዲ መሐመድንና መስፍን አማረ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚባሉ አውንም በድርጅቱ ውስጥ ያሉ ግን አቋሙን የሚቃወሙ አሉ ። አቋማቸውም የማሌሊት ፕሮግራም ትክክለኛ ፕሮግራም አይደለም ፡ ጠቅላላ የኢትዮጵያን ክብር የሚገረር ነው የሚል ነው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- የጉባኤው ተሳታፊ እንደመሆንም ሁሉ በጉባኤው ላይ እንዲሳተፉ የተጋበዙ ድርጅቶች ነበሩ ? በዚያ ላይ የነበረውን ሥነሥርዓት ቢገልጹት ፡ ጉባኤውስ በምን ዓይነት ቦታ ነው የተካሄደው ?

<u>መልስ</u>፡- «የማሌሊት ፡ የሕወሓት» ስብሰባ በየጊዜው ይካሄዳል ። ማንም ከውጭ የሚመጣ ሰው የለም ። በአብዛኛው ጊዜ የሚመጡት የፀሸበኢያ» አባሎች ናቸው ። በ«ማሌሊት»ም ስሬታ ጊዜ ዘግይተው ነው የመጡት ። ምክንያቱም አካባቢው በአይሮፕላን ያመታል የሚል ስጋት ስለነበር በጊዜው አልደረሱም ። የ«ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ» (ኢሕዲን) በስብሰባው ላይ ተገኝቷል ። ስለ «ኢሕዲን» ማወቅ የሚያስፈልግ ይመስለኛል ። «ኢሕዲን» በስብሰባው ላይ በሙሉ ድምፅ ነው የተሳተፈው ። አንድ ድርጅት በሌላው ውስጥ እንዲህ ዓይነት መብት አለው ? ነገሩን ሳይንሳዊ በሆነ ትንተና እንየው ። ለምሳሌ የቤቱ ጌታ አቶ ኃይሉ ቢሆን በቤቱ የሚያስተዳድረው እሱ መሆን አለበት ። ሌላ ሰው መጥቶ በኃይሉ ቤት እንደ ነገር አንሱ ማለ ለማለት መብት አለው? የለውም ። በድርጅትም ውስጥ ድምፅ የሚሰጥ ፡ የሚመረጥ የድርጅቱ አባል ብቻ ነው ። የ«ኢሕዲን» መሪዎች በምር ሚም ድምፅ ሰጥተዋል ። ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በሙሉ ድምፅ ነው የተካፈሉት።

ጉባኤው «ወረኢ» ነው የተካሄደው ፡ እንድ ሽንኮር የመሰለ ወደ ውስጥ የገባ ቦታ አለ ። እዚያ ዳስ ተሥሎ ነው የተካሄደው ። በውስጡ «የሕወሓት የማሌሊት» ባንዲራዎች ነበሩ ። ጥቅሶችም ነበሩ ከጥቅሶቹ ውስቱን ማንሳት እፈልጋለሁ ። ሌላው ትዝ አይለኝም ። ጉባኤውን የሚመራው ጎፈዚዲየም የተተመጠበት ጠረጴዛ ላይ ጨርቅ ለብሶአል ። እያንዳንዳቸውም ላይ እስክርፕቶ አንጎታቸው ላይ ጠምጠሞል ፡ ላይ ቆብ አድርገዋል ፡ እንዲሁም ላይ ጨርቅ እጃቸው ላይ አስረዋል ። ስለጉባኤው ያየሁ እንድ ሰዕል ሳይሰጥ አይተርም ። ጉባኤውን የሚመራው ዓባይ ወሐፍ ነበር ። በሱ ፈት ለፈት «ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትግራይን እንመሠርታለን» የሚል መፈክር ነበር ። ከምክትል ሰብሳቢው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከስዩም ዮሴፍ አጠገብ ደግሞ «ለኤትራ ሃገራዊ የቅኝ ግዛት ጥያቄ እስከመጨረሻ ደማችንን እናፈሳለን» የሚል መፈክር ነበር ።

ጥያቄ፡- አንድ ስብሰባ ሲካሄድ የአመራር ጉባኤ ይሰየማል ፡ እንግናችው አመራሩን የያዙት ? ለአመራርስ ድጋፍ ነበራችው ወይ ?

መልስ፡- ለአመራሩ ዓባይ ፀሐዬ ፡ መለስ ዜናዊ ፡ ገብሩ አሥራት እና ሌሎችም እንዲመረጡ ተደረገ ፡ ምርጫው ዲሞክራሲያዊ አልነበረም ። አብረን እንደመቆየታችን መጠን እንተዋወቃለን ። የዓባይ ፀሐዬና የመለስ ዜናዊን የትውልድ ቦታ አውቀዋለሁ ። በዚህ ቡድን አመራር የተቀመጡት የኤርትራ ተወላጆች ናቸው ። ዓባይ ፀሐዬ ራሱ የኤርትራ ተወላጅ ነው።

የማን ኪዳኔ ጃማይካ ተብሎ በቅፅል ስም የሚጠራውና ከመጀመሪያ ጅምር በ«ሻዕቢያ» ተልኮ «በሕወሓትና በማሌሊት» አመራር ላይ ያለ ፡ ተወልደ ገ/መስቀል ፡ ሳሙኤል ገብረማርያም የሻዕቢያ አመራር አባል የነበረው (የተከላይ ወንድም) እነዚህና ሌሎችም የኤርትራ ተወላጆች ናቸው ። ከነዚህ በተጨማሪም ፡ ጻድቃን ገብረእየሱስ ሰሎሞን ተስፋዬ ፡ ዓለሙ ወልዴ ፡ ስዩም አብርሃም ወልደ ሥላሴ ነጋ (በማማሽ) ሃያሉም አርአያ ይገኙበታል ። ከሃያ ሶስቱ የአመራር አባላት ውስጥ አስራስድስቱ የኤርትራ ተወላጆች ናቸው ማለት ነው ። ከትግራይ ተወላጆች ደግሞ አረጋሽ ተስፋዬ ፡ ገብሩ አስራት ፡ ቢተውልኝ አስፍሃ ፡ ዓለም ሰገድ ገብረ አምላክ ፡ ክንፈ ገ/መድህን፡ አበበ ተክለሃይማኖት የሚባሉ አሉ ። ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን የያዙት ግን የኤርትራ ተወላጆች ናቸው ። እነሱ ናቸው «ሕወሓትን» እንደ ሰዓት የሚጠመዝዙት ፡ ለምሳሌ ዓባይ ፀሐዬ አስራ አምስት ዓመት ሙሉ ቦታውን አለቀቀም ።

የትግራይ ተወላጆች ምንም ሥልጣን የላቸውም ፡ የታዘዙትን ፈፃሚ ናቸው ። ድርጅቱ ራሱ ዲሞክራሲያዊ አይደለም ። ግንባሩ ውስጥ ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረጉ እንዳይመረጡ የተደረጉና «ማሌሊት» ውስጥ ያልገቡ አሉ ።

ለምሳሌ አረጋዊ በርሄ ግደይ ዘርዓፅዮን ፡ ተክለ ሃዋዝ ፡ ሀዲሽ መስፍን ፡ አማረ ሰመሩና ክብሮም እንዳይመረጡ ተደርጓል ። ለዚህም ቀደም ብሎ የተሠጠን መመሪያ ነበር ። ድምፅ አሰጣጡም ሆነ ጥቆማው በሚስጥር የተቀነባበረ ነበር ። እኔ እንድጠቁም የተሰጠኝ የማዕከላዊ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኮሚቴ አባልና የግንባሩን አመራር አባል ተወልደ ወልደ ማርያምን ነበር ።

በጋርቲው ውስጥ እንዳይገባ የተደረገት የትግራይ ልጅት ናቸው ። ለምሳሌ ያማነ ኪዳኔ (ጀማይካ) በንጉሡ ጎሊናና በአንትስትሰ ከወዲሽ መስሩን አይበልጥም ፡ ግን የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆኖ ተመረጠ ። ይህን በመገናኛ ብዙሃን ስንልጽ እንደሚሰሙ አርግጠኛ ነኝ ። አራሳቸውን የሚመታ እውነት እንደሚሆንባቸው መኖ በመኖ አርግጠኛ ነኝ ። ምክንያቱም የምንተማመን ሰዎች ይህ ለምን ይሆናል ብለን በወትሮም እንጠብቀ ነበር ። በይፋ ለሚወጡት ግን አደገኛ ነበር ። በዚህ ጉዳይ ላይ ቅሬታ ያለን መሆኑን ቢያውቁ ኖሮ የአንድ ሰዓት እድሚ አይሰጡንም ነበር ። ከመሞት መሰንበትን ደግሞ ማንም ይመርጣል ።

ጥያቄ፡ «የሕወሓት» አመራር በተለይም ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎች በ«ሻዕቢያ» እንደተያዙ ነው የተገለጸው ። የዚህ ምስጢር ምንድነው? አርትራን ለማስገንጠል ዓላማ ያለው መሆኑን «ሕወሓት» ም ሆነ «ማሌሊት» በፕሮግራማቸው ገልጠዋል ። በአንድ በኩል «ሕወሓት» «የትግራይ ሪፐብሊክን አመሠርታለሁ» ይላል ፡ በሌላው ወገን ደግሞ ትግራይና አርትራን በማዋሃድ "የትግራይ ትግራኝ መንግሥት የመመሥረት" ነገርም አለ ። «የሕወሓትና የማሌሊት» አመራር በሻዕቢያ ሰዎች መያዙ የትኛውን ዓላማ ለማስፈጸም ነው ?

መልስ፡ «ወያኔና ሻዕቢያ» አባትና ልጅ መሆናቸውን በስፋት አብራርቻለሁ ። ወያኔ ከጉንደር ሰቲት-ሁመራን ፡ ጠለምትንና ወልቃይት ጠገዴን ፡ ከወሎ ራያና ቆቦ እስከ አሸንጌ ድረስ ያለውን አካሉ በካርታ አስገብቶ ይዞታል ። በወያኔ አንጋገር ይህ «ትግራይ ትግራኝ» በማለት ይጠራል ። በ1974 ተደም ብሎ የወጣ «ፌዴሬሽን» የሚል ጽሑፍ የፀትግራይን ሪፐብሊክ የመመሥረት ጉዳይ እንዳለ ሆኖ አስፈላጊ ከሆነ ኤርትራ ነፃ ከወጣች በኋላ የትግራይ ሕዝብ ከኤርትራ ጋር በፌዴሬሽን መንግሥት አንድ ግዛት መመሥረት ይችላል» ይላል ። አመራሩን የያዙት ይህንን ዓላማ ለማራመድ ነው ።

ጥያቄ፡ «አሕዲን» «በማሌሊት» መሥራች ጉባኤ ላይ ተማኝቶ ድምፅ ሰጥቷል ። ለምድነው ድምፅ የሰጠው? ዓላማውስ ምንድ ነው?

መልስ፡ ተደም ብዬ አንድ ድርጅት በሌላ ድርጅት ውስጥ ገብቶ ድምጽ የመስጠት ፡ አመራሩንም የመምረጥ መብት እንደሌለው፡ አሰራሩም ትክክለኛ እንዳልሆነ ገልጫለሁ ። ያም ሆነ ይህ «አሕዲን»

t.me/OLDBOOKSPDF

የ«ሕወሓት» ልጅ ነው ። አንድ ናቸው ። በ«ኢሕዴን» አመራር ላይ ያለ ሰምት አማርኛ ተናጋሪ ናቸው ። ይህ ለታክቲክ የተደረገ ነው ። እኛን የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለሚመራን አማርኛ ተናጋሪ አካል ማስተመሳ አለብን። «ኢሕዴን» ን ለማስመሰያ በመጠቀም የኢትዮጵያን አንድነት መበታተን አለብን ። ይህ ነው አጀሙ ። በሰልጣን ላይ ያሉትም የ«ኢሕዴን» የአመራር አባላት ይሆን የሚያፋጥኑ ናቸው ። አንድ ድርጅት በሌላ ድርጅት ውስጥ ገብቶ ድምፅ መስጠት የሚያመለክተው ቅጥረኛነቱን ነው ። «ማሌሊት» እና «ሕወሓት» የ«ሻዕቢያ» የበኩር ልጆች ሲሆኑ «ኢሕዴን» ደግሞ የ«ሕወሓት» ልጅ መሆኑ ነው ። ስለዚህ እነዚህ ድርጅቶች አንድ ናቸው ። «ኢሕዴን» የራሱ የሆነ አንድም ሠራዊት የለውም ። አለ የሚል ይምጣና ፊት ለፊት እንነጋገር ። የ«ኢሕዴን»ሠራዊት ወይም የ«ኢሕአዴግ»ሠራዊት እየተባለየሚጠራው ፡ የትጉሃንና የወሎን አካባቢዎች የሚበጠብጠው ፡ ኢትዮጵያን ሰላም የሚነሳው ፡ የሌላ ሳይሆን የወያኔ ሠራዊት ነው ። «ኢሕዴን» የማስመሰያ ቡድን ነው ።

<u>ጥያቄ</u>፡– «ማሌሊት» የተመሠረተው በ1977 ላይ ነው ፡ ይህ ደግሞ የትግራይ ክልል አስክሬ በሆነ ድርቅ የተመታበት ዓመት ነበር ። በመቅ «ሕወሓት» ከፍተኛ እርዳታ አግኝቶ አልሆነ ቢታ ላይ እንዳሞለው ይነገራል ። በዚህ ጊዜ ደግሞ እንደ «ማሌሊት» ያሉ ድርጅቶችን መመሪትን ብለው የተለያየ ውጊታ የአሳዩበት ጊዜ ነው ። በዚያ ችግር ወቅት የእሱና የሕዝብ ውጊታ ምን ይመስል ነበር ?

<u>ዘዐልስ</u>፡–«ማሌሊት» በ1977 በሰኔ ወር ላይ የተመሠረተ ድርጅት ነው። «ሕወሓትና ማሌሊት» ከውጭ በብዛት እርዳታ አግኝተዋል ። በጣም የሚገርመኝና የሚያሳዝነኝ ማሌሊት በተመሰረተበት ጊዜ በአንድ ወገን ሕዝብ በርሃብ እየረገፈ በአንድ ወገን ደግሞ ወደር የሌለው ፌንጠዝያ መደረጉ ነበር ። « ማሌሊት» ሕዝባዊ ኃይ ይላል ። ስለእደረጉት ፌንጠዝያ ስዕላዊ ገለፃ ለማድረግ ያስቸግራል ።
ለድርቅ ተብሎ በመጣው እንደልብ ነው የፌንጠዝንበት ። ሌላው ተርፍ ውስኪ እንደውሃ ነው የጠጣነው ። ቢራ ፡ ጠጅና ፡ ሌላም በጣሩ ነበር የቀረበልን ። በሕዝብ ስም ተለምኖ በፖርትሱዳን በኩል ተጭኖ ወደትግራይ የገባው እርዳታ ዊስኪና ልዩ ልዩ መጠጥ ነው የተገዛበት ። ሌላውስ?

t.me/OLDBOOKSPDF

በቀን ሰባት በሬ እየታረደ ለምሳና ለራት እንበላ ነበር ። ለቱርስ የሚሆነው ለእርዳታ የመጣ የታሸገ ምግብና ፍራፍሬ ነበር ። ሕዝቡ ከዚህ ምንም ነገር አላገኘም ። አንድ ጊዜ ከዓለያወሐዬ ጋር ስንሄድ በረሃብ የወደቁ አንድ ሰውዬ አገኘን ። በእድሜ 60 65 ይሆናሉ። ዓለያወሐዬ የሕዝብ ወገን ነኝ ይላል ፡ ግን እየሳተ ነው ያለፈው ።

<u>ጥያቄ፡</u> ለድርቅ የመጣው እህል ለምን አልታደለም?

<u>መልስ፡</u> በሱዳን የነበረ ሰው ያውቀዋል ። የዕርዳታ እህሉ የመጣው በፖርት ሱዳን (በሱዳን መደብ) በኩል መሆኑ ይታመታል ። የእርዳታው እህልና ሌላም ዕቃ በገፍ በመምጣቱና የፖርት ሱዳን መደብን በማጣበቡ ይጋግመው አንሱልን እስከ ማለት ጠይቀዋል ። ያሆን ሁሉ እህል ወደ ትግራይ የሚያመላልሱ ብዙ ካሚዮኖች ነበሩ ። አሰፈላጊ የሚሆናቸውን ከያዙም በኋላ አንድም ነገር ለሕዝቡ አልሰጡም ። ትግራይ ውስጥ ለሠራዊት ቀለብ ከተከማቸ በኋላ «ዋንዛ» በሚል የነጻ መጠሪያ በብዙ ሚሊዮን ብር ለሱዳን ነጋዴዎች ተሸጠ ። የሱዳን ነጋዴዎች «ሕወሐት» በእርዳታ ያገኛቸውን እህል ለመሸመት ይሽቀዳደሙ ነበር ። አቶ አብርሃም ያየሀ ሊመሰክር ይችላል ። እኔ ገቢውን ገንዘብ ብቻ ነበር የምቆጣጠረው ። ከእጄ ይገባ የነበረው የሱዳን ፓውንድ ቁጥሩ ትዝ አያለኝም ። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ነው ገቢ የሆነው ። ከዚህ ገቢ የወጪው ሠራዊት ያገኘው የለም ። በሙሉ ለአመራር አባላት መዝናኛ ነው የሆነው ። አንድ ነገር ልጥቀስ ። በዚያን ጊዜ የእኔ የበላይ አለቃ የፖለቲቢሮ አባል ገብሩ አሥራት የሚባለው የልብ በሽታ ስለነበረበት ወደ ውጭ አገር ለሕክምና ይሂድ ተባለ ። አርባ ሺህ የአሜሪካ ዶላር ስጠው የሚል ትዕዛዝ መጣልኝ ። በጥሬ ገንዘብ አርባ ሺህ ዶላር ቆጥሬ ሰጠሁት። አርባ ሽህ ዶላር ለአንድ ሰው በሚከፈልበት ወቅት የትግራይ ሕዝብ አንድ ቅጠል ያለ ምንም እርዳታ ይረግፍ እንደነበር መታወቅ አለበት ። ሕዝባዊ ነኝ የሚለው ወያኔ ሕዝባዊ አለመሆኑን ይህ አያረጋግጥም?

<u>ጥያቄ፡</u> የድርጅቱ የፋይናንስ ኃላፊ ነበሩ ። ለመሆኑ የፋይናንስ ምንጮቹ ምን ምን ነበሩ? ከየት እንደሚያገኝ ቢገልፁልን?

<u>መልስ፡</u> የገንዘብ ምንጮች ልዩ ልዩ ናቸው ። አንደኛ ነገር ለእርዳታ ተብሎ የሚመጣው ብዙ ሚሊዮን ሚትሪክ ቶን እህል ተሸጠ ይገባል ። ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ለሰብአዊ እርዳታ የሚሰጠው የገንዘብ ርዳታም የገቢ ምንጭ ነው ። ከእርዳታ ሰሞኖች ውስጥ አከሰፋም ፡

t.me/OLDBOOKSPDF

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያናትና የመሳሰሉት ይገኙበታል ። እነዚህ ድርጅቶች እርዳታ የሚያደርጉት ለሕዝብ እንዲደርስ ነው ። የትግራይ ሕዝብ በፈ ሞቶበታል። ፍየሎቹም ሞተውበታል ። ባዶ ቤት ነው የቀረው ። «ሕወሓት» ለመደመሚያ እርዳታ ብላ ታመጣለች ። ለሕዝቡ የደረሰው ነገር የለም ። እዚህ ላይ መደ ኃላ ተመልሽ እንድ ነገር ልዋቸስ ። በ1974 የተበላሸውን እህል አይቶ የሚጣልውን የሚጥል ኮሚሽን ተዋቸም ነበር። ይህን የሚመራ አንድ ሰው ነበር ። በኢኮኖሚው በኩል እኔ አለሁ ። የተበላሸው እህልና የታሸገ ምግቦች ሁሉ እንዲጣሉ ተባለ ። በፅሑፍም ይዣዋለሁ ። 45 ሺ ኩንታል ያህል ተከዜና ካዛ ወንዝ ውስጥ ጣልን ። ያህ እህል ግን የትግራይ ሕዝብ በረሃብ እንዲጥል በሚረግፍበት ጊዜ የተጠራቀመ ነበር። እኔህ «ሕዝባዊ ነኝ» የሚሉ የሚሠሩት ይህንን ነው።

<u>ጥያቄ</u>፡- ድርጅቱ ቀረጥ ያስከፍላል ይባላል ። እንዴት ነው የሚያስከፍለው?

<u>መልስ</u>፡- ይህ እውነት ነው ። የቀረጥ ፖሊሲ አለ ። እኛና ከእኔ ጋር የሚተባበሩ ነን ፖሊሲውን የምናወጣው ። አንድ ዶሮ ሽጠ የሚሔድ መኖም የሚገዛ በአንድ ዶሮ ሃያ አምስት ሳንቲም ቀረጥ ይከፍላል ። በሬ የሸጡ መኖም የገዙ ደግሞ እያንዳንዳቸው ሃያ ብር ይከፍላሉ ። በቅሎ ፣ ግመል ሽጦ በሚሄድበት ጊዜ ትሸጦም ሻፈሙም አንዳንድ መቶ ብር ይከፍላሉ ። ቀረጣቸው ይህን ይመስላል ። ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ አልኮሆል ፣ ውስኪ ፣ አረቄ ፣ ድራፍጂን ቢራ ። እነዚህ ቀረጥ ሲከፈልባቸው ይገባል ወይስ አይገባም? ግን የመጠጥ ዓይነቶች ሁሉ ቀረጥ እንዳይከፈልባቸው ተወስኗል ። አብዛኛውን የመጠጥ ዓይነት የምንገዛው እኛ ነን ። መጥፎ ባህልም እየዳበረ ነው ። ለምሳሌ ሲጋራ የማያጨስ ጅል ነው ፣ ያልሰለጠነ ነው ይባላል ። የቢ·ቢ·ኤል·ኤፍ «ዲሞክራሲያዊ አሠራር» ነው ። ሴቷም ወንዱም ሁሉም ያጨሳሉ ። በብዛት ሲጋራ ይመጣል ፣ ግን ሲጋራ ደግሞ ቀረጥ አይከፈልበትም ። አብዛኛው ጎብረተሰብ ጥቅም ላይ በሚያውላቸው ዕቃዎች ላይ ግን ከባድ ቀረጥ ይጣላል ። እህል ከሸመትህ በኩንታል የምትከፍለው አለ፡ ማር ቅቤም ከገዛህ እንደዚሁ ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ድርጅቱ በቅጣትና በመሳሰሉት ገቢ ያገኛል ይባላል አብረው ቢያብራሩልን?

t.me/OLDBOOKSPDF

መልስ፦ ይህ ትክክል ነው ። አንድ ነገር በለመደኩው የተናገረ መይም ከተናገርሀ ይህ ፀረ መያኔ ነው ፡ የደርግ ሰላይ ነው ይባላል ። ለማንኛውም ሰው በም ይሰጠዋል ። ያ ሰው ደርግን ላያውቅ ይችላል ። በነዚህ ላይ ከፍተኛ ቅጣት ይጣልባቸዋል ። ግማሹን አንድ ሺህ ብር ፡ የለሙም ከተባለ አምስት መቶ ብር ፡ ምንም የለሙም ከተባለ ደግሞ በእሥራት ይቀጣል ። ስለዚህ ፀረ መያኔ አቋም አላቸው እየተባሉ እሥር ቤት እየገቡ የሚቀሙ ብዙ ናቸው ። «መያኔ» መቀጫን እንደ አንድ ገቢ ትቀጥረዋለች ።

ጥያቄ፦ አቶ ነብረ መድኅን በሕክምና አስተዳደር ሠርተው እንደ ነበር በውይይታችን መጀመሪያ ላይ ገልፀውልናል ። «ሕወሓት» የትምህርትና የጤና ፖሊሲ አለኝ ይላል ፡ ማብራሪያ ቢሰጡን?

መልስ፦ «ሕወሓት» የትምህርትና የጤና ፖሊሲ አለኝ በማለት በፕሮግራሙ ላይ አውጥቷል ። የትምህርት ፖሊሲ አንድ የነበረ ምንም ነው ። ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡት ከ14–15 ዓመት ዕድሜ ያሳቸው ናቸው ። እያንዳንዳቸው አምስት አምስት ብር ይከፍላሉ ። ትምህርት ያገኛሉ ወይስ አያገኙም? ትምህርት የሚባለው "ሕወሓት" የጠቅላላ መያኔን ታሪክ የምታስጠናበት ፡ ተዋጊ የሰው ኃይል የምታገኝበት ዘዴ ነው። ተማሪው ክረምት ፡ በእዝመራ ወቅት ፡ በእርሻ ሰዓት ሁል ጊዜም ወደ ትምህርት መምጣት አለበት ። ነልመጣ ደግሞ ቅጣት ይጠብቀዋል ። ወላጆቻቸው የሚታሠሩ ብዙዎች ናቸው ። የአዝመራ ወቅት ነው ሰብላችንን አውሬ ይበላብናል ፡ ልጅቻችንን አንልክም የሚሉ ወላጆች ተገደው እረሳቸው እንዲጠብቁ እየተደረገ ልጅቻቸው ወደ ትምህርት ይመጣሉ ። ከዚያ የራዕን ቅስቀሳ ታካሂዳለች ። በኋላም የኪነት ዝግጅት ይደረጋል ። ከወጣቶች አንዱ በ«ሕወሓት» የተጠቀመ ፈነዛሬ ጅምሮ ወደ ትግል ሚዳ እሄዳለሁ» ብሎ መፈክር ያሰማል ። ንቃተ ኅሊናቸው ያልበሰለ በመሆኑ ጓደኛዬ ሄዶ እኔ እንዴት እተራለሁ እያለ ወደ በረሃ ይጮርፋል ። እኔ ራሴ ጓደኛዬ አረጋዊ በርሄ ሲገባ እኔ እንዴት እተራለሁ ብዬ ነው የገባሁት ። ወያኔ የትምህርት ፖሊሲ የምትለው የማይበረበረያ ፖሊሲ ነው ። ፈጽሞ አታስተምርም ፡ የምታስተምረው ስለፕሮፓጋንዳ ። የኤርትራን የትኛ ግዛት መሆንና ለዚህም ሂደው እነሱ እንደሚታገሉ ፡ ኤርትራነት መውጣት እንዳለባት ፡ «የትግራይ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት »

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለማጂያም ታስተምራለች ። በዚህ ከንቱ ኅሮፖንነቱ የትግራይ መጣዮች ባፈንቱና ሳህል በረሃ ሄደው ሞተዋል ።

የትግራይ ሕዝብ ሕክምና እጣንት አያውቅም ፡ ሁል ጊዜ በወባ እና በመሳሰሉት በሽታዎች እንደተሰቃዩ ነው ። በዚህ ሰቀያ ላይ አያለ መያአው ለሕክምና የሚሆን ገንዘብ አዋጡ ብሎ በሰው የሚከፍሉትን እንደ ግብር ያስቀምጥላቸዋል ። በጣም ድሃ የሆኑ እናቶች ሃያ ብር ፡ አላቸው የሚባሉ ሰዎችም እንደ ሽህ ብር ፡ አብዛኛው ሰው ላይ ከሃምሳ ብር በላይ ይጣልበታል ። ይህ ገንዘብ ለህክምና ተብሎ ይዋጣል ። የ«ቲ-ፒ-ኤል ኤፍ» ፖሊሲ ክሊኒክ እናቲቱግለን ህክምና እንክፍለን ይላል ። ግን እኔ ራሴ የህክምናው ኃላፊ በንበርሀበት ጊዜ «ሕመሉት» ምንም ዓይነት የሕዝብ ሕክምና መስጫ ጣቢያ አላጂመችም ። እርግጥ በየቦታው ክሊኒክ ተብለው የተከፈቱ አሉ ። እውነቱን ልንገራችሁ ። እንድ ቅርቅር ቲትራሳያክሊን እንድ ቅርቅር ክሎሮኩዊን መያም የሆነ መድኃኒት እዚያ ይታመጣል ። ከወሎ አካባቢ ዘርፉ የወሰደችው የስጋደዊ መድኃኒት ነበር «ያብሳን» የሚባል ። ምን መድኃኒት አለ ብዬ ስጠይቅ «ይህንኑ መድሐኒት በየክሊኒኩ እየላክ አስያርድር» የሚል ትዕዛዝ ተሰጠኝ ። ክሊኒኮች በዚው መድሃኒት ተጥለቀለቁ ። እዚያ አካባቢ ወባ አለ ። ሰው ወባ ይዞት ሲመጣ የሚያገኘው ይህን የስጋ ደዌ መድሃኒት ነው ። ገንዘብ የከፈለው ለምንድነው ? ይህ ራሱ የወያኔው የገቢ ማማኛ ነው ። ለገቢ ምንጭ ማማኛ ተብሎ የተመሬ ነው ። በ1980 በአጠቃላይ ለትምህርትና ለጤና ፖሊሲ ተብሎ እኔ በንበርኩበት አስከ 1980 ድረስ ከ12 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ መግኘቱን ለማዕከላዊ ኮሚቴውና ለሊቀ መንበሩ ሪፖርት አቅርቢአለሁ ። ይህ ደግሞ ከትግራይ ሕዝብ ከ1975 አስከ 1976 ድረስ ባለው ጊዜ የተሰበሰበ ነው ። ሕዝቡ ፍየሉን ፡ አህያውን እየሸጠ ነው የከፈለው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- በተቃዋሚነትም ሆነ ወይም ቅጣት ተጥሎባቸው በቁዋጥር ስር የሚውሉት ሰዎች እንዴት ነው የሚያዙት ?

<u>መልስ</u>፡- ይህም ጥሩ ጥያቄ ነው ። ወያኔን የተቃወመ ያው የሞት ፍርድ ነው የሚጠብቀው ። ወያኔን መቃወም ማለት የኤርትራን መገንጠል አለመደገፍ ፡ የትግራይን መንግሥት መቋቋም አለመደገፍ እና የብሔረሰቦችን መለያየት አለመቀበል ማለት ነው ። እነዚህ ዋና ዋና

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳዮች ናቸው ። በነዚህ ተቃውሞ ካነሳህ በቀጥታ ትገደላለህ ። ተክለ ሃዋዝም የተገደለው እነዚህ እነዚህን አሰባስበህ ያህ ድርጅት ትክክል አደረሰም በማለቱ ነው ። እነዚህን ስታሰተርብ በቀጥታ ያለምንም ሚቅሙት የሚጠብቅህ ሞት እንደሆነ ታውቃለህ ። ዝበዝ ከሠንሰለ አምልጠህ ትሄዳለህ ። ያህ አንዱ ነው ።

በእዚህ ጉዳይ ያህ ድርጅት «ዲሞክራሲያዊ ከሠሩ ለተርብ ይፈልጋል ። አንድ ነገር ልናሰስ ፡ በ1975 ላይ ነኖት ቦታ እንደተማረው በላውቃም ከሰባ በላይ ምርኩኞች ነበሩ ። ለመማረል ተፈለገ ። ሳይኖሮድ» ያሚባል መርዝ አለ ። ከቀመስከው ትሞታለህ ። ውሻ ሲያብድ አሱን በሥጋ ብትሰጠው ያሞታል ። መለስ ዜናዊ ራሱ ለሕዝግሩው የተከፈለ ነፍስ ሃላፊ ለነበረው ለአባዲ መሰናን መተዙን እንዲሌነስት መመረያ አስተላለፈ ። የጌሰር ቤቱ ሃላፊ ብስራት አማረ ሄደ ሳይጎይዱን ማለት መጀሃኒቱን ያህ መጣ ። የቴክራሲያነለን ጁቀት ነገውል እየነፈሩ በውሰጡ የነበረውን መጀሃኒት እያራገፉ በሳይኖሮድ መርዝ ሞሉ እንደነበር አደረጉት ። ሁሉን ነገር ካሰብነከሉ በኋላ በዚህ አካባቢ ሚኒንጀይትስ በሽታ ስለነባ እንዳትታመሙ ይህን መጀሃኒት ዋው ብለው ሰጡአቸው። የሚጠጡት ውሃ ከሚቀመጥበት እንስራ ውስጥ ሁሉ መጀሃኒቱን ጨመሩበት ። መጀሃኒቱን እንደጥጡ ሁሉም ረገፉ ። ሰብዓዊነት ከአለ በምርኩኝ ላይ እንዲህ ያደረጋል? አሁን ያህን ያህል ምርኩኛ ለቀቅን የሚሉት ለምን እንዚያን አለቀቋቸውም? እነዚህ ሰዎች እኮ አሐዮጵያውያን መንድሞቻችን ናቸው ። እነሱ በጎላማቸው «ሕወሓትን» ሊወጉ ሄዱ ። «ዲ·ሞ·ክ·ራ·ሲ» ደግሞ በጎላማሃ የአሐዮጵያን ሕዝብ ትወጋለች ። የሰብዓዊነት ምልክቱ እነዚህን ሰዎች ያዘሀ አስተምረህ መልቀቅ ነበር ። ግን «ሕወሓት» መለስ ዜናዊ እራሱ ባለበት እንዚህን ሰዎች አስፈጀ ። ያህ አረመኔያዊ ተግባር ነው ። ተደም ብዙ እንደገለጽኩትም ጥያቄ ካነሳህ ትረሸናለህ ። ብዙ ሰዎች አሉ የተረሸኑ ። «ሕወሓት» ዜጌም ወረ ዲሞክራሲ የሆነ ፡ የዲሞክራሲ ባህሪያት የማያጋይበት ድርጅት ነው።

ጥያቄ፡- የትምህርትና የሕክምና ፖሊሲውን እያተናል ። ሌላ የማንበራዊ ፖሊሲ አለው? ትኩረቱ ምንድነው? እንደትስ ነው ተግባራዊ የሚሠነው?

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠለስ፡- ፖ.ሲ. ሲባል ለነብረተሰቡ የሚያገለግል ነው መሆን ያለበት። ማንበራዊ ፖ.ሲ. ሲባል ደግሞ ኅብረተሰቡ በየት በየት በኩል እራሱን እንደሚያዳብርና የሚሰጡ አገልግሎቶች ምን መሆን እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው ። ድርጅቱ ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ መስጠትም አለበት። ፖ.ሲ. በ«ወያኔው» ዘንድ ግን የተገላቢጦሽ ነው ። ለነገሩ «ወያኔው» ፖ.ሲ. ብሎ አውጥቶ አሰራጭቶአል ። ለኅብረተሰቡ ሠርግ ፡ ትዳር መመሥረት ፡ ልጅ መውለድ ይህ ከማንበራዊ ጉዳዮች አንድ ክፍል ነው ። በገጠሩ የትግራይ ክልል ግን ከ1975—1977 ድረስ ባለው ጊዜ ሠርግ ማድረግ በጣም ጥብቅ በሆነ ደረጃ ተከልክሎ ነበር ። ለምን ተከለከለ? እነዚህ ከተጋቡ ፡ ትዳር ከመሠረቱና ልጅ ከወለዱ መደቢት ንብረታቸው ስለሚያዘነብሉ መሣሪያ የሚያነሳ ፡ ወታደር የሚሆነን የለም በማለት ነው የተከለከለው ። በጣም ሚስጥር በሆነ መንገድ ሲፈጸሙም ምስጢሩ እንዲጠበቅ ግድ ነበር ። የትግራይ ኅብረተሰብ እራሱ ይህን ክልከላ እንደ እንድ ዋና ጥያቄ አንስቷል። በማናውቀው ጉዳይ ከወንድሞቻችን ጋር ጦርነት ውስጥ ገመራችሁን ፡ ችግር ወስጥ ከተጋችሁን አሁን ደግሞ ሠርግ ከለከላችሁን ለምን ይኸ ይሆናል? ብሎ ጠይቋል ። በዚህ ጊዜ ሠርግ ከልከለው ብዙ ወጣቶች አስገድደው ወደ በረሃ ወስደዋል። በትግራይ መንደሮች ብትሄዱ ትዳር ለመመስረት የሚችሉና ትዳር የመሠረቱ ወጣቶች አታገኙም ። እኛ ወተት ሳይሆን ደም ነው የምናፈሰው ፡ ከእኛ ጋር ደማችሁን ማፍሰስ አለባችሁ ብለው ወስደዋቸዋል ።

ጥያቄ፡- ወደኋላ መለስ እንበል ። የዚሁ ድርጅት የፋይናንስ ኃላፊ ማለት እንደ ንንዘብ ሚኒስትር ሆነው ሠርተዋል ። «ማስለት» ሲመሰረት የተባለው አባልና ተሳታፊ ነበሩ ። ይህን ድርጅት እውግዘው ተመልሰዋል ። ከድርጅቱ የወጡበትን እንደገና በእምነሩ ቢገልፁልን?

ሠለስ፡- ቀደም ሲል ከ1975 ጀምሮ ነው ቅሬታ በድርጅቱ ላይ ያደረብኝ ። በዚያን ጊዜ የትግራይ ልጆች በሳህል በረሃ ለ«ሻዕቢያ» ሲሞቱ ሕይወታቸው አልፏል ። ወድተው ቀርተዋል ። እኔ ሙሉ በሙሉ የትግራይ ተወላጅ ስለሆንው ነገሩ ይሰማኛል ። ለምንድነው እነዚህ ልጆች እዚያ ሄደው የሚሞቱት? ለምን «ሻዕቢያዎች» ራሳቸው አይዋጉም? ይህ አንዱ ነው። ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት የሚለውን እቋም ከመጀመሪ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይው አልደግፈውም ። ይህ የራሴ አቋም ነው ። ሰው ሰው እንደመሆኑ መጠን በራሱ እምነት መመራት አለበት ። ይህ እምነቱ ነው ። ስለዚህ ይህን የወደኔ ጥያቄ እቀመጣለሁ ። ሴላው የጠላብ ብሔረተኝነት ስሜት ነው ። የትግራይን ራዕብለኝ እንመሠርታለን ፡ ብሔረሰቦች የራሳቸውን መንግሥት ሊመሠርቱ ይችላሉ ፡ የሚለውን ፡ እነዚህን ሁሉ እቀመጣለሁ ። እኔህ በልቤ እየጠፋ ሄዱ ። አንዳንድ ጊዜ ተቃውሞዉ እያመለጠኝ ስለሚወጣ ፍርሃትም ነበረብኝ ። ይህ በዚህ ይቆይ ።

በረሃ እያለሁ አንድ ሚስት አግብቼ ነበር ። ትምህርቷን የጨረሰች ችው አዲስ አበባ ንግድ ት/ቤት ሲሆን ትውልዷ ራያ ፡ ዉርዉር ነው ። የስምንት ወር እርጉዝ ነበረች ። አንድ ቀን ስብሐት ኑጋ መጣና ከሳድ ማመል ያለው ሬዲዮ ጣቢያችን በአይሮፕላን እንዳያመታ ሴላ ቦታ መውሰድ እንፈልጋለን ፡ አነአነሱ ይሄዳሉና አብረህ ሂድ አለኝ ። እኔን አያመለክተኝም አልሁት ። ሃሳብ ልትሰጣቸው ትችላህ ፡ አነሱም አብረሃቸው እንድትሄድ ፈልገዋል ብሎ ላከኝ ። ልክ እኔ እንደሄድኩ መድኃኒት ነው ብለው ከመጠን በላይ ክሎሮኪን ሰጧት ። ወዲያው ሕይወቷ አለፈ ። ገደሏት ። አለቀሰሁ ። ይህ ሲፈጠር በዓይኔም አራሴን መቆጣጠር አቃተኝ ።

ጥያቄ፡- አደጋው የደረሰው መድሃኒት ለመጠጣ ከለመጅል ወይስ ይሁን ተብሎ እርስዎን ለመጉዳት?

መልስ፡- ሆን ተብሎ እኔን ለማጥቃት ነው እንጂ ። ባለቤቱ ንጹህ ሰው ናት ። እኔ ከነርሱ ጋር አንዳንድ ግጭት ሊኖረኝ ይችላል ። ባለቤቱ ግን መጐዳት አልነበረባትም ። በሕክምናው ዓለም ክሎሮኪን እንኳን ለእርጉዝ ሴት ለጤነኛም ሰው በሆን ከመጠን በላይ አይሰጥም ። ከሰጠኸው መርዝ ነው፡ ይጐዳል ። ለእሷ ግን አስር ክኒን ነው የሰጧት ። የአስም መድሃኒት ስለሆነ በአንድ ጊዜ ዋጡው ብለው ነው እንድትውጠው ያደረጉት ። አልውጥም ብላ ተከላከለ ነበር ። አንድ ሐኪም አምጥተው ነው እንድትውጥ ያደረጉት ። መድሃኒቱን ወስዳ ራሷን ስትስት ደግሞ የክሎሮኪን መርፌ ወጉት ፡ በዚያው ሞተች ። ከሸሹም ወደ ላይ ወጀቸች ብዬ ነበር ፡ ምንም የሆነ ነገር የለም ። አሁን የተናገርኩት ያላሰብኩትን ነው ፡ ጥያቄው እንድናገር ገፋፋኝ ። በአጠቃላይ ፡ ይህ ድርጅት ወረ ሕዝብ ፡ ወረ አንድነት ወረ እኩልነት

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ። ኢትዮጵያን በጐሳ ከፋፍሎ ለመግዛል የተነሳ ድርጅት ነው ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቆሚአለሁ የሚለውም የውሸት ውሸት መሆኑን ከፕሮግራሙና ከድርጊቱ እያየናል ።

ሦስት፦ አመሳጥም በባለቤትም መገደል ብቻ ሳይሆን አራስም ያስጮት በነበረው ተቃውሞ እንደሆነ ገልጸውልናል ። ድርጅቱ የሚረን እንትስታስ ያክሂዳል ፣ በአባላቱም ላይ ከፍተኛ ስለላ እንዳለ ገልፀውልናል ። እንደዚህ ከዚህ አምልጠው እንደመጡ ቢያብራሩልን?

መልስ፦ የዚህን ድርጅት (የሕወሓትን) ወደ ከውስጡ ጀምሮ አውቀዋለሁ ። ከእኔ በላይ በአመራር ላይ ያሉት ሰዎች የሚያውቁትን እንም አውቀዋለሁ ። ምክንያቱም እዚህ አስከደረስ ድረስ ያሳደገኝ ድርጅት ነው ። በምወጣበት ጊዜ እንደማያለቅኝ ስለማውቅ ብዙ ገንዘብ የተጠቀምኩት ። ባለቤቱ ከተገደለች በኋላ ሁለም ነገር ግልጽ እየሆነ በመጣልን ጊዜ አመመኝ ብዬ ወደቅሁ ። ከወዲያ ወዲህ ቢያንላብጡኝም ምንም ነገር ሊያውቁ አልቻሉም ። ግራ ተጋባ ። ወደ ሃኪም እንድሄድ ፣ተቀዱልኝ ፣ ላኩኝ ብለቻቸው እምቢ አሉ ። በፖለቲካ ጉዳን ለሚያዩት ሁሉ ይህን ዕድል አይሰጡም ። እንደ እድል ሆኖ በአግዚአብሔር እርዳታ በተሰያየ መንገድ ወደ ሱዳን ገባሁ ። ሱዳን ከደረስሁ በኋላ አንድ ያከተር ፕሮፌሰር አየኝ ። ሌሎች ሁሉ አይተውኛል ። ፕሮፌሰሩ ግን ለብቻዬ እንደ ክፉል አስገብቶ አንተኮ በሽታ የለብህም አለኝ ፣ እርግጥ ደኽ ሰው እውነተኛ ሐኪም ነው ።

እኔም «ሕወሓት» የተባለው ድርጅት አባል ነኝ ። ከዚህ ድርጅት ጠፍቼ ወደ ሀገሬ ለመግባት አፈልጋለሁ አልሁት ። ባጠቃላይ በዚህ ሥልት ተጠቅሜ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ እጄን ሰጠሁ ።

ጥያቄ፦ ስለ ድርጅቱ ሬዲዮ ጣቢያ አንስተዋል ። የት እንደሚገኝ ፣ እንዴት እንደተቋቋመና ስለአመራሩም የሚያውቁትን ቢገልጹልን?

መልስ፦ ሬዲዮ ጣቢያው አሁን በ«ሕወሓት» አመራር ላይ ያሉት ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ጥረት ውጤት ነው ። መጀመሪያ መያነው የ«ሻዕቢያን» ሬዲዮ ጣቢያ እየተገለገለ ፕሮግራሞቹን ያሰራው እንደነበር የምታውቁት ይመስለኛል ። በሻዕቢያ ሬዲዮ ሲገለገል ከቆየ በኋላ ለተመሰን ጊዜ በራዲዮ ጣቢያው አትገለገሉም ሲል «ሻዕቢያ» ከልከለ ነበር ። ይህ ለታክቲክ የተደረገ ነው ። የ«ሕወሓት» ራዲዮ ጣቢያ ሲጀምር ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሻዕቢያ» አስር ሺ ዶላር ሰጥቷል ። ይሆን በሚሰጥበት ጊዜ በተለይ በ1975 በድርቅ በተመቱ የትግራይ አካባቢዎች በአንድ ቦታ አንድ መቶ ኩንታል እህል በሌላው ሁለት መቶ ኩንታል እንዲሁ እናስተምጣለን ። ለራዲዮ ጣቢያው ማቋቋሚያ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት የተየሰነው ስልት ነበር ። ከውጭ አገር የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ተወካዮች ይመጣሉ ። ለድርቅ የሚሆን እህል ይሸውላችሁ ብለን እናስገበኛቸዋለን ። እኔ በዚያን ጊዜ መሐመድ ተብዬ ነበር የምጠራው ። ደንበኛ ነጋዴ ሆኜ አቀርባለሁ ። የ«ቲ·ፒ·ኤል·ኤፍ» አመራር አባላት ይዘዋቸው ይመጡና ነላፊው ነጋዴ እሱ ነው ብለው ያስተዋውቁኛል ። (ልብ በሉ እኔም እነሱም ሁለታችንም አባል ነን) እኔ መሐመድ ነኝ ብዬ እተዋወቃለሁ ። የእህል አቅራቢ ነጋዴ ሆኜ ማለት ነው ። በድርቅ ለተጐዱት እርዳታ ሊሰጥ ከመጣው ዕርዳታ ሰጭ ወገን ጋር ዋጋ እንገባርና እህሉን እሸጥለታለሁ ። ገንዘቡንም እቀበላለሁ ። በዚህ መልክ የዕርዳታው እህል ተሸጠ የተሰበሰበ ገንዘብ ነው ራዲዮ ጣቢያው የተቋቋመበት ። በዚህ ላይ ደግሞ በትግራይ የሚኖሩ እና በውጭ የሚገኙ የትግራይ ተወላጅች አስፈላጊ የሆነውን ራዲዮ ጣቢያ ለማቋቋም ገንዘብ አዋጡ ተብለው አዋጥተዋል ። በዚህ መንገድ ተገዝቶ ነው ራዲዮ ጣቢያው በክሳድ ግመል ደጀና ላይ የተቋቋመው ። ለዚህ ደግሞ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በውጪ ያደርግ የነበረው ራሱ «ሻዕቢያ» ነው ። ብዙ የ«ሻዕቢያ» አባሎች ገንዘብ እንዲያዋጡ ተደርጓል ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ጋብቻ ተከልክሎ ነበር ብለውናል ። እርስዎ ደግሞ አግብተው ባለቤትም ሞተውብዎታል ፡ እንዴት እንዲያገቡ ተፈቀድልዎ? ባለሥልጣን ስለሆኑ?

<u>መልስ</u>፡- ወያኔዎች ለእኔ ጋብቻን የፈቀዱት ወይው አይደለም ። ለምሳሌ እኔ አሥር ዓመት ሙሉ ሴት የሚባል ነገር አላውቅም ነበር ። ወደ ሴት ከሄድህ ትረሸናለህ ፡ ብዙ ሰዎች ናቸው የተረሸኑት ፡ የተገደሉት ። ግን ችግሩ አልጠፋም ፡ ይህ ወረ ተፈጥሮ እቂም ነው ። ተፈጥሮ ደግሞ ለማንኛውም ነገር ያስገድዳል ። እራሱ ዓባይ ወሐዬ በ1974 ፈትለወርቅ የምትባል ልጅ አስረግዞ እኔና አባዲ መስፍን በጣም ጥብቅ በሆነ ሚስጥር እንድታስወርድ አደረግን ። ሌላውን ግን ጸታዊ ግንኙነት ስላደረገ ሳየሕወሓትኦን እቂም ተግርረሃል ብለው ይገልፁታል ። መከልከሉ ትክክል

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ብለው የሚያምኑ ከሆነ ለምን ዓባይ ወሐዬ እራሱ አይገደልም? ለምን
ፈትለወርቅ አትገደልም? ይህን አንድ በል ። ዘርዓይ የሚባል የአመራ
አባል እንዲሁ አደረገ። ሉሎችም አሉ ። የአሁኑ መታደራዊ ጉዳይ ጎላ
የሆነው ሥዩም በ1975 አንዲት ልጅ አስረግዞ አሁንም በሳም ጥቂት
በሆነ ምስጢር ነው እንድታስወርድ ያደረግነው ። ይህን እኔና አባ
መስፍን ብቻ ነን የምናውቀው ። አባዲ መስፍን ዘህነምና ባለሟ
በመሆኑ የቴክኒክ ሥራውን ይሠራል ። ሌላ ሰው እንዳይሰማ እ
እንዳንድ እርዳታ አደርግለታለሁ ።

አረጋሽ የምትባል የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል አለች ። በ1978 እርግ
መጣች ። ከማን እንዳረገዘችም አናውቅም ፡ እንድታስወርድ የሕክምና
ዕርዳታ ያደረግንላት ግን እኔና አባዲመስፍን ነን ። ይህና ይህን
የመሰለው እየገፋ ሲመጣ በ1977 ሠርግ ፈቅደናል አሉ ። ሠርግ ፈቅደናል
ሲባል እንዴት ነው ? ታገባለህ ለሶስት ፡ ወር አብረህ ትቆያለህ ከዚያ
መፍታት ከፈለግህ ትችላለህ አሉ ። ይህ ደግሞ ጎብረተሰቡ ከአለው ባህል
ጋር የማይሄድ ፍጹም ዋልጌነትን የሚያስፋፋ ነው ።

ታዬ አስግዶም የሚባለው ሰው ሚስቱንና ልጆቹን ይዞ ነው ወደ
«ሕወሓት» የወጣው ። መጋባትን ሲፈቅዱ ሚስቱን ለሌላ ሰው ሰጪተ
እግዚአብሔር ያሳያችሁ ሁለቱ አብረው ያደጉ የወለዱ ወጣ ማዕረግ ያ
ነበሩ ። እንድታገባው የታዘዘላት ሰው ሊጋብዝ በጠዬታትም እ
ፈቃደኛ አልሆነችም ። ባጠቃላይ ብልግና የተሞላበት ጋብቻ ነ
የፈቀዱት ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ከ1977 በኋላ ጋብቻና ፍቺ ተደንግጎ ነበር ማለት ነው?

<u>መልስ</u>፡- አም ለሌላው ሳይሆን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ያደረጉት
ነው፡ ሁሉም ሰው አልቆባቸዋል ፡ ነትቶባቸዋል ።

<u>ጥያቄ</u>፡- አቶ ገብረመድህን አንድ የምናነሳው ጥያቄ አለን
በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ስሞች በመያዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያምታ
አሉ ። «አሕዴን» እና «አሕአዲግ» የሚባሉ አሉ በተለያዩ መልኮ
የተፈጠሩ። ተደም ሲል ከአቶ አብርሃም ያየህ ጋር ባደረግነው ውይይት
«አሕዴን» «የሕወሓት» የአማርኛ ክፍል ነው ብለውን ነበር ። እርስዎ
ደግሞ «አሕዴን» «የሕወሓት» የበኩር ልጅ ነው ብለውናል ። እንዚህ
ስሞች ለምንድነው የተፈጠሩት ? ለምን ነው ደግሞ «አሕአዲግ»
የተቋቋመው ? ለምን ነው እንዚህ ስሞች የተነጣጠሉት ?

t.me/OLDBOOKSPDF

በዘሪሁ፡- «አሕዴን» ናሚባለውን አጥ አብርሃም «የሕወሓት» እማርኛ ክፍል ነው ማለቱን ሰምቻለሁ ፡ ትክክለኛ አባባል ነው ። በአጠቃላይ «በአሕዴን» ውስጥ ያሉት አማርኛ ተናጋሪዎች የአመራር አባላቱ ብቻ ናቸው ። ሠራዊት የላቸውም ። «አሕአዴግ» የሚባለው ሰፊ ግንባር ፈጠርን የሚባልበት ነው ። ወያኔ ትግራይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማምታታት ያደረገው ነው ። «የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄን» እና «አሕዴግን» በማቋቋም የኢትዮጵያን ሕዝብ ስማጅናገረ ነው ። ከዚህ አቋም የመጣ ነው ፡ ፕሮግራማቸው በታሪክ ምንም ልዩነት የለውም ። የፌዴሬሽኑ ፕሮግራም ነው የተቀበለው ። እንደኛ «አሕዴን» እንደ «ሕወሓት» ሁሉ ኤርትራ ቅኝ ግዛት መሆኗን እና መገንጠል እንዳለበት ሙሉ በሙሉ ያምናል ፡ ሁለተኛ በትግራይ ውስጥ መንግሥት መቋቋም እንዳለበት ሙሉ በሙሉ ያመነ ቡድን ነው ።

ሶስተኛ ብሔረሰቦች ተገንጥለው የራሳቸውን መንግሥት ማቋቋያ አሰባቸው ብሎ ያመነ ነው ። በአጠቃላይ ሲታይ አጥ አብርሃም እንዳለው ጥሩም ስያሜ አግኝቶለታል ፡ «አሕዴን» «የሕወሓት» የእማርኛ ክፍል ነው ። በምንም ዓይነት ለኢትዮጵያ የቆመ አይደለም ። ዕውነቱ ለሕወሓት ዓላማ የቆመ የኢትዮጵያ አንድነትን የሚፃረር መሆኑ ነው ። አንድ ነገር ልጠቅስ የምፈልገው «የአንድነት ግንባር» በሚል ርዕስ «ሕወሓት» ስላወጣው ጽሁፍ ነው ፡ የጋራ ግቁባር ስለመመስረት ነው ጽሁፉ ። ማህቲመ «የሕወሓት» ነው ። የዚህ ጽሁፍ አንቀፅ አራት እንዲህ ይላል ። «ከሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ ጋር የአንድነት ትግል ጣምራ ይዞ የሚኸድ ድርጅት ወይም ወገን ፡ አንደኛ—የኤርትራን ቅኝ ግዛትነት አምኖ የኤርትራን መገንጠል ሙሉ በሙሉ በተግባር የሚያውል ፡ ሁለተኛ—በትግራይ ውስጥ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትን መቋቋም አምኖ ሙሉ በሙሉ በተግባር የሚተረጉም ፡ የብሔረሰቦች እኩልነት ተጠብቆ የመገንጠል መብታቸውን የሚያምን መሆን አለበት» ይላል ። ለኢትዮጵያ ቆሚአለሁ የሚል ድርጅት ከሆነ ይህን ይቀበላል ? ወይስ አይቀበለውም ? እኔም እናንተም ኢትዮጵያውያን ነን ፡ ይህንን ትቀበላላችሁ ? የሚቀበል ሰው አለ ብላችሁ ታምናላችሁ፤ የኢትዮጵያን መበታተን የሚቀበል ያለ አይመስለኝም ።

«አሕዴን» ግን ይህን ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ በፕሮግራሙ ያወጀቀ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው ። የኢትዮጵያን መንግሠት አምኖ ፡ ኤርትራ ኢትዮጵያዊ አይደ
ችም ፡ ቅኝ ግዛት ነች ፡ ብሎ የተቀበለ ፡ ብሔረሰቦች መገንጠል አለባቸ
ብሎ ያመነ ድርጅት ነው ። «ኢሕዴን ወይም ኢሕአዴግ» በአጭሩ
ሁለቱም አንድ ናቸው ። ቀደም ብዬ መሪኔ የሻዕቢያ ልጅ ናት «ኢሕዴን
ደግሞ «የሕወሓት» የበኩር ልጅ ነው ብዬ ነበር ። በሌላ አገላለ
«ኢሕዴን» የሻዕቢያ የልጅ ልጅ መሆኑ ነው ።

እንዚህ ሶስቱ በስትራቴጂ ደረጃ አንድ ናቸው ። አስትራቴጂአቸ
የኢትዮጵያን አንድነት ቆራርሶ በታትኖ መጣል ነው ። በታክቲክ ደረጃ
ደግሞ ሕዝቡን አደናግሮ ሕዝቡን ከፋፍሎ በኢትዮጵያ የእርስ በር
ጦርነት ነግሶ ፡ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ የጦርነት ሜዳ ሆና እንድትቀ
ማድረግ ነው ። ይህ ነው ታክቲካቸው ።

ጥያቄ፡- ሙይይታችንን ለማጠቃለል አቶ ነብረመድህን ፡ እርስዎ
የትግራይ ተወላጅ በመሆንዎ ቀደም ሲል ከመሰልዎቹዎ ጋር የትግራይን
ጥያቄ ለመመለስ በማለት ወደ በርሃ በመግባት ሲታገሉ ነበር ። ትግሉ
መልኩን ለውጦ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ የሚያፋጅ ፡ የሚያ
ዋጋ፡ የኢትዮጵያን በአጠቃላይም የሕዝባችንን ታሪክ ወደሚያጉድፍ
አቅጣጫ ተቀይሮ በማግኘትም ምንድነው የሚሰማዎት?

መልስ፡- ይህ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጥያቄ ነው ። አሁን
በሀገራችን ላይ ተከስቶ ያለ ጦርነት ኢትዮጵያውያንን በሙሉ በየቤታ
ቸው እየገባ የሚወጋ ነው ። ሁላችንም እንደምናውቀው ጦርነቱ
ያልነካው ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም ። ይህ ጦርነት ለስትራቴጂ ተብሎ
በፈለጉት ሐርነት ትግራይ» የተፈጠረ ነው ። ይህ ከሆነ ዘንድ ኢትዮጵያው
ያን እርስ በርስ ከተማቱ በኋላ ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ እርስ በር
መበጣበጥና ጦርነት ከተነሳ ፡ የምንፈልገውን ግብ (ኤርትራን የመገን
ጠል) እንጨብጥን ብለው የተነሱበት ነው ።

አንድ ተረት አለ«የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል» የሚል ። አንድ
ሌባ ሰርቆ ለመሔድ ከፈለገ ግርግር ማስነሳት አለበት ። ግርግር ከተነሳ
በእጁ የገባውን ዘርፎ መሄድ ይችላል ። ለዚህም ነው ወያኔም ጦርነት
የከፈተችው ። እርስዋን አስመስላ ያቆመችው የእርስዋ የበኩር ልጅ
«ኢሕአዴግ» ምንድነው? የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ ከጦርነት
ውስጥ ገብቶ ሲማቅቅ እሷ የምትፈልገውን ታመጣለች ። የኤርትራ

t.me/OLDBOOKSPDF

መንግስት ያመጣል ። የራሷን መንግሥት ታዋቅማለች ፡ ሉሎች ብሔረሰቦች ይገንጠሉ ማለት ነው ። የኢትዮጵያ አንድነት ፈርሶ ለእነሱ የተመቸ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ነው ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ።

ኢትዮጵያ በታሪኳ የኮራች ሀገር ናት ። እሁን ወያኔ መርነት የምትከፍተው ለምንድነው? ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብላ የከፈተችው አይደለም ፡ ለራስዋ ጥቅም ነው ፡ በሥልጣን ላይ ያሉት የወያኔ መሪዎች ለራሳቸው ጥቅምና ከ«ሻዕቢያ» ለተቀበሉት አደራ ሲሉ ነው እንዲህ ያደረጉት ። አረጋዊ በርሄ ባለፈው ጊዜ የጠቀሰው አለ ። በአሁኑ ጊዜ በብሔረሰብና በብሔር ስም ይህን ይህን እናደርጋለን ማለት የሚያዋጣ ነው ፡ ዋጋ የለውም ነው ያለው ። አሁን «ሕወሓት» የምታካሂደው መርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደ እርስ በርስ መርነት የሚከት ነው ። የዚህ መርነት አቅጣጫ ወደ'ት ነው ? የት ላይ ነው መድረሻው? የኢትዮጵያን አንድነት ይበታትናል የኢትዮጵያን ታሪክ ይደመስሳል ። ወያኔ የባረዩ ቱን ኢትዮጵያ አላውቅም ፡ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገርም አልነበረችም ብላለች ፡ እንደገና ወደ ኋላ ፡ ወደ በሰነ መሳፍንት ለመመለስ የተሸረበ ሴራ ነው ። ልገልጸው የምፈልገው አንደኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ነገር አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ አለበት ። እንዴት ነው የኤርትራ ተወላጅች ኤርትራን ለመገንጠል ብለው መጥተው ፡ ለትግራይ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቆመናል ብለው ሲያደናግሩ የቻሉት?

ወያኔ የሚያደርገው መርነት የኢትዮጵያን አንድነት ለመበታተን ፡ ኢትዮጵያ ብትንትን ብላ እንድትቀር ነው ። ሰፊው ሕዝብ ለዚህ ምን ዓይነት ምላሽ እንደሚሰጠው አኔም ራሴ በጉጉት የምጠብቀው ነው ። አገራችን ከምትቀረስ ፡ ተበታትና ከምትቀር ያለ ንያላችንን አሰባስበን ይህን መንበሩ መደምሰስና ማጥፋት አለብን ፡ ይህ ግዴ ነው ።

ሰላም በኢትዮጵያ ውስጥ ለማንገሥና ለማምጣትም ሲባል «ወያኔ ሓርነት ትግራይን» ማጥፋት አለብን ። ይህ ነው የሚሰማኝ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የመጀመሪያው የቀድሞ አባላት የነበሩት አቶ አብርሃም ያየህና አቶ ገብረመድህን አርአያ ከጋዜጠኞች ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ።

ጥያቄ፡— አቶ አብርሃም ለሰባት ዓመት በስደት ፡ አቶ ገብረመድህን ደግሞ ወያኔው በሚንቀሳቀስበት በበረሃ ለአሰራ ሁለት ዓመት ቆይታችኋል ። በቅርቡ ደግሞ ድርጅቱን አውግዛችሁ ተመልሳችኋል ። ሁለታችሁ እዚህ በመገናኘታችሁ የሚሰማችሁን ብታብራሩልን ?

አቶ አብርሃም፡— በመሠረቱ ከገብረ መድህን ጋር የምንተዋወቀውወደ በረሃ ከመውጣቱ በፊት ጅምሮ ነው ። በትግራይ ውስጥ የአንድ አውራጃ ሰዎች ከመሆናችንም ሌላ በቤተሰብም የምንተዋወቅ በመሆኑ እዚህ በመገናኘታችን በበኩሌ በጣም ደስ ብሎኛል ። በእንቅስቃሴው ውስጥ በነበርንበት ጊዜ አዲስ አበባ ተገናኝተን በግልጽ እንደምንነጋገረው እንነጋገርም ነበር ። የራሳችን የሆነ መታቀብ (ሪዘርቬሽን) ነበረን ። ገብረመድህንን መጀመሪያ ያገኘሁት ካርቱም ነው ። በካርቱም የቡድኑ ከተመኘ ስለሆንኩ ከበረሃ የሚመጡትን የወያኔ አበላት የማስተናግደው እኔ ነበርሁ ። ገብረመድህን ካርቱም ሲመጣ በጣም ተጐሳቁሎና ታሞ ነበር። ብዙ የመንፈስ ጭንቀት ነበረበት ። የእሱ ዓይነት ስቃይ የደረሰባቸው ሰዎች ስለማውቅ በጣም ነበር ያዘንሁት ። ገብረመድህንን ስለማውቀው በማስታመም ይሁን እንዳንድ ነገር በማድረግ ተባብረዋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሁ ። ሊመሰክር ይችላል ። መጀመሪያ እንደተገናኘን ተማምነን ለማውራት ችግር ነበር ፡ የስለላ ጉዳይ አለ ። እሱም ቢሆን ተጨላቁሎ በመምጣቱ አንዳንድ ሁኔታዎችም እየጠሩ በመምጣታቸው ሙሉ በሙሉም ባይሆን በተወሰነ ደረጃ ግልፅ ሆነን ተነጋግረናል ። በተለያዩ ደግሞ ግጭት ዘርዓጽዮን ካርቱም ስለነበር ከእሱ ጋር ያገናኘውአቸው እኔ ነበርሁ።ከእርሱ ጋርለመገናኘት መፈለጉእራሱየተሻለምልክትሆኖል። ብዙ ተወያይተናል ። ሌላው ደግሞ እኔ በክተማ ውስጥ በሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ የተወሰንሁ በመሆኑ ፡ እሱ ደግሞ በረሃ ውስጥ የቆየ እንደመሆኑ እኔ ላውቃቸው የምፈልጋቸውን በርካታ ነገሮችን ያውቃል። እንደዚህ ዓይነት መድረክ ያጋጥመኛል ፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማሳወቅ እችላለሁ ብዬ ባልገምትም ስለዚሁ ጉዳይ ለመግባባና በተለያዩ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ለማሳወቅ ፍላጐት ነበረኝ ። ሦስም አንዳንድ የመረጃ እጥረት ነበረብኝ ። ግብረመድህን ከመስራች አባሎች አንዱ ስለነበር ፡ በውጣ ውረዱ ውስጥም ስለቆየ ፡ ለእኔ ጥሩ የመረጃ ምንጭ ሊሆንኝ ስለሚችል ይጠቅመኛል ። ከዚያ የሚንቀሳቀስ ሁኔታ ወጥቶ የሰላም አየር በመተንፈሱና ካርቱም ውስጥ የነበረው ሁኔታ ተለውጦ ሰው መስሎ በማየቱም ደስ ይለኛል ።

<u>ሶቶ ግብረመድህን፡—</u> ትውውቃችን አጥ አብርሃም እንደገለፀውነው ። በአንድ ት/ቤትም ተምረናል ። የእሱን ወደሀገሩ መምጣት በራዲዮ ስሰማ የተሰማኝ ደስታ ልገልጸው የምችለው ዓይነት አልነበረም ። እሱን ለማግኘት ብዙ ነው የደከምኩት ። አንዳንድ የትግራይ ሰዎች ላገኘው እንድምችል ገልፀው ቀጠሮ ያዙልኝ ። አብርሃም እንዳለው ሱዳን ላይ ስንገናኝ የመንፈስ ጭንቀት ነበረብኝ ። ወያኔውና ዓላማውን በትርብ ስለማውቀው የኢትዮጵያን ታሪክ ማጉደፉ ፡ የኢትዮጵያን ለዓላዊነት መድፈሩ ፡ የሕዝቡን አንድነት እደጋ ላይ መጣሉና ሌሎችም ተደማምረው ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት አስከትለውብኝ ነበር ። እንዳለውም ተጨላቁዬ ነበር ። ወደ ሃኪም እንድሄድ የረዳኝ እሱ ነው ። ከወንድም በላይ ረድቶኛል። ካርቱም ስንገናኝ ያው በ«ሕወሓት» አመራር ከፍተኛ የስለላ መረብ ስለአለ ላምነው አልቻልሁም ። ለሚያደርግልኝ ሁሉ በማመስገን አልፈው ነበር ። ጥብቅ ጉዳዮችን አንስተን ለመወያየት ግን አልቻልሁም ። ከግደይ ዘርዓጽዮን (የወያኔው ምክትል ሊቀመንበር

t.me/OLDBOOKSPDF

የነበረው) ጋር አገናኘን ። ግደይን ስለአብርሃም ብዙ ጠየቅሁት ። ግደይ ዘርዓጽዮን አብርሃም ፀረ—ወያኔ አቋም እንዳለው ገለጸልኝ ። እንተም ፡ እኔም ፡ አረጋዊ በርሄም ፡ አብርሃም የሚፈልገውን ነገር እንስጠው ስለአለኝ ተማምነን መጠራጠራን ተውኩት ። ትዝ የሚለኝ ነገር አለ ፡ አንድ ጊዜ አራት ልጋብዘህ ብሎ አብርሃም አንድ ቦታ በራሱ መኪና ወሰደኝ ። በጣም ሙሽ ። ጥርጣሬ በሰውና ታችን የሰረጸ በመሆኑ ምን ሊያደርገኝ ነው ብዬ ፈርቼ ነበር ። በመጨረሻም ትክክለኛነቱን ካወቅሁ በኋላ ብዙ ነገር አብረን ሠርተናል ።

<u>ጥያቄ</u>፡— የጠነከረ ሙተዋወቅ እንዳላችሁ አውተናል ። እንዳችሁ በረሃ ፡ ሌላኛችሁ ካርቱም በስደት በቆያችሁበት ጊዜ ውስጥ አሁን ወደዚህ መድረክ ባመጣችሁ የአንድነት አቋም ላይ ተገናኝታችሁ ለመወያየት የቻላችሁበት አጋጣሚ ነበር ? የእናንተን መግለጫ የተከታተሉ ብዙ ሰዎች የሚያገናኛቸው አንድ ነገር መኖር አለበት ? ስለሚሉ ነው ጥያቄውን ያነሳነው ።

<u>አቶ አብርሃም</u>፡— ገብረመድህን ሊያነሳው እንደሞከረው እኔም በሥልጣናቸው ላይ ለመቆየት ሲሉ የወያኔው የስለላ መረብ ሰዎች እርስ በርሳቸው እንዳይወያዩ ያደርጋል ። ስለዚህም ብዙ ሰው ግልጽ አያደለም። ለዚህ መክራም ያደረሰን የግልጽነት መጥፋት ነው ። ሁሉም በድኑ ያለውን ያንፀባርቃል ፡ ያስተጋባል ። እኔ በእውነቱ ካርቱም ያሉ የወያኔው አባሎችና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን እንደሚያውቁት በግልጽ አናገራለሁ። እኔ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ዓይነት ቋንቋ ይናገራል ብዬ ነው የማምነው ። ገብረመድህንም ሊያምንኝ የቻለው በግልጽ ስለተናገርኩ ነው ። አባቱና እጮቹን አውቃለሁ ። የእኔንም ያውቃል ። ለኢትዮጵያ ነፃነት የከፈሉትን መስዋዕትነት ያውቃል ። የእነሱ ልጆች ሁነን በእኛ ስም ኢትዮጵያ ስትገነጣጠል ቆሞ ማየት አንፈልግም ። ሞት እንደሆነ ስንት ጊዜ ሞተናል ። አንዳንድ ሞት የሚፈሩ ሰዎች እናያለን ። አስር ጊዜ ሲሞቱ አይተናቸዋል ። ሞት ለዚህ ዓላማና አቋም የሚፈራ አያደለም ። እርግጥ በሁለታችን መካከል ፍጹም የሆነ መተማመን አልነበረም ። እሱ ወደዚህ ሲመጣ እኔ ወደ ጎጃሪፍ ሄጄ ነበር ። ወደሀገሩ መግባቱን ሳይነግረኝ ነው የመጣው ። ምናልባት ተጠራጥሮኝ ሊሆን ይችላል ። በዚህ ወቅሼዋለሁ ። ቡድኑ በመሠረታዊው የኢትዮጵያ አንድነት ላይ የተሳሳተ አቋም መውሰዱን ፡ ይህ ደግሞ ለሌላ ድርጅት

t.me/OLDBOOKSPDF

መሣሪያ ለመሆን ካልሆነ በስተቀር የትግራይ ሕዝብ አጅም ነው ብለን ልናራምድ እንደማንችል በሥልጣን ላይ ስንሆን በግልጽ ተናግረናል።

ንብረመድህን ከውስጥም ሆኖ በአመራር ላይ ካሉት የኤርትራ ተወላጆችና የትግራይ ነፃ አውጪ ኃን ከሚሉት ሰዎች ጋር ያለውን አንካሳ ስላንትያ አውቃለሁ። አጠናም ነበር። ያንንም በማስታከክ በሙሉ ልብ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ፡ ስለቡድኑ የወሻፅቢያ» መሣሪያነትና በረ ሕዝብነት ግልጽ አድርጌ ነግሬዋለሁ ፡ በዚህ ሁሉ ችግሮችንም እንስማማለን። የኮሶለው ምንድነው ? በመካከላችን መተማመን ስለአልነበረ በተቀናጅ መንገድ የወያኔውን ፀረ አንድነት ባህርይ ለማጋለጥ አልቻሉንም ነበር። እኔ በውጭ አገር መኖር አትቶኝ አልመጣሁም ፡ ከዚህ መንግሥት ጋር መተማመን ሊኖረንም ላይኖረንም ይችላል። በዚህ መንግሥት ላይም ጥያቄ ሊኖረኝ ይችላል። ይህ ሁለተኛ ጉዳይ ነው። በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ግን ሁላችንም አንድ ቋንቋ ነው የምንናገረው። በዚህ አኳያ ከንብረመድህን ጋር ተነጋግረናል።

<u>ለቮ ንብረመድህን፡—</u> ስለ ኢትየጵያ አንድነት ከአብርሃም ጋር ተነጋግረናል። እኔን በሽታ ላይ የጣለኝ «ወሻፅቢያ» መልእክተኞች በነመለስ ዜናዊ የኢትዮጵያ አንድነት እድጋ ላይ መውደቅ ነው። ምን ማድረግ አለብን ? በምን ላይ መነጋገር አለብን ? ዓላማችን ምን መሆን አለበት ? በሚለው ላይ ተነጋግረናል። ከተነጋገርንባቸው አንዱ የብዙ ሺህ ዓመታት እድሜ ያለው የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ ነው። ይህ እንዴት በወያኔ ይፈርሳል ? ለምን አንድ ነገር አናደርግም ? ብለን ተወያይተናል። ይህን ሲገልጽልኝ ሃሳቡ እንደሚደገፍ ገልጨለታለሁ። እኔ የኤርትራን የቅኝ ግዛት ጥያቄ በሚመለከት ፡ በትግራይ ውስጥ ስለሚቆመው መንግሥት ፡ የብሔረሰቦች መገንጠል ያስፈልጋል ስለሚሉበት ምክንያት፡ አሁን «አሕዴን» ተብሎ የሚጠራው ቡድንና «ሕወሓት» በምን እንደተያዩ ፡ ቁርኝታቸው እንዴት እንደሆነ የሚገልጽ ሰነድ ይዤ መጥቼ ስለነበር በስፋት ማብራሪያ ሰጥቼዋለሁ። እንዲያነብም በርካታ ጽሑፎችን ልሰጠው ነበር። ሆኖም አንዳንድ ሰነዶችን ግደይ ዘርዓ ጽዮን ለጊዜው አፈልጋቸዋለሁ ስላለኝ ወስዷቸዋል። ከአብርሃም ጋር አንድ ዓላማና አቋም እንዳለን ተግንዝቤያለሁ። ለግደይ ዘርዓጽዮንና ለአረጋዊ በርሄ ወደ ኢትዮጵያ እንደምገባ ገልፀዉሉላቸዋለሁ። እነሱ ምን መሥራት እንዳለባቸው ፡ እኔም አገሬ ውስጥ ምን መሥራት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደምችል ተነጋግረናል ። ለአብርሃም ግን አልነገርኩትም ። አብርሃም በነበረም የአንድ ኩባንያ ሥራ አሥኪያጅ ስለነበረ ፡ አብርሃም እንተን ስለሚወድህ ስለሚፈልግህም ምናልባት ብዙ ባንያው ውስጥ ሊያስቀጥርህና እንዳትሄድ ሊያደርግህ ይችላል ሲል ግደይ ዘርዓጽዮን ስለነገረኝና ዝም በል ስላልኝ ዝም ብዬ መጣሁ ፡ በዚህ አድራጐቱ አብርሃም ወቅሶኛል ።

<u>ጥያቄ</u>፡— ሁለታችሁ ሰሞኑን በጣም ግልጽና ጠቅሚ የሆነ መልዕክት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተላልፋችኋል ። የወያኔውን ቡድን እዙይ ተልዕኮ በሚገባ አብራርታችኋል ። አቶ አብርሃም ሰሞኑን የወያኔውን ምንነት አስመልክተው ባስተላለፉት ትንተና ላይ አንዳንድ ነገሮችን ወርውረዋል ። አባላችንም እያደለም ፡ አልነበረም ፡ በራዲዮ ፡ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ ያስተላለፈው መልዕክት ሁሉ ውሸት ነው በማለት እያናፈሱ ናቸው ። በዚህ ላይ የምትሰጡት አስተያየት ካለ ?

<u>አብርሃም</u>፡— ይሆን ትጠይቁኛላችሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር ፡ ግን እኔ የእነሱ ራዲዮ ያናፈሰውን ስለሰማሁ በመሐረሻ ላይ አመላክቻለሁ የሚል ሃሳብ ነበረኝ ። መጠየቁ ጥሩ ነው ። ከእነዚህ ሰዎች ጋር እንካ ስላንቲያ ለመክፈት አልፈለግም ። ተቀባይነት ባለው ነገር ላይ ነው የምናገረው ። በወረቀት ላይ በተጻፈና በውስጥም በውጭም ያለ የትግራይ ተወላጅ በሚያውቀው ፡ በውጭ ያለ ኢትዮጵያዊ በሚያውቀውና ግን እዚህ ሀገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ምንም የማያውቀው በመሆን እንጂታችንን ይበላን በነበረው ጉዳይ ላይ ነው የምናገረው ። ወቅቱ የእንካ ስላንቲያ ሳይሆን አሁን ወሳኝ ወቅት ላይ ነው ያለነው ።

የእነርሱ ራዲዮ ካለው ተነስቼ ላስረዳ እችላለሁ ፡ ትርኪ ምርኪውን ትተን በቁም ነገሩ ላይ እናተኩር ። ጓላስቡ ለደረደረው ውሸት መልስ ለመስጠት አይደለም ይሆን የምንለው ። ለሁሉም ውሸቶች መልሱ ውሸት ማለት ነው» ብለዋል ። እኔ ለዋሸሁት ውሸት ፡ ውሸት ማለት በቂ ነው ባይ ናቸው ። <u>አንደኛ</u> የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው ሲል ቡድኑ በፕሮግራሙ ማስገባቱ ፡ <u>ሁለተኛ</u> የትግራይ ሪፑብሊክን መንግሥት መመሥረት ይቻላል ፡ መመሥረትም አለበት ማለቱን ገልጫለሁ ። የእነሱ መልስ ይሆን ብለናል ብሎ ማመን ወይም አላልንም ብሎ አብርሃምን ዋሽ ማድረግ ነው ። <u>ሦስተኛ</u> «ማሌሊት» እውነት ማርክሲስት ሌኒንስት ከሆነ ለምን እዚህ ካለው ማርክሲስት መንግሥት ጋር ይዋጋል ? እላለሁ ። ይሆን ደግሞ አውጭም በነበርኩበት ጊዜ የምናገረው ነው ። እዚህ ያለው

t.me/OLDBOOKSPDF

መንግሥት ማርክሲስት ነው ወይም አይደለም ነው ማለት ያለባቸው ። እኔ እዚህ ፓርቲ ሲመሰረት አልነበርኩም ፡ የፓርቲም አባል አይደለሁም። የኢህዴሪ መንግሥት ሲቋቋም አልነበርሁም ። አሁን ያለው መንግሥት ካፒታሊስት ነው ፡ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም ቅጥያ መንግሥት ነው ብለው ይናገሩ ። እነሱ ማርክሲስት ነን እያሉ ይሽኛውን ማርክሲስት መዋጋት አለባቸው የለባቸውም ነው ጥያቄው ። ለድርቅ እርዳታ የመጣው እህል ተሽጦ ለእነሱ የፖለቲካ መሣሪያ ሆኗል ብያለሁ ። ይህን ደግሞ ካረቱም ፡ጓዳቸው ፡ ፓርቲ ሱዳን ፡ከሰላ በየስደተኛው ካምፕ መጠየቅ ነው ። ዋናው ጉዳይ እኔ የእነሱ አባል መሆን አለመሆኔ አይደለም። ፕሮግራማቸውን የትም ሆኜ ላንብ እችላለሁ ። በሚሉት ላይ መናገር ፡ ሀሳቤን መሰንዘር እችላለሁ ። «አብርሃም ያየህ ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ በአባልነትም ይሁን በታጋይነት የማያውቀው ግለሰብ ነው ። ግለሰቡ ከኢፒዲኤ ፡ ከኢዲዩ ፡ ከሲአይኤ ጋር ይሠራ የነበረ የደርግ ሰላይ ነው ። ስለዚህ ታጋይ አልነበረም ። ከመጀመሪያው ጀምሮ ለደርግ ቅጥረኛ ሆኖ የተንቀሳቀሰ ነው። ለዚህም ማስረጃው ተመልሶ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ ነው» ብለዋል። ለዚህ በጣም ቀላል የሆነ መልስ መስጠት ይቻላል ። በዋናው ንጥብና የኢትዮጵያ ሕዝብ አቋም በወሰደበት ጉዳይ ላይ ከሕዝብ ጋር ይንጋገሩ ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የማወቅ መብት አለው ብዬ ነው ወደዚህ የመጣሁት ። ቸግሮኝ ለመለመን አይደለም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የማወቅ መብት ስለአለው ፡ ስለሚያደምጥም ለሚያናግሱት መልስ መስጠት አለብኝ። ያለነው ከሰው ጋር ነው ፡ እየተወያየን ነው። ሕዝብ የወሰደውን አቋም አይተናል ። አባል አልነበረም ከእሱ በኋላ "በተባባሪነት እንዲቀጥል ፈቅደንለት ነበር» ብለዋል ። ደግሞ ለአንድ የወያኔ ቡድን አባል ለመሆን ምን ፈቃድ ያስፈልጋል ? በዚህ ዓይነት ቡድን ገብቶ ለመሳተፍ የምትችለው ከፍለህ እንጂ ተከፍሎህ አይደለም ። እንደኔ ያለ ይብዛም ይነስ መጠነኛ እውቀት ያለው ሰው ተቀበለኝ ብሎ ለምኖ በኋላ በተባባሪነት ፈቀድንለት ይላሉ ። እኔን ለመርዳት «ሲሳይ» ውስጥ ለማስገባት ታስቦ ! ይህ እርስ በርሱ ነው የሚጋጨው ። አባል አልነበረም ከእሱ እንዴት በተባባሪነት ሊቀበሉኝ ይችላሉ? ደግሞስ የሲአይኤ ፡ የኢፒዲኤ ፡ የደርግ ሰላይ ከሆነው እንዴትስ በተራ ተባባሪነት ይቀበሉኛል? ተራ ተባባሪ አባል ቢሮ ውስጥ ይገባል ። ሰነድ በእጁ ይገባል ። ከመሪዎች ጋር ይገናኛል ፡ ስንት መረጃ ሊያወጣ ይችላል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ እንደሌት ይሆናል ?

ሌላው «በሕወሓትና በደርግ መካከል የእርቅ ሰላም ሀሳብ አትርቡ የውለቱ ትራኔ በሚያብ ትግል የሚፈታ እንጂ በሽማግሌ የሚያልት የእድርተኞች ጠብ አለመሆኑ ተንግርታል» ብለዋል ። የእርቅ ሰላሙን ጉዳይ ወልደ ሥላሴ ነጋ በመሠረተ ሀሳቡ ተተብልት በመግኛ ብዙሃን ያገለጽ መደም አደገለጽ በሚባልበት ጊዜ ነው «ማሌሊት» ከመትዕበት መጥቶ አመራሩ ሲለወጥ የተደናቀፈው ። ይህ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጥያቄ በመሆኑ «ተንግርታል» የሚባል አደደለም ። የእርቅ ሰላሙን ጉዳይ ከዚህ በፊት የገለፅሁት ስለሆነ እዚህ አላንሰውም ። ሳንሳ የሚፈልገው ግን እንድ ነገር አለ ። እውነት ይኸ መንግሥት የመደብ ትግል አደካሂድም ወይ ? ምን ዓይነት የመደብ ትግል እደካሂደ ነው ? የካፒታሊስቱን ? እዚህ የመደብ ትግል አንሶት የፀረዕቢደው» ተቀጣይ ወደኔ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የመደብ ትግል ደካሂዳል ! የመደብ ትግል ስለሆነ ከደርግ ጋር በእርቅ የምንጨርሰው አደኖለም ይላሉ ። ውሸት ነው ። እኛ ተናግረናል ። የታሪክ ወሐፊዎችም ነግ ይሰሩሉ ። እውነቱ የሚታደ ነው ።

«የደርግ ቅጥረኛ ሆኖ ከመጀመሪያው ጀምሮ የተንቀሳቀስ ነው ። ለዚህም ማስረጃው ወደ ኢትዮጵያ መመለሱ ነው» ብለዋል ። እኔ ከኢትዮጵያ የመጣሁበትን ምክንያት መንገር ለሚገባቸው ወገኖች ተናግሬ አለሁ ። በሱዳን ከኢትዮጵያ ኤምባሲ ጋርም ብዙ ተጨቃጭቄያለሁ ። የደርግ ሰላይ ብሆን ኖሮ ቅኪቱን ቆርጠው ይልኩኝ ነበር ። እኔ የመጣሁት ግን በራሴ ወጭ ነው ። ከኢትዮጵያ ለመጣሁበት ምክንያት ደግሞ ሩቅ መሄድ አደስፈልግም ። እኔ እሠራበት ከነበረው የብሔራዊ ኬሚካል ኮርፖሬሽን የምዕዋ ጨው ፋብሪካ የግል ማንደራን ማየት ይቻላል ። በአሥመራ አካባቢ እኔን የሚያውቁ ስምት ምን ዓይነት በደል እንደደረሰብኝ ሊገልጹት ይችላሉ ። የተፈፀመብኝ በደል እኔን የደርግ ሰላይ አድርጉ የሚያስወጣ መሆን አለመሆኑን መገንዘብ አደጓግትም ። እኔ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ሀሳቡም አልነበረኝም ። የመደኔውን የፀሸበቢያ» መሣሪያ መሆን በሚያወላውል መንገድ አምነን ተቀምጠናል ። በወደኋው እንቅስቃሴ ውስጥ ስለነበርን የእርቅራን ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አድርገን የተረመድን አየመሰላቸው ብዙ ኢትዮጵያውያን በነፃ ዓይን, እደተውናል ። በውጭ የሚገኙ እኔ የማውቃቸውና የሚያነጋግሩኝ ሰዎችም አሉ ። እንድ ነገር ማድረግ እንዳለብን ተሰምቶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኛል ። ስለ ጉዳዩ መጻፍና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መላመት ፈልጌ ነበር ። ይሁንና በታንዛኒያ ፡ በኡጋንዳ ፡ በኬንያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን «እንተ የሳፍሽውን ማን ታደነ ያደርግልሃል ? ማን ያትምልሃል ? መጨውም ቢሆን እንዴት ይቻላል ? ሌላ መንገድ መፈለግ አለበት ፡ ዋሽንግተን ዲሲ በአለው የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ ብትገልፀው ብዙ ሊጠቅም ይችላል» ብለውኛል ። ወደ አሜሪካ ለመሣባት ያማም ነፃ የለኝም። ላገኝም አልችልም ። በዚህ ምክንያት በመጨረሻ የተወሰደው አቋም የፈለገው ዓይነት እድጋ ይኑር ኢትዮጵያ ወስጥ ገብቶ ለሕዝብ መንገር ፡ ከዚያ በኋላ ሕዝብ የፈለገውን ያድርግ ብዬ ጉዳዩን በመሣለጼ አንድ ኃላፊነት ወርዶልኛል ። በኢትዮጵያዊነቱ የሚፈለግብኝን ተወጥቻለሁ ። <u>ማንም ያስተዳድራት ማን በኢትዮጵያ ውስጥ እንኖራለን ። መንግሥት በየጊዜው ይለዋወጣል ፡ አገር ግን አይለዋወጥም</u> ። ኢትዮጵያዊ ስለሆንሁና ኢትዮጵያዊ ሆን መኖር ስለምፈልግ ማንም በዓይነ ቁራኛ እንዲከታተለኝ አልፈልግም ። ከዚህ በኋላ ማን ምን ይሁን ? የሚያስፈልጉኮን አያደለም። ይሆን ለማድረግ ግን በራሴ አነሳሽነት በራሴ መጨ ነው የመጣሁት ።

ይኸ ችግር ሁሉ የሚደረገውና የሚያርሰው በትግራይ ሕዝብ ስም ነው ። ሰሞኑን አንድ ጓደኛዬ የነገረኝ ተልድ አለ ። አንድ ትግሬና አንድ ጉራጌ በጉርብትና ጓደኞች ሆነው ይኖራሉ ። እነዚህ ሁለት ጓደኞች ሆነው አብረው ሲበሉና ሲጠጡ ከቆዩ በኋላ ሰው ሆኖ የማይጣላ የለምና አንድ ቀን ተጣሉ ። ጉራጌው ወደ ቤቱ ሲገባ ሚስቱ ውስጥ እንዳይገባ ፡ መረማመጃ እንዲሆነው ድንጋይ አስቀምጧል ። «የት አባቱ ይህ ጉራጌ ዛሬ ተጣልቶኛል ፡ ይሆን ድንጋይ ማንሳት አለብኝ» ብሎ ያነሳዋል ። ጉራጌው ሲጠጣ እምሽቱ በሚስቱ ተፈላግልቶ እቤት ይገባና «ድንጋዮን ማን አንስ አላችሁ ?" ብሎ ልጅቱን ያጠይቃል ። "እኛ አይደለንም ጓደኛህ ሐጐስ ነው» ይሉታል ። ወዲያውም ስልክ ይመቱ "ሃሎ ! ሐጐስ ይህችም ድልድይ ሆንችና አፈረስህብኝ" አለው ብሎ ነገረኝ ። ይህ ተልድ ነው ። እኛ ድልድይ አፍራሾች ፡ የኢትዮጵያን አንድነትና ሰላም አደናቃፊዎች ነው የሆነው ። ይህ ነው የወጣልን ስም ። «ይህችም ድልድይ ሆንችና አፈረስህብኝ" ብሎ መናገር ሊያስች ይችላል ፡ ግን እንደ ተልድ ሊመሰድ አይችልም ። ብዙ የሚያውቁኝ ሰዎች «እኛ ድሮም በሆን

t.me/OLDBOOKSPDF

አንተን አንወራህም ነበር ። ይህን በመናገርህ እግዚአብሔር ይስጥህ» ብለውኛል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለዚህ ጉዳይ ቅንጣት አያውቅም ነበር ነው ያሉኝ ። <u>ነገሩ በትግራይ ሕዝብ ስም ነው የሚያርገው</u> ።

ብዙ ሰዎች አውን አናግረው ይገድሉኃል ያሉኛል ። ተጠንቀቅም የሚሉኝ አሉ ። ሞት ምንም አያደለም ። የዘመዶቼንና የወገኖቼን ታሪክ አበላሽቼ ከምሞት <u>እኔ ልሙትና ኢትዮጵያ በአንድነት ትኑር</u> ። የትግራይ ሕዝብ ስም እየጐደፈ ዝም ብሎ ማየት አይቻልም ። ሌላው ችግር ምንድነው የውስጥ ችግር በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን ለውጭ ጠላት እንዳጋለጠ ነው ። አውን ደግሞ የውጭ መራሪ ባይኖርም ሀርባሪ ሞልቶናል። በሰማሌ ጦርነትም አይተነዋል ። <u>እኛ ውስጥ ለውስጥ ስንፋተግ ጠላት ሊገባ ይችላል ። የውጭ ጠላት የሚገባው ደግሞ በውስጥ ድክመት ነው</u> ።

አንድ ታሪክ ልናገር ። የጦር ሚኒስትር የነበሩትን ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን ለማንጋገር አንድ የኢጣሊያን ጋዜጠኛ ይመጣና «ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ መፃፍ ስለምፈልግ ስለ ሰገሌ ጦርነት ይንገሩኝ» ይላቸዋል። ሰገሌ እንደሚታወቀው የወሎው ንጉሥ ሚካኤል ከሸዋ መኳንንት ሠራዊት ጋር የተዋጉበት የጦር ሜዳ ነው ። ሰገሌ ላይ ስለነበረ የኢትዮጵያውያን የእርስ በርስ ጦርነት ቢፅፍ ለጣሊያን ሕዝብ ምን ይጠቅመዋል ? እሱ ማወቅ የፈለገው በውስጣቸው ያለውን ችግር ነበር ። ብዙ ሰዎች እንደሚናገሩላቸው ፊታ ሀብተ ጊዮርጊስ ብልህ ሰው ነበሩና «የሰገሌ ጦርነት የገና ጨዋታ ነው ። እርስ በርሳችን እንጋጠምና እንዴ ያሸንፋል ። ይህ የውስጥ ጉዳይ ነው ። ጥሩ ታሪክ ጸሐፊ ከሆንህ ለምን የአድዋን ጦርነት አልነግረህና ለጣሊያን ሕዝብ አትፅፍለትም» አሉት ይባላል ። <u>እኛ እንደቱሬ አሞሬ እርስበርሳችን በምንፈፋፈህበት ወቅት ጠላት በውስጥ ጉዳያችን ስለሚገባና የኢትዮጵያ ሀልውና ሊጠፋ ስለሚችል አንድ አብርሃም ያየህ ይመጣና የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳዩን ይወቀው ባይ ነኝ</u> ።

ወደ ሌላው እንለፍ ። «ወደትግራይ ልግባ ብሎ ስለፈራነው ከለከልነው ። ይህ ሴራ የአሜሪካ ኢምባሬያሊዝም ሴራ ነው» ብለዋል ። በእትላንታ የሰላም ንግግር እያደረገ «የሕወሓት» ተከታይ መነፈት «ሻዕቢያ ያሳደገውን ውሻ ነው እንዲናከስ የላከው» ብሎ እዚህ መጥቼ ሲናገሬ የኢምባሬያሊዝም ሴራ ነው ተብሏል ። እግዚአብሔር ያሳያችሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ድርጅና የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም አንድ ናቸው ከተባለ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያፋሪድ ። «ሰላም ስለመስለን ወደ ትግራይ እንዲገባ አልፈቀድንለት» ለአለት የኢትዮጵያ መንግሥት አንድ የሻዕቢያ» ሰላይ ሲባል ቢሰው «የለም የሻዕቢያ ሰላይ ስለሆነ እንፈትድም» ይሰኛል እንጂ ለት ነው ። የማይመስል ነገር ነው ። «የሲአይኤ ፡ የኤፍቢኤ ፡ የኢጂፕሳ የደርግ ሰላይ ወደ ትግራይ ልግባ ሲል እነመለስ ዜናዊ ይከለክላሉ ማለት የልጅች ፊዴዎታ ነው ። እኔ ሰላይም ልሁን ወይም አልሁን እኛ መንገዝ ያለብን በፕሮግራም በሰፈረ ጉዳይ ላይ ነው ።

የጋርቱሙም የግንባሩም ፕሮግራም አንድ ነው ። ከዛጽ አንድ ልዮነት «የባሬሞ ኢትዮጵያ ከመቶ ዓመት በፊት አልነበረችም ፡ ምኒልክ ናቸው የፈጠሩዋት" ይላል ። የማን እንደነበረች ያንገሩን ። በዚህ ላይ ነው የምንነጋገረው ። ሌላው በዚሁ ፕሮግራማቸው ገፅ ስድስት ፡ አንቀጽ ሁለት ላይ «የግቸው አማራ ዋና ፖሊሲ ትግራይን አስረዘ መግዛት ነው ፡ ያሀ ፖሊሲ በምኒልክና ዚንዶስ በላቲ በግልጽ ታውጀ ሲሥራ ያንበረ ሲሆን ሕዝቡ ተርቦ እንዲቸት ያለመ ወይም ያቀደ ነበር" ይላል ። ፕሮግራም ያላችሁ ማየት ትችላላችሁ። የትግርኛውን ትርጉም ነው የተናገርሁት ። ኢትዮጵያውያን ነን ይላሉ ። «ኢሕአዲግን መሥርተናል ይላሉ ፡ ግን ፕሮግራማቸውንና ልሳኖቻቸውን በትግርኛ እንጂ በአማርኛ ፡ በኩራማኛ ፡ በወላይትኛ ወይም በሌላ ብሔረሰብ ቋንቋ አያጽፉም ። አማራው ወይም ሌላው በምን ያንብበው ? ይህ መንግሥት ያማም ሕገ መንግሥቱን ዘተለያዩ ቋንቋዎች ጽፏል ። መሰረተ ትምህርት በአሥራ አምስት ቋንቋዎች ያስተምራል። «ሕወሓት» የሚጠቀምበት ትግርኛ ራሱ የትግራይ ሰዎች የሚናገሩት ሳይሆን የኤርትራ ተናጋሪዎች የሚጠቀሙበት ነው ። ማንም ሊመሰክረው የሚችል ነው ። "የኢትዮጵያን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ለመመስረት ተነሳው የሚል ቡድን ወያኔም ብሉት ሌላ ለአማራው ሕዝብ በምን ነው ፕሮግራሙን የሚያደርስ ? ይህ የ «ሻዕቢያ» ማደናገሪያ ማስመሰያ (ፎርጀሪ) ነው ።

ያም ሆነ ያህ የእነሱ ሬዲዮ ከአናፈሰው አንዣር ደግሚ የምናገረው «የኤርትራ ጥያቄ የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው» ብለናል ወይም አላልንም ? «የትግራይን ሪፐብሊክ መንግሥት እንመሠርታለን» ብለናል ወይም አላልንም ፡ «እኛ ማርክሲስቶች ለዚያውም የአልባኒያ ማርክሲስቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

ንጉሠ ወይም አያስለንም ፣ በነዚህ ሦስት ጉዳዮች ላይ ነው በግልፅ መናገር ያለባቸው ። ስለ ድርቱ ጉዳይ ሱዳን ያለው ሕዝብ የሚያውቀው ነው ። ስለ እኔ ይሆን ካሉ ስለ ኅብረመድሀን ምን እንደሚሉ ለመስማት ደግሞ እንጓጓለው ።

ጥያቄ፡ የወያኔው ቡድን አባላት ወረ ሲአያኤ መሰለው ለመታየት የሚያደርጉት መከራ እንዳለ ይታወቃል ። በኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ሲአያኤ የሰራቸውና ያሉት ዓላማዎች የታወቁ ናቸው ። እነሱ በዚህ አንፃር ሲታዩ ምን ያህል ከሲአያኤ ይቃረናሉ ?

አብርሃም፡ እነዚህ ሰዎች ምንጭ ከአሜሪካ ያመጣሉ ፣ ፖለቲካ ደግሞ ከአልባኒያ መስደዋል ።

ይህ በታ እስትራቴጂያዊ ነው ። የምዕራቡ መንግሥት ይህን አካባቢና ኢትዮጵያን ይፈልጋል ። እንመለስ ዘንዊ በኢትዮጵያ ያለው መንግሥት የመደብ ትግል አያካሂድም ይላሉ ። ምዕራቡ ይህን መንግሥት ለመጣል የሚፈልገው በታክቲክነ ስለሆነ መያኔዎችን መርዳት ይኖርበታል ። ይህን ከጣለ በኋላ ደግሞ መያኔዎችን ለማጥፋት ቀላል ነው ፣ መያኔዎች ከትግራይ በሚያገኙት ገቢ ብቻ አይኖሩምና ። የምዕራቡ ዓለም የኤርትራን መገንጠል እንደማይደግፍ በትክክል አውቃለሁ ። ይህን አልጠራጠርም ፣ ምሥራቱም ቢሆን አያደግፉም ። ሁለቱም ቢደግፉ የሚያስከትለው ብዙ ጣጣ አለ ። አሻንጉሊት መንግሥታት ቢፈጠሩ የሚከተለው ሽኩቻ ብዙ ነው ። እዚህ ያለውን ለማጥፋት በተወሰነ ደረጃ ትንሹን ዘንዶ መጠቀም አለበት ። እነዚህ ሰዎች ሌላም ዓላማ ሊኖራቸው ይችላል ።

ኤርትራን ማስገንጠል ገና ከጠዋቱ ጣጣበር ገሥገሥቲ ብሔረ ትግራይ ሲቋቋም የነበበት ነው ። አሁን አሁን እንዲት ዓይነት ጣጣ ውስጥ ገብቼ ነበር ነው የምለው ። ያንን ሁሉ እርዳታ እና ምጣብ እየበሉ የአልባኒያ ኮሚኒስት ነኝ ማለት የማይሆን ነው ። ሌላም የማናውቀው ተልዕኮ ሊኖራቸው ይችላል ።

ጥያቄ፡ ከዚህ ሳንርቅ የምናነሣው የመደብ ትግል ነው ። ይህም የሚፈታው በመርህ ነው ይላሉ ፣ ይህ ወረ ሰላም ፖሊሲ አቋም ይመስለናል ። የመያኔ አባሎች በሰላም ጉዳይ ላይ እንዲወያዩ ከአመራሩ የተረበሳቸው ሀሳብ አለወይ ? በራዲዮአቸው ሰላም ፈላጊ መስለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ይቀርባሉ ፡ ሴላ ጊዜ የመጀመሪያ ትግል ስለምናካሔድ በእርቅ የምንፈታ
እደደለም ፡ እንታረቅም ይላሉ ። ስለዚህና ከዚህ ጋር ስለሚገናኙ ጉዳዮች
የምታውቁት ነገር አለ ?

አብርሃም፡- ገብረመድህን መልስ ሊሰጥበት ይችላል ። እኔ ግን
መጀመሪያ በዚህ በራዲዮ ስለሚያናፍሱት የምጨምረው ነገር አለኝ ።
ይህን ቡድን መታወም የጀመርሁት እዚህ ከመጣሁ በኋላ አይደለም ።
በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ያውቃሉ ። ሱዳን ውስጥም
አንድ ዓመት ሽንጨን ገትሬ ተፋልሚአቸዋለሁ ። እኔን እንደ ግንባር
አፍነው አድራሻዬን የሚያጠፉኝ ሰው አይደለሁም ። የምፈራውም ሰው
አልነበረኝም ። አሁን መግለጫ ከሰጠሁ በኋላ "የደርግ ሰላይ ነው ፡
የሲአይኤ ወኪል ነው" ከማለት ለምን ቀድመው አላደረጉትም ፣ ለምን
«አብርሃም ያየህ የትግራይ ሕዝብና የሻዕቢያ ጠላት ስለሆነ ንቅሳትሽ
ጠብቁ» ብለው ከመር ወይም ከሁለት ወር በፊት አልሰፈሩም ? ይህ ሁሉ እኔ
በማር ጠቅልለው ሊያጉርሱን የነበረውን መርዝ ከመጣሁ በኋላ እደደ
ለም? እነዚህ ሰዎች አሁን ጠርነት ያስፋፉበት ዋናው ምክንያት
ምንድነው ? መጀመሪያ ወሎ ከተሞች ሲገቡ የወታደር ካምፑ ሳይሆን
የእርሻ ሰብል ገበያ መጋዘን ነው የያዙት ። የገበሬውን እህል እሸት ነው
ቆርጠው የወሰዱት ። ሙቱሌ ፡ አክሱም ፡ አዲግራት ፡ እድዋ ወዘተ ያለው
ሰው ምንድነው ከአልባኒያ ያመጣቸሁት ? ሲላቸው ወሎ ሄደው እሸት
ቆረጣ ጀመሩ ። በዚህ ወቅት የጦርነቱ ሁኔታ እያየለ መምጣቱ የጎለም
ጎብረተሰብ በምሥራቅ አፍሪካ ቀንድ እንዲኖር የሚፈልገውን የሰላም
ጥረት ያናጋል ። «ሻዕቢያ» በጨዋ ደንብ አትላንታ ሄዶ ተነጋግሮአል ።
ሰላም አያፈልጉም እንዳንባል ወደአትላንታ ሄደናል ፡ እናንተ ያማሞ
ተኩስ ክፍታችሁ ወደፊት ግፉ ብለው የላኩአቸው «ሻዕቢያዎች»
ናቸው ። እኛ ኤርትራ ንብተን ብዙ ጊዜ ተዋግተናል ። በቀይ ክክብ ጊዜ
መጥቼ ምሽጐች ውስጥ ያለቱት የትግራይ ልጆች ናቸው ። የትግራይ ገበሬ
«ልጅቻችንን ኤርትራ ወስዳችሁ ታስፈጃላችሁ» ብሎ ተቃውሞአል ።
ትግራይ ውስጥ ብዙ ጊዜ ጠርነት ነበረ ። ምንው የኤርትራ ንጉሣዊት
አልመጡልንም ? ግን ወደ አትላንታ ለመሄድ «ሻዕቢያ» እየተዘጋጀ ሻቢ
ሳይ ለመጀመሪያ ጊዜ በጋራ የኢትዮጵያን ሠራዊት አጠቁ ። አሁንም
«ሻዕቢያ» ከስድስት በላይ ብርጌዶቹን ወደ ጐንደርና ወደ ወሎ ልኮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወያኔን እያገዘ ነው ። እዚያ ምን አሰው ? ከቻለ የኤርትራን ጉዳይ እዚያው ኤርትራ ያስፈፅም ። ከሶ ከመሠረቱ ወያኔው ፀየሻዚያ መሣሪያ ነው የሆነው ። ወ/ሮ በመሄዴ ብዙ ተምሬ ነው የመጣሁት ። እዚህ ተሰም ፋብሪካ አሰራ ነበር ። ብዙ የምረዳቸው የኤርትራ ተመላጅች ነበሩ ። ያሳዝኑኝ ነበር ። ውሎው ሄደን ደግሞ እንዳንኖር ከጎረብ ጋር ተመሳጥረው የሚያጀርጉንን አደነናል ። እዚህ አዲስ አበባ ግን ተቻችረን ነው የምንኖረው። መሣሪያ መሆኛችንን ደጋግሚ ተናግራአለሁ ።

<u>ጥያቄ</u>፡- አቶ ገብረ መድኅን የወያኔው የፋይናንስ ኃላፊ ሆነው ከመሥራችዎም በላይ በቀኝያዩ ኃላፊነቶችም ላይ ነበሩ ። በንበረምት የፋይናንስ ኃላፊነትና በሌሎችም ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ስለአቶ አብርሃምም ሆነ ስለ ሌሎች አባሎች ማወቅ ይችላሉ ። ወያኔ አቶ አብርሃም አባላችን አልነበረም ብሏል ። እርስዎ በዚህ ላይ የሚሉት አለ ?

<u>አብርሃም</u>፡- አብርሃም የወያኔ አባል መሆኑን ከመጀመሪያው ጀምሮ አውቃለሁ ። በተለይም በነርቱም የተለያዩ ተግባሮች ላይ ተንቀሳቅሷል ። ከርቱም ላይ ወያኔዎችን ከሱዳን መንግሥት ብልሥልጣናት ጋር ያገናኝ የነበረው አብርሃም ነው ። ወያኔዎች እንቀበላችሁም ፣ እትገቡም ሲባሉ ከመከላከያ ሚኒስቴርም ይሁን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኃላፊዎች ብንድ እንዲያቀርባቸው የሚጠይቁት አሱን ነበር ።

በ1977 ድርቅ ጊዜ ከትግራይ ወደ ሱዳን ተሰደዱ ተብለው የሄዱ የትግራይ ተወላጆች ነበሩ ። ስደተኞችን ተቀብሎ በሰፈሞ ፣ በእንጉርጎ ፣ በተዋላ ያስተናግድና እንቅስቃሴውን ይመራ የነበረው አብርሃም ራሱ ነው ። ወያኔ በ1977 ያገኘችውን የአሀል እርዳታ በነርቱም ፣ በጓዳሩና በመድኔ እና በሌሎች ቦታዎች እየተዘዋወረ ለሱዳን ከፍተኛ ኃላፊዎች ይሸጥና ያሞጉል የነበረው አራሱ አብርሃም ነው ። አብዛኛውን ጊዜ ይደርሰኝ የነበረው ገንዘብ በአብርሃም ያየሀ አማካይነት ተሸለ እንደተገኘ የሚገልፅ ነው ።

በ1978 ጠቅላላ የድርጅቱን የሂሳብ አሰራር ዘዴ የምቀይሰው እኔ ነበርው ። ረዳት አስፈለገኝ ። ራሱ የወያኔው ሲተ መንበር (አሁን መርዴል) ዓባይ ወሐዬ አብርሃም ያየህ አንተ ብንድ መጥቶ እንዲሠራ ይብጻቤ ፅፈንለታል ። አንተ ሙሉ ዝግጅት አድርግ ብሎኝ ነበር ። እሽ ብዬ ሙሉ ዝግጅት አደረግሁ ። አብርሃም ቀረ። አሱን ለማምጣት ተክለ ሐዋዝ ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሱዳን ሄዶ ከመር በኋላ ብቻውን ተመለሰ ። 1979 ጎጻር መር ላይ ይህንኑ የሚሳብ እሥራር እንደገና ለመቀየስ የአብርሃም መምጣት እድሚያስፈልግ ለዓባይ ፀሐዬ ነገርዑት ። አብርሃም አልመጣም ስለአልን ነው እንጂ እኛማ የሚሠራውን አዘጋጅቶ እንዲመጣ ነግረነዋል ብለኛል ። እኔ ካርቱም ሂጀ እንዳመጣውም ታስቦ ነበር ። በአንዳንድ ምክንያት ግን ሳልሄድ ቀረሁ ።

በ1977 «ማሌሊት» (ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ) እንደተመሠረተ በሱዳን ውስጥ ለሚገኙ የትግራይ ተወላጆች መግለጫ እንዲሰጥ ተደረገ ። የመግለጫ ሰዓውን በድን መርቶ የሄደው እራሱ አብርሃም ነው ። እዚያ በሚኖሩየትግራይተወላጆች ስለዚህ "የሻዕቢያየበኸርልጅ" (ወያኔን ማለታቸው ነው) ምን እያልህ ነው ? ተብሎ ተሰድዐ ነው የመጣው ። ይህ መካድ የለበትም ። ሱዳን ያሉትስ ምን ይላሉ — ብለውም አልጠየቁም ። ሃቅ ካላቸው ለምን በዚያን ጊዜ የሲአይ ኤ ትጥረኛ ነህና እኛን ወነለህ አትናገርም አይሉትም ነበር ? ሌላው ይቅር፡ ወያኔን የሚደግፉ ብዙ የትግራይ ተወላጆች አሉ ። ከነዚህ ውስጥ በውጭ ይኖር አሰፋ አብርሃ የሚባል የታወቀ የእርሻ ምርምር ኤክስፐርት አለ ። ትግራይ ውስጥ ለገብኝት መጥቶ ነበር ። እንደ መጣ ስብሃት ነጋና ገብሩ አስራት ነበሩ ጠርተው የወሰዱኝ ። ይኸኑሩ አምስት መቶ ብር አርዳታ ሰጠ ። በትግራይ ያለውን ድርቅ ለመርዳት ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰና እንዴትም ለሕዝብ እንደሚከፋፈል ማየት አፈልጋለሁ መረጃ ስጡኝ ብሎ ጠየቀ ። ገብረ መድህንን እንድታነጋግር ይብጻቤ ይሰጥሃል አሉትና ሶስታችን ተሰባሰብን ። የሲአይኤ ሰላይ መሆኑ እንዳይጋለጥበት ነው ለኛ አምስት መቶ ብር የሰጠን ተባለ ።

በ«ማጎበር ሪድኤት ትግራይ» ውስጥ ለሚሠራው ተክለ ወይኒ ለሚባለው ከላይ ከላይ ብቻ እንዲያስጐበኘው አውስጥ ገብተው እንዳያወ ያዩት ይብጻቤ ዓፍለት ብለው ገብሩ አስራትና ስብሐት ነጋ አዘዙኝ ፡ ዓፍሁለት ። የፖለቲካ ቢሮ አባልና የእኔ አለቃ የሆነው ገብሩ አስራት እንዲፈርምበት አድርጌ ተላከ ። ሰውየውም ለአስራ አምስት ቀን ቆይቶ በጉብኝቱ ሳይረካ ተመለሰ ። እኔም የሰውየው ስም በአጉል መጥፉት አሳዝኖኝ ወረቀቱን ያገሀ ። በአጋጣሚ እኔና ይክተር አሰፋ ካርቱም ላይ ተገናኝተን ስለ ቡዱኑ ብዙ ተነጋገርን ። የሲአይኤ ተወካይ ነህ ትባላለህ እንዴት ነው ? ብዬ ጠየቅሁት ፡ ይነገጠ ። እኔ የትግራይ ሕዝብ መከራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለመረጃዉት ፡ በድርቅ ሰለተጠቃ አስዉ እንጅ የእንግሊዝ መንግሥትና የተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ ደመወዝ ይከፍሉኛል አለኝ ። ቀጥዬ መረቀቱን አሳየሁት ። በጣም ተናደደ ። ከሦስት ቀን በኋላ ትክት ቆርጦ ለንደን ገባ ። «ሕወሓት»ንና እነሱን የሚጠላውን ሰው አሰቀድመው ሲአይ ኤ ብለው ስሙን ያጠፉሉ።

ፕሮፌሰር ሐጎስ ገብረየስ የሚባሉ የአጋሚ ተወላጅ ፡ የታወቁ የታሪክ ተመራማሪ ናቸው ። በካናዳ በአንድ ዩኒቨርሲቲ ያስተምራሉ ። ወያኔዎች ምን ይላቸዋል ? ሐጎስ የሚባል የአዲግራት አጋሚ ተወላጅ የሰኢይኤ ቅጥረኛ ፡ የደርግ አቀንቃኝ ሆኖ የኢትዮጵያን ታሪክ ያለውንና የሌለውን እየዘባረቀ ይጽፋል እያሉ ይዘልፏቸዋል ።

እኔን ከመጀመሪያው ጀምሮ አብረን ስለተንቀሳቀስን እንዲህ ዓይነት ስም ሊያወጡልኝ አይችሉም ። እኔ ፕሮፌሰር ሐጐስን እንዲህ ዓይነት ስም መስጠታቸው በአጠቃላይ የሚያሳየው ዋልጌነታቸውን ነው። ለማጠቃለል ግን አብርሃም የወያኔው ተወካይ በመሆን ከሰዳን ይንቀሳቀስ የነበረ ሰው መሆኑን በሚገባ አውቃለሁ ።

<u>አብርሃም</u>፡- የምጨምረው አለኝ ። ዶክተር አሰፋን አውቀዋለሁ ። «ባንድ ኤድ» የሚባል የኪነት ሰዎች ያስተባበሩት እርዳታ ሰብሰ ድርጅት ነበር ። ለኢትዮጵያውያን ስደተኞች ብዙ እርዳታ ሰጥቶአል ። ዶክተር አሰፋ ስለዚህ ጉዳይ ይጽፍ ነበር ፡ ያባንድ ኤድ» በትግራይ ውስጥ ሌላ ድርቅ የተከሰተ እንደሆነ እንዴት መከላከል እንደሚችል የሚገልፅ ቀዳሚ ጥናት ለማድረግ ነበር የመጣው ። እነሱ መረጃ ሊሰጡት አይፈልጉም ። አማሮሚስትና በእርሻ ሥራዎች ከፍተኛ እውቀት ያለው ሰው ነው ። «በማጎበር ረድኤት ትግራይ» ውስጥ የሚሠራው የኤርትራ ተወላጅ ሰሎሞን እንቋይ የሚባለው ዶክተር አሰፋን ከእኛ ጋር ሃፍ ብንለው እምቢ ብሎ ለብቻው ተደብቆ ይፅፋል እያለ አምቱልኛል ። ሰሎሞንም ይፅፋል ገቢ በሚያስገኝ መልኩ ፡ አሰፋ መረጃ ሲጠይቀው ሰሎሞን አይሰጠውም ። አሰፋንም ሆነ ፕሮፌሰር ሐጐስን እንዲህ ማለታቸው ግን የትግራይ ተወላጅ የሆኑትን ለማራቅ ሲሉ ነው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- በተከታታይ የሰጣችሁትን መግለጫዎች የሰሙ ሁሉ አንዳንድ ማብራሪያዎችን ጠይቀውናል ። ከዚህ አንፃር ላነሳ የፈለግሁት የወያኔው ቡድን «ማጎበር ገሥግስቲ ብሔር ትግራይ (ማገብት)» ብቻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይሆን ቀድም ብሎ «ማኅበር ተጋሩ»ና «ማኅበር ትግራይ ትግራኻ» የሚሉ ሥሞችን ይዞ ተስ በተስ በ«ሻዕቢያ» ድጋፍ እያገኘ ከዚህ ደርሷል ይባላል ። የምታውቁት ካለ ይበልጥ ብታብራሩት ?

አብርሃም፡ ብዙ የትግራይ ሰዎች የሚጠይቁኝ ነው ። ይህን ጉዳይ በጥልቀት አያውቁትም ነበር ። ይህ ድርጅት በኤርትራ ጥያቄ ምን አቋም እንዳለው ፡ ምን ያህል በመሣሪያነት እንደ«ሻዕቢያ» እንደተጠቀመበት አያውቁም ነበር ። ስለዚህ ነገር በጥናት መልክ ሰፋ አድርጎ መጻፍ ይቻላል ።

ግን መድረኩ ጠባብ ነው ። ይሁንና ለውይይታችን ያህል እንዳንድ ጉዳዮችን መጥቀስ እፈልጋለሁ ። ከመሠረቱ ሲጀመር በተደ ሞው ቀዳማዊ ንይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የነበረውን የተማሪ እንቅስቃሴ የኤርትራ ቡድኖች በከፍተኛ ደረጃ ተጠቅመውበታል ። የዚያን ጊዜ በኤርትራ የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች «ተራማጅና ዲሞክራቲክ ንይሎች» ናቸው ፡ እንቅስቃሴው ለመሀል አገሩም አስተዋፅኦ ይኖረዋል ተብሎ በመገመቱ ፡ ሁለተኛም የተማሪው እንቅስቃሴ ሕዝቡን ለማንቃቃት ጥሩ አስተዋፅኦ ቢኖረውም ጠለቅ ብሎ ታሪካዊ ይዘት ይዞ በመሄድ በመጨረሻ ምን ያመጣል የማይባልበት የስሜትና የሽሚያ ጉዳይ ነበር ። በዩኒቨርሲ ቲው መድረክ እየተጠቀመ የ«ሻዕቢያ»ን ስራ የሚሠራ አንድ አፍራም ስብሐት የሚባል ልጅ ነበር እኔ የማውቀው ። ከመጀመሪያው ጀምሮ የኤርትራ ቡድኖች የተማሪውንና የሠራተኛውን እንቅስቃሴ (አኔም ነበርሁበት) ሠርገው ገብተውበት ነበር ፡ ለምሳሌ ፍስሐ ዕዮን የኢትዮ ጵያ ሠራተኞች ማኅበር ሊቀመንበር የነበረ ሲሆን እሁን ከፍተኛ የ«ሻዕቢያ» አቀንቃኝ ነው ።

ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም ብሎ መጽሐፍ ጽፏል ። «ማንብት» ተብሎ ሲጀመር የዚያን ጊዜ ብዙ ጥያቄዎች ተነስተዋል ። እንሱ ለአሰራ አራትና አሥራ አምስት ዓመት የተበተቡትን በተሳሳ ማወቅም ያስቸግራል ። እንደዚያም ያለየነቃ ሕሊና የለም ። ልክ «ማንብት" ሲጀመር የኢሳያስ አፈወርቂ የአክስት ልጅ የማን ኪዳኔና ሚቸ.ሙሴ በቀጥታ ትግራዎች ነን፡ ሊያሰሩን አልቻሉም ፡ ብላችሁ ማበ ተብለው ገቡ። ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ ከ«ሻዕቢያ» ጋር ሆኖ «ጀበሃን» መሣዱአል ። የ«ጀበሃ» ሰዎች እኛን እንደቡችላ ነው የሚቆጥሩን ። «ሻዕቢያ የጀበሃ ልጅ ከጀበሃ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወልዶ ጀበሃን እንዳጠፋ ይህችኛዋም እናቷን ታጠፋለች» ይሉናል ።
ትግራይ ሕዝብ ስም የሚንቀሳቀሰው ይህ ቡድን ምን ያህል ለኢርትራ
ድንጥቅምእንደሞለበሚገባ መረዳት ይቻላል ። በልሳኖቹና በፕሮግራሙ
ስተካክሎ ሙሉ በሙሉ «ሻዕቢያ»ን ነው የሆነው ።

<u>ገበረ መድህን፡-</u> በ1964 በቀድሞው ቀ ን ዩ እና በሌሎችም
ምህርት ቤቶች ምን ዓይነት የተማሪ እንቅስቃሴ እንደነበር ይታወ
ል። በዩኒቨርስቲው የነበሩ የኤርትራና የትግራይ ልጆች ነበሩ ።
ተጠቀሰው «ማኅበት" እና «ማኅበር ተጋሩ» ምን ዓይነት ይዘት
ንደነበራቸው ለመግለጽ እሞክራለሁ ። በ1964የኤርትራ ቡድኖች«ሻዕቢ
ና ጀብሃ» እንድ መላ ፈለጉ። በትግራይ መሬት መንቀሳቀስ የሚችል
ንድ ቡድን ለማቋቋም ፡ በትግራይ የተማሩና የትግራይ ልጆች የሚያውቋ
ቸውን ሰብስቦ ማደራጀት በሁለቱም የተያዘ አቋም ነበር ።

በዚህ ወቅት ጀብሃ በትግራይ ውስጥ «ማምባር ነድሊ ትግራይ»
ለትም (ቲ.ኤል.ኤፍ.ን) አቋቋመ ። በ«ሻዕቢያ» የተመለመለ ደግሞ (ቲ.
ኤል.ኤፍ) «ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ» የተባለ ቡድን መጣ ።
ዚህ በኋላ በአዲስ አበባ የተማሪውን እንቅስቃሴ በቅርቡ ሆነው
ሚመሩ ፡ የወያኔውን እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ የኤርትራ ተወላጆች
በሩ። በተለይ አሁን የ«ሻዕቢያ» የፖሊት ቢሮ አባል የሆነው ጴጥሮስ
ሎሞን በአድዋ ሚሽን ተማሪ ከነበረው ከመለስ ተክሌ ጋር ይገናኛል ።
ጥሮስ ፡ መለስ ተክሌን ይይዝና መለስ ዜናዊን ፡ ዓባይ ፀሐዬን እና
ሎችንም የኤርትራ ልጆችን ይመለምላል ። እነ አረጋዊ በርሄን
ትግራይ ልጅ) መልምለው «ማኅበትን» ያቋቁማሉ ።

ወደ «ጀብሃ» እንመለስ «ማንባር ነድሊ ትግራይ» የሚባለው ደግሞ
ቁቋመው ግደይ ገብረዋህድ ፡ ወዲዘማሚ የተባለ መቀሌ የሚኖር
ዓረብ ልጅ ፡ አማረ ተስፋና ሌሎችም ተሰባስበው ነው ። እኒህ ሁለቱ
ቁቋሙበት ጊዜ የአሁኑ ወያኔ በ«ሻዕቢያ»፡ «ማንባር ነድሊ ትግራይ»
ግሞ «በጀብሃ» የተዘጋጀ ፕሮግራም ይዘው ወጡ ። ከወያኔው በፊት
ንቀሳቀስ የጀመረው «ማንባር ነድሊ ትግራይ» ነው ። ለሱ ሙሉ ትጥቅና
ርጅት የሰጠውና የኢኮኖሚ ትብብር ያደረገለት «ጀብሃ» ነው። በተዋጊ
ት ያሰለጠኑአቸውም «ጀብሃዎች» ናቸው ። በሌላ በኩልም በየካቲት
ት ያሰለጠኑአቸውም «ጀብሃዎች» ናቸው ። በሌላ በኩልም በየካቲት
967 የአሁኑ ወያኔ ከ«ሻዕቢያ» አስፈላጊ ትጥቅና የኢኮኖሚ ድጋፍ ይዘ
ትግራይ ውስጥ መንቀሳቀስ ጀመረ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሠለቱ ጥያቄ ምን ነበር? «ማንባር ገድሉ ትግራይ» ትግራይ
የኢትዮጵያ አካል አያደለችም ፡ «ቅን ግዛት ናት» የሚል ነጦግራም ያ
ነው የወጣው ። ይህም በ«ጀብሃ» ተቀባይነት አግኝቷል ። በ«ሻዕቢያ
የተፈጠረው ወያኔ ደግሞ በያዘት «ከማንባር ገድሉ ትግራይ» ጋ
የሚመሳሰል ቢሆንም ጎብረተሰቡን ለማደናገር በሚያመች መንገ
የተቀናበረ ነበር ። «እኛ ለትግራይ ብሔር ብሔረ ሰሙን ፡ የትግራይን መንግሥት
እናቋቁማለን» ብሎ ተነሳ ። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ «ጀብሃ» የ«ሻዕቢ
ያ»ን ውላጅ ማጥፋት ሲፈልግ «ሻዕቢያ»ም እንዲሁ «ማንባር ገድሉ
ትግራይ»ንማጥፋት ፈለገ ። በአርትራያ ያሉ ሠለቱም ዙድኖች አንዱ ሲላመ
የፈጠረውን ዙድን (በትግራይ ውስጥ) ለማጥፋት ተዘጋጁ ።

በ1968 መጀመሪያ ላይ በ«ሻዕቢያ» ተንድር በአሁኑ ወያኔ በከፋ
አንድ ጥያቄ ተረበ ። እኛ ሠለታችን የትግራይን ሕዝብ መነሰን ናቅን
ቢሆንም በመካከላችን ልዩነቶች አሉ ። ያሁን አስመግደን በጋራ
ብንንቀሳቀስ ይሻላል ሲሉ ዓላይ ወሐዩ ፡ መለስ ዜናዊና ገይይ ዘርዓዩን
ለ«ጀብሃ» ሀሳብ አቀረቡ ። በሃሳቡ ከተስማማችው ሠለታችው ማለት
«ማንባር ገድሉ ትግራይ» ና የአሁኑ ወያኔ ተነጋገሩ ተባለ ። ግን ሲላ ዘይ
በመሰጠ ነበረው ። በ1968 መስከረም ወር በአጋሚ አመራጅ «አይ.ነ»
ከሚባል ቦታ ሠለቱም ነጦግራሞቻቸውን ይዘው ተገናኙ ። «ማንባር ገድሉ
ትግራይ» ይዛ የቀረበችው «ትግራይ ቅን ግዛት ናት» የሚል ሲሆን
«የትግራይ ሕዝብ እንዳይመታን ፈርተን ነው እንጂ ልዩነት የለውም ።
በዚህ እንስማማ ። ምን ዓይነት ነጦግራም እንደምንጽፍ በኋላ እንነጋገራ
ለን» ተባለ ።

በጥቅምት መጨረሻ 1968 ላይ ሠለቱ እንደገና ተገናኙ ። ከ«ሻዕ
ቢያ» ሰለሞን ጴጥሮስ ፡ ከ«ጀብሃ» አንድ ሰው መጥተው አስታረቁ።
ይሁን ይሁን ተባለ ። ቀደም ሲል «ሻዕቢያ» ለወያኔ አባላት አብራችሁ
ስትሁኑ እረሽኗቸው ሲል ያስተላለፈውን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ
አብረው እንዲሁኑ ተደረገ ። የአሁኑ ወያኔ ብረቱን አስተካክሎ
ይጠብቃል ። የእንቅስቃሴው መሪ ስዩም ዮሴፍ ነበር ። ከሌሊቱ አስር
ሰዓት ሲሆን ምልክት እንደሚሰጣቸው (ለወያኔዎች) አስቀድሞ ተንገሮ
አቸዋል ። እንደተባለው «የማንባር ገድሉ ትግራይና» የአሁኑ ወያኔ
ተዋጊዎች አብረው ተኙ ። ሰዓቱ ሲደርስ ምልክቱ ተሰጠ ። ተከሰ
ተከፈተ ። «የማንባር ገድሉ ትግራይ» ተዋጊዎች ብዙ ሞቱ ። ጥቂት

t.me/OLDBOOKSPDF

ምልጠው ሄዱ ። ግንባሩ ተደመሰሰ ። ወያኔው «ግንባር ገድሊ ትግራይን» ስለመታ በ«ጀብሃ» እንዳይመታ ሙሉ የ«ሻዕቢያ» ጥበቃና ክለከል ተደረገለት ።

ለማጠቃለል «ማኅበር ነስገስቲ ብሔረ ትግራይ» የሚባለው የአሁኑ ያኔ የሆነው የ«ሻዕቢያ» ውልድ ሲሆን «ማኅበር ትግራይ ትግረኝ» ግሞ በ«ጀብሃ» ተቋቁሞ የነበረው «ግንባር ገድሊ ትግራይ» የተባለው ው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- «ማኅበር ተጋሩስ?»

<u>ገብረ መድህን</u>፡- «ማኅበር ተጋሩ» የተባለው ደግሞ ለሁለቱም ንደ አገናኝ ሆኖ የተፈጠረ ኮሚቴ ነው ። ከትግራይ ለሚመጡ ተማሪዎች ራ ቢያጡ ለአንዳንድ ርዳታ እንዲያገለግል የተቋቋመ ማኅበር ነው ። ሱን አቀፍ ነበር ። እነዚህ ሁለቱ ቡድኖች ሊመሠረቱ የቻሉበት ዋና ክንያት መነሳት አለበት ። የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ የሚያም ና ለአንድነቱ የቆመ ሕዝብ ነው ። በኤርትራ ውስጥ ደግሞ የቅኝ ግዛት ያቁ ተነስቷል ። የትግራይ ሕዝብ አይደግፈውም ። የትግራይ ሕዝብ ማንኛውም ጊዜ ተንቀሳቅሶ እንዳይደመሰሰን እንዳይመታን እነዚ ን ቡድኖች እናቋቁም ተባለ ። የትግራይ ሕዝብ የኤርትራን በረሃዎች ውቃቸዋል ። በየት በየት እንደሚንቀሳቀስ ያውቃል ። ካለምንም ሌላ ርዳታ የኛን መገንጠል በመቃወም ሊያጠፋን ይችላል ብለው ስለፈሩ መከፋፈል ያደረጉት ነው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለህም ፡ ትግራይ ኢትዮጵያ ትገንጠል ቢባል አይቀበለንም ከሚል እምነት የተነሳ ነው ይስ ለማታለያ የመጣ አቋም ነው?

<u>ገብረ መድህን</u>፡- አዎ ፡ ለምሳሌ «በግንባር ገድሊ ትግራይ» ቀረበው «ትግራይ ቅኝ ግዛት ናት» የሚል ነበር ። ይህን ሕዝቡ ይቀበልም ። ቅኝ ግዛት ነን ቢሉ አያንቀሳቅስም ። ወያኔው ያቀረበው ብሔር ጥያቄ ነው ። የብሔር ጥያቄ ደግሞ በዚያን ጊዜ እኔንም "ንድነው ብለህ ብትጠይቀኝ በስሜት ተገፋፍቼ ዓላማውን አራምድ በር እንጅ አላውቀውም ። በዚያን ጊዜ በ«ሻዕቢያ» የተቀየሰው ብሔራዊ ትግልን ሽፋን በማድረግ እነሱን እንዳይመታቸው ማድረግ ው ። መጀመሪያ ስንጠነሰስም ሆነ አባላትንም ስንመለምል የተንቀሳቀ ነው ይህን ዓላማ ሽፋን በማድረግ ነበር ። የኤርትራ ገንጣዮችን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንቅስቃሴ የትግራይ ሕዝብ እንዳያመታው ጥሩ መከላከያ ነው የሆ
ነው ። ቀንደኛ ተዋረጅም ነው የሆነው ። የትግራይ ልጅች አብዛኞ
በሳህል ፡ በባሪንቱ፡ በባርነ ነው ሲሞቱ ያለቱት ። አብርሃም እንደ ገለፀ
የወያኔ ንኡል አብዛኛው የቀረው አርትራ በረሃ ውስጥ ነው ።

አብርሃም፡ በዚህ ጉዳይ በቂ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል ። የኢት
ጵያ ሕዝብ በተለይም የትግራይ ሕዝብ ይህን ውጥንቅጥ ሳያውቀው ቀር
ለዚህ መፈናቀልና መመሳቀል ምክንያት መሆኑ ያሳዝናል ። የትግራ
እንቅስቃሴ ሲጀመር በዕድሜ ከእኛ ከፍ የሚል ገመሞ አየሰ የሚባል ሰ
ነበር ። አሁን ግን በምንም ውኔታ ይህ ሰው በወያኔው ስም እያጠራም
በረሃ ሲገዙ ያዟቸው የገባው እሱ ነው ። አሚሚቱም አያታውትም ፡ እን
ግን «አዲዩ» ገደለው ያላሉ ። እነሱም ገደለው ሲሆን ይችላል ። ከሱ
ሲጠጣ የገኘውት ፍንጭ አለ ። ያህ ሰው የትግራይ ሰው ነው ፡ ድሮ በሽፈ
በሽፍትነት የታወቀና በተድሞ ጋርሊማም ተመርጦ የመራ ነበር
ምንአልባትም የገደሉት ስለአርትራ ያላቸውኔተልዕኮ ለማስፈፀም የማያ
ችላቸው ሆኖ አግኝተውት ሊሆን ይችላል ። የትግራይን ጉዳይ ብ
እናስፈፅማለን የሚሉ ሰዎችን ወደ ስም ያጠፋሉ ወይ ይገድላሉ ። ሁድ
በአጠቃላይ ለአርትራ ጉንጣዮች መሣሪያ ሆኖ የተንቀሳቀሰ ነው ፡ እርግ
የትግራይ ጥያቄ አልነበረም ማለት አይደለም ። እነሱ የሕዝቡን ቁስ
በመነካካት ለዓላማቸው አሰለፉት ።

ገብረ ዘይኑን፡ በቀድሞው በቀንዩ የተንፀባረቁ ነገሮች እንደ
በሩ መጨመር አፈልጋለው ። ያህ «ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ» የሚባል ትጠ
አውራጃዊ ነው የሚል ስያሜ በዚያን ጊዜም ተሰጥቶታል ። «ቲ.ፒ.ኤ
ኤፍ» በብዛት እንቅስቃሴ ያደረገ የነበረው በአድዋ ፡ በሸዲና በአክሱ
ልጅች ጠንሳሽነት ፡ ቁልጭነትና አራማጅነት ነው ። ምክንያቱ
ለአርትራ ቅርብ በመሆናቸውና ከዚያ የሚመጡ ስለ «ጀብሃ»ም ይሁን ስ
«ሻዕቢያ» አንዳንድ መረጃዎች ያገኙ ስለነበረ ነው ። ለምሳሌ ፡ መሰ
ዜናዊ የአድዋ ፡ አረጋዊ በርሄ የአክሱም ፡ ግደይ ዘርጎይ ዕዮን ደግ
የሽሬ ተማሪዎችን ይሰብክ ነበር ። እነሱ ወደ በረሃ ሲገቡም ደግ
የአድዋ ፡ የአክሱምና የሽሬ ልጅች ናቸው በብዛት የተከተሏቸው ።

በአጠቃላይ የወያኔ መሪዎች አድዋ ፡ አክሱምና ሽሬ የተማሩ
ናቸው ። በዚያን ጊዜ ከነሱ ቀጥሎ ያለው ንላፊነት የሚሰጠው
መጀመሪያ ለአድዋ ቀጥሎ ለሽሬ ከዚያ ለአክሱም ልጅች ነበር ። አንዳ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድርታ ፡ ከልተ አመላለ-እና ራያና አዘቦ ለምን በአመራር ውስጥ ድርሻ እድኖራቸውም ? የሚል ጥያቄ ተነሳ ። ስለዚህ ወአሽአ የሚል ስያሜ ተፈጠረ ። ደብም አክሱም ፡ ሽሬ አድዋ ማለት ነው ። እነዚህ መወጣጫ አለባቸው የሚል እንትስታሲ እስክ 1970 በስራት ተካሄደ ። በመጨረሻም አስችኳይ ወታደራዊ ጉባኤ ተጠራ ። ደብ ከወግዝት» ሲያያዝ የመጣ ቃል ነው ። ለዚህ የደረሰት አብዛኞቹ የዚያ መሥራቾች ናቸው ። እንትስታሲውም እንድተጀመረ አክሱም ፡ አድዋና ሽሬ ተያዙ ። አስችኳይ ወታደራዊ ጉባኤ እንደተጠራ ከዕንደርታ ንብሩ አስራትን ለደስሙላ ቃላቀሉ ። ከማደጨው ብቻት ያለው ሰው ስለሌለ ለመምረጥ አልቻልንም አሉ ። ከአንሚ ሰዩም ዮሴፍን ሲመርጡ ከከልተ አመላለም እንዲሁ ለአመራር የሚበቃ ሰው ስለሌለ ልናስገባ አልቻልንም ተባለ ። ከተንቢንም ምንም ሰው የለም ተባለ። በኋላ ስዩም አብርሃምን ያመጡትም ስጋት ስለአደረባቸው ነው ። በራሱ በትግራይ ውስጥ እንኳ ስለሚከፋፍል መያዣው የትግራይን ሕዝብ አይወክልም ።

<u>ጥያቄ</u>፡ ኢሳያስ አፈወርቂ በእናቱ አድዋ ነው ይባላል ፡ ቡድኑን የፈጠረውና ያጠናከረው ደግሞ «ሻዕቢያ» ነው ። አመራሩ በዚህ አካባቢ ልጆች በብዛት የተያዘው ከዚህ ጋር በተገናኘ መንገድ ይሆን ?

<u>አብርሃም</u>፡ ኢሳያስ በሚያጠራጥር መንገድ በእናቱ አድዋ ውስጥ «የሃ» ከተባለ ቦታ ይወለዳል ። የማን ኪዳኔና ሰሎሞን እንቂይም የዚያው ተወላጆች ናቸው ። ለአንድ ዓላማ በሁለት ድርጅቶች የተሰለፉ ናቸው ። ብዙ ሰዎችም በተዳዩ ጽፈውበታል ። የተስፋ ፅዮንን መጽሐፍ ማየት ይቻላል ። በትግራይና በኤርትራ መካከል ጋብቻዎች አሉ ። አሁን «ከማሌሊት» አመራር ከሃያ አራቱ አስራ አምስቱ ኤርትራ ውስጥ ያደጉና የተወለዱ ናቸው ።

<u>ጥያቄ</u>፡ እንደተባለው ወያኔዎች ትግራይን ያወክላሉ እንዲባሉ በኩል ከየበታው አንዳንድ ሰው አምጥተዋል ። ለምሳሌ ፡ ስዩም የሴፍ ከአንሚ የመጣ ነው ይባላል ። ጎብረተሰቡ ማንነታቸውን እንዲያውቅ ትክክለኛ መጠሪያቸውን ብትገልጹልን?

<u>ሰኖ አብርሃም</u>፡ የዘረፃ ስም ማለት የፈረስ ስም እንደሚባለው ነው። ስማቸውን ለውጠዋል ። ለምሳሌ አረጋዊ በርሄ በራሁን ፡ ወልደ ስላሴ ነጋ ስብሐት ነጋ ፡ ለገሠ ዜናዊ መለስ ዜናዊ ፡ ገብረስላሴ አርአያ

t.me/OLDBOOKSPDF

እሰየ ፡ አታክልት ወሐዩ ዓባያ ወሐዩ እየተባሉ ይጠራሉ ። የሌሎች
ገብረመድህን ሊገልጽ ይችላል ።

ጥያቄ፡ ገብረተሰብ ከሚያቀርባቸው ጥያቄዎች አንዱ ወያኔ
«የሐለዋ ስድሳት» ወይም «ባይስድስት» የሚባል አስር ቤት አለው
አቋሙን የማይደግፉትንና የሚታመሙትን እዚህ አስር ቤት እያ
እንደሚያሳቅቅ ይነገራል ። አቶ ገብረ መድኅን በውስጡ ስለነበሩ ስለ
የሚያውቁትን ቢነግሩን?

አቶ ገብረዘመድህን፡ «ሐለዋ ወያኔ» ወይም «ባይ ስድስት» ቀ
ብሎ «ሐለዋ ሰውራ» ይባል ነበር ። ይህ ስም የተመሰረተው ከኤር
ገንጣዮች ነው ። በ1975 «ሐለዋ ወያኔ» ተባለ ። «ባይስድስት» የ
መጠሪያ ነው። ወህኒ ቤቱ የተሠራው ከመሬት በታች ሁለት ሜ
ጥልቀት ተቆፍሮ ጣራው በእንጨትና በአሸዋ የተሸፈነ ነው ። በጣ
ትንሽ የብርሃን ማስገቢያ ቀዳዳ ብቻ አለው ። ሰው እንዴት እዚህ ው
ይታሰራል? የሚል ጥያቄ ታነሳ ይሆናል ። እዚህ የሚታሠሩ ሰዎች አን
ወያኔ ኤርትራን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብላ ስትንቀሳቀስ ይህ
የሚታመሙና ታሪክ የሚያውቁ የሚታሰሩበት ነው። ሁለተኛ እና
እዚህ የመጣችሁት ከወንድሞቻችን ጋር ልታጣሉን ፡ ሠርተን እን
በላ ልታደርጉን ነው ። ይህ ትግል የምትሉት ምንድን ነው ቢቀር ፡ በ
በጦንደር ያለ ሠርቶ ይበላል ። እኛም ሠርተን እንብላ ብሎ ተታመ
የሚያነሳ ይታሰርበታል ። በሦስተኛ ደረጃ ወያኔ ከሕዝብ አስገ
የምትወስደውን ግለትም እህል ፡ በሬ ፡ ቅቤና የመሳሰሉትን አንሰጥ
ልጆቻችንን እናሳድግበታለን ብለው የሚታመሙ ሰዎች የሚታሰሩ
ነው ።

እዚያ የሚታሰር ሰው ምን ዓይነት ምርመራ ይደረግበታል? ብላች
ትጠይቁ ይሆናል ። በጋለ ሩም በመሰለ ብረት ነው እንደከብት የሚት
ት ። ብረት በለበሰ ጭማ የሰው አካላት የሚተፈትፋት እዚያ ው
ነው። በእንድ ታል ሕዝብ የሚያሰቃይበት ቦታ ነው ። እዚህ ጨለማ ቤ
ውስጥ አስገብተው እንደ እንስሳ በጋለ ብረት የሚተኩሷቸው የትግ
ልጆች ነው ። ወያኔ የደርግ ሰላይ ናቸው ብላ የያዘቻቸው
ማራዝማች በላይ ፡ እነ ፊታውራሪ ንዴለሰላሴ ፡ እነ አቶ አረጋዊ የተ
ሰዎች ናቸው ። በመጨረሻም በጥይት ረሽናቸዋለች ። እንዚህ ሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማለት አገራችንን ጠላት በወረረበት ጊዜ ከየጎጡና የአርበኝነት ሥራ የሰሩ ለእምቢት ኅሙትም በዘረፉ የቆሉ ናቸው። እኛንም ብላችሁበት አነዘዘ ታቀፍኑን አላነሳንም ፡ እንዳናገኝ አድርጋችኋል ፡ እርሷም አልሆም ብላችኋል ብለው ነው ያሠኑ ሁሉ የፈጁሙ ብቻ ። እነ ቴዎ እርእያ ከእነሱም ፡ አስፋው መ አረጋያ ከጎጂ ፡ ወ ሮ መድሀን ከሽራሮ የደረግ ሰላዮች ናቸው ተብለው ነው የተረሸኑ ት ። አስር አለት አዘጋም የሬም ዘሐረሰብ አባል ነበር ። መጀመሪያ ማረኩት ፡ ትንሽ አቆይተው አስቃደው በሃያት ደብድበው ገደሉት ። ሙት አለታ መርዕድንም እንዲሁ ። ንዲሉ ገብረመስቀልን ያጣም ወሃጅብን ሰላይ ነው ብለው ነው የገደሉት ። ቀኛዝማች ንዲለ ስላሴንም ብዙ ጣር ሙሰጡባቸዋል ። ፈሐስዋ ወያኔዎች አረመኔያዊ ሥራ የሚፈጽሙበት በታ ነው ።

ለዮ ለዘርሳይ ፡ ቡድኑ ስዩ ሠነህ ሰለስድኑ እ. ሰ በጎ ስራዎች ስትሰማ እያሞቀልህም ። በቅርብ የአረጋዊ በርሄና የተክለ ሃዋዝ ዘመድ የሠነ ቴዎድሮስ ር.ሥድት የሚባል ጋዜራቱ አነበቱን ሊጠይቅ ይሄዳል ። ከዚያም ያሳንቱና ሰባ ሁለት ተን አቆያቸው በአምአስቲ እንተርናሽና ልና በሱዳን ሲከራቲ ትብብር ተፈትዮ መጣ ። እስርቤቱ ምን እንደሚመስል ጠየቅነው ። እስር ቤት ሙሰዎ በነበረ ጊዜ እጁ የፊጥን እንደታሠረ ሲበላ እንኳ በታሠረው እጅ እየተጠማዘዘ እንደነበር ነግሮናል ። መጸዳጃ ቤት ለመሄድ ወይም ለመነሳበጥ ዘበኛውን ማስፈቀድ እንዳለም ነግሮናል ። ከአንድ ገደል ላይ አውጥተው በዚህ ልንከትህ ነውና አረጋዊ በርሄ ምን እንደሚሠራ ንገረን ብለው እንዳስፈራሩት ገልጾል ል ። ፊንጂ ፈትተው በማስያዝ ለቀነው ልንሂድ ነውና ከምትሞት ተናገር ብለው ስታዩን እንዳሳዩት ገልጾልናል ። አድራጎታቸው ከፋሽስ ቶች ያልተለየ ነው ። የቀኛ ንዲለስላሴ ዘላይ ዘመድ የሆነ ሐጐስ አዕብሃ የሚባል ሰው ዘመድ ለጠያቅ እንርሱ ወደአለበት ይሄዳል ። ወንጀል ቢፐርበት ኖሮ ለመሄድም እያሞነበርም ነበር ። ያዙና አሰሩት ። የትግራይን ሕዝብ ነፃ ለማውጣት ቆሚያለሁ የሚል ድርጅት እንደዚህ ያድርጎል? እያያኋችሁ ። አስረው በመርዝ የሚገድሉት ፡ መንገድ የሚያስጠርጉት ፡ ምቡን የሚያስቆፍሩት ምርኮኞችን ነው ።

የትግራይ ልጆች ከአገራቸው ሲወጡ ስማቸውን ይለውጣሉ ። ሱማን እያለው አንድ ሃለን የምትባል ልጅ እራት ጋብዛኝ አንድ በታ ሄድኩ ። ንድኛዋ የጠሎ ልጅ ናት ። ወርልድቪዥን በሚባል ድርጅት ውስጥ ትሰራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር ። አስፋዋ፡ል ፡ ከሰብዓዊ ርህራሄ ውጭ ጉዳት አድርሰውባ፡ል
ይህች ጓደኛሽ ለምን በክፉ ዓይን ታየኛለች ብየ ጠየቅኋት ። ልጅ
«አናንተ ዘረኞች ናችሁ ። በደቡብ አፍሪካ እንኳ እንዲህ ዓይነት ድርጊ
አያፈጽምም ።» አለችኝ ። ይህን ለማለት ምን አነሳሳሽ ብዬ ጠየቅሁ
«እንዴት የአርዳ፡ ሰፊ ድርጅት ታጠቃላችሁ?» ስለ አልሙ የደ
ሰላይ ናት ብለው በጋለ ብረት አሰቃይተውኛል ብላኛለች ። ጓደኛ
እንደነገረችኝም በደረሰባት ጉዳት የተነሳ ከወንድ ጋር መገናኘ
እንደማትችል ገልፃልኛለች ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ከዚህ ቀደም ከወያኔው የገቢ ምንጭ እንዱ ቀረ
መሆኑን ገልፀውልን ነበር ። ይህንን ፕሮግራም የተከታተሉ ሰዎች ለዚ
የቀረጥ ክፍያ የተጋለጡት የትግራይ ተወላጆች ናቸው ። በዚያ አካባቢ
የሚኖር የኤርትራ ተወላጅ ግን አይጠየቅም ይላሉ ። ይህ ምን ያህ
እውነት ነው?

<u>ለተ ገብረመድህን</u>፡- ባለፈው ጊዜ እኔም በትግራይ ሰዎች ላ
ከፍተኛ ቀረጥ እንደሚጥሉ ባለመግለጼ የአካባቢው ተወላጆች ሰምተ
ብለው ጠይቀውኛል ። ወያኔው በትግራይ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ቀረ
ጥሏል ። አንድ የትግራይ ተወላጅ ገበያ ወጥቶ ገዝቶ ሲሄድ የሚጣልበ
ቀረጥ አለ ። ቀረጡ ከያዙር ጀምሮ እስከ እህል ያለውን ሁሉ ያካትታ
የኤርትራ ተወላጆች ግን ከዚህ ቀረጥ ነፃ ናቸው ። ያሮም ይህ
ግመል ፡ ፍየል ፡ በሬ ፡ እህል ገዝተው ሲሄዱ ከቀረጥ ነፃ ናቸው ። ቀረጡ ነ
የሆነበት ምክንያት አለ ። ወያኔው ለትግራይ ሕዝብ ቆሜአለሁ ይበል
እንጂ የትግራይን ሕዝብ ለማሰቃየት የቆመ ነው ። ወያኔ የከፈተው
ጠርነትም የሚያርፈው በትግራይ ሕዝብ ላይ ነው ። ልጅቱ በንግግ
ተገደው ወደ ጦር ሜዳ ሄደዋል ። ወደ ትግራይ መንደሮች ብትገቡ ወጣት
የሆነ ሰው ፡ ሴት ይሁን ወንድ አታገኙም ።

ከኤርትራ የሚመጡ የኤርትራ ተወላጆች ሁሉ ወደ ትግራይ ሲመ
ይዘውት የሚመጡት ከዐሻዕቢያ» የሚሰጥ ወረቀት አለ ። እነሱ የተባለው
የኤርትራ ተወላጅ መሆኑን የሚያመለክት ወረቀት ስለሚያገኙ የፈለገው
ያህል ገዝቶ ይወስዳል ። ቀረጥ አይጠየቅም ። ለምን የትግራይ ሰው እንዲ
ይሠናል? እኔም የትግራይ ተወላጅ በመሆኔ በደላቸው ይሰማኛል
ያሳዝነኛል ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ፡ ሕዝቡ የተረጥ መድልዎ እንደሚደረግበት ያውቃል? ቅሬታውንስ ለማሰማት ምክርአል?

አቶ ገብረመድህን፡ በትክክል ያውቃል ። ብዙ ጊዜ ተቃውሞ አስቶአል ። ለምሳሌ በሽሬ ገበያ ሠማቶአል ። ለምንድነው ከኤርትራ የሚመጡትን የማትጠይቋው? ሊላው ተርቶ እኛ የምንፈልገውን እኛን ግፍተው ገዝተው ይሄዳሉ እያለ አሮሮውን ያሰማል ። በተምቢን ፡ በእድዋ ፡ በአክሱም አውራጃዎች ፡ በሰሜን ገበያዎች ስንቱ ቅሬታውን አሰምቷል ። በወያኔው የሚተርበው ምንድነው? ለእናንተ ስለምንታገል ነገዘብ ያስፈልገናል ። የግድ መክፈል አለባችው ። ነገ በመሬቱ ላይም ግብር እንጥላለን ይሏቸዋል ።

አክርሮ የተቃወመው ደግሞ ታስር «ሐለዋ ወያኔ» ይገባል ። የኤርትራ ተወላጆችን ግን እንኳን ተረጥ ሊያስከፍሏቸው በየት ገባህ በየት ወጣህም አይሏቸውም ።

ጥያቄ፡ በ1969 ከሲቲት መንዝ በስተደቡብ ያለውን የጋሽ አካባቢ ምናልባት በሽሬ ውስጥ ያለም ሊሆን ይችላል ፡ ወያኔው የትግራይ ክልል ነው ይገባኛል ብሎ ጥያቄ አቅርቦ ነበር ። በዚያን ጊዜ በአካባቢው ይንቀሳቀስ የነበረው «ጀብሃን» ለማስለቀቅ ፈልጉ ነበር። «ጀብሃ» መሬቱ ነው አሰትም ሲል «ሻዕቢያ» ግን ጥያቄውን ተቀብሎ ይግባት እንደነበረ እነ ይክተር በረከት ሀብተስላሴ ሁሉ በመጽሐፋቸው ላይ አስፍረውታል ። ያሆን እንደ'ት ታዩታላችሁ?

አቶ አብርሃም፡ የ«ሻዕቢያ» ቡድን ትግራይ ውስጥ መሬት አለኝ ስለሚለው ልንናገር የምንችለው ተረካቢዎች እነ ኤፍሬም ስብሃት ፡ አስረካቢዎች እነ መለስ ዜናዊ መሆናቸውን ነው ። ባሮራ «የአይጥ ምስክሯ ድንቢጥ» እንደሚባለው የኤርትራ ተወላጆች ለኤርትራ የትግራይን መሬት አስረካቢ ሆነዋል ማለት ነው ። ስለ አዲስ የትግራይ ካረታና ከወሎ ፡ ከጐንደርና ከአሰብ ተቆርሰው ስለተወሰዱ ቦታዎች ከዚህ ተደም ተናግረናል ።

የትግራይ ሰዎች ከኤርትራ የሚጠይቁት ገለሎና ሽምበቆ የሚባል ቦታ አለ ። በዚህ ጉዳይ ላይ ካርቱም ውስጥ አንድ ስብሰባ ተደርጉ ነበር ። የትግራይ ሕዝብ ምን ይላል ለማለት የ«ሻዕቢያ» ሰዎች በስብሰባው ላይ ተገኝተው ነበር ። «የትግራይ ሰዎች ኤርትራ ውስጥ መሬት አለን

t.me/OLDBOOKSPDF

ትላላችሁ ይህ ምንድነው?» ሲል ጉባኤውን ያመራ የነበረው ኒ
(የኤርትራ ተወላጅ ነው) ጥያቄ አቀረበ ። «አሁን የምንነጋገ
ስለመሬት ጉዳይ እያደለም። ስለ መሬት ጥያቄ ሲሆን ከኢትዮጵያ ሕ
ጋር እንወሰናለን» የሚል መልስ ተሰጠ ። የሃሳብ ትራኤው ምንድነው እ
ላይ ወያኔዎች ከትንደር ፡ ከወሎና ከአሰብ መሬት ለመውሰድ ሲ
ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆነው አልወሰኑም ። የኤርትራ ጉዳይ ሲሆን
ከኢትዮጵያ ሕዝብ ያመከራሉ ። ትጥፋት የበዛበት ነው ።

«ጅብሃ» በትግራይ ውስጥ መሬት አለኝ ብሎ ሲጠይት «ሻዕቢ
ራሱ መሬት የለህም የትግራይ ነው ይል ነበር ። አሁን «ጅብሃ» የለም
የፈጠራቸውና ያሳደጋቸው «ሻዕቢያ» በመሆኑ ስለትግራይ ሕዝብ ጉ
የተነሳ ጥያቄ የለም ።

ድርጅቱ ነፃ ነው ለማስኘት የሚፈጥሯቸው የቀልድ ቅራኔዎች
ሂሶች አሉ ። ብዙ ጊዜ «ሻዕቢያ» ስለ ትግራይ አይዕፍም ብለናል ፡ ጠቡ
ይግሞ ከቃል አልፎ ወደ መሣሪያም ትግል ሊሸጋገር ይችላል ። አንዱ
ጎይነቱ ሁኔታ ወያኔ «ከሻዕቢያ» ፡ «አሕዲን» ይግሞ ከወያኔ ጋ
በሚያደርጉት ግንኙነት ሲከሰት ይታያል ። «የሳሲበላውን አጥሬሽ
ወያኔው ብቻውን እንዳከሄደው ቆጥር እኛ እንዳልተሳተፍንበት አ
ርጉ ገለፀው» ሲል በአንድ ወቅት «አሕዲን» ስሞታ ያቀረበ
በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። ሁሉም «ከሻዕቢያ» አስከ «አሕአዲግ» ያ
የትጥፋት ሥራ ነው ።

<u>ጥያቄ ፡</u> ወያኔው በሃይማኖት ተቋሞች አካባቢ ችግር ያፈጥራል
ሆን ብሎ በተ ክርስቲያን አካባቢ ተኩስ ከፍቶ ዘረፋ ያካሄዳል ፡ በዚ
ላይ አስተያየትዎን ቢሰጡን?

<u>ገብረ መድኅን፡-</u> ወያኔዎች ብዙ ጊዜ መርኃት በተ ክርስቲያ
አካባቢ ያከናውኑ ። እኔም በሚገባ የማውቀው ጉዳይ ነው ። የኢትዮጵ
ሠራዊት ከአንድ ወገን ሲመጣ እሷ እንደምሽግ የምትጠቀመው ቤ
ክርስቲያንን ነው ። በሁለቱ መካከል ተኩስ ሲከፈት ቤተ ክርስቲያ
እንዲመጠል ለማድረግ ነው ። ከጥቃጠለ በኋላ የደርግ ሠራዊት አጠፋ
ለማለት ነው። ሌላም በስፋት የተንቀሳቀስንበት የመስጥ ምክንያት አለ
ወያኔ የአልባኒያ ደጋፊ ነኝ ስለምትል ፡ የክርስትናንና እስልምና
ሃይማኖቶችአትቀበልም፡አታምንም።«ሃይማኖት የሚባልከፋፋይመማ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው እንጂ ምንም ጥቅም የለውም ነው» የምትለው ። አሁን ለደስመላ በሃይማኖቱና በእኩልነቱ ላይ እንዲህ ሆነ እንዲህ ተደረገ ትላለች ። ስለ ትርሳ ትርስ ጥሩ ምሳሌ አለኝ ። ውትሮ አካባቢ አብርሃ አፅብሐ የሚባል ጥንታዊ ቤተክርስቲያን አለ ። ብዙ የታሪክ ትርሶችን የያዘ ነው ። እዚያ ላይ ያለውን የቤተ ክርስቲያኑን ትርስ ወስደን ማስተመጥ አለብን አለች።

በሕዝብና በወያኔው መካከል ብዙ ሚትሚቅ ተነሳ ። ይህ ትርስ ከድሮ ጀምሮ የነበረ ፡ ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ ለእኛ የደረሰ ፡ አባቶቻችን ጠብቀው ያቆዩን ነው በማለት እንስጥም ብለው አምቢ አሉ ። የቤተ ክርስቲያኑ ገበዝና አለቃ በወያኔው ታሠሩ ። የሚፈልጉትን ትርስ ሁሉ ሰዱን ወስደው ሸጡት ። በአድዋ አውራጃ እንዳ ማርያም የሚባል ሌላ ቤተ ክርስቲያን አለ ። ይህ ቤተ ክርስቲያን እንደ ላሊበላ ዓይነት ከዋርዝ ድንጋይ የተሠራ ነው ። ቤተ ክርስቲያኑ የታነፀበት ድንጋይ የተጠረበበት መሣሪያ ነበር (ስሙን አላውቀውም) እሱም እንዲሁ ለብዙ ጊዜ የቆየ ነው ። እሱንም እወስዳለሁ አለች ። ሕዝቡ አሁንም ተስማሙም ቢያቀርብም መሣሪያ ስለያዙች አውርዳ ወሰደችው ።

በ1972 አክሱም ላይ ኦፕሬሽን እንዲደረግ ዕቅድ ወጣ ። ኦፕሬሽኑ ለሁለት ነገር ነው የተዘጋጀው ። አንደኛው ትድስት ማርያም የሚባል በጣም ዘመናዊ ሆስፒታል አለ ። እዚያ ውስጥ ያለውን ዕቃ ለመዝረፍ ፡ ሁለተኛም የአክሱም ዕዮንን ቤተ ክርስቲያን ለመዝረፍ ። አክሱም ዕዮን በጣም ታሪካዊና ጠቅላላ የኢትዮጵያ የጥንት ትርሶች የተከማቹበት ቤተ ክርስቲያን ነው። የሆስፒታሉን እቃዎችና የቤተ ክርስቲያኑን ትርሶች የሚወስድ ሰው ይመደብ ተባለ ። ሰው ተዘጋጀ ። መርኑቱ ተከፈተ ። በአክሱም ዕዮን በኩል ሥራዊቱ በጣም ስለተከላከለ ወያኔው መሣሪያ አልቻለም ። የትድስት ማርያም ሆስፒታል ዕቃዎችን ግን ፡ በሽተኞችን ሣይተው ከአልጋ አውርዶ መሬት እየጣለ ወያኔው ዘረፈ ።

<u>ሰኞ ሰብረሃይ፡ በዚህ ምስቅልቅል ጊዜ ኢትዮጵያ ካጣቻቸው አንዱ ውድና ብርቅ የሆኑትንና ልዩ የሚያደርጓትን ትርሶቿን ነው ።</u> ናይሮቢ በነበረውበት ጊዜ ያለውን ቤተ ዐሉት የደርግ ቤተ ክርስቲያን ነው ተብሎ በ«ሻዕቢያ» ጋዜጦች ብዙ መከራ ደርሶብናል ። ቤተክርስቲ ያን ሁለት አገልግሎት ነው ያለው ፡ ክርስቲያኑ ሕዝብ ዐሉት ያደርግበ ታል ። ሌላው ደግሞ ስለ አገራችን አንድነት ፡ ስለ ነፃነታችን ፡ ስለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማንነታችን የሚገልጹ የታሪክ ማስረጃዎች የተከማቹበት ሀገር ነው። ስለ ሀገሩና ስለ ማንነቱ ሲከራከር ከታሪክ ተነስቶ ነው። ከዚህ ተነስተን የምንከራከርባቸው ብዙ መጻሕፍት በየዘመኑ ከርስቲያን አለን። ናቸዉ በነበረውበት ጊዜ የተናገረውት ያሆነ ነው። ከሉላው የአፍሪካ ሕዝቦች ልዩ የሚያደርገንም ነው። እኛ የተለየ ሥልጣኔ የነበረን ሕዝብ ነበርን። ሃይማኖት ባህል ነው። እኛ እምነት ነበረን። በድንጋይ የሠራነው አሻራችንም ነበር። ያ ዘመን ከርስቲያን ደግሞ ከአፍሪካም ሆነ ከሌሎች የሰብዓዊው ዓለም ሕዝቦች ልዩ የሚያደርገንን ፊደል መዘዙ ያቆየ ነው። ቤተክርስቲያን ብዙ ታሪክ የያዘ ነውና ቅርስ እንዳይጠፉ ብዙ ጥረት መደረግ ያስፈልጋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ብዙ ዘመን ከርስቲያን፣ ብዙ ቅርስ ነው ያለው። ብዙ የብራና መፃሕፍት ጀርመን ተወስደው የጀርመን ሕዝብ ሀብት ሆነዉብኛል። እኛ እዚያ የምንሄደው ለማየትና ለመዋሰስ ብቻ ነው እንጂ ለመሸጥ አንችልም። ድሮ ዐረቦች፣ ግሪኮችና እንግሊዞች የወሰዷቸው መፃሕፍት ብዙ ናቸው። የተረፈውን እንደመጠበቅ ሩኒኮ የእንድነታችንን የታሪክ መረጃዎች በማጥፋት ምስክር የምናደርገውን ሊያሳጡን የፈለጉ፣ ናቸዉም የኢትዮጵያ ልጆች ያሉዋቸው ናቸው።

መያኔዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ ስለሚያደርሱት ጉዳት እንደ የማውቀው ጉዳይ አለ። የአድዋ ደብረብርሃን ሥላሴ እዴ የሐንስ ያሰሩት ቤተክርስቲያን ነው። ሰዓሊዎቹ ከግብፅ አገር መጥተው የሠሩት በማየ ታሪካዊ ነው። እዚያ መያዉሙ ምሽግ ሠርቷል። ቦታው ተራራማ ከመሆኑም በላይ ወደ ሠሩ የሚመለከት ነው። ተክለ ሃዋዝን ክርቱም መቀሳ «እንዴት እናንተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትመሽጋላችሁ? ቤተ ክርስቲያን ከተመታ በኋላ ደርግ ቤተክርስቲያን ያፈርሳል ለማለት ለጥርጣሬ ንዳ ከሆነ የምትጠቀሙበት ሃርሥጋንዳ ይበልጣል ወይስ የቅርስ መጥፋት? ይህ ቤተ ክርስቲያን እንደነና ቢሠራም ያ ጊዜውን ጠብቆ የኢትዮጵያን ታሪክና ባህሏን ይዞ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን እንዲፈረስ እንዴት እዚያ ትመሽጋላችሁ?» አልዎት። ወዲያ የምሠራው የስለላ ሥራ ነው፣ ይህን የወታደራዊ ጉዳይ ሰምችን ጠይቅ» ብሎ ነው የመለሰልኝ። እሱም እንዳ እዚያው ተወልደን ነው ያደግነው፣ አባቱ የደብሩ መላከ ብርሃን ናቸው። ለምን ታሪክ ይጠፋል? የመለሰልኝ ግን የሚለው ንገር ጠፍቶት ነው። ሌላ ጊዜ ደርግ ቤተ ክርስቲያን ያሠራል

t.me/OLDBOOKSPDF

እያለም ፕሮፖጋንዳ ይነዛሉ ።

ጥያቄ፡- መሃኒው ቅርሳችንን እያወደመ ጠላትን ለጥፋት እየጸረግ ነው ። የእምነት ነፃነትም እየነፈገ ነው ። የክልሉ ሕዝብ ለእንደነዚህ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈለ ሕዝብ ነው ። እንዲህ ዓይነት መከራ ሲወድቅበት እንዴት እየተመለከተው ነው? ተቃዋሚ ክፍል በዚያ አካባቢ የለም ወይ?

ገበረ ዘሠናይ፡- በአጠቃላይ የትግራይ ሕዝብ ከመጀመሪያው ጀምሮ መሃኒውን ይታገላል ። በተምቤን ፡ በአክሱም እና በአድዋ ይንቀሳቀስ በነበረበት ጊዜ «ነጠበት» ተብሎ ይጠራ ነበር ። በአማርኛ ያልታሰበ አደጋ ወይም «ዱብእዳ» ማለት ነው ። የትግራይ ሕዝብ በሙሉ መሃኒውን አይደግፉም ስላም አሳጥፎታል ።

«አብዮግሞ» የሚባሉ የአፋር ብሔረሰብ አባሎች የሠኑ አሉ ። ስሙን የሰጣቸው መሃኒው ነው ። ትርጉሙ «ዘረ ሕዝብ» ማለት ነው ። እነሱ የሰፈው ሕዝብ አነስ ናቸው ። መሃኒ ግን የሕዝብ ጠላቶች አድርጉ ስም ሰጥቷቸዋል ። እኚህ የአፋር ተወላጆች መሃኒን ከጎላ ጎላ እየተከተሉ መሃ አስከጠላ የገፉ ጅግኖች ናቸው ። ከዳሎል ጀምሮ አዕቢድሬ የሚባል አለ ። ይህ ቢቃ በነልተ አውላሎ ውስጥ የሚገኝና መሃ አፋር በርሃ መውረጃ ነው። መሃኒ እዚያ ክልል አትገባም ። አውንም ወልቃይት ገዳም ስትገባ ሕዝቡ በሙሉ ምሽግ ይዞ ወንበይ አናስገባም በሉ ነው የተዋጋው ። በአውነ ወቅት የመሃኒው ንዩል ስለጠነከረ ፍርሃት አደረበት እንጂ በአክሱም አውራጃም በተለይ በአዲትና በዛና ያለው ሕዝብም ይብድባል ።

በአጠቃላይ ሲታይ ከትግራይ ውስጥ መሃኒን ያልሙታ ሕዝብ የለም ። "አብዮግሞ» የምትላቸው የአፋር ተወላጆች አውንም እየተጠቀት ነው ። «አብዮግሞ» የሚል ስያሜ በመሃኒው የተሰጣቸው የአፋር ብሔረሰብ አባሎች ከራሱ ከጎበረተሰቡ የመጡና በራሳቸው መሣሪያና ትጥቅ የሚንቀሳቀስ ናቸው ።

ጥያቄ፡- ከኤርትራ ወደ ትግራይ የ«ሻዕቢያ» መረቀት ይዘው የሚመጡ የኤርትራ ተወላጆች ምንም ቀረጥ እንደማይከፍሉ ተገልፀል ። በተመሳሳይ መንገድ «ሻዕቢያ» ወደሚቆጣጠረው ክልል የሚገቡ የትግራይ ተወላጆችስ? እናንተስ በኤርትራ ክልል መብታችሁ እስከምን ድረስ ነው?

t.me/OLDBOOKSPDF

ልዮ ገብረመድህን፡ የትግራይ ተወላጆች ኤርትራ ሄደው እንዳች ነገር አይጎዙም ። እንደኛ ከዚያ ያለው በተለይም ከኤርትራ ጋር የሚዋሰኑ የትግራይ ሕዝብ ማለትም ከበድሜ ፡ ከሽራሮ ፡ አደአሮ ፡ አዲቋላ ፡ አዲንብራ እስከ ሞላ ድረስ ያለው ሕዝብ ኤርትራ ሄዶ ምንም ነገር አይገዛም ። «ሻዕቢያ» ራሷ «እህል ፡ ከብት ፡ ማሞል መይም ሌላ የትግራይ ተወላጆች ኤርትራ መጥተው መግዛት የለባቸውም» የሚል ፖሊሲ አላት ።

ይህን ፖሊሲ ያላወቁ የትግራይ ተወላጆች ኤርትራ ሄደው ሲገዙ ይወረሳሉ። ለዚህ ማስረጃ ላቅርብ ። በሽሬ አውራጃ በአደአባ ወረዳ የሽራሮ ከተማ ነጋዴዎች እስከ ሱዳን ድረስ ሄደው ይገዛሉ ። ገዝተው ሲመለሱ በኤርትራ ክልል ስለሚያልፉ ይወርሷቸዋል ። የሽራሮን ሰው በብዛት ስለማውቅ የተወረሱትን ሰዎች ስም መጥቀስ እችላለሁ ። የትግራይ ሕዝብ ኤርትራ ሄዶ ምንም ነገር የመግዛት መብት የለውም ፡ ከገዛም ይወረሳል።

ጥያቄ፡ ድርቅና እርዳታን በተመለከተ አንዳንድ ነገሮች ቀደም ባሉት ውይይቶች ተነስተዋል ። በ1976 እና በ1977 በትግራይ አካባቢ ከፍተኛ ድርቅ ነበር ። መንግሥት ለአካባቢው የሚልከውን የእርዳታ እህል ወደኔ መንገድ ላይ በማድፋጥና አደጋ በማድረስ ይዘርፍና ያቃጥልም ነበር ። ቡድኑ ከመንግሥት የሚላከውን እያቃጠለ ፡ ሕዝቡን እያሰረ ፡ ወደ ስደት እየላከ ፡ እንዲት ያፈናቅለው እንደነበረ አቶ ገብረመድህን ቢገልጹት ፡ አቶ አብርሃም ደግሞ ከውጭ በሰብዓዊ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ይመጣ የነበረው እህል በትክክል ይከፋፈል ነበር ወይ? ይህን ቢያብራሩት ፡

ሊቀ አብርሃም፡ ይህ የድርቅ ዕርዳታ ጉዳይ በዚህ ሕዝብ ስም ተሰብስቦ መጥቶ ብዙ ሻጥር የተሠራበት ነው ። የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ መሆናቸውን እስማለሁ። የሰጡት እርዳታ በትክክል ለሕዝቡ መድረሱን መቆጣጠር ተገቢ ነው ። ለምን ግን የዚህ ዓይነት ቁጥጥር በነዚህ አሻንጉሊት ቡድኖች (በመያኤውም ሆነ በሻዕቢያ) ላይ አይደረግም? አንድ የማስታውሰው ነገር አለ ። አንድ ሪፖርት ሲሠራ ተሳትፌአለሁ ። ሪፖርቱ ታትሞ ለእርዳታ ሰፈሮች ተዳርሷል ። በዚህ በእርዳታ ብዙ ፈረንጅም ተጠቅሞአል ። በስደተኛ ውም ስም ተጠቅሞአል ። በትርቡ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉዳይ ንላፊ ብዙ ሚሊዮን ብር አባክኖ ከሥራው ተመንዶአል ። በእኛ በስደተኞች ስም በመጣው ገንዘብ የሚኖሩበት ቪላ የሚያሽከረክሩት መኪና ልዩ ነው ። በቢሮክራሲያንና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ስም ነው እርዳታው የሚገኘው ።

«የማንበር ረድኤት ትግራይ» ብዙ ጊዜ የእራት ግብዣ ያደርጋል ፡ እኔም እየተጋበዝሁ እገኛለሁ ። የሚጠጣው መጠጥና የሚሠራው አሮስቶ ልዩ ነው ። እርዳታ ሰጪዎቹም ወያኔዎች የሚያቀርቡላቸውን ሪፖርት ይቀበላሉ ። ወፍጮ ተከለን ፡ የውሃ ጉድጓድ አስቆፈርን ፡ የእርሻ መሣሪያዎች ሰጠን ፡ ለገበሬው በሬ ገዛን ፡ እህል ፡ ዘር አደልን ፡ ትምህርት ቤት ከፈትን ይላሉ ። የሴሰ ቲጥር በአስተቲስቲክስ ይቀርባል ። ይህን አስተቲስቲክስ ወንድወሰን የሚባል የወያኔ ትጥረኛ (የአዲስ አበባ ልጅ) ያቀርብላቸዋል ። በአንድ ወቅት ሃያ አምስት ሚሊዮን ይላሉና ከዚያም በላይ ለዚህ አወጣን ብለው ሪፖርት አቅርበዋል ። ፈረንጆች ግድ ስለሌላቸው ሂደው አያረጋግጡም ። አንድ ፈረንጅ የዓፈሙ ትዝ ይለኛል። የራሳቸውን መረጃ ለመሰብሰብና ምርመራ ለማድረግ አያሞክሩም ። በገንዘብ የተያዙ ወሐፊዎች አሉ ። በጋዜጠኛ መልክ የሚመጣም አለ ።

«ትግራይ ኢትዮጵያንስ እንዴሎጂካል ሂስትሪ» የሚባል መጽሐፍ ታትሚል ። እዚያ ውስጥ ፎቶግራፎች አሉ ። የወያኔ መሪዎች ገበሬ መስለው እንዳመረተ ሰው ይቀርባሉ ። ከሩቅ እህል ከማምጣት ገንዘቡን ይዛችሁ ። ከሱዳንም ልናመጣ እንችላለን ስለሚሏቸው በእርዳታ የመጣውን እህል እንደገና ይሸጣሉ ። በትዋቢና በአንተርጅ በሌሎችም የስደተኛ ሰፈሮች የሚደረገው ከዚህ ጋር የተመሳሰለ ነው ። በአጠቃላይ ይህ የእርዳታ ገንዘብ የማን አለብኝነት ስሜት እንዲጠናወታቸው ያደረገና በሚያሳዝንና በሚያንገበግብ ውኔታ ከታሰበለት ዓላማ ውጪ የሞለ ነው። ይህን ማንም ሊያየው የሚችል ነው ።

ብዙ ሰዎችን የሚያሳስተው ደግሞ ለትግራይ ከመጣው የእርዳታ እህልና ገንዘብ የኤርትራ ሰዎችም ተጠቃሚዎች መሆናቸው አለመታወቁ ነው ። ፈረንጅ የኤርትራ ይሁን የትግራይ ተወላጆች ሊያውቅ አይችልም ።

<u>ለቅ ገብረ ዘሩድህን ፡-</u> ለዕርዳታ የመጣውን እህል የወያኔው አባሎች ንጋያ መስለው እየተረቡ ደጋግመው እንደሚሸጡት አንም አቶ መሐመድ የሚል መጠሪያ እንደነበረኝ ከዚህ ተደም ገልጫለሁ ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ነገር ሲነሳ የታመሰኝ ጉዳይ አለ ፡ አንድ ክርስቲ የምትባል በሱዳን የምትኖር እንግሊዛዊት አለች ። በየጊዜው ወደ ትግራይ ትመጣ ለች። በ1975 ላይም ወደ ሶስት ሚሊዮን የሚሆን ገንዘብ የያዙ እርዳታ ሰፈሮች ይዛ መጥታ ነበር ። ለእኔ አስቸኳይ ትእዛዝ ተሰጠኝ «እህል ይደረደርልሃል ፡ ልብስህን ለውጥና ንጋይ መስለህ ሽጥ» የሚል ። ከዚህ ቀደም እንደገለጽሁት መሐመድ ተብየ ፡ የትውልድ አገሬን ተንቤን ፡ ብዙ ለሸጥኩት እህል ሦስት ሚሊዮን ተቀብያለሁ። በ1967 አራት ሚሊዮን ይዘው የመጡ ፈረንጆች ነበሩ ። ከዝዚ ወንዝና በሌሎችም አራት ቦታዎች በሙቱ የሚቆጠር ኩንታል ተደርድሮ ተሸጠላቸው ።

<u>ጥያቄ</u>፡– ድርቅ አለ እየተባለ የተደረደረውን እህል ሲያዩ ከየት መጣ የሚል ጥያቄ አያቀርቡም ?

<u>ሶቶ ገብረመድህን</u>፡– አያቀርቡም ።

<u>ጥያቄ</u>፡– ይህቺ ክርስቲ የምትባል የፍሪላንስ ጋዜጠኛ ወደ ትግራይ ከሚመላለሱት ጋዜጠኞች የመጀመሪያ ሳትሆን አትቀርም ። ከየማን ኪዳኔ (ጀማይካ) ጋር ያላት ግንኙነት ምንድነው?

<u>ሶቶ ሰብርሃም</u>፡– እኔ እምፈራው ክርስቲ ዘሯ ተቆጥሮ የትግራይ ሰው እንዳትሆን ነው ። በጣም ሲበዛ በነገሩ ገብታ የምትዳክር የድርጅት ተቀጣሪ ናት ፡ ቀጥረው ያሠሯታል ። የእሷን ሥራ ሊሠሩ የሚችሉ ብዙ የትግራይ ልጆችም አሉ ። ለምን «ማኅበረ ረድኤት ትግራይ» ተቀጠረች ብዬ ጠየቅሁአት ። ኃይሌ ኪሮስ የሚባል እንግሊዝ አገር የሚኖር የወያኔ ተወካይ ወዳጇ መሆኑን ገለፀችልኝ ።

<u>ሶቶ ገብረ መድኅን</u>፡– በትግራይ ስም የመጣውን እርዳታ እንደት እንደተጫወቱበት ገልጸናል ። የዘረፋ ጉዳይ ቀደም ብሎ ተጠቁሞ ነበርና ወደሱ ልለፍ ። መዝረፍ በ1976 ለመጀመሪያ ጊዜ በወጣው ፖሊሲ ላይ የተቀመጠ ነው ። በተለይ ኮረም በመጀመሪያ ደረጃ ለጥቃት ከተያዙት ቦታዎች ቅድሚያ የተሰጣት ነበረች ። ከዚያ ሌሎች ይቀጥላሉ ። የወያኔ ሠራዊት ሁሉን ነገር ማግኘት አልቻለም ። በኮረም ውስጥ ያለውንና ለእርዳታ የመጣውን እህል መውሰድ አለብን ተብሎ ያላትን ሠራዊት እንቀሳቀሰች ። በኢትዮጵያ ሠራዊት ምላሽ ተሰጣት ፡ ተመታች ። የታሰበውም ሊሆን አልቻለም ። በኢትዮጵያ ውስጥ ለድርቅ ተብሎ የመጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

መድኃኒት ፣ እሀል ወይም ሌላ መዘረፍ አለበት ተብሎ በፖሊሲ ደረጃ ተቀምጦ ነበር ።

ጥያቄ፡- አቶ አብርሃም ስለ ሰፈራ ጠቀስ አድርገዋል ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ከትግራይ አካባቢም ሆነ ከሌሎች በድርቅ ከተጠቁ አካባቢዎች ለም ወደሆኑት ክልሎች በመውሰድ የማስፈር ፖሊሲ አለው ፣ ወያኔውም የሰፈራ ፕሮግራም አለኝ ይላል ። አጠር ያለ መልስ ብትሰጡን ?

ሰቶ አብርሃም፡- በመሠረቱ ጉዳዩን ስናየው ለሰው አስፈላጊ ነገሮች እስከተሟሉለት ድረስ ከተወለደበትና ካደገበት አካባቢ የተሻለ ነገር የለም ። ሰው በአንድ አካባቢ ሲሰፍር አገርንም የመጠበቅ ጉዳይ አለበት ። ድንጋይ አገር አይጠብቅም ። የትግራይ ሰው በትግራይ ውስጥ አቅርቦት ካለና የሚፈለጉ ነገሮች ከተሟሉ፣ ድርቅም ከሌለ ፣ በትግራይ ውስጥ መኖር አለበት ። ለምን ወደ ወለጋ ወደ ኢሉባቦር ይሄዳል? አሁን የሆነው ትግራይ በተለያዩ ጦርነቶች ምክንያት ፣ በነበረው የአዜ ጎይለ ሥላሴ ፖሊሲ የገጠር ልማት ባለመስፋፋቱ በረሃው ከሰሀራ ጀምሮ በትግራይና በኤርትራ በኩል እየሰፋ የመጣ በመሆኑ ትግራይ ውስጥ ምንም ነገር የለም ።

ሰሞኑን አንዳንድ ጓደኞቼ አካባቢያችሁ ሲፈርስ በዚህ በኩል የለማውን እናሳይህ ብለው ሲያሳዩኝ አለቀስሁ ። እዚያ አፍርሰን ጨርሰናል ፣ እዚህ ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው ። ጦርነት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ላይ መንግሥት መሠረተ ልማት (እንፍራስትራክቸር) ሊዘረጋ አይችልም ። ሕዝብ ሱዳን ሄዶ ከሚፈስ ወለጋ ሄዶ ቅጠል ቢበላ ይሻላል ። ብዙ የሚበሉ ስራስሮች አሉ ። ሱዳን ሲሄድ የሚያገኘው አሸዋ ብቻ ነው ። ደግሞ ትግራይ ሰላም አግኝታ ልምላሜዋ ከተመለሰ ከወለጋ ከኢሉባቦር ተመልሶ መግባት ይችላል ። ማንም አትመለስም ብሎ አይከለክለውም ።

ጥያቄ፡- ወደ ሶስት መቶ ሺህ የሚጠጉ የትግራይ ሰዎች ወደ ሱዳን መመሰዳቸው ይነገራል ። በእንቅስቃሴው ጊዜ አቶ ገብረ መድኅን ስለነበሩ ሕዝቡ እንዴት ወደ ሱዳን እንደተጓዘ ሁኔታውን ብትገልጹልን?

ሰቶ ገብረ መድኅን፡- ሕዝቡ በብዛት ተገዶ እንዲሄድ የተደረገው በ1977 ላይ ነው ። ወያኔው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሰፈራ ይቃወማል። ወደሱዳን የሚደረገውን ስደት እንደ ትክክለኛ ይቆጥረዋል ። አብርሃም ገልጾልል ። በሀገር ውስጥ መኖር ይሻላል በውጭ አገር? እኔ አገሬ ብዬ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደመጣው አገሬን እመርጣለሁ ። ስዳን ውስጥ ብንኮሳኮስ ለእኔ የሚሆን ደመወዝና ሥራ አላጣም ነበር ። ግን ስዳን ውስጥ ከሚገኘው «ሀብት» በላይ ያሻልኛል ብየ ነው የመጣሁት ። ሰው በሠላሩ በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ ተጉዶ አይገኝም ።

ነገሩ እንደ ፖለቲ ነው የተቀመጠው ። ጠቅላላ በትግራይ ውስጥ ከዛድ ድረስ ሰለገባ በትግራይ ያሉ ሰዎች ሱዳን ሂደው መሰፈር አለባቸው ተባለ። ሰፈራ የሚባለውም በጎ ዎች የጎደሉቱ ናቸው ። እንደኛው ሰፈሞ ሌላው ተዋሳ ሌላው እንጉርጅ ነው ። ሌሎችም አሉ ። እነዚህ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ለመሣባት ፍላጐት ነበራቸው ። ግን ወደኋላ ግንኙውም ወደ ኢትዮጵያ የሚሄድ የትግራይ ተወላጅ እንዲያዝና ፍርዱን እንዲያገኝ መመሪያ አውጥቷል ። ወደየከተሞቹ የሚወስዱ መንገዶች ተዘግተው ነበር ። ወደ ከተሞች ሲገባ መንገድ ላይ የሚጋደለው ከንቤተሰቡ ተደብቶ ደጋሰራል ። በመጨረሻ ግን አገራችን መምጣ አለብን ብለው የተመለሱ ብዙዎች ናቸው ።

<u>ጥያቄ</u>፡ በ1969 «ሻዕቢያ» በትግራይ ውስጥ ማዛት አለኝ ብሎ ተረበው ጥያቄ ምክንያት ወደኋላና «ሻዕቢያ» ቅራኔ ፈጥረው ነበር ይባላል ፡ እንዴት ነው? በድርጅቱ አባትና ልጅ ሆነው እያለ እንዴት ይህን የመሰለ ቅራኔ ውስጥ ሊገቡ ቻሉ?

<u>ለጥ ገብረ ዘዮሐንስ</u>፡ አውን የተባለው «ሻዕቢያ» በ1969 የመሬት ይገባኛል ጥያቄ አቅርቧል ። ይህንን «ጅብሃም» አንስቷል ። «ጅብሃ» ከወያኔ ጋር በነበረው ቅራኔ መሰረት ስለተመታ ብዙም አልነገሩበትም ። ጥያቄው የተነሳው በ1969 ላይ ነው ። በትግራይ ውስጥ ከባድም ጅምር ያለውን ያይዛል ። መሃ ላይ ስትመጣ ያጣም አዲ ሠራይ ፡ አዲ ነበረኢ ፡ አዲ ቋላ ፡ አዲ ደውሮን ያቅፋል ። እነዚህ በሽሬ አውራጃ የሚገኙ መሬታምች ናቸው ። በመሉ ከ፡ ገጠሞች ናቸው ። ቀዮሉ የጭላ አለ ። ከእሱ አልፎ ደግሞ እሳዬ የሚባል አንድ ወረዳ አለ ። በአንጠጅ ወረዳ ውስጥ አለ ። እነዚህ ወረዳምች አድሞ አውራጃ ውስጥ ናቸው ። እሱን አልፎ ወደ ዛላ አምበላ ይሄዳል ። እሱ ደግሞ በአንጫ አውራጃ ውስጥ የሚገኝ ነው ። ሁሉም የተያያዙ ናቸው ። እነዚህ የአርትራ ናቸው ይገዙናል የሚል ጥያቄ በ«ሻዕቢያ» ቀረበ ። በመሃኔ የተሰጠው

t.me/OLDBOOKSPDF

መልስ ምን ነበር? እዚያው ቁሜ ስነበር ስለ ሀገሬ መመስከር ግድ ይሆንብኛል ። በዚያን ጊዜ ለድርድር የተጠሩት ዓባይ ፀሐዬና መለስ ዜናዊ ናቸው ። «እርግጥ ነው ። ይህን ቦታ በታሪክ ጥናት የኤርትራ አካል መሆኑን ደርሰንበታል» አሉ ። ከታሪክ አግኝን ይላሉ እንጂ የመረጃ ምንጫቸውን ይፋ አያደርጉም ። ስምምነቱ በዚህ ቆመ ። ግን ቦታውን «ሻዕቢያ» እንዴት ትረከብ ወይም ትተበል ተባለ ። ለዚህ የተሰጠው መልስ «አሁን ይህን መሬት ቆርሰን ለሻዕቢያ በምንሰጥበት ጊዜ በጠቅላላ የትግራይ ሕዝብ በራሳችን ላይ ስለሚነሳ ይህን ነገር ተፈራርመን እንቅይ» ተባለ ። ከወያኔው ዓባይ ፀሐዬና መለስ ዜናዊ ከ«ሻዕቢያ» ወዲ ኡፍራምና ጴጥሮስ ሰሎሞን ተፈራረሙ ።

ከላይ የዘረዘርሁት የትግራይ ክልል የኤርትራ ነው የሚለው ውል ከተፈረመ በኋላ የትግራይ ሕዝብ እንዳያመታን ጉዳዩ መገለፅ የለበትም ፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከወደቀ በኋላ ፡ ኤርትራም ከአማራው መንግሥት ቅኝግዛት ነፃ ከወጣች በኋላ ፡ ትግራይም የራሷን መንግሥት ስትመሠርት ጥያቄው በተግባር ይተረጐማል የሚል ዶኩሜንት ተይዟል ። ይህን ውል የፈረሙት እነመለስ ዜናዊ ደግሞ ከየት እንደመጡ በስፋት ተነጋግረናል። ተራው ወያኔ ግን ይህን ጉዳይ አያውቅም ። ነገሩ ጥብቅ ምሥጢር ተብሎ በዶኩሜንት የተያዘ ነውና «ከነዓንት» በኋላ ይከፋፈሉታል ማለት ነው ። ይህ ፀረ ሕዝብ ቡድን በትግራይ ሕዝብ እስከዚህ ነው የሚጫወተው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ከወያኔው ስም ሌላ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተለያዩ ስሞችን እንሰማለን ፡ ለምሳሌም ፡ «ኢማሌን» ፡ «ኢሕዴን» «ኢሕአዲግ ወዘተ የእነዚህ ስሞች ምንጭ ምንድን ነው? ሕዝቡስ እንዴት ነው የሚመለከታቸው?

<u>ለብርሃም</u>፡ ሰሞኑን የእነሱን ሬዲዮ ሳዳምጥ «ይህን ያህል ጠመንጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት አድርገናል» ሲል ሰምቻለሁ ። እነዚህ ወያኔዎች ከዚህ የሚሰርቋቸውን ቃላት መልሰው የሚናገሩ ናቸው ። "መልከጥፉን በስም ይደግፉ" እንዲሉ ማንም ድርጅት ተነሥቶ እንዲህ ነኝ ሊል ይችላል ። ዋና መለያው ፕሮግራሙና ተግባሩ ነው ። ወያኔዎች «ኢሕዴን»ን ፈጥረዋል ። «ኢሕዴን» ወያኔውን አስመስሎ የተሠራ ማኅተም ነው ማለት ይቻላል ። «ኢሕዴን» በራሱ ፕሮግራም አደንቀሳቀስም ። የ«ሻዕቢያ» ፕሮግራም የ«ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ» ፕሮግራም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖ እንደወጣ ሁሉ የ«አሕዲን» ደግሞ እንዲሁ የመጀመሪያው ነው ። በእግርኛ ከመጻፉ በስተቀር ። እሁን «አሕዲን»ን ስለፈጠሩ ለአትዮጵያ ጥቅም ቆመዋል ማለት አይቻልም ። ማንም ሰው ኮሮጌዎችን ማንበብ ይችላል ። እጠቅሳለሁ «...ሙቱን ብሔሮችና ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን ፡ እስከመገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት ማረጋገጥ» ይላል። አትዮጵያዊ ነኝ ብዙ «አሕዲን» በኮሮጌዎቹ የሚለው ፡ የማንኛውም ብሔረሰብ ማለትም የኮራጌ ብሔረሰብ ፡ የአፋር ብሔረሰብ ፡ የጊሚራ ብሔረሰብ መሆኑ እየኮነነ የራሱን መንግሥት ይመሥርት ፡ የራሱ ሰንደቅ ዓላማ ይኑረው ነው ። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ወይም እንደሚኖሌት አላወቅም ።

ሙቱን ብሔሮችና ብሔረሰቦች ለሚደርስባቸው ብሔራዊ ጭቆና ፖለቲካዊና ዲሞክራሲያዊ መፍትሔ የመስጠት ፡ የማንኛውም ሙቱን ብሔርና ብሔረሰብ ሕዝብ ራሱን ተከላ በሚችልም ኮንዶል ሳይሆን በራሱ መሳኘት ይጠቅመኛል የሚለውን እንዲወስን ማድረግ ፡ ብሎንም የራሱን ብሔራዊ መንግሥት ለመመሥረትም ሆነ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በእንድነት የመኖር መብቱን ማወቅ» ይላል ። «የራሱን መንግሥት ማቆም» ብቸር ኤል ኤፍና ሻዕቢያም» የሚሉት ነው ። ይህ «አሕዲን»ን አትዮጵያዊ ያደርገዋል ? ሊሆን አይችልም ። እንድ ሰው ብንሥት አትዮጵያዊ ሊሆን አያችልም ። አትዮጵያዊ የሚያደርገው መለኪያዎች አሉ። ዜግነት ፡ የመታወቂያ ወረቀት ጉዳይም አይደለም ።

ወያኔው የሙሎ ጉዳይ ፖሊሲ ከሚለው ደግሞ ልዩ ቀሰ፡ «የኤርትራ ሕዝቦችን የነፃነት ትግል መደገፍና የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን እስከ ነፃነት ድረስ ያላቸውን መብት ማረጋገጥ» ይላል ፡ ይህ አሥራ አራተኛው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ «ሀ» ላይ ይገኛል ። «ከኢትዮጵያ እስከመገንጠል ድረስ» እያለ «አሕዲን» አትዮጵያዊ ሊሆን አይችልም ። እኛ ይኸው የምናውቀውን እያወናገርን ነው ፡ ለሚጠይቁንም ሰምች መልስ እየሰጠን ነው ። እንድ የታሪክ ጸሐፊ እንዴት ጠፋ ? እዚህ ወጥ መናገር አይችልም ? ኢትዮጵያ ታሪኳ እንዴት ነው ? ሕዝቡ ራሱ ታሪክን አገላብጦ ማወቅ አለበት ።

<u>ጥያቄ</u>፡ የ«ማሌሌት»ን የወጭ ጉዳይ ፖሊሲ ይዘት ብታብራራልን? <u>ለብርሃይ</u> «የማሌሌት» (የፓርቲው) ኮሮጌም ማዕድና መደብ ምልክት ያለው ነው ። የግንባሩ ማለትም «የሕወሓት» ኮሮጌም መሣሪያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ አማርኛ ቢተረጉም ልምንም እንኳ በኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች የረዥም ዘመን ታሪካዊ ሙተሳሰር ያላቸው ቢመስልም የአሁኗ ኢትዮጵያ አዲ ምኒልክ የፈጠሯት አገር ናት» ይላል ። በገጽ ስድስት ደግሞ «የአማራ ገዥ መደብ የትግራይን ሕዝብ ጨቁኖና አስርቦ የመግዛት ፖሊሲ ከምኒልክ ጀምሮ አውጥቶ ነበር» ሲል ይገልጸዋል ።

<u>ጥያቄ</u>፡ ከምኒልክ በኋላ እንጂ ከዚያ በፊት አንድ ኢትዮጵያ የምትባል የለችም ማለታቸውን ገልጠውናል ። ወያኔዎች ታሪካችንን ሲክዱ መጀመሪያ የሚያደርጉት ሰንደቅ ዓላማችንን ነው ። የእነሱ ሰንደቅ ዓላማ ምንድ ነው ?

<u>አብርሃም</u>፡ አስካሁን ስለሰንደቅ ዓላማ በውይይታችን አልተነሣም፣ የነሮግራሙን ጉዳይ ልጨርስና ወደ ጥያቄው እመለሳለሁ ። «የትግራይ ሕዝብ ብሔራዊ ጭቆናውን የሚከላከልለትና ጥቅሙን የሚያሟላለት ፣ በሰፊው ሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲመሠረት ስለሆነ ፣ ይህ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብቱ ተጠቅሞ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለመመሥረት መታገል አለበት» ይላል። ይህ የሚያሻማና ግልጽ ነው ። «የትግራይን ሪፐብሊክ ለመመሥረት ነው ።» የጠቀስሁት የግንባሩ ፕሮግራም ነው ። ግንባሩና ፓርቲው ደግሞ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ።

የነሮግራሙ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አንቀጽ አሥራ ሰባት ምን ይላል ? «ሁሉንም ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ኃይሎችን መደገፍ» ይልና «የኤርትራ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ ለመወሰን በሚያደርገው ትግል ነፃነቱን እስኪያገኝ ድረስ መደገፍ» ይልና በቀጥታ ወደ ናሚቢያ ፣ አዛኒያና ምዕራብ ሰሐራ ይሔዳል ። «ከኤርትራ ጋር አገናኝቶ ለዚሁ ሁሉ ድጋፍ መስጠት» ይላል ። የኤርትራንም ጉዳይ እንደ ውጭ ጉዳይ አይቶ ከናሚቢያ ጐን ነው ያስቀመጠው ። ይህንን የሚለው ግንባሩ ነው ፣ ፓርቲውም ቢሆን የሚለው እንደዚሁ ነው ።

<u>ገብረ መድኅን</u>፡ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲው አብርሃም እንደገለጸው ነው ። የአልባኒያ ኮሚኒዝምን እናመጣለን የሚል ተጠቅሶ ነበር ። ይህ ትክክል ነው ። ወያኔ የአልባኒያን ኮሚኒዝም ትደግፋለች ። የአልባኒያ ኮሚኒዝም ደግሞ ምን እንደሆነ ሁላችሁም ታውቃላችሁ ። ከማንም የዓለም ኅብረተሰብ ጋር የማይገናኝ ዝጣ ፖሊሲ ነው ። ወያኔ በስፋት

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትንቀሳቀሰው የአልባኒያን ኮሚኒዝም ለማስፈን ነው ። በትግራይ የሚመሠረተውን «መንግሥት» በዚህ መንገድ ማስተካከል ። ከአልባኒያ ግንኙነት ለማድረግ ወያኔ ብዙ ጊዜ ሞክራለች ። «እኛ የስታሊንን ርዕዮተዓለም የምንከተል ነን ፡ ስታሊን ያለውን ሁሉ እንተበላለን ፡ ተግባራዊም እናደርጋለን ፡ ከእናንተም ጋር በአንድ መሥመር እንገናኛለን ። ዓላማችን ኮሚኒዝም ነው ። ከእናንተ ጋር ጉብረት ያስፈልገናል ፡ ቀጥተኛ ግንኙነት ከአልባኒያ ጋር በማድረግ ፡ በእውኑ መቅት አልባኒያ በቴክኒዮሎጂ ያበልጥ እያደገች ስለሆነ ከዚያ እናመጣለን» ያላለ ወያኔም ።

«ለኢትዮጵያ እኩልነት እናመጣለን» ስለምትለው ውሸት መሆኑን ከፕሮግራሙ እየጠቀስን በማስረጃ ተጠቅመን አስረድተናል ። «ኢሕዴን» የተባለው የወያኔ የበኩር ልጅ ራሱ የሚከተለው ያንኑ የአልባኒያን ኮሚኒዝም ነው ። እንደሚለት ሆኖ ፡ የአልባኒያ ኮሚኒዝም በጎባ ያሀች አገር አትኖርም ማለት ነው ።

<u>ጥያቄ</u>፡- ባወጡት ፕሮግራምና በራዲዮ በሚያስራጩትም ልፈፋ የምሥራቁንም ፡ የምዕራቡንም እንደማይደግፉ ነው የሚገልጹት ። ዓለም ደግሞ በሁለት ካምፖች የተከፈለች ናት ። ይህን እንዴት ታዩታላችሁ?

<u>ለብርሃም</u> እንዚህ ሰዎች ኮሚኒስቶች ስለሆኑ ከምዕራቡ ዓለም መጣባት አይኖራቸውም ። በሶቪየት ጉብረት እንዳያደገፉ ደግሞ ሶቪየት ጉብረት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ግንኙነት አላት ። ከአልባኒያ ኢንዱስትሪ መጥቶ ትግራይ ሊቋቋም ፣ እብደት ነው ። ለመቃወም ብቻ ከሆነ ጥቂቶን ነጭ ብሎ መቃወም ይቻላል ። አልባኒያ ማለት ደግሞ ፡ ያልታጠበ ቤተክርስቲያን ፡ የተዘጋ ቤት ማለት ነው ።

ቀደም ሲል የተነሣ ነባድ ጥያቄ አለ ። የሰንደት ዓላማ ጉዳይ ምንም ጭቅጭቅ የሌለው የማያነታርክን ነው ። «አጼ ምኒልክ ኢትዮጵያን ከምናምኑ ሐገራልተው አቡክተው ሠሩ» ብለዋል ። ባንዲራ አጼ ምኒልክ ሠሩ የሚል ግን የለም ። ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ቡድን ወይም ሰው በዚህ ሰንደት ዓላማ ፡ በዚህ ዓርማ ማመን ይኖርበታል ። አሁን ትግራይ ውስጥ ያለው ሕዝብና በውጭ አገር ያለው ሕዝብ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ሰንደት ዓላማ ሲያውለበልቡ አይቻለሁ የሚል የለም ። የትግራይ ወያኔ የኢትዮጵያን ሰንደት ዓላማ እንዳርማ ያጠቀማል የሚል ካለ ራሱ በራሱ ፈርጀ ገዘያ ላይ ወጥቼ ምላሴን አስቅርጣለሁ ። ኮክብ ያለበት የራሳቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

«ባንዴራ» አላቸው ። የትግራይ ካርታም አላቸው ።

በትግራይና በኤርትራ አንድ ባህል አለ ፡ ሰው ሲሞት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ፈላውን ቀድሞ ይሸፍናል ፡ ወይም አስከሬኑ ይጠቀለልበታል ። ይህ ባህል በኤርትራ «ሻዕቢያ» በሚንቀሳቀስበት አካባቢ ቀድሞ ብሎ ነው የተከለከለው ። በእውኑ መቅትም በትግራይ ሰንደቅ ዓላማ አጅበት የሚሄድ አስከሬን የለም ። ወያኔው ከልክሏል ። ምንም ተወዳጅ የሌለው ጥፋትና ማወናበድ ነው የሚሠራት ።

ጥያቄ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ አስራአምስት የአብዮት ዓመታት ያከናወናቸው ተግባራት በርካታ ናቸው ። ብዙ ነገሮች ይባላሉ ። ለመሆኑ በርሃ ያለው ሠራዊት ወይም እናንተ አመራር ላይ ያላችሁት የእኛን ማለትም የኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያዎችን ትሰማላችሁ ወይ?

ገብረመድህን ፡- በርሃ ያለው የወያኔ ሠራዊት የኢትዮጵያን ራዲዮ አይሰማም ። ይከለከላል ። ለምን ነው የሚከለከለው? በአገራቱ ስለሚካሄዱ የግንባታ ጥረት ከሰማ እኛን ምን ሠራችሁ ብሎ ይጠይቃል ፡ ጥሎንም ይሄዳል የሚል ስጋት ስለአለ የተከለከለ ነው ። ይህ ሠራዊቱን በሚመለከት ነው ። ሠራዊቱ የሚሰማው የ«ሻዕቢያ» ን ራዲዮ ጣቢያና የራሱ የወያኔውን ነው ። ከፍተኛ ቦታ ላይ ወደነበርነው ስትመጣ ደግሞ በየግላችን ራዲዮ አለን ። ቀስ ብለን ከፍተን እናዳምጣለን ። በአመራር ላይ ያሉትም መልስ ለመስጠት ያዳምጣሉ ። በተረፈ ለሌላው የተከለከለ ነው ።

አብርሃም፡- ካርቱም ውስጥ ታዲስ ወጋዬ የሚባል አንድ ጓደኛ አለኝ ። ይህ ሰው አገር ውስጥ ቆይቶ ወደ ወያኔው ከጣባ በኋላ የኢትዮጵያን ሬዲዮ ይከታተል ስለነበረ አስረው ፈቱት ። በወያኔው ውስጥ በ«ማህበረ ረድኤት ትግራይ» ውስጥ ይሰራ ነበር ። ፍስሐ የሚባል የወያኔው ደጋፊ ደግሞ ውጭ ጉዳይ ውስጥ የሚሠራ አለ ። ራዲዮ የሚያዳምጠው ገና የደርግ ስሜት ስላለተለው ነው እያለ ታዲስን ይተቹው ነበር ። ሕዝቡ ሁለት ነገር መስማት ቢችል ኖሮ ጥሩ ነበር ፡ እኔ የሚለውን ፡ እኛም ስንታወም የምንለውን ፡ ቢሰማ ጥሩ ነበር ። ሕዝቡ በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንደሚመለከት የጋሪ ፈረስ ሆኗል ። የወያኔ ራዲዮ የሚለው ሲደጋገምበት እውነት ይመስለዋል ። ሌላ ሚዛናዊ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችለው ሁኔታ የለም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጥያቄ፡ የወያኔ መሪዎች ከተራው ሠራዊት ጋር አንጻፅራችሁ ስታዩት ኑሮአቸው ምን ይመስላል?

ገብረመድህን፡ በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ የወያኔ መሪዎች ያላቸው ምቾት ከፍተኛ ነው ። በጣም ተንደላቀው ነው የሚኖሩት ፡ የሚበሉት ምግብ ከውጭ አገር የሚመጣ ነው ። ውስኪና በቅርቡ የታሸገ ቢራ ነው የሚጠጡት ። ለዚህ ገንዘቡ ከየት ይመጣል? ልትሉት ትችላላችሁ ። መሪዎቹ የሚንደላቀቁበት ገንዘብ የሚገኘው በትግራይ ሕዝብ ስም ከሚሰበሰቡት የድርቅ እርዳታ ነው ። በመሪዎቹና በሠራዊቱ መካከል ያለው የኑሮ ልዩነት የሰማይና የምድር ያህል ነው ። አንድ ጊዜ ስብሐት ነጋ «የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች እንዳባይ ወሐዬ የምግብ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል ፡ በአስቸኳይ አዲስ የታሸገ ምግብ ከሱዳን እንዲመጣ አድርግ» አለኝ ። ስብሃት ነጋ የማዕከላዊ ኮሚቴ የፖለቲካ ቢሮ አባል ነው። እሺ ብዬ ደብዳቤ ጻፍሁ ። የታሸገ የቅርቅር ምግብ ፡ የምግብ ሳሕን፡ ብርድ ልብስ ፡ በአየር የሚነሱ ፍራሽ መጣላቸው ። ሌላው ያህን አያጎኝም ።

ለብረሃየ፡ አብያተ ክርስቲያን የሚባል በካርቱም የፈጣነበረ ረድኤት ትግራይ» ተጠራ አለ ፡ የእሱ ሚስት ወለደች ። ከእንግለዝ አገር ሁለት ሙያ የሚሠጎ ፈለጊ ሙያ ድርጅት» ና የሕፃን መወጫጃ ፈጠረች ነው የመጣው ። የመለስ ዜናዊ ሚስት የደጃ ታዬ እህት አሜሪካን ለመኖር ሲሄዱ በአንድ ላንድ ክራዘር አጀቧ አድርጋ ነው የሸኘቻቸው ። ሴትየዋ የሚኖሩበት ዶም የሚባል ቦታ አለ ። እዚያ ጎርቲ ተደግሶ ነው የተጨፈረው ። የመለስ ሚስት የአንድ ማኮሚያ ቤት ሥራ አስኪያጅ ናት ። የወያኔው መሪዎች ወደ ሜካ ሲሄዱ ለማስመሰል ጉማ ጫማ ያደርጋሉ ። ከተማ ሲገቡ ደግሞ የሚጠጡት ውስኪ ነው ።

ጥያቄ፡ ወያኔው ሰለሰላም እየለፈለፈ መርኃቱን ያፋፍማል ፡ ለመሆኑ የቡድኑ አባላት ስለ ሰላም ተመያይተው ያውቃሉ?

ገብረመድህን፡ ተነስቶ አያውቅም ። የማያነሳበት ምክንያት ደግሞ የቡድኑ አመራር አባላት «የአማራን ጎሸ ብሔር እስክ መጨረሻ ካልደመሰስን ሰላም አይኖርም» የሚል አቋም ስላላቸው ነው። በወያኔ ዘንድ ስለ ሰላም ምንም ተነስቶ ስለማያውቅ ሁሉም ያለው አመለካከት የመርኃት ብቻ ነው ። መርኃት ከፍተኑን «የአማራን ጎሸ ብሔር መንግሥት

t.me/OLDBOOKSPDF

መቸ እናጠፋለን» ካልሆነ በስተቀር ሰላም ተነስቶ አያውቅም ።

<u>ሰብርሃም</u>፡ በውነቱ ሰላም በጣም አስፈላጊ መሆኑን በዚህ አጭር ጊዜ ከሰጠናቸው መግለጫዎች አንባር በየመንገዱ የሚያገኙን ሰዎች የሚሰጡት ድጋፍ ከምንገምተው በላይ ነው ። በአሁኑ ሰዓት ሰላም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ፡ በተለይም በሁለቱ ራስ ገዝ አካባቢዎች በትግራይና በኤርትራ ሕዝብ ዘንድ ምን ያህል አንገብጋቢ ጉዳይ እንደሆነ ተረድተናል ። የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ እኛ ይህንን መግለጫ ስለሰጠንና ወቅቱም ስለፈቀደ ብዙ ሰው ያነጋግረናል ። የማናውቀው ሰው ሁሉ በየመንገዱ እየጠራ ይጠይቀናል ። በተለይ ለሰላሙ ጉዳይ ትልቅ ተስፋ በተደረገበት ሰዓት እንዲህ ዓይነት ጠርነት መከፈቱ ምን ያህል ጉጂ እንደሆነ የሚገልፁልን ኢትዮጵያ አገራቸውን የሚወዱ ብዙ ናቸው ። እነዚህ ሰዎች የተነሱበት ዓላማ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጉዳይ ለማስፈጸም እስካልሆነ ድረስ ሰላም በሚገር ተጠቅልሎ ቢሰጣቸው የሚዋጥላቸው አይደለም ።

ሰንድ አስፈላጊ ነው ። አንድ ነገር ከምንፈልጉ ሲቀርብ አሳማኝ ይሆናል ። «የወያኔውና የሕዝባዊ ግንባር ሐርነት ኤርትራ ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ የጋራ መግለጫ» የሚል ሰንድ እኔ ዘንድ አለ ። የወጣው ሰኔ 1/1980 ነው ። መግቢያ አለው ። በዛ ያሉ ጉዳዮችን ያካተተ ነው ። ዲሞክራሲያዊ አብዮትን በሚመለከት ፡ የሶቪዬት ጎበረትን በሚመለከት፡ የኤርትራን ጥያቄ በሚመለከት ፡ የኤርትራና የኢትዮጵያን ሕዝቦች ትግል መሠረታዊ ዝምድና በሚመለከት ፡ በሚሉ አርእስቶች የተከፋፈሉ ጉዳዮችን ይዘአል ። አውን ለዚህ ጥያቄ ተገቢ ማስረጃ ለመስጠት የሚያበቃን አርእስት የኤርትራን ጥያቄ በሚመለከት የሚለው ነው ።

ይህን እንዳለ እጠቅሰዋለው «የኤርትራ ጥያቄ በታሪክም ሆነ በፓለቲካ ፡ በኢኮኖሚያዊም ሆነ በሕጋዊ ማስረጃዎች ፡ የቅኝ ግዛት ጥያቄ በመሆኑ ለጥያቄው ብቸኛ መፍትሔ ሕዝቡ በራሱ ነፃ ውሳኔ ፡ በሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ መንገድ እድሉን እንዲወስን ማድረግ መሆኑን ያምናሉ ። (ሁለቱ ድርጅቶች ማለት ነው) ይህ መብት ሊረጋገጥ የሚችለው ሰፊው የኤርትራ ሕዝብ በሚያደርገው በማያታረት ወረ ትኝ አገዛዝ ግጭሚያ እንደሚሆንና ፡ ለሰላማዊ መፍትሔ በሙያት ለመርኑቱ አልባት ሊያመጣ የሚችለው ጠላት ሽንፈቱ ተረጋግጦ ሲቀበል መሆኑን ያምናሉ ። ከጠላት ሽንፈት በፊት ከጠላት ጋር የሚደረግ ሙያት ደግሞ ጠላትን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለማጋለጥ በሚያመች ሁኔታ እንደየሁኔታው እየተመዘነ በታወጀ ቁጥር ሲደረግ እንደሚገባ ያምናሉ» ይላል ። ይህ «ሻዕቢያና መያኔ» ያወጡት የጋራ መግለጫ ነው ።

ከዚህ አንድ ዋና ነገር እንውሰድ ። «ከጠላት ሽንፈት በፊት ከጠላት ጋር የሚደረግ ውይይት ያጣም ጠላትን ለማጋለጥ በሚያመች ሁኔታ እንደየ ሁኔታው እየተመዘነ በታወጀ ቁጥር ሲደረግ እንደሚገባው ያምናሉ» ሲል ምን ማለቱ ነው? ጠላት የማይሸነፍ ከሆነ (ጠላት ማለት የኢትዮጵያ መንግሥት ነው) ለሰላም አልቆሙም ፡ ዐረ ሰላም ናቸው እንዳይባሉ ይህንን ሲያረጋግጥ በሚችል ሁኔታ ሰላም ፈላጊ መስለው ይቁ ፡ ሉ ማለት ነው ። በ1980 ሰኔ ወር ያወጡት መግለጫ ያረጋገጠው ኦነት ቢኖር በአትላንታ ያደረጉትን ነው ። የኢትዮጵያ መንግሥት መልዕክተኞችን ላከ ። የ«ሻዕቢያ» መልዕክተኞችም እጃቸውን ለሰላም የዘረጉ መስለው ሄዱ ። የሰላሙ ጉዳይ በዚህ ላይ እያለ (መያኔ ሙቸም ሻዕቢያ መሆኑን ያጋግመን አሳያተናል) የ«ሻዕቢያ» ወኪሎች በትግራይ አሙራባች አካባቢዎች ላይ ጦርነት ከፈቱ ።

ብዙ ሰው ስለሰላም ይናገራል ። የትግራይ ሰዎች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የውስጥ ችግሩ በሰላምና በውይይት እንዲፈታ ይጠይቃሉ ። የሕዝብ መበታተንን ስለሚቀንስ እኔም እጠይቃለሁ ። እኔም ለትግራይ ሕዝብ ጥቅም መብቱ እንዲከበር የቆምሁ ነኝ ። ይህ ደግሞ በጠበንጃ አይደለም ። የርእዮተ ዓለም ልዩነት አለመኖሩን አስገንዝበናል ። በጦርነቱ የሚሞተው መለስ ዜናዊ አይደለም ። የሚሞተው ደሀው ነው ። እንሱን አይነካቸውም ። ሰላም ትክክለኛ መፍትሔ ነው ፡ እነሱ ግን ለሰላም የቆሙ አይደሉም ።

<u>ጥያቄ</u>፡- መያኔው ምን ዓይነት ሥርዓት እመሠርታለሁ ይላል? ራዲዮናቸውን ስንሰማ አብዮት አካሂዳለሁ ይላል ፡ ራዲዮ ጣቢያቸው ራሱ «የትግራይ አብዮት ድምፅ» ነው የሚለው ። ምን ዓይነት ርእዮተ ዓለም ነው የሚከተለው?

<u>ገብረመድህን</u>፡- ከዚህ በፊት የምገልጻቸው አሉኝ ። ርእዮተ ዓለሙን ለአብርሃም እተውለታለሁ ። መያኔው በሚደርስበት አካባቢ ሶሲሲ አለው ። አንደኛ የመንግሥትን ፡ ሁለተኛ የማኅበራትን ንብረት ያፈርሳል ፡ ይዘርፋል ፡ ይወስዳል ፡ ሶስተኛ በየአካባቢው የተደራጁ ማኅበራትን ያበታትናል ፡ አራተኛ በማኅበሩ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎችን

t.me/OLDBOOKSPDF

ከያዘ በኋላ ያስራል ፡ እስከማድያም ድረስ ይሄዳል ። ይህ በፖሊሲ ቀርጻ ያስተመጠው ነው ። ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ የራሱን ማኅበራት ያቋቁማል ። የገበሬ ፡ የወጣት ማኅበራትና ሌሎችንም ለሱ በሚጠቅም መልክ ያደራጃል ። እነዚህ ደግሞ ለእሱ ታማኝ ሆነው መረጃ የሚያቀብሉ ናቸው ።

አብርሃም፡ ሁለት የፖለቲካ ድርጅቶች በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ መስመር ሊኖራቸው ይችላል ። በነዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚካሄደው እንቅስቃሴ ለሕዝብ እስከሆነ ድረስ ሕዝቡ የተሻለውን መምረጥ መቻል አለበት ። ሕዝብ ደግሞ የመናገር ፡ ሃሳብን የመግለፅ ፡ የመቀበልወይምያለመቀበልመብትሊኖረው ያስፈልጋል ። በትግርኛ አንድ ተረት አለ ፈሙሽራውን ሳይዙ ሚዜ ያማርጣሉ» የሚል ። እነዚህ ሰዎችና ምንም ነገር ሳይኖራቸው ብዙ ጽፈዋል ። እስካሁን በሰጠናቸው መግለጫዎች በፖለቲካና አልፎ አልፎም በማህበራዊ ፖሊሲዎቻቸው ላይ እንጅ በኢኮኖሚ ፖሊሲያቸው እጅግም አልነባንም ።

ክፍል ሁለት ፡ የግንባሩ ፕሮግራም አንቀጽ አምስት ፡ ንዑስ አንቀጽ ፡ «ለ» ምን ይላል «የወጪና የገቢ ንግድ ባንኮች ፡ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ፡ ሌሎች የፋንዘብ ተቋሞች ፡ ሠቴሎች ፡ እንዱስትሪዎች ፡ የመገናኛና የመጓጓዣ ተቋሞች በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ» ይላል ። ምን አዲስ ነገር አመጣ! አሁን ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፡ የኢትዮጵያ የመድን ድርጅት ፡ የመገናኛና የመጓጓዣ ተቋሞች የሕዝብ ሊሆኑ ነው ማለት ነው ። እንዲያውም ይህ መንግሥት ያልወረሳቸው የመጓጓዣ ተሽከርካሪዎች አሉ ። ያንንም ጨምረው ነው እነሱ የመንግሥት የሚያደርጉት? ምንድነው አዲስ ነገር ይዘውልን የመጡት? ከሶቪዬት ኅብረትም ሆነ ከምዕራባውያን ዘንድ ሊጠጉ አልቻሉም ። እነሱ ደግሞ ከእኛ በላይ አብዮተኛ የለም ባዮች ናቸው ። ሶቪዬት ኅብረትን ያወገዙ ፡ የምስራቅ አውሮፓ ኮሚኒስት አገሮችን ያወገዙና የቢኮን ፡ የዐፄን ኮሚኒስቶች እኛ ብቻ ነን ባዮች ፡ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አውጋዦች ናቸው ። ይህ አቋማቸው ሲመረመር ኤርትራን ከማስገንጠል ሌላ ዓላማ እንደሌላቸው ያስገነዝባል ። ከዚህ የተለየ ዓላማ ካላቸው እኔ አንተን እሰማለሁ ። አዲስ ነገር ይዘው ከመጡ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያንገሩት ፡ እኛ ደግሞ ለነዮቻቸውን ይዘን እንተርባለን ።

ጥያቄ፡ የወያኔ መሪዎች እርዳታ ከሚያደርጉላቸው ድርጅቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

ከባድ ማሽነሪዎችን ፡ አልፎ ተርፎም በትግራይ አካባቢ የማያገለግሉ የትንሽት እቃዎችን ጭምር እንደሚያጓጉና እነሱም ያጎጉትን ርዳታ እንደሚሸጡ ይነገራል ። ከዚህም ያካበቱት ንብረት እንዳለም ይነገራል ። ይህን ብታብራሩልን?

<u>አብርሃም</u>፡- ተደም ብለንም ጠቅሰንዋል ፡ ዋናው ነገር ግን መያኤውም ሆነ በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በሙሉ ድርቅ ባይኖር ኖሮ እስከዛሬ ዕድሜአቸው ያጥር ነበር ። ገዳራፍ አንድ ትልቅ ጋራዥ አላቸው ። የሱዳን ከፍተኛ ባለሥልጣን መኪናዎችና የሱዳን ጦር ሠራዊት ተሽከረካሪዎች ሳይቀሩ የሚጠገንበት ነው ። በርዳታ ስም ነው ጋራዡ የተሠራው ። ፈረንጆቹም በጥቅም የተያዙ ናቸው ። ወንድሞቻችን የምንላቸው የሰፈቁን ፈረንጅ ቢሰርቀን ደግሞ አያስደንቅም ። የምትፈልጉትን አጥንታችሁ አቅርቡ ይላሉ ። የተለያዩ ሰዎች አሉአቸው ። በሱዳን ውስጥ ተፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ገብያ ገብተው ያጠናሉ ። ትግራይ ውስጥ ገብተው ሊሠሩ የማይችሉ ትራክተሮች ፡ የመበየጃ መሣሪያዎች ይጠይቃሉ ። የኤሌክትሪክ ጀኔሬተር ሱዳን ውስጥ አስፈላጊ ነው ። በየጊዜው መብራት ይቋረጣል ። ኤሌክትሪክ ማለት ለሱዳን ደግሞ ሕይወት ማለት ነው ። ማቀዝቀዣው የሚሠራው በኤሌክትሪክ ነው ። የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ፡ የትምህርት መሣሪያዎች ፡ በዕርዳታ ይመጣሉ ። የህክምና መሣሪያዎች ፡ የመንገድ መስሪያ ክሬኖች ፡ ፎርክሊፍተሮችም የማይመጣ አለ ። ይህን ሁሉ ነው ለሱዳን የሚሸጡት ፡ ከሱዳን አልፎ ለጂቡቲና ለሶማሊያም ይሸጣሉ ። የሱዳን መንግሥት በዚህ ከፍተኛ ጥቅም ያገኛል ። መያኤው አሁን የቀረው ፈለትግራይ የባቡር ሀዲድ በሽራሮ አድርገው በአዲአቦ ልንዘረጋ ስለፈለግን ጥናቱን አጠናቅቀናል» ማለት ነው ። ይህን ይህን ሁሉ እየመሰዱ ይሸጣሉ ። በገንዘቡ «ማሌሊት» ይመሠረትበታል ። ሽርሽር ይከድበታል ። ዋልጌነት ይስፋፋባታል ። መሪዎቹ ከሕዝቡ ጉርሮ እየነጠቁ በምቾት ይኖሩበታል ።

<u>ጥያቄ</u>፡- መያኤው በፈጠረው ችግር ስደተኛውም ገንዘብ እንዲያ ዋጣ ይደረጋል ይባላል ። ይህ እንዴት ነው?

<u>አብርሃም</u>፡- እኔም ስደተኛ ነበርሁ ። ሥራ ቢኖረኝም በስደተኛነቱ አዋጣ ነበር ፡ እህቶቻችንም አካላቸውን ሽጠው ከሚያገኙት ያዋጣሉ ። ባትሰጥም ደግሞ ተፅዕኖ አለ ፡ የደርግ መደም የሲአይኤ ሰላይ የሚል ስም

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሰጥሃል ። የሱዳን መንግሥት የሚያደርግላቸው ጥበቃ አለ ። የደርግ ሰላይ ነው ብለው ለፖሊስ ጠቁመው ያሳስሩታል ። የአረጋዊ በርሄን የእህት ልጅ የደርግ ሰላይ ነው ብለው ነው ያሳሰሩት ። አፍነው ያሰሩትም፣ ያስቃዩትም እነሱ ናቸው ።

<u>ጥያቄ፡</u> የኤርትራ ንጥላይ ቡድኖች ዓላማቸውን ለማስፈጸም ሰዎችን በመመልመል ፣ እንዲሁም የራሳቸውን ሰዎች አስርገው በማስገባት ጥፋት ያደጽማሉ ። በብዛት እንደሚታየው ከሆነ በተለያየ ስም የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች አብዛኛው በሻዕቢያ» እደራጅነት ነው ይባላል ፣ ስለዚህም የምታመለክቱን ብታስረዱን ።

<u>ሶበርሃም፡</u> በአጠቃላይ የኤርትራ ንጥላዎች ተራማጅነት ባላቸው የተማረምችና የሠራተኞች ማህበርች መርዛው በመግባትና በመሳተፍ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ እንደሚሩ ተደም ሲል አስረድተናል ።

«ከአሕአፓ» ጋር የነበረውን ግንኙነታቸውን እንመልከት ። «ሻዕቢያ» የኤርትራ መገንጠል እስከደገፉት ድረስ እኛን የተዘረጋ ነው አላቸው። «አሕአፓ» አጠናለሁ አሉ ። አስከያዝነውም ድረስ መለስተኛ ትብብር ነበር ። «አሕአፓ» ግን የኤርትራን መገንጠል መቀበል አልቻለም ። እንደማይቀበል ሲረዱ በወያኔ አስመቱት ። «አ·ር·አ·ል· አ·ፋ» «ተ·ገ·አ·ል·አ·ፋ·ን» በፈጠረበት ሩብረካ ነው «አሕዴን» የተሠራው ። «ሻዕቢያ» «አ·አ·ል·አ·ፋ·ን» ያረጃል ፣ ወታደር ያሰለጥናል።የኤርትራ ጥያቄ የትኛ ማህበ ጥያቄ ነው ፣ ኤርትራ መገንጠል አለባት የሚል ምንም ዓይነት ድርጅት ቢፈጠር «ሻዕቢያ» ያረጃል ።

ካርቱም በነበርኩበት ጊዜ ያጋጠመኝን ልናገር ። አንድ የኤርትራ ተወላጅ ካርቱም አገኘሁ ። አዲስ አበባን ታውቀዋለህ ወይ? አልኩት ። ዋቢሸበሌና የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሲመታ ከነመለስ ተክሌ ጋር አዲስ አበባ የሄድኩት እኔ ነኝ አለኝ ። ከመቀሌ ፈንጂውን በራሳቸው መኪና ጭነው ያመጡላቸው ሰዎች በመቀሌ የሚኖሩ የኤርትራ ተወላጅች አሁን በሱዳን የሚገኙ ሰዎች ናቸው ። ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው ይህን ያደርጋል? እነሱ ተልዕኮአቸው ኢትዮጵያን ማፍረስ ነው ። ኢትዮጵያም አትፈርስም ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የኢትዮጵያን ጉዳይ አስፈፅማለሁ ብሎ በኢትዮጵያውያን ስም በሚነሳ ድርጅት የ«ሻዕቢያ» እጅ ያልገባበት አይገኝም ። የኤርትራን መገንጠል የማይቀበሉ ግን ይህን መንግሥት የሚቃወሙ ንያሉች አሉ ። «ሻዕቢያ» መኖራቸውን እንኳ ለማወቅ አይፈልግም ። አድንቦ ናቸው ይላቸዋል ። ይህን መንግሥት እስከተቃወሙ ድረስ እንኳ በታክቲክ ሊረዱአቸው ይችሉ ነበር ፣ ግን አያደርጉትም ። ኢትዮጵያን ለመበታተን ዓላማ ያለው ከሆነ ግን ወይ ይፈጥሩታል ፣ ተፈጥሮ ከአገኙት ደግሞ በቀጥታ ይረዱታል ።

ወያኔዎች ኢትዮጵያዊ ነን ይሉናል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ለአንድነቱ ምን ያህል እንደሚቆም በሱማሌ ጦርነት አይተናል ። ሶማሌ ሞጆ ድረስ የእኔ ነው ብላ ነበር የተነሳችው ። ሕዝቡ በአንድነት ግልብጥ ብሎ ነው የወጣው ። የ«ሻዕቢያ» ተቀጥላ የሆኑት ወያኔዎች «ሱማሌ ኢትዮጵያ ውስጥ መሬት አላት ፣ የምዕራብ ሱማሌ ነጻ አውጪ ድርጅት ፍትሐዊ ነውጥ ብለው ነው ድጋፍ የሰጡት ። በዚህ መንግሥት ተወጥሮ በተያዘበት ጊዜ ነበር በትግራይ ከፍተኛ ወረራ አድርገው የሶማሊያ መንግሥት በደሩ ያወቃቸው ። እኔ የማውቃቸው የትግራይ ልጆች ለእድገት በህብረት ዘመቻ ወደ ምስራቅ ኢትዮጵያ ይሄዳሉ ። በአንዳንድ ምክንያት ወጥተው ሱማሊያ ይገባሉ ። ሱማሊያ ውስጥ የኤርትራ ተወላጅ ነኝ ካልህ የሚነካህ የለም ። እነዚህ ልጆች የት ነው አገራችሁ ሲሏቸው ኢትዮጵያ አሉ ፣ አሥሯቸው ። የትግራይ ሰው ኢትዮጵያዊ ነኝ ነው የሚለው ። እንደአማራውና እንደ አሮሞው ታሠሩ ። የዚያን ጊዜ የልጆቹ መታሰር በራዲዮና በጋዜጣ ተገልጾ ሰለነበረ ፣ ወያኔዎች ሊያስፈቱ ሲሄዱ ልክ እንደ አንድ መልዕክተኛ ነበር የሱማሌ መንግሥት የተቀበላቸው ፣ ለመኖሪያና ለቢሮ የሚሆን ቤት ሰጥቶአቸው ነበር ። ያማን ከዳኔ ነው የታሰሩትንም ሄደ ያስፈታቸው ። ወያኔው ስላስፈታቸውም የወያኔው አባል የሆኑ የማውቃቸው ልጆች አሉ ። ወያኔዎች ሱማሊያ ኢትዮጵያ ውስጥ ያደረጓቸውን ወረራ በቀጥታ የደገፉ ናቸው ። ይህ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ነኝ በሚል ሰው ወይም ሁድን የሚደረግ አይመስለኝም ።

ዛሬ የወያኔ መሪዎችና የኤርትራ ተወላጆች ጭባይ ፣ ጅጻ ፣ ሪያድ ሲሄዱ የሚጠቀሙት በሱማሊያ ፓስፖርት ነው ። ኢትዮጵያና ሱማሊያ እርቀ ሰላም አድርገዋል ። ወያኔዎች ግን አሁንም ቢሆን መሐመድ ፣ አብደላ ፣ ሳላህ ወዘተ እየተባሉ የሚገለገሉት በሱማሌ ፓስፖርት ነው ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዚህ ሰዎች ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል የመሬት መንቀጥቀጥ እንኳ ቢደርስ ደስ ያላቸዋል ። እንዚህን ኢትዮጵያዊ ባህሪ ብሎ የሚያሳምንኝ ሰው አያገኙም ። ያህ ደግሞ ከማናገራት ብቻ ሳይሆን ከሚሠሩትም የሚታይ ነው ። በእጠላላይ የኤርትራ ንቅሳት (ሽፅዚያ ምች) ኢትዮጵያን ለመበታተን የሚነሱ ድርጅቶችን የፈጠሩ ። ጠመ አጥብቀው ያሳደጉና የሚያሳድጉ ናቸው ።

ገብረፃዲቅን፡ አቶ አብርሃም ከመጣው ያገኘውን መረጃ ተልጸተል ። እኔ ደግሞ ሙስጥ ስለነበርው በሱማሌ ሠርነት ጊዜ መያዜው በነበረው አቋም ላይ የምገልጸው አለኝ ። በዚያ ወቅት በቅጥረኛ መያዜው እንድ ጽሑፍ አውጥቶ ነበር ። «የሱማሌና የኢትዮጵያ ሠርነት ምን ያመስላል?» የሚል ። መያዜ እንድ አቋም መሰደች ። «ሱማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር የምታደርገው ሠርነት ፍትሐዊ ነው ብላ ኢህያን የሱማሌ ነው» አለች ። ጽሑፉ ወጣ ። እኛም በዘዙን ለማበረማር ተንቀሳቀስን ። ያህ የመጀመሪያው ከባድ ሠርነት በነበረበት ከ1969 እስከ 1970 መጋቢት ወር ድረስ ነው ። «የሱማሊያ ሠርነት ፍትሐዊ ሠርነት ነው መረራ አያደለም ። ኢትዮጵያ ተሰፋፊ እንደመሠኗ መጠን በንደል የያዘችው መሬት ነው» አለች ። መያዜ ለዚህም ሙለታዋ ከሱማሊያ መንግሥት ብዙ የወር መሣሪያዎች አግኝታለች ። እርዳታው በሱማን ሠር ነው ትግራይ የገባው ።

ሱማሊያ ያሠን ከደረገች በኋላ ለትግራይ መያዜ ተወካይ ሁነው ከሄዱት መካከል አንዱ ያነበርር ይመስማና የሚባል ነበር ። ሱማሊያ እንድ እንድ ነጻ መንግሥት አምባሳደር ነበር የተቀበለችው ። በምታከብራቸው ብሔራዊ በዓላት ሁሉ ላይ የመያዜው ተወካይ ከእንድ ነጻ አገር አምባሳደር እኩል ተከብር እንዲገኝ ይደርግ እንደነበረም ገለጸ ተደርጕል ናል ። ሁለት ላንድሮቨሮችና እንድ ሌላ መኪና ተሰዋውአቸዋል ። ያሠን ደግሞ ራሳቸው ፅፈውታል ። ታሪክን ለተመሰነ ጊዜ መሸፈን ፡ ማድበስበስ ያቻላል ፡ ግን ጨርሶ ማጥፋት ስለማያቻል አያከፋትም ።

ጥያቄ፡ መያዜው በየድረሰበት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እያወረደ የራሱን ያሰቅላል ። የወሎና የጉንደር ሕዝብ እንደገለጸውና የሳያነ ምስክሮችም እንዳረጋገጡት ሰንደቅ ዓላማችንን እንደሚያከብር ልና እንደሚተድም ታውቋል ። እዚህ ላይ ያላችሁን አስተያየት ብትገልጹልን?

t.me/OLDBOOKSPDF

ገብረመድን፡- ወያኔ በፀረ ኢትዮጵያና በፀረ አንድነት አቋም የምትንቀሳቀስ መሆኗን ገልጸናል ። መንቀሳቀስ ከጀመርንበት ጀምሮ እስከ 1970 ድረስ ባንዲራ አልነበረንም ። በ1971 የወያኔው አንደኛ ጉባኤ በተደረገበት ጊዜ ያመጣነው ባንዲራ ነበር ። መደቡ ጥቁር ፡ ሶስት ማዕዘን ሆኖ ከዳር የሚመጣው ቀይ ቀለም ነበረው ። የጥቁሩ ትርጉም «ትግራይ በአማሮች እየተጨቆነች በጨለማ ውስጥ የምትገኝ ብሔር ናት» የሚል ሲሆን ፡ ቀዩ ደግሞ «እኛ ወያኔዎች የትግራይን መንግሥት ለማቋቋም ለምናደርገው እንቅስቃሴ ምልክት ነው» የሚል ነበር ። በዚህ ሰንደቅ ዓላማ እስከ 1975 ተንቀሳቀስን ። በዚያው ዓመት ግንቦት ወር በሁለተኛው የወያኔ ጉባኤ አዲስ ሌላ ባንዲራ መጣ ። ይኸ ደግሞ መደቡ ቀይ ሆኖ በሶስት ማዕዘን የገባ ቢጫ አለው ። ቀዩ ላይ ቢጫ ኮከብ አለበት ። የዚህ ትርጉም ደግሞ ቀዩ «የትግራይ ሪፐብሊክ መንግሥትን የምንመሰርትበት የትግል ምልክት ነው ።» ቢጫው «ተስፋና ልምላሜን ሲያሳይ ኮከቡ ደግሞ በሁሉም አለን አለን ባይነን» ማለት ነው ። በዚህ ጊዜ አንድ ሞቅሞቅ ያሰኘ ጉዳይ ነበር ። እሁን ያለው ኮከብ ቦታው ተለውጦ ቀይ እንዲሆን የሚል ሀሳብም ቀርቦ ነበር ።

በ«ሻዕቢያ» የቀረበ ሌላ ባንዲራ ነበር ። እንደትጠልያ ሆኖ የወይራ ዝንጣፊ አለበት ። ለስብሰባ ስንገባ የምናደርገው ባጅ አለ ። ያ ባጅ በ10ኛው የወያኔ ዓመት ክብረ በዓል ላይ ያወጣነው የወያኔ ዓርማ ነው ። ዓርማው ላይ የአክሱም ሐውልት አለ ። ለዚህ የተሰጠው ትንተና «የአክሱም ሐውልት እሁን ኢትዮጵያ ተብላ የመትጠራውን ሀገር አያመለክትም ። የትግራይ ብቻ ነው» የሚል ነው ። መዶሻው የወዛደሩ ሲሆን ከላሽኑ ደግሞ «ወደነፃነት የሚወስደን ጉዳና ትግል ነው ።» የሚል ነው ። ገብሱ ደግሞ «ትግራይን ልምላሜ እንሰጣታለን» የሚል ነው ።

ለብርሃም፡- የትግራይ ሰዎች ወያኔው ባንዲራ እንዳለው አያውቁም። አንድ ጊዜ ምዕራብ ጀርመን ቦን ውስጥ ነበርሁ ። ሳልፍ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አየሁ ። ከኢትዮጵያ ብዙ ርቀን ነው የምንነኘው ። ቦን ኢትዮጵያ ኤምባሲ ግቢ የተሰቀለውን ባንዲራ እያየን ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ለማሽ ሰዓት ተመያየን ። ባንዲራ ከፍተኛ የሕዝብ ስሜት የያዘ ነው። ባንዲራ ከሱት አምጥተህ የምታንጠለጥለው ተራ

t.me/OLDBOOKSPDF

መያኔው የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ ለመተካት ያዘጋጀው "ባንዲራ"

ጨርቅ አይደለም ። ይህ ባንዲራ ደግሞ ብዙ ኢትዮጵያዊያን የሞቱለት ፡ የተሰቃዩለት ነው ። ጨዋታ አይደለም ።

መያኔዎች ትግራይ ከተሞች ውስጥ ገብተዋል ። ወደ ጐንደርና ወደ ወሎም ወረራቸውን አስፋፍተዋል ። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው አያውቁም ፡ ወረዳ ከተማ ሲይዙ የሚሰቅሉት ባንዲራቸውን ነው ። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውርደው የራሳቸውን ይሰቅላሉ ። አከሉም ያደረጉት ይህን ነው ።

መያኔዎች የ«ሻዕቢያ» መልእክተኞች ፡ ራሳቸውም «ሻዕቢያዎች» ናቸው ። «ሻዕቢያ» የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እንዲያውለበልብላችሁ ትፈልጋላችሁ እንዴ? የኢትዮጵያ አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተዋሕዶ እምነት ናሮት የኢትዮጵያዊ የሚል ቃል ስለለለ ብንገባ ኢትዮጵያዊ ያደርገናል ብለው የሚያስቡ ሰዎች ናቸው ።

ማወቅ ያለብን ሰንደቅ ዓላማው የደርማ ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መይም

t.me/OLDBOOKSPDF

የምኒሊክ ወይም የዮሐንስ አለመሆኑን ነው ። ከጥንት ጀምሮ ለዘመናት ሳርማችን ፡ የኢትዮጵያዊነት መለያችን ሆኖ የቆየ ነው ። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ባንዲራ የትግራይ ሕዝብ ከመሞታቸውም በተጨማሪ ስለ ሰንደቅ ዓላማው ታሪክ ሆነ ትንተና የሚሰጥ ሕዝብ ነው ። እኔ የማውቃቸው በአድዋ ከተማ ያኖሩ የነበሩ አለቃ ተወልደ መድህን የሚባሉ ሰው ነበሩ ። አለቃ ተወልደ መድህን በዘመናቸው በአካባቢያችን ተወዳዳሪ ያልነበራቸው ሊቅ ነበሩ ። ወደ ፍልስፍና ወደ ታሪክ እየገቡ ስለኢትዮጵያ ብዙ ያናገሩ የነበሩ ሰው ናቸው ። ልጅ ሆኜ እሳቸው አርጅተው አልጋ ላይ ሆነው «የሰው ልብ» በሚል ርዕስ የጻፉትን መጽሐፍ ያሰጡኝ ነበር ። በቅርብ የማውቃቸው ሰው ናቸው ለማለት ነው ። ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ምን ብለው ነገሩአቸው «የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተለማች አተማመጥ ፡ እንዲህ መሆን የለበትም ነበሩ እንዲህ ሆኖ አተማመጡ ግን አረንጓዴ ከታች ፡ ቢጫ ከመሐል ፡ ቀይ ከላይ መሆን አለበት ። የዚህም ምክንያቱ አረንጓዴው ልምላሜ ነው ፡ ዘር ነው ፡ እና አንድ ነገር ሲበቅልም መጀመሪያ የሚወጣው ቅጠሉ ነው ። ከዚያ ከማፍራቱ በፊት አበባ ያወጣል፡ ቢጫው ደግሞ አበባው ነው ፡ ከአበባ በኋላ የሚመጣው ደግሞ ፍሬ ነው ፡ ቀዩ ፍሬ ነው ፡ እና እንዲህ መሆን አለበት ብለዋቸዋል ። አጼ ኃይለሥላሴም ታሪኩን ተቀብለው ፡ ዛሬ ያለው የሰንደቅ ዓላማችን አተማመጥ በተባበሩት መንግሥታትና በተለያዩ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተመዘገበና የታወቀ ስለሆነ ችግር ይፈጥራል ። ታሪካዊ አመጣጡ ግን ያሉት ትክክል ነው ብለው ነው መልስየሰጪቸው ። አለቃ ተወልደመድህን የወለዱን ልጅች ዛሬ እሳቸው ስለሞቱና የኤርትራ ተገንጣዮችም መሣሪያ ስለሆንን ሌላ ባንዲራ ፈጥረናል ። በጣም የሚያሳፍር ሽፍጥ ነው ።

ዘርዓይ ድረስ ጣሊያን አገር የኢትዮጵያ ባንዲራ ስለተረገጠ ነው የሞተው ፡ የናቱ ቅሚስ ስለተረገጠ አይደለም ። ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ክብር ሲደፍሩ አይቶ ነው ሕይወቱን የሰዋው ። አባቶቻችን የተዋደቁለትን ባንዲራ እኛ እሱን ተፈጥረን ልንለውጠው አንችልም ። እነዚህ ሰዎች (ወያኔዎች) የስታሊንን ፖስተር ለአክሱም ሕዝብ ይዘው የመጡ ሰዎች ናቸው ። እንዳልነውም ፡ ባንዲራም ይዘውለት መጥተዋል ። ሕዝብ ወያኔዎች የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው ሲያውለበልቡ አያቻለሁ ከአለ ፡ ደጋማዊ እንደተናገረውት የትኛውም ፍርድ ቤት ሳልተረብ

t.me/OLDBOOKSPDF

አንተን አስቆርጣለው ። ከኢትዮጵያ ማሕፀን ያልተፈጠሩ ወይዮች ናቸው ።

የወያኔው ድርጅት የትግራይን ጉዳይ ለማስፈጸም የቆመ የኢትዮጵያ ልጅ አይደለም ። ከሰንደቃቸው እየተነሳን ነው የምንናገረው ። «በኢትዮጵያ ውስጥ የአማራ ብሔር ሞቶና ከቀን ወደ ቀን እየሰፋና እየተጠናከረ በመሄዱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድነት ሊታገሉ አይችሉም ። አልፎም በአንድነት መኖር የማይችሉና መበታተናቸውም አስፈላጊ ነው» ይላል ። ሌላ ላምባ «ብሔሮች የብሔር ጥያቄ በተናጠል ያንሳሉ። በተናጠል ማንሳታቸውም ለኢምፔሪያሊዝም ፡ ለፈውዳሊዝምና ለቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ተጻዳ መክፈት እንጻይሆን የተለያዩ ብሔራዊ ጥያቄዎችን እያነሱ በንብረት መታገል ፡ ድል ካደረጉም በኋላ ብሔርነታቸው ይጠበቅላቸዋል ማለት ነው ። ስለዚህ ልዩ መልክ ባለው ንብረት በሶስቱ ጠላቶች ላይ መነሳት ብሎም መገንጠል ነው ይላል ።» ይህ ምን ማለት ነው?

ብሔሮች የብሔር ጥያቄ በተናጠል ያነሳሉ ፡ በተናጠል ማንሳታቸው ለኢምፔሪያሊዝም ፡ ለፈውዳሊዝምና ለቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ተጻዳ ስለሚከፍት በንብረት መታገል ይኖርባቸዋል ። ድል ካደረጉ በኋላ መገንጠል ይችላሉ ። ንብረት ለትግሉ ሲባል የተያዘ ታክቲክ ሲሆን ፡ መገንጠል ደግሞ የትግሉ የመጨረሻ ግብ ስትራቴጂ ሆኖ ተቀምጧል ። ንብረት ለታክቲክ ፡ መገንጠል ለስትራቴጂ የተጠቀ ነው ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከቁራን ላይ ያለውን ብጠቅስ እኔ ሳልሆን መጽሐፉ ነው ነጻፈ ። በመጽሐፋቸው ፡ በፕሮግራማቸው በባንዴራቸው ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደዋል ።

<u>ገብረ መድህን</u>፡ አሁን በተለያየ ቦታ ላይ ወያኔው በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚያደርገውን ትሰማላችሁ ፡ በተለይ እኔ በሙስዋ ስለነበርው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የተሰቀለበትን እናመርዳለን ። ከዚያ የወያኔውን ሰንደቅ ዓላማ እንሰቅላለን ። የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እንረግጠዋለን ፡ ቀድን እንጥለዋለን ። ይህ ውልጊዜ የሚደረግ ነው ።

<u>ስብርሃይ</u>፡ ሞላጥ ለማስያዝና ማንዛዜ ለማስገንዘብ ያህል በማም በጠራ መልኩ የምናውቀውን እውነት ተናግረናል ። ማለት የምንፈልገ ውን ብለናል ። ይህን ባለማለቱ ይደርስብኝ የነበረው የመንፈስ ሚንቀት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንኳን ቀለልኝ እንጂ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለራሱ ሕልውና ሲል የሚወስነው ነው ። ይህ ፖሮፓጋንዳ አይደለም ። ይህ በታሪክና በተፈጸመው ማንዛቤዎች ፡ በመረቀት ላይ በሰፈሩ ፡ የተጻፉ ነገሮችን ይዘን ነው የምንናገረው ። <u>ስለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ቦታ ላይ ለአንድ ደቂቃ ቆሞ ማሰብ ይኖርበታል</u> ።

t.me/OLDBOOKSPDF